# - 7 -

# የባህር ጉዞ

አልገባኝም ለምንድን ነው ያዳላኸው
አንዱን ጌታ አንዱን ሎሌ ያደረከው?
ለግማሽ ሰጥተህ ለግማሽ የነፈከው
እውነት እውነት ጠልተኸው ነው
ያልፈተንከው የምታንደላቅቀው?

ከብዙ ቆይታ በኋላ ጉዞ ተጀመረ:: «በሰላም አስገባን» አሉ ሴቶቹ:: እኔም በውስጤ ደገምኩት::

አሁን የውሀው ድምጽ ብቻ ነው የሚሰማው:: ሁሉ ነገር ፀጥ ረጭ ብሏል:: ምክንያቱም ተሳፋሪው አወራለሁ ቢል በያዙት ዱላ እናት አናቱን ነው የሚሉት:: በጀልባው የኋላኛ ክፍል ነው የተቀመጥኩት:: እፍግፍግ ከማለታችን የተነሳ አንዱ የአንዱን ጠረን በግዱ ይስባል::

ከ12 እስከ 16 ሰው የምትጭን አነስተኛ አሳ ማስገሪያ ጀልባ ነች:: የገጠር አጥር ይመስል የጀልባዋ ዳር ዳሩ ዙሪያውን አጣና ተመቷል:: ሸራ ላስቲክም አልብሰዋታል:: ከላይ ክፍት ናት:: «ቀና ብዬ ሳይ እዩት ሰማይ ደፈረሰ..» የሚለውን ዘፈን አስታውሼ ቀና አልኩ:: አልፎ.. አልፎ ጣል..ጣል ያሉትን ከዋክብቶች ሳይ ጭላንጭል ተስፋ ታየኝ::

«ግሩምዬ ተጫወት እንጂ ዝም አልክ» ሰናይት ነች::

«እሺ!..» ሌላ ምን እላለሁ? የምን መጫወት አመጣችብኝ? እንኳን ልጫወት እያቅለሸለሸኝ ነው:: ገና ጀልባው ላይ እንደወጣን ባደሉን ስስ ላስቲክ የመጀመሪያውን ዙር አስተናግጀበታለሁ:: ቀሪም አለ መሰለኝ ይንጉጠኛል:: ሰውነታችን ላይ የቀረው የባህሩ ውሀ ሽታ፣ አሁንም ባህሩ






የሚለቀው የሚተነፍግ ግማት፣ እወደላይ ያለን (የቋቅታ) ሽታ፣ በዱላ ሲመቱ ደንግጠው ወደ ታች ያላቸው፣ ካላላቸውም ጋዝ የለቀቁ ለአየሩ ብክለት አስተዋፅዎ አድርገዋል:: የባህሩ ውሀ የነካው የጫማ ሽታ፣ የብብት፣ የሲጋራና ሀሺሽ ሽታ..ሀሺሹን እንኳን ድፍረት እንዲሰጠኝ ብዬ አጠገቤ ካለው ሶማሊያዊ ተቀብዬ ሳብ..ሳብ አድርጌለት ነበር:: ምን ያደርጋል እኔ ላይ ሲሆን አይሰራም መሰለኝ ፍርሃቴ አለቀቀኝም:: ብቻ ሽታዎች ሁሉ ህብረት ፈጥረው የፈነዳ ሽንት ቤት ጉድጓድ ውስጥ የተቀመጥኩ ነው የመሰለኝ:: አቤት!!.. ጨጓራዬ በምላጭ ይሁን በማጭድ እየፈቀፈቀኝ ነው:: ወደ ላይ ብሎ ፌስታል የሚሞላው ሰው በጨመረ ቁጥር ለራሴ እየፈራሁ ነው:: የፈራሁት ግን አልቀረም እኔም ዳግም ፌስታሌን ተጠቀምኩበት:: ደሞ ሌላ ፍርሃት:: በሁሉም ልብ ውስጥ ነግሶ ዝምታን ያነገሰ ፍርሃት:: እኔም ስለባህሩ የሰማሁትን አስታውሼ በውስጤ ያለ የሌለ ጸሎት ይገፍለሁ:: እንደዚያን ቀን ጸልዬ የማውቅ አይመስለኝም::



(የጀልባዋን ሁኔታ በቃላት ከገለጽኩት ጋር እንደታነጻጽሩት ብዬ ነው ይህን ምስል ያስቀመጥኩት:: በዚህ አይነት ነው ለ40 እና ከዛም በላይ ሰዓታት የተንዝነው:: ፎቶ ከኢንተርኔት የተወሰደ)

ለምን እንደሆነ አላውቅም ልጄ ደጋግሞ በሀሳቤ ይታየኝ ጀምሯል:: «ሰላም ይሁን፣ ሰላም ያድርግልኝ» አልኩ በልቤ:: እናቴም በሀዘኔታ አይታኝ «ልጄ የኢትዮጵያ አምላክ ይጠብቅህ፣ ይከተልህ!!» ያለችኝ መሰለኝ:: ቀና ስል ግን ባዶ አየር ነበር:: ደነገጥኩ ለምን አንዴ እናቴን አንዴ ልጄን አስታወስኩ? ለነገሩ በእውንም እንዲህ ብላኝ ነበር:: ቁርጡ መጥቶ ክ/ሀገር ዞር ብዬ ላሳልፍ ነው ያልኳት ጊዜ «የኢትዮጵያ አምላክ ይከተልህ.. ይጠብቅህ» ብላኝ ነበር:: አስታውሳለሁ በዛን ሰዓት ኢትዮጵያ አምላክ አላት እንዴ? ለምን ዘላለማችንን ረሳን? ሁሌ ስደተኛ ሁሌ ረሃብተኛ ሆነን.. የኢትዮጵያ አምላክ አባባል ነው:: ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሄር



(የጀልባዋን ሁኔታ በቃላት ከገለጽኩት ጋር እንድታነጻጽሩት ብዬ ነው ይህን ምስል ያስቀመጥኩት።
በዚህ አይነት ነው ለ40 እና ከዛም በላይ ሰዓታት የተንዝነው። ፎቶ ከኢንተርኔት የተወሰደ)

ትዘረጋለች ይባላል:: እውነቱ ግን ወደ ፈረንጆቹ ነው እጆቿን የዘረጋችው የሚል ሀሳብ ሽው ብሎብኝ ነበር::

**ሌሊት 7 ሰዓት አካባቢ:-**

ከብዙ ጉዞ በኋላ ሌሊት ሰባት ሰዓት አካባቢ «ግሩም ተኛህ እንዴ?» የሚል ድምጽ ሰማሁ ሠናይት ነች:: አይ መተኛት እቴ! በሃሳብ ላይ ሃሳብ፤ በጭንቀት ላይ ጭንቀት... በዛ ላይ አሁንም እያቅለሸለሸኝ ነው:: እናም በዝምታ ውስጥ ሆኜ ዝምታዬን ማዳመጥ... ዝምታ ውስጥ አድፍጬ የራሴን ሀሳብ ማንሸራሸር ነው የፈለኩት:: ሁላችንም ኩርምት..ኩርምት.. ብለን ነው የተቀመጥነው:: ግዴለሽነት ይሁን ሀሳብ መጣል ካሁኑ እንቅልፍ የጣላቸው ሰዎች አሉ:: እነ ሰናይት መልስ ስላልሰጧቸው

«ውይ! እናቴ ለቡሩክ ተኛ ሊያሳዝን..» አለች አልማዝ፣ ረገጥ አድርጋ በምትሰባብረው አማርኛዋ:: «አንቺ ለወንድሜ ነው ሚመስል ሳየው ሆዴ ረበሽበሽ አለ::»

«አይ! እረፊ ያን የመኪና ረዳት ወንድሜን ትመስላለህ ብለሽ ልቡን ያቆምሽበት ዘዴ እዚህ አይሰራም::»

«ውይ..ውይ..ሰኒ ግፍ ላትናገሪ ለንደዚህ አላሰብኩም:: ብቻ ሳየው ለወንድሜ መሰለይ በቃ! ላንቺ ያሰብሽው አላሰብኩም» የተሰባበረው አማርኛዋ ከወፍራም ድምጿ ጋር ያምራል::

«አይመስለኝም» አለች ሰናይት

«ሳጭወረውር አይደለም:: ያኮ ለሹፌሩ ላሰኘው ጊዜ ሊመጣኝ.. ሊጎትተኝ ሲል ለረዳቱ መረጥኩ::»

«ከሁለቱ ማን ይሻላል?» ሰናይት ጥያቄዋን ማንም ሰሚ እንደሌለ አድርጋ በማሰብ በሹክሹክታ ነበር ያቀረበችው:: እኔ ግን በውስጤ «አመጡት ጨዋታውን» ብያለሁ::

«ለረዳቱ ወጣት ሆን ይሻላል:: የሹፌሩ ላባም ነው ይሸታል:: ሁለቱም ወንድ ይመስሉ ቀበዝበዝሎ ነካ..ነካ..አረጉ ይተዋሉ:: አይችሉም..»

የሰማሁትን ማመን አቃተኝ:: ተገደው ያደረጉት ላይም አርካታን ይጠብቃሉ? ገረመኝ:: ግን እንዴ የተኛሁ መስያለሁ መጠየቅ አልችልም::

«ወንድ ሁሉ ወንድ ነው እንዴ? ከልካዩ ላይ ያደርን ጊዜ ያ-ሰውዬ ሊያስገድደኝ አስታወስሽ?» አለች ሰናይት

«የቱ?»



«ከእኛ ጋር ሽንኩርት መኪናው ላይ ተጭኖ የነበረው ሱማሌ?»

«እ... ያ የሚያፈጠው? በግ አይን:: ከጥቁረቱና ቅጥነቱ ጋር ርዝመቱ ተጨምሮ በአስማት የቆመ ጥቁር ወስፋት ነው እኮ የሚመስለው::» አገላለጽዋ ተመቸኝ:: ርግጥ የተናገረችው እኔ እንደጻፍኩት አይደለም:: ሰብርብር ያለና በትግርኛ የታገዘ በመሆኑ ለአንባቢ እንዳያስቸግር አስተካክዬዋለሁ::

«አንቺን ሹፌሩ ሲጎትትሽ እሱ እኔን ጎተተኝ:: እንቢ ስለው በጥፊ አላጮለኝ መሰለሽ?..» አለች ሰናይት::

«ኪ...ኪ...ኪ...ኪ...» አልማዝ ሳቀችና «አይ ሰናይት ላንቺም የእኔ ዕጣ ደርሶሽ ዱላ ቀምሰሻል?»

«አንዴ መሰለሽ? ደጋግሞ ጨፈጨፈኝ እንጂ:: ብጮህ ማን ይሰማኝ:: እየጎተተ እናንተ በሄዳችሁበት አቅጣጫ ሳይሆን በተቃራኒው ይዞኝ ሄደ:: ቀሚሴን ለመግለብ ሲታገል እኔም ላለማስገለብ ስታገል ብዙ ተናነቅን:: ከጭኔም ሳይደርስ ሸርጡን አራሰው:: ተገላገልኩ» አለች በኩራት::

«ለካ ከሹፌሩም የባሰ አለ?»

«ገና ጭኔ ሳይገባ ስልሽ! ጥዬው ወደ መኪናው እመለሳለሁ ብዬ ስሮጥ እናንተ ገና ግብግብ ላይ እያላችሁ የመጣሁት:: ዞር ስል ረዳቱ ያቺ የራያዋን ልጅ አሳሯን ያሳያታል:: መኪናው ጋር ስመለስ ያ-ምስኪን የምንለው ልጅ ብቻውን ቁጭ ብሏል:: ሲያየኝ «ምን ሆንሽ?» አለኝ:: ነገርኩት:: አምልጬ መመለሴን ሲያውቅ እሱም ነብር ሆነብኝ:: አነቀኝ ለካ ከኋላው መኪና ላይ ያሉት የሚያረጉትን እያዳመጠ ስሜቱ ተቀስቅሷል::

«አይይይ!..ያ-ምስኪን የምንለው ጨዋ ልጅ? እሱም?..» አልማዝ አቋርጣ በአግርሞት ጠየቀቻት::

«እንደ ምስኪንነቱ እንዳይመስልሽ ሁሉንም ያስንቃል:: እጄን ጠምዘዝ አደረገና ብቻ ተይው..ተይው ልኬን አሳየኝ::»

የሚያወሩት ግራ ገባኝ:: ተገደው መተኛታቸውን ወደውት ነበር? ጆሮዬን ሁሉ ተጠራጠርኩት:: በስቃይ ውስጥ፤ በመገደድ ውስጥ ደስታን መፈለግ? አልዋጥልህ አለኝ:: ወይስ ሲያልፍ እንደቀልድ አድርገው ማውራታቸው ነው? በተለይ ሰናይትንማ የማውቃት..የማውቃት አልመስልህ አለኝ:: እኔ ሳውቃት ቁጥብ እንደበት ያላት ብዙም ከሰው

የማትቀርብ ነበረች:: ነገሮች ሁሉ ተገላበጡ ወይስ ቦሳሶ እዛች ዳስ ውስጥ አሻሻጭ ሆና ለጥቂት ጊዜ መቆየቷ ይሆን ይህን ያህል የለወጣት?

«ለእኔ ያላየሁት ስቃይ አለ እንዴ?» አለች አልማዝ ደግሞ:: ሀሳቤን ወደ እነሱ መለስኩ:: ቀጠለችናም «...ለቡሮው (ቡሩቶ ለማለት ነው.. የሶማሊያ ከተማ ነች) ሰውዬ አስታወስሽው?»

«አዎ! ያ-አረመኔ?»

«እ...ንቅ አረገይ በቃ! ለሚስቱ ቤቱ ትቶ..» በእንጥልጥል ተወችው:: የሚቀጥለውን ለመስማት ጓጓሁ:: ቀጠለች:: በዝምታ ሰማሁ:: ግን አስጠላኝ:: አማረልን ብለው ነው የሚያወሩት? ከዚህ በኋላ ይሄ አስጠሊታ ወሬያቸውን መስማት አልፈለኩም:: በመባነን አይነት ከእንቅልፌ የነቃሁ መስዬ ላስቁማቸው እያልኩ ሳስብ አንዱ ከእንቅልፉ ባኖ ብድግ አለ:: ሶማሌው «ፈሪሶ ያ-አባሀወስ» ብሎ በቡጢ አጎነው:: መደዳ የተቀመጥነው እግራችን ላይ ወደቀ:: ጥሩ አጋጣሚ ሆነልኝ:: መቼ እንደ ሚቀጥሉት ባይታወቅም ለጊዜው የእነሱም ወሬ ተቋረጠ:: እኔም ከውሸት እንቅልፌ ነቃሁ::

«ምነው ግሩሜ አመመህ እንዴ? ወይስ ደከመህ? በጊዜ ተኛህ?» አለች ሰናይት:: አለመተኛቴንና ስሰማቸው እንደነበር ብነግራት ምን ሊሰማት እንደሚችል እያሰብኩ «በጣም ደከመኝ» አልኳት:: መቼስ ይሉኝታ ያጠቃን የለ? የዘቀጠ የጀብድ ወሬያቸው ጆሮዬን ሲያበላሸው ቆይቶ እኔው አፍሬ እንዳያፍሩ ስል ዋሸሁ:: በመሀል በመሀል እየተጨዋወትን አብዛኛውን ጊዜ ግን ግርምቴ በተፈጠረብኝ ስሜት በዝምታ እንደተሸበብኩ ጉዞው ቀጠለ:: ከፀጥታው ብዛት የተነሳ የባህሩ ውሀ የጀልባው ሽክርክሪት ሲቀዝፈው የሚያወጣው ድምጽና የሞተሩ ድምጽ ብቻ የሚሰማበት ጊዜ አለ:: የጀልባው ሞተር ተለውጦ የኤንትሬ ከባድ መኪና ሞተር ነው የገጠሙለት:: ልክ ገጠር ያለ በናፍጣ የሚሰራ ወፍጮን አይነት ድምጽ አለው:: ለሞተሩ ከፀሀይና ዝናብ ከለላ ሰርተውለታል:: ከላዩም ጋርደውት እንደመኝታ ይጠቀሙበታል:: አንድ በርሜል ናፍጣ መጠባበቂያ ይዘዋል:: በመሀል እያቆሙ ይሞላሉ::

ቀና ብዬ ሳይ ሰማዩ በባለሞያ የተንቆጠቆጠ ውብ ጥበብ የፈሰሰበት ይመስላል:: ጨረቃዋ የሙዝ ቅርጽ ይዛ «አለሁ» የምትል ትመስላለች:: ከዋክብቱ አጅበዋት «...አሁን ደመቅሽ አበባዬ..» የሚሉ ይመስላሉ:: እኛ ተፋፍገን 16 ሰው በምትጭን አሳ ማስገሪያ ጀልባ ላይ 126 ሰው ተጠቅጥቀን ስቃያችንን እናያለን:: ጨረቃዋ ደግሞ ያን በሚያክል ቦታ ተንሰራፍታ በኮከብ ታጅባ ትጠቅሰናለች:: አስቀናችኝ:: በእውነት አስቀናችኝ:: በማይቀና ቀናሁ አይደል?



## ሌሊት 10 ሰዓት ተኩል አካባቢ

ከፊት የነበረችው ጀልባ ቆማ ጠበቀችን:: የእኛዋም ቆመች:: ምን እንደሚሉ እንጃ ያወራሉ:: መደማመጥ ባልሰፈነበት ሁኔታ በጩኸት ያወራሉ:: ጀልባዎቹን አጠጋጉና እኛ ጋ ካሉት ግማሾቹ ዘለው ወደዛኛው ጀልባ ሄዱ:: መፍቻ ይቀባበላሉ:: ብረት አቅልጠው መጥረቢያ የሚሰሩ ይመስል ይቀጠቅጣሉ:: ብልሽት እንዳለ ተረዳሁ:: «ኦ..አምላኬ አውጣን» አልኩ:: አንደኛውን ጀልባ ለመስራት ረጅም ሰዓት ታገሉ:: ጀልባው መስራቱን ሳይተማመኑ ያን ያህል ሰው ጭነው ባህር ለማቋረጥ መሞከራቸው ምን ያህል ህይወታቸውን ቢጠሉ ነው?

ድቅድቁን ጨለማ ደብዛዛ ብርሃን ያጎናፀፈችው ጨረቃ ምስጋና ይግባትና በአጠቃላይ ያለነውን ሰዎች ብዛት ለማየት አገዘችኝ:: ወንድሜ የጠፋብኝ ይመስል አይኔን እያንከራተትኩ ጅብሪልን እፈልገው ጀመር:: ላየው ግን አልቻልኩም:: ሌላ ጀልባ...የትኛው ላይ እንደሆነ ግን አላውቅም:: አሁን ተበላሽቶ የቆመው ላይ ይሆን? ፈጣሪዬ አውጣን አልኩ:: ፍርሃቴ ከልክ በላይ ሆኗል:: የተበላሸውን ለመስራት ሲታገሉ መንጋት ጀመረ:: ሶስተኛው ጀልባ ከኋላችን ቢደርስም በቅርብ ርቀት ቆመ::

ሲነጋጋ ገመድ አውጥተው የተበላሸውን እኛ ያለንበት ጀልባ ላይ አሰሩና መጎተት ጀመሩ:: «እነዚህ ሰዎች እብድ ናቸው:: ሁለቱም ቢበላሽ ጥግ አስይዤ ላቁም የሚባልበት መሬት ላይ ያሉ መሰላቸው እንዴ? ተያይዘን- መስመጣችን መሆኑን አያውቁም» አለ ከፊቴ ያለው ልጅ:: የውስጤን ነው የተነፈሰው:: ተያይዘን እንዳንሰምጥ ፍርሃቴ ቀላል አልነበረም:: ጨረቃዋ መንጋቱን አላወቀችም መሰለኝ ብርሃኗ ደብዝዞ ትታያለች:: «ሲምቦሊክ ነው» አልኩ ለራሴ፣ የእሷን አለመግባት ከእኛ አለመስመጥ ጋር ላቆራኘው ፈልጌ:: ፍጥነት ቀንሰው ወደ ተኩል ሰዓት ከተጓዝን በኋላ ገመዱ ተፈታ:: ውስጤን የሸበበው ፍርሃትም አብሮ ተፈታ:: ጭንቀቴ ለጊዜው ለቀቀኝ:: ፍርሃቱ ቢለቀኝም ሌላ ጭንቀት፣ ፍርሃት፣ ሀዘን የሚፈጥር ነገር ገጠመን::

«እዩ..እዩ ጀልባዋ ሰመጠች» አለ አንዱ ከመሀላችን:: ቀና ብዬ ሳይ ማመን አቃተኝ:: ሁሉም እየዘለሉ ወደ ባህሩ ይገባሉ:: በጣር ተይዘው ወደ ባህሩ ይዘላሉ እንጂ ማን ያን የሚያክል ባህር ዋኝቶ ሊጨርስ ነው? ግማሾቹ የድረሱልኝ ጥሪ ይጮሀሉ:: ዘለው ወደ ባህሩ የገቡትም ቦጭረቅ.. ቦጭረቅ ያደርጋሉ:: ብቅ ጥልቅ ይላሉ:: የእኛ ጀልባ ጉዞውን ለደቂቃዎች ገታ:: «ለመከራ ተፈጥረን በመከራ ኖረን በመከራ የምናልፍ አሳዛኝ ዜጎች..» ብዙ.. ብዙ አሰብኩ:: እንባዬ ከቁጥጥሬ ውጭ ዱብ ዱብ አለ::

የጀልባው ግማሽ አካል እየሰመጠ ነው::

ባህሩ በደንብ ይታየኛል:: የጀልባው ግማሽ አካል እየሰመጠ ነው:: በጭረቅ..በጭረቅ..ብቅ ሁሉም ውሃው ላይ ነፍሱን ለማዳን ይፍጨረጨራል:: በጭረቅ..በጭረቅ..ብቅ ጥልቅ የሚለው ሰው..ለማዋኘት የሚፍጨረጨረው..ሰቆቃ ያዘለው ድምጽ ሁሉ ነገር እጅግ ያሳዝናል:: በጣም በጣም ያሳዝናሉ የሚለው ቃል ከሚገልፀው በላይ አሳዘኑኝ:: አይናችን እያየ ጀልባ ሙሉ ወገኖቻችን ሲሰምጡ ምንም ማድረግ ባለመቻላችን የሚሰማንን ቁስለት ማን ሊረዳው ይችላል? ቃላት ስንኩል ሆነው የውስጥን ሀዘን እንደማይገልፁ በዚህ ሰዓት ነው የተረዳሁት:: ለዚህ እልቂታችን ለዚህ ስደታችን ተጠያቂ ማነው? ብዙ ነገር በሰከንዶች ውስጥ ታሰበኝ:: አይኔ እንባ ቢያፈስም ሀዘኔ እንኳን ያኔ አሁንስ መች ወጣ? የሰመጠው ጀልባ ዘዋሪዎች ሶስቱም በዋና እኛ ያለንበት ጀልባ ላይ ወጡ:: ከዚህ በኋላ ውስጤ በፍርሃት ይርገደገድ ጀመር:: ዕጣ ፋንታቸው ምን ይሆን? የእኛ ጀልባ ጉዞውን ቀጥሏል:: ለአይኔ እየራቁ.. እየራቁ ከአይናችን ተሰወሩ:: በልቤ ግን እያሰብኳቸው ነው:: እንኳን ያኔ አሁንም ያን ትዕይንት ሳስታውስ ስቅጥጥ ይለኛል::

በዚህን ጊዜ ሰናይትና ጓደኛዋ አለም ዘጠኝ ብለው እንቅልፋቸውን ያጣጥማሉ:: ጉልበቴን ተንተርሶ የተኛው ሶማሌማ ለእንቅልፉ ማጀቢያ ያዘጋጀውን ሳውንድ ትራክ/ማንኮራፋት/ ቅኝቱን እየቀያየረ በረጅሙ፣ በአጭሩ እያደረገ ለቆታል:: መታደል ነው:: ሰው ህይወቱን ሽጦ በዚህ ባህር ላይ እየተሻገረ እንዴት ይተኛል? መንፈስ-ጠንካራነት ነው ልበ-ደንዳናነት? እኔ በበኩሌ ትንሽ ጭንቀት ወይም ሀሳብ ካለብኝ እንቅልፍ ዝር አይልብኝም::

## እሁድ ጠዋት

እሁድ ጠዋት... ላለለት በሀገሩ ላለ ሰው ቤተክርስቲያን ሄዶ ማስቀደሻው ሰዓት ነው፣ ላደለው ቤቱ ያለ የንጋትን ጣፋጭ እንቅልፍ ያጣጥማል:: ስራ ያለውም ቁርስ መብያው ሰዓት ነው:: እኔ ግን ባየሁት ሰቅጣጭ ነገር ደንዝዤያለሁ:: ቶሎ..ቶሎ..ገጭ ገርገጭ የማደርጋት ውሀ ሂደቷን ጨርሳ መውጣት ፈለገች:: «እንዴት ይሆን መንገዱን የማመቻችላት?» ስል አሰብኩኝ:: ሌሊት ላይ ውሀ ባመጣንበት ባዶ ላስቲክ ሞልተው ወደ ባህሩ ሲያሽቀነጥሩ ማየቴ ትዝ አለኝ:: እኔም ባዶ ላስቲክ ነበረኝና ተንፈስ አልኩባት:: ተንቅሳቃሽ ሽንት ቤት መሆኗ ነው::

«ሰላም ሁኚ ሽንቴ ለህንድ ውቅያኖስ ቆሪጥ ግብር..» ብዬ ቱርር.. አደረኳት-ላስቲኳን:: የህንድ ውቅያኖስ ቆሪጥማ አይናችን እያየ ይህን ሁሉ ወገናችንን በልቶ የለ? ሀሳቤ በየቦታው እየሄደ መዳከሩን ቀጠለ «ሴቶቹስ? ሽንታቸው ሲመጣ እንዴት ይሆናሉ?» አሰብኩ:: ሀሳብና ጭንቀቴን ተከትዬ በሚመለከተኝም በማይመለከተኝም ጉዳይ ብዙ ኳተንኩ:: ዛሬ እነዚያን ሁሉ ጭንቀቶች ማስታወስ አልችልም::



ጉዞው ቀጥሏል:: እሁድ ወደ ስድስት ሰዓት ላይ ከላይ በፀሀዩ ንዳድ ነፍረናል:: ከታች መቀመጫዬ አካባቢም ባስ ያለ ሙቀት ተሰማኝ:: ትንሽ ቆይቶ ደግሞ ቀዘቀዘኝ:: በትክክል ልብሴን ያለፈ እርጥበት ተሰማኝ:: «ሰናይት ከየት ነው ውሀ ተደፍቷል ወይም ገብቷል:: ረጠበኝ..» ተናግሬ ሳልጨርስ ሳቋን ለቀቀችው:: ስለሳቀችብኝ ተናደድኩ:: የሆነ ስህተት የሰራሁ ወይም የተናገርኩም መሰለኝ:: «ምን ያስቅሻል?» ድጋሚ ሳቀችብኝ:: አልማዝም እሷን ተከትላ ሳቀች:: የሆነ ነገር እንዳሳቃቸው ገመትኩ:: ከፊቴ ከተቀመጡት ሶማሌዎች አጠገብ የተቀመጠ አንድ የሐረር ልጅ «ሴቶቹ ሽንታቸውን ሸንተው ነው» ሲል ነገረኝ:: ይኸኔ እኔም በመታሰሴ ሳኩኝ:: «እስከአሁን አልሸናችሁም ነበር ማለት ነው? ከሸናችሁ ታዲያ እንዴት አልታወቀኝም?»

«ጠዋት ላይ አልታወቀህም ነበር?»

«ኧረ አልታወቀኝም ሸንተሽ ነበር እንዴ ሰኒ?»

«ታዲያስ!!» በጣም ብርዳማ ጠዋት ስለነበር ይሆናል ያልታወቀኝ የሚል ሰበብ ለራሴ ሸለምኩትና

«አሁንስ ማነው?» ስል ጥያቄዬን አስከተልኩ:: ሰናይት ድምፅዋን ወዳጠፋችው ጓደኛዋ በጣትዋ ጠቆመችኝ:: አልማዝ ሚጢጢዬ ሀፍረት ቢጤ ለጊዜው ሽው አለቻትና አቀረቀረች:: እጥፍጥፍ ብዬ የተቀመጥኩበት እግሬ ከመደንዘዙ ጋር ሽንቱ መቀመጫዬን ስላቃጠለኝ ሰውነቴን ላፍታታ ቆም አልኩ:: ከየት እንደመጣ ያላየሁት ሶማሌያዊው የጀልባ ዘዋሪ በያዘው ዱላ አናቴ ላይ ነረተኝ:: ዞሮብኝ፣ ልጆቹ ላይ ወደኩ:: ጀልባዋን የሚዘውሩት ሁሉም ሽጉጥ፣ ጩቤ የታጠቁ ናቸው:: የእኔ መፍጨርጨር ምን ሊረባ ብዬ ዝም አልኩ:: ራሴ ላይ የመታኝ ማዞር ብቻ ሳይሆን ደሜ ተንዠቀዠቀ:: ከሙቀቱ ጋር አልቆም አለ:: አንዱ ሶማሌ የሰናይትን ሻርፕ ተቀበለና ጫፉን ይዞ ወደ ባህሩ ወርውሮ አራሰው:: በኋላም አናቴ ላይ እንድይዘው ሰጠኝ:: ውሀው ጨዋማ ስለሆነ የማቃጠሉን ነገር አትጠይቁኝ:: እልህም ውስጤን ይንጠው ጀመር:: ግን ከሀገሬ ስነሳ ህይወቴን አድናለሁ ብዬ ነውና የባሰ ህይወቴን እንዳላጣ ዝምታን መረጥኩ:: ገለው ወደ ባህር ቢወረውሩኝ ማን ይጠይቃቸዋል? ግን ዝምታዬም ቢሆን ያመጣው ነገር የለም::

አንደኛው ሀሺሹን እያጨሰና ዱላውን እየነቀነቀ ወደ እኔ መጣ:: ወይ ጣጣዬ ደግሞ ምን ሊለኝ ነው? አመጣጡ ሊማታ ስለሚመስል ተሸማቀቅኩ:: እሱ ግን የያዘውን ሀሺሽ ቁስሌ ላይ ተረኮሰልኝ:: መጀመሪያ ላይ ቢያደፋፍረኝ ብዬ ያጨስኩት ሀሺሽ አመዱ ለቁስሌም ደረሰው:: አጨስ እንደሆነ ጠየቀኝ::

«አዎ!..» አልኩት አሁንም ድፍረት እንዲሰጠኝና ውስጤ የሸመቀውን ፍርሃት ፍርሃት የሚል ስሜት ለመቅረፍ አስቤ:: ሰጠኝ:: ደጋግሜ ሳብኩት ምን እንደተሰማኝ አሁን ትዝ ባይለኝም ራስ ምታቱ እንደባሰብኝ ግን አስታውሳለሁ:: ደሜም ይብስ መፍሰሱን ቀጠለ:: ከብዙ ትግል በኋላ እንደ ምንም ደሜ መፍሰሱን አቆመ:: ተመስገን!!!

በቀጣዩ መሬት የመርገጥ ጉጉት ሰቅዞ ያዘኝ:: አቤት!!..ያኔ የፀለይኩት ፀሎት.. እስከዛሬም የያዘኝ እሱ ነው ማለት ይቻላል:: በዚህ የባህር ጉዞ ላይ ብዙ ነገሮችን ለመታዘብ ብችልም የአንዱ ልጅ ነገር ግን ሁሌም ይገርመኛል:: ልብሱን አወላልቆ ራቁቱን ቆመ:: እሱን ሲሆን ሳይመቱት እየሳቁበት ዝም ማለታቸው ገረመኝ:: በኦሮሚኛና በሶማሊኛ እየቀበጣጠረ ዘሎ ወደ ባህሩ ገባ:: አጠገባችን ያለው ልጅ «እዚህ ሱቅ ደርሼ ሲጋራ ገዝቼ ልምጣ» ማለቱን ነገረኝ:: ከሶማሊያዊያኑ ናኩዳዎች አንዱ ዘሎ ገብቶ አወጣው:: ገረመኝ:: ሰው ወደ ባህር ይከታሉ ሲባል ነበር የሰማሁት:: ጥሩ ለውጥ ነው:: ደስም አለኝ:: ተለክፎ ነው ወይስ ተጠርቶ ምን ሆኖ ነው ዘሎ ወደ ባህር የገባው? እንዴትስ አዘኑለትና አወጡት? መልስ የሌለው ጥያቄ ሆነብኝ:: አጠገቤ የተቀመጠው ልጅ ግን አዝነው ሳይሆን ምክንያቱ ሌላ ነው አለኝ:: «ሌሊት እዛ ላይ ውጣ ሲለው ነበር አይተኸዋል?..» ሲል ጥያቄ አከለልኝ:: አለማየቴን ነግሬው ከጥያቄው በስተጀርባ ያለውን እውነት ለማወቅ ስለፈለኩ «...ያ-የሚተኙበት አይደል?» አልኩት::

«እኔም እኮ ያልኩህ እሱን ነው:: ታዲያ ምን ሊያደርጉ ውጣ ይሉታል?» ሲል ዳግም ጥያቄ አቀረበልኝ:: አሁን የገመትኩት ነገር አለ:: ግን እንዴት ይሆናል ብዬ ላስብ?..እሱው እስኪነግረኝ ጠበኩት:: «ምን ሊያደርግ ያስወጡት መሰለህ?..» ግምቴን እንድነግረው የፈለገ መሆኑ ቢገባኝም ነገር ማገንገኑን አልወደድኩለትም::

‹‹ስለተጠቀሙበት ነው አዝነው ማውጣታቸው..ወይም ዛሬም ሊጠቀሙበት ፈልገውት ይሆናል::..›› ወንድን ወንድ ተጠቀመበት መባሉ ያሳፍራል:: እነሱ ጋ ግን እንደቀላል አይተውታል መሰለኝ:: እንደዛ ባይሆን ያሳፍራል:: እነሱ ጋ ግን እንደቀላል አይተውታል መሰለኝ:: እንደዛ ባይሆን ይህ ሁሉ ሰው ባለበት እንዴት እንዲህ ያደርጉ ነበር? መቼም ለእኛ መስማቱ ራሱ ያሳፍራል:: ልጁስ በዚህ ችግር ታላቅ ሀፍረት ወድቆበት ይሆን እንዴ ወደ ባህሩ የገባው? ነገሮች ተደራርበውበትም ይሆናል:: ጀልባው ላይ ካየኋቸው ነገሮች ሌላው ደግሞ ጀልባው ውስጥ የሚገባውን ውሀ የሚመጠው ሞተር አይሰራም:: አፉ በተቆረጠ ጀሪካን በሰው እየተቀዳ በቅብብሎሽ ይደፋል:: ሞተሩ የራሱ ሳይሆን የከባድ መኪና ሞተር በመሆኑ ጪኸቱ የገጠር ናፍጣ ወፍጮ አይነት ነው:: ለጆሮ ይቀፋል:: መጀመሪያ ጀልባው ላይ እንደወጣሁ ያስገቡኝ እዛ ውስጥ ነበር:: ጉድጓድ ነገር ውስጥ ከገቡት አንዱ ድክም ብሎ ራሱን ስቶ ወደላይ ሲያወጡት ባላንስ ካልሆነ





እንሰምጣለን፣ ግርግር አታብዙ ብለው ሲያነሱት ወደ ንፋሱ ሲያስጠጉት መስሎኝ ነበር:: ወደ ባህር ከነነፍሱ ጣሉት::

በጣም ደነገጥኩ:: እስከ አሁን ውሀ ብቻ ነው የምጠጣው:: ያለ እህል 40 ሰዓት ያህል ተጓዝኩ:: ገና መጀመሪያ ላይ ከያዝኩት አቡ-ወለድ ብስኩት ብቀምስ ሁለቱ ወደ ላይ ስላለኝ መብላቱን ፈርቼዋለሁ:: በበላሁ ቁጥር ስስ ፌስታል ፍለጋ መሯሯጥ ሆነብኝ:: እንቅልፉ ሲደፋኝ እያንጎላጀጀኝ ነው:: አቅም አጥቻለሁ:: እኔ ደግሞ እንዳይወስደኝ እየታገልኩ ነው:: የሚሆነውን ሁሉ አፍጥጬ እያየሁ ይሁን ባይ ነኝ:: ሰውነቴ ሁሉ ዛል አለብኝ:: ከላይ ጸሀዩ ደግሞ መድከማችንን አውቆ የበረታብን መሰለኝ::

## አርባኛው ሰዓት:-

ጀልባው ጉዞውን ሊያጠናቅቅ ከአንድ ሰዓት በላይ ይቀረዋል:: አቅጣጫ ስተዋል:: ባይስቱ ኖሮ ከ36 እስከ 38 ሰዓት ብቻ መጓዝ በቂያችን ነበር:: አንድ ጀልባ ወደ እኛ ስትከንፍ መጣች:: ነጫጭ የለበሱ መሳሪያ የያዙ የየመን ባህር ሀይል ባልደረቦች ናቸው:: መሳሪያውን ወደ ላይ ያንጣጡት ጀመር:: ሶማሊያውያኑ ምንም ምላሽ አልሰጡም:: የባህር ሀይል ጀልባዎቹ ቁጥር እየጨመረ መጣ:: መሳሪያውን እያንጣጡ ከበቡን:: እጅ አንሰጥም ብለው ከተታኮሱ አለቀልን ስል አሰብኩ:: ሶማሌዎቹ ግን አንድም ሳይተኩሱ ጀልባውን ገልብጠው ለማምለጥ ነው የፈለጉት:: ትግልም ጀመሩ:: በቢጫ የዘይት ጀሪካን ቁራጭ እየተቀዳ የሚደፋውን ወደ ጀልባዋ የሚገባ ውሀ እንዳይቀዳ ከለከሉ:: ባህር ሀይሎቹ ሶማሊያውያኑ ላይ ደግነው ጉዞ ተጀመረ:: ለመገልበጥ የሚያደርጉት ጥረት ይበልጥ አሳሰበኝ:: የፈለገ ዋና የሚችል ሰውም ቢሆን ዋኝቶ መሬት መርገጥ የሚችል አልመሰለኝም:: የእኔ የዋና ችሎታ ደግሞ ብዙም የሚያወላዳ አይደለም:: እነሱ በጣም የሚመኩበት የዋና ልምድ አላቸው:: ሴቶቹንም አሰብኩ:: እንዴት ሊሆኑ ነው?

መሬት የሚባል ነገር አይታይም:: እኔን ዘንግቼ ስለሰው አስባለሁ ራሴስ እንዴት ልሆን ነው? የፈለገ ዋና ብችል ከዚህ የመውጫ አቅም ኖሮኝ አልወጣም:: አሁን ሲከፋኝ የልመና እሩምታዬን የምተኩስበትን አቅጣጫ አነጋጥጬ አየሁ:: ተጨማሪ ልመናዎች ላኩኝ:: ‹‹መቼም በዚህ ሰዓት እያየኸኝ ነው ያን ሁሉ ፈተና እንድወጣ አድርገህ ባህር ላይ አታስቀረኝም:: ፈጣሪዬ ሆይ ፈርቻለሁና ከዚህ አውጣኝ:: ብትፈልግ መላዕክትም..›› ድው..ድው.. ድው..ተኩሱ ከፀሎት ልመናዬ መንጥቆ አወጣኝ:: አቋረጡኝ ያቋርጣቸውና:: ነጭ የለበሱት የየመን ባህር ሀይሎች ጀልባቸውን አስጠግተው ወደ እኛ ጀልባ ዘለው ወጡ:: ሶማሊያውያኑ ሊገለብጡን እንዳሰቡ አውቀዋል:: መሳሪያ ደግነውባቸው ተቀጣሉ:: ሶማሊያዊያኖቹ ናኩዳዎች

ሆን ብለው ጀልባዋን ለማስመጥ ሙከራቸውን እንደቀጠሉ ባህር ኃይሎቹም እየተኮሱ፣ እየከለከሉ መሬት ልንረግጥ ጥቂት ሲቀረን ጀልባዋ ሙሉ ለሙሉ መስመጥ ጀመረች:: እየዘለልን ወደባህር መግባት ግድ ሆነ:: የባህር ሀይሎቹ ትናንሽ ጀልባዎች የሚችሉትን ያህል በተለይ ሴቶቹን ቅድሚያ እየሰጡ ማዳኑን ተያያዙት:: የፍርሃቴን መጠን ዛሬ ስናገር ቀንሼዋለሁ ወይ ቃል አጥቼለታለሁ እንጂ እንዲህ በዋዛ ፈራሁ ተብሎ አይገለጽም::



ይህች ቦታ ሁሉም መሬት በመርገጡ ፈጣሪውን የሚያመሰግንበት ቦታ ነው:: የአካባቢው ነዋሪዎች የሬሳ ሽታ አሳለቀምፕ ስለሚሳቸው በየጊዜው ባህሩ የሚተፋውን ሬሳ በመቅበር ተግባር ላይ እንደተጠመዱ ይናገራሉ:: ዘውትር ሙትና ቁሜ የምታስተናግድ፣ ለቅሶና ደስታ የሚሰማባት መርገምተ ሞት የሚበርቅባት ..ብዙዎች ተሳቀው የሚያልፉባት ሽቡዋ የተባለችው የየመን ባህር ዳርቻ ናት::

ውሀ ጠጥተው ሆዳቸው የተነፋ..ሰምጠው የቀሩ ቁጥር ትንሽ አይደለም:: ትንሽዬ ዋና በመቻሌ የያዝኳትን ቦርሳ በጀርባዬ ይዤ ተፍጨረጨርኩ:: እግሬ አልታዘዝ ብሎኝ በእጄ ብቻ ነበር የምቀዝፈው:: ያነገብኩት ቦርሳ አመለጠኝና ለማዳን ስል ልሰምጥ ነበር:: ብቅ ጥልቅ ብዬ የተወሰነ ውሀ እንደጠጣሁ ራሴን ለማዳን ስታገል ባህር ሀይሉ እጄን አፈፍ አርጎ አንጠለጠለኝ:: ጀልባቸው ላይ ወጣሁ:: መሬትም ረገጥኩ::

አዎ! ህይወቴ ተረፈችና መሬት ለመርገጥ በቃሁ:: ከረገጥኩ በኋላ በመጀመሪያ ፈጣሪዬን ቀጠልኩና የየመን ባህር ሀይሎችን አመሰገንኩ:: ከዚህ በኋላ የፈለጉትን ያድርጉኝ ብዬ ሰውነቴን ማሳረፍ ፈለኩ:: ለ41 ሰዓት ኩርምት ብዬ የተቀመጥኩበት እግሬ ውሀውን ለመቅዘፍ አቅቶት በእጄ ብቻ ነበር የተጠቀምኩት:: ገና ከመነሻው አሞኝ ስለነበር ባዶ ሆዬን ነው የተጓዝኩት:: ርሀብ አጥወልውሎኛል:: ውሀ ግን ብዙ ጠጥቻለሁ:: ሽንቴንም ሁለት ሶስት ጊዜ በላስቲክ እያደረኩ ወደ ባህር ቱር!. አድርጌያለሁ::

አልፎ..አልፎ በርቀት ነጥብ ያህል ሆና ትታየን የነበረችው ሁለተኛ ጀልባ ከቆይታ በኋላ በየመን ባህር ሀይሎች ታጅባ መጣች:: እስካሁን





ተደናግጨ ይሁን ተዘናግቼ ያላስታወስኩት ጅብሪልን ጀልባዋን ሳይ አስታወስኩት:: ያ-እግሩን የሚያመው ልጅስ? ሁለት ልጆች ታቅፋ የነበረችው እርጉዝስ? ሰቀጠጠኝ ለምን ይሆን?

ጀልባው ለመሬት ቀረብ ብሎ በመቆሙ ብዙም ጉዳት ሳይደርስባቸው መሬት ረገጡ:: ይኸኔ ጅብሪልን አየሁት:: የትንሽ ቀን ጓደኛዬ ሳይሆን ወንድሜ መሰለኝ:: በጣም ተደሰትኩ::

ይበልጥ የገረመኝ ደግሞ እሱም ገና መሬት ሳይረግጥ በአይኑ ሲፈልገኝ መቆየቱ ነበር:: ሲያየኝ ፈገግ ቢልም ፈገግታው በድካም የዳመነ ነበር::



# - 8 -

# የየመን መሬት ላይ

ሰውነቴ እምጦ ፍርሃት ወልዶ
ፍርሃቴ ተጨንቀ በፍርሃት ተርገድግዶ
እምጠናል እልቅሰናል እምጠናል
ለካ ወንድም ያምጣል ያማምጣል
ጭንቅ ሲመጣ ነገር ይገሰበጣል

ጅብሪል ሮጥ..ሮጥ ብሎ ገና አጠገቤ እንደደረሰ «አል-ሀምዲሊላህ ተጨንቄ ቆየሁ የሰመጠው ጀልባ ላይ የነበርክ መስሎኝ ነበር::»

«የሰመጠው?..ጀልባ ላይ?..አይታችሁታል እንዴ?»

«አዎ!..እያየን ሰመጠች:: ትላንት ጠዋት 4 ሰዓት አካባቢ ነው የሰመጠችው» ለካ መከራም ሲበዛ ልብ ያደነድናል:: ለዘብ አርጎ ነገረኝ:: ብርክ ያዘኝ:: ሰውነቴ ተንቀጠቀጠ ውስጤን ሲያጥወለውለኝ ይታወቀኛል:: ቀና ብዬ ወደ ሰማይ አየሁ:: ስለተረፍን ፈጣሪዬን አመሰገንኩት:: የሞቱት ወገኖቼ..ወንድሞቼ ግን በሀዘን ውስጤን አቆራመዱት:: «ምነው ፈጣሪ መከራውን አበዛህብን እኛ ፍጡሮችህ አይደለንም? ምነው ረሳኸን..» መልስ አልባ ጥያቄዎቼ ብዙ ናቸው:: «ለመከራ ተፈጥረን፣ በመከራ ኖረን፣ በመከራ የምናልፍ አሳዛኝ ዜጎች..ምነው ዘነጋኸን?..» ብዙ..ብዙ አሰብኩ:: ጠየኩት:: ለምን ተዳፈርከኝ፣ ማን ጠያቂ አደረገህ ብሎ ነው መሰለኝ ይበልጥ ቀጣይ መከራዬን በደንብ አበዛው::

ስንነሳ በሶስት ጀልባ ነበርን:: መሀል ላይ አንዱ ተበላሽቶ ሁለተኛው ጀልባ ሲጎትተው ነበር:: አሁን መሬት የረገጥነው ሁለቱ ጀልባ ላይ ያለን ሰዎች ነን::





ጅብሪል ያየውን እየነገረኝ መሆኑ ነው:: «..አንደኛው ተበላሽቶ ሁለተኛው ጀልባ በገመድ ሲጎትተው ነበር:: እኛ ያለንበት በርቀት ቆሞ ነበር:: ሞተሩ ተነሳላቸው..» አለ:: መልስ አልሰጠሁትም:: ሞተሩ ተነስቶላቸው ሳይሆን መስመጥ ሲጀምር ገመዱን እንደበጠሱባቸው አላወቀም ማለት ነው? አልኩ በውስጤ ለራሴ:: «ናፍጣ የተሞላበት በርሜል ላይ ነበር የተቀመጥኩት:: ባህሩ በደንብ ይታየኛል:: እኛ ስንቃረብ የጀልባው ግማሽ አካል እየሰመጠ ነው:: ሁሉም ውሃው ላይ ነፍሱን ለማዳን ይፍጨረጨራል:: በጣም..በጣም ያሳዝናሉ:: ሁሉም ቢጮሁ ሁለቱም ጀልባ አልጫናቸውም:: እንዲያውም ጥለዋቸው መጡ::..» ረገጥ እያደረገ የሀዘን ድባብ በተላበሰ መልኩ ነው ያወራልኝ:: ምን ማለት እንዳለብኝ ግራ ገባኝ:: ምንም አላልኩትም:: «ሁሉንም እየተከታተልኩ ነበር አይቻለሁ:: ጭካኔ ነው በጣር ላይ እያዩ ትተዋቸው..» ሳግ አላስጨረሰኝም:: በሀሳቤ ድቅን ሲሉብኝ እንባዬ ቀድሞ ቁልቁል ተምዘገዘገ::

«ምን ያርጓቸው? ጥፋቱ መጀመሪያ ነው:: ከአግባብ በላይ ባይጭኑ የተወሰነ ሰው ማዳን ይቻላቸው ነበር» አለኝ:: ልክ ነበር:: መጀመሪያ ጠቅጥቀው ባይጭኑ የተወሰነ ሰው ማትረፍ በቻሉ:: የእኔና እሱ ይህን ማሰብ ምንም የሚያመጣው ነገር ስለሌለ ማዳመጡን ትኩረት አልሰጠሁትም:: እንዲያውም አዳምጥ የነበረው ውስጤን ነው ማለት እችላለሁ:: መቆሙ ስላቃተኝ ተቀመጥኩኝ:: ግን ተቀምጬም ደከመኝ:: ሰውነቴ ዛለ፣ አልታዘዝህ አለኝ:: ወታደሮቹ ደግሞ አስነስተው አሰለፉን:: በውስጣችን ለምን ይሆን ማለታችን አልቀረም:: በሰልፉ መሰረት ቁጭ አደረጉን:: አንድ ሳይቀር የያዝነውን እቃ ሁሉ መፈተሽ ጀመሩ:: እጅ ላይ ያለ ሰዓት ያስፈታሉ:: ገንዘብ የሶማሊያ ሽልንግ እንኳን ሳይቀር ይወስዳሉ:: አመል ሆኖ እንጂ ከመገልገያነት አንጻር ምንም አይሰራላቸውም:: የያዝኩትን ብር ቀስ ብዬ አሸዋውን ጫር...ጫር አድርጌ ቀበርኩት:: ፈትሾኝ ሲያልፍ ቀስ ብዬ አውጥቼ ኪሴ ከተትኩት:: እነ ሰናይት የያዙትን በሶ አይተው «ሀሺሽ...»[7] እያሉ ፖሊሶቹ ጮሁ:: ከመሀላችን አረቢኛ የሚችሉ ልጆች ሀሺሽ አለመሆኑን አስረዷቸው:: እየቀመሱም አሳዩዋቸው::

እነሱም ቀመሱ::

ብዙ ጊዜ በባህር የሚገቡ ህገ-ወጥ ተጓዦች ሀሺሽ ይዘው ስለሚገቡ ነው አብጠርጥረው መፈተሻቸው:: በዚህን ጊዜ ነው እነሰናይት በህይወት መትረፋቸውን ያወኩት:: ደስ አለኝ:: ተነስቼ ወደ እነሱ መሄድ ፈለኩ:: ግን

---

*[7] ፖሊሶቹ ሀሺሽ..ሀሺሽ..እያሉ እንደዛ የሆኑበትን ምክንያት ሰነዓ ከገባሁ በኋላ ነው ያወኩት:: ሲጀናል መርከዚ (ከርቸሌ እንደምንለው መሆኑ ነው) በሀሺሽ ሰበብ የታሰሩ ከ25 ልጆች በላይ አይቻለሁ:: ሞት ተፈርዶባቸው ወደ እድሜ ልክ የተቀየረላቸው ዘጠኝ ልጆች አውቃለሁ::*

አቅም ከየት ይምጣ? ሀሺሽ ያሉት በሶ እነሱ ጋር መኖሩን ማወቁ የርሀብ ስሜቴን ኮረኮረው::

የመጣንበት ጀልባ ሳይሰምጥ የቀረው አካል ትንሽ..ትንሽ ይታያል:: የመጣንበት ጀልባ ሳይሰምጥ የቀረው ... አካባቢውን ሲያስስ የቆየው የየመን ባህር ሀይል ጀልባ ወደ እኛ መጣ:: በዚህን ጊዜ የተያዙት የሁለት ኢትዮጵያዊያን ሬሳ ይዞ ነው የተመለሰው:: ከመካከላቸው ጀልባውን ሶማሊያዊያኑን በሌላ አቅጣጫ አሰልፈዋቸው ነበር:: ሲዘውሩ ከነበሩት ውስጥ አንዱ ተነስቶ ወደ እኛ መጣና ሁላችንንም ቆጠረ:: «ተጨማሪ 6 ሰው ይጎላል» አለ::

ወይኔ ባህር በልቷቸዋል ማለት ነው:: ከሁለቱ ጋር አጠቃላይ 8 ሰው ሞቷል ብዬ አሰላሁ:: ሬሳውን ስናይ ሁላችንም ስለተላቀስን የመኒዎቹ ባህር ኃይሎች ግራ ተጋቡ:: እነሱ የሚያውቁት ቤተሰብ ላልሆነ ሰው «አሳህ ይርሀመው» ብለው ዝም ነው:: «እነዚህ ሁሉ ለሞቱት ቤተሰብ ናቸው? ለምንድነው የሚያለቅሱት?» ብለው መጠየቃቸውን ስሰማ በጣም ነበር የገረመኝ:: ትንሽ ቆይተው አሰልፈው ሊወስዱን ሲሉ ቋንቋ የሚችሉት ሬሳውን እንቅበር ሲሉ ጠየቋቸው:: ፍቃደኛ ሆኑ::



ብዙ ጊዜ ሸቡዋ የተባለ አካባቢ ባህር ውስጥ የሚሰምጠውን ሰው ሬሳ ይተፋዋል:: እነዚህ ሸቡዋ የተባለው አካባቢ ባህር የተፋቸው ሁለት ኢትዮጵያዊያን ናቸው:: ቀይ መስቀል እዚህ ቦታ በየጊዜው ሬሳ ለቀማ ያከናውናል:: የአካባቢው ሰዎችም ሬሳው ያልተነሳ ጊዜ ሽታው ስለሚያስቸግራቸው ይቀብራሉ:: በመቅበር ተግባር ረገድ መሰላቸታቸውን በአንድ ወቅት የቀይ መስቀል ሰራተኛ ያናገራቸውን አስመልክቶ በጋዜጣ የጻፈውን አይቻለሁ:: በአካባቢውከዚህ ጋር ተያይዞ የሚቀለድ ቀልድ ላካፍሉት:-

አሳ ሊያጠምዱ ወደ ባህር ሲሄዱ ጠግቦ ፀሀይ ለመሞቅ የወጣ አሳ ነባሪ አገኙ:: ተረባርበው አውጥተው ሆዱን ሲሰነጥቁት የተገኘው መታወቂያ ብዛት..ሲገለጥ ከራያ፣ ሲገለጥ ከትግራይ፣ ሲገለጥ ከራያ፣ ሲገለጥ ከአርሲ፣ከአርሲ..ከአርሲ..ሐረር..ሐረር፣ ድድጋ..ባሌ...እያለ በመታወቂያ ተሞልቷል:: በሌላው ጎኑ እንደ ጅምላ መቃብር በርካታ ኢትዮጵያዊያን ተቃቅፈው ተኝተዋል:: በህይወት የሉም:: 2






ህፃናት የታጋይ መታወቂያ፣ ጎጃም አዘነ፣ የራያ ጥበብ፣ የኦሮሞ የባህል ልብስ፣ የወላይታ ልብስ ደዘው እየለበሱ እያወለቁ ይጫወታሉ:: የአሳ ነባሪውን ሆድ የሚቀዱትን ሰዎች ሲያዩ እናታችንስ? ብለው ጠየቁ.. «..ቀዶ ሀዘ ጻሲያ ሀበሺ...እንሰልም ሰሰፋራ ሊተጂ..» አሉ ይባላል:: (ደሄስ የሀበሻ ኮሙኒቲ ነው ለኢትዮጵያ ኢምባሲ እንሰጠው ማለታቸው ነው) ይህ ቀልድ ከቀልድነት ያለፈ መረር ያለ መልዕክት አለው:: ግን ቀልድ ይመስላል:: ቀልድ የአመለካከት ነጸብራቅ ነው ማለት ደሄ ነው:: አሳ ነባሪው በኢትዮጵያዊያን ሬሳ ጠግቧል:: ይህ ምን ያህሉን ወገን ባህር እንደሚበላው ገላጭ ነው:: አልባሳቱም ሆነ ባንዲራውን ከራሴ ጥምረ መግለጽ የፈለኩት ምን እንደሚያሳይ ጠቋሚ አያሻም:: ህፃናቱም ተጠቂ መሆናቸውን ያሳያል:: (ፎተው ከኢንተርኔት የተወሰደ ነው)

ቅበሩ ሲሉን የሁላችንም ድካም ወደ ብርታት የተቀየረ መሰለ:: እኔ እንኳን ተነስቼ ወደ እነሰናይት መሄድ ያቃተኝ ብርታት አገኘሁ:: በእጅ አሸዋውን መጫር ተጀመረ:: ሌሎች መቆፈሪያ የሚሆን ነገር ፍለጋ በየአቅጣጫው ሮጡ:: ስንቆፍር ቀድሞ የተቀበረ የሰው አጽም ሁሉ እናገኝ ነበር:: በተገኘው ነገር ሁሉ የተቻለውን ያህል ተቆፈረ:: አቤት ያለ ርብርብ..ትብብር..ወደ ውጭ ማልቀስ የማይሆንልኝ እኔ እንኳን ተሳካልኝ:: ይህ ያላሳዘነ ምን ያሳዝናል? ይህ ያላስለቀሰ ምን ያስለቅሳል? ተንከራተን መጨረሻችን ይህ መሆኑም ጭምር ነው ያስለቀሰኝ:: እንደገና አሰለፉንና ጉዞ ተጀመረ:: ወዴት እንደሚወስዱን አላውቅም:: ማወቅም አይጠበቅብኝም:: ባለቤት እንዳጣ ከብት እየነዱን ነው:: ሰውነቴ አልታዘዝ አለኝ:: መርገድገድ ጀመረ:: እግሬን መሬት ለመሬት እያንፏቀኩ ለመሄድ ሞከርኩ:: ብዙም መንዝ አልሆንልህ አለኝ:: ምን እንደሆንኩ አላውቅም ተዝለፍልፌ ወደኩ:: ልጆቹ እንደነገሩኝ ከሆነ ስወድቅ ድንጋዩ ልቤ ላይ መቶኛል:: ያለው አማራጭ ስለሆነባቸው እኔን ደግፈው መሄድም የእነሱ እዳ ሆነ:: የወሰዱን ወደ ቀይ መስቀል ግቢ ነው:: አናስገባም ስላሏቸው ከግቢ ውጭ ተደረደርን:: ደግፈው የያዙኝ ልጆች የያዝኳትን በባህሩ ውሃ የራሰች ቦርሳ አስደግፈው አስተኙኝ::

ወደ ታሪኩ ስመለስ ራሴን ያወኩት ቀዝቃዛ የጠርሙስ ጭማቂ ነገር ሲያጠጡኝ ነው:: የሰጡኝን ብስኩት ለመብላት ጉሮሮዬ የተጣበቀ ወይም የጠበበ ሁሉ መሰለኝ:: በሌላ በኩል መተንፈስ አቅቶኛል:: ቦርሳዬን ለማዳን ስታገል የተጎነጨሁት የባህር ውሀ ጥሩ ስሜት አልፈጠረብኝም:: ያጥወለውለኛል:: ሆዴን የነፋኝም መስሎኛል:: አቅም አጣሁ ድካም ተሰማኝ:: ለ42 ሰዓት ስንጓዝ ለሰከንድ እንቅልፍ በአይኔ አልዞረም:: ሜዳው ላይ ጋደም እንዳልኩ እንቅልፍ ወሰደኝ::

ለምን ያህል ሰዓት እንደተኛሁ ባላውቅም ወታደሮቹ አንስተው መኪና ላይ ሊጭኑኝ ሲሉ ነው የነቃሁት:: ትላልቅ የጭነት መኪና አምጥተው እየጫኑ «ማይፋ» የሚባል የሶማሊያዎች ማስተናገጃ ካምፕ እየወሰዱን ነበር:: የመጨረሻው መኪና ላይ የመጨረሻ ተጫኝ ነኝ:: ለምን ያህል ሰዓት በምን ሁኔታ እንደተጓዝን ምንም አይነት ትዝታ የለኝም:: በኋላ ባገኘሁት



መረጃ 130 ኪሎ ሜትር አካባቢ ከባህሩ ወይም ቢራሊ ከሚባለውቦታ እንደሚርቅ ለማወቅ ችያለሁ::

«ማይፋ» ካምፕ ስንደርስ ጨላልሟል:: በግምት ሶስት ሰዓት ይሆናል:: ከመኪናው ላይ እንደ ምንም ወርጄ ሰው ወደ ተሰለፈበት ቦታ አመራሁ:: ገና ስወርድ ደጋግፈው ቃሬዛ ላይ ሲያደርጉኝ ደህና ነኝ ብዬ ለመነሳት ስሞክር ተንገዳግጄ አንዱን ይዤ ከመውደቅ ተረፍኩ::

መልሰው አስተኙኝ:: እንደተኛሁ ሳይ ለካ ከእኔም የባሰ አለ:: ወደ 16 ሰው መነሳት እያቃተው በቃሬዛ እየተቀባበሉ አወረዷቸው:: እነሱን ሳይ ደህና ነኝ ብዬ እንደምንም ተነሳሁ:: ለመመዝገብ ወደ ተሰለፉት ሄድኩ:: መዝጋቢው ልክ ከባህር ስንወርድ እንዳየኋቸው ወታደሮች ጉንጬ ተወጥሮ የአፉ አቅጣጫ እስኪንሻፈፍ ጫቱን ወጥቋል:: ቅርፍፍ ማለቱ ያናድዳል:: መቆም አቅቶኝ አስሬ እየተቀመጥኩ ወረፋዬ ከመድረሱ በፊት አዞረኝና ወደኩኝ:: ከዚህ በኋላ ራሴን ያገኘሁት አንድ ፅዳቱ አስቀያሚ የሆነ ክፍል ውስጥ ጉሉኮስ ተሰክቶልኝ ነው:: ደነገጥኩ:: አንድ ሰው ቆሞ አዘቅዝቆ ያየኛል:: ቀደም ብሎ ሲመዘግብ ያየሁት ሰው መሰለኝ:: ሀዘኔታ ተሰምቶት ይሁን አይሁን በማላውቀው ሁኔታ እጁን ግንባሬ ላይ አድርጎ ትኩሳቴን የሚለካ መሰለኝ::

«ከየት ነህ?» አማርኛ ተናጋሪ መሆኑ አስደሰተኝ:: ከሀገሬ ውጭ ቋንቋዬን ተናጋሪ በማግኘቴ ደስ ያለኝ መስሎኛል:: */አሁን እዚህ ጋ ያለውን ነገር ሙሉ ለሙሉ ማስታወስም መግለፅም ይከብደኛል:: እንደ ህልም ነው የሚታወሰኝ::/* «ከየት ነህ?» ጠየቀኝ::

«ከኢትዮጵያ»

«ገብቶኛ ነው በአማርኛ የማወራህ አካባቢህ ማለቴ ነው»

«አዲስ አበባ»

«አዲስ አበባ የት?»

«አራት ኪሎ..»

«ለምን መጣህ?»

«የግል ፕሬስ ጋዜጠኛ ነበርኩ::» ድምጼን ዝቅ አድርጌ ነው የነገርኩት:: ትኩር ብሎ አየኝ:: አስተያየቱ የመገረም መሰለኝ:: አስተያየቱ የገፈተረኝ ይመስል አይኑን መቋቋም አቅቶኝ ፊቴን አዞርኩኝ:: መሬት ላይ በየቦታው ስፖንጅ ፍራሽ ተነጥፎላቸው ተኝተው የሚታከሙ ይታዩኛል:: እኔ በምን እድል አልጋ እንዳገኘሁ እግዜር ይወቅ:: ክፍሉ ህክምና ቦታ አልመስልህ አለኝ:: እስር ቤት ነው እንዳልል ጉሉኮስ ተሰክቶልኛል:: ሁሉም ነገር ህልም ህልም መሰለኝ:: ተጠራጠርኩ::





መልሼ ስዞር እውን መሆኑን ያረጋገጥኩት ያ-ሰው ወረቀት ይዞ ቆሟል:: «ጋዜጠኛ ነኝ ነው ያልከው?» ሲል ጠየቀኝ:: «ማስረጃ አለህ?» አከለበት::

«አዎ!..ማስረጃም አለኝ»

«ጉሉኮሱን ጨርስና አናግረኝ»

«እሺ!..»

የተሰካልኝን ጉሉኮስ ስጨርስ ብርድ ብርድ እያለኝ እየተንቀጠቀጥኩ ላናገረው ብሄድ ራትህን ብላና ተመለስ ብሎ የሰጠኝን ካርድ ነገር ይዤ ምግብ ወደሚታደልበት ቦታ ሄድኩ:: ሩዝ፣ ወተት እና ዳቦ ተሰጠኝ:: ብርታት ነገር ቢሰማኝም ትንሽ ርሀብ ቢጤ ሸንቆጥ ስላደረገኝ ምግብ የምመርጥበት ሁኔታ አልነበረም:: እንጂማ ንክች አላደርገውም ነበር:: ሩዙ በድንች በዱባና ከባሚያ ወጥ ጋር ተለውሶ የተጨማለቀ ነው:: መብላት አይበለው በላሁ::

ስፖንጅ ፍራሽ ታደለን:: የሚፈልግ ገላውን ይታጠብ አለ:: ይሄ መታደል ነው:: ፈጥኜ መጀመሪያ ተሰለፍኩ:: መቼም መፍጠን የሚለው ቃል መስገብገቤን ለመግለጽ ተጠቀምኩበት እንጂ አቅም ኖሮኝ እንኳንስ ልፈጥን ,በቅጡ መራመድም አልችል:: ታጥቤ በኋላ አናግረኝ ያለኝን አማርኛ ተናጋሪ አረብ ፍለጋ ሄድኩ:: አገኘሁት::

«በኋላ አናግረኝ ብለኸኝ..»

«እ..እ..እ..» አላስጨረሰኝም:: «ግባ..»

· ገባሁ:: ማስረጃዬን ለማሳየት የያዝኳን ሻንጣ መሬት ላይ አሳረፍኩና ፍለጋዬን ተያያዝኩት:: በሳሶ እያለሁ ሲያረጉ አይቼ የያዝኩትን ማስረጃ ሁሉ በላስቲክ ጠቅልዬ በሻማ አቅልጬ አሽጌዋለሁ:: ይህ ዘዴ ጠቅሞኛል:: ከላይ ጋዜጦቹ ቢርሱም መሀል ላይ የጠቀለልኳቸው መታወቂያዎች ድነዋል:: ሶስቱን አንስቼ ሰጠሁት::

«ኦ..የጋዜጠኞች ማህበር አባል ነህ?»

«አዎ!..» መታወቂያውን እያየ መጠየቁ ገርሞኛል:: ከአይኑ ይልቅ ጆሮውን ነው የሚያምነው አሰኘኝ::

«የአስኳል ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ነህ?..»

«አዎ!»

«ይሄ የራስህ ድርጅት ነው?» ሶስተኛውን መታወቂያ እያየ ጠየቀኝ::

«አዎ!..ገመና የሚባል ጋዜጣ ነበረኝ::»

«አሳ ነባሪው» ብሎት በሰው ታዝሎ ከንፈሩን መጠጠ:: ያ-እግሩ አልታዘዝህ ብሎት በሰው ታዝሎ የሚሄደው ልጅ ያለኝ ትዝ አለኝ:: የት ይሆን? ወጥቼ ልፈልገው አሰብኩኝ:: «ከንፈር እየመጠጠ ገደሉኝ..» ነበር ያለኝ:: በጣም ልክ ነው የእኛ ሰው ከንፈር መምጠጥ ይወዳል:: አሁን ለእኔም ከንፈር ተመጠጠልኝ:: «ከንፈር መጠጣ ደም መጠጣ ነው..» ያለውንም አስታወስኩ::

«ለማንኛውም እዚህ የምናስተናግደው ሶማሊያዊያንን ነው:: አንተ አደን ወይም ሰነዓ መሄድ አለብህ:: መንገድ ላይ እንዳይዙህ ለአስር ቀን የሚያገለግል ወረቀት ይጻፍልሀል:: ጠዋት 2 ሰዓት ላይ መምጣት ትችላለህ እንዳታረፍድ::» ማስጠንቂያው ሰነዓ የምሄድበት ሳይሆን ገነት የምገባበት ካርድ የሚሰጠኝ ነው ያስመሰለው::

«እሺ!..አመሰግናለሁ» መታወቂያዬን ተቀብዬ ልወጣ ስል «ሰነዓ ከሆነ መሄድ የምትፈልገው አንድ የሚረዳህ ሰው አለ:: ትውልደ ኢትዮጵያዊ ነው እገሌ..የሚባል ታዋቂ ጸሀፊ ነው:: ስልኩን ልስጥህ?»

«እ..እ..እ..አውቀዋለሁ:: መልካም ፍቃድህ ከሆነ እባክህ ስልክ ቁጥሩን ስጠኝ?..» ያን ሀያሲ ለመጀመሪያ ጊዜ ያወኩበት 30ኛው አመት የደራሲያን ማህበር በዓል ትዝ አለኝ:: በ1982ዓ.ም በአዲስ አበባ ስነ-ጥበብና ቴያትር ክፍል የተሰጠውን የቴያትር ጥበብ ኮርስ ወስጃለሁ:: በዛን ወቅት ለመጀመሪያ ጊዜ የሚሰጠውን ኮርስ ስካፈል ነበር የደራሲያን ማህበር ሰላሳኛ አመት የተከበረው:: እዛ እንድገኝ ያደረገን ተስፋዬ ሲማ ነው:: በዚያን ጊዜ ነው ከዚህ ሀያሲ ጋር የተገናኘነው:: ለስነ-ጽሁፍ ካለኝ ቅርበት አንጻር ቦታ ሰጠሁት:: ከዚያም በኋላ የተገናኘንበት ጥቂት የስነ-ጽሁፍ ምሽቶችና ዝግጅቶች ትውስ አሉኝ::

ስልክ ቁጥሩን ተቀብዬ ወጣሁ:: ሰውየው ከንፈር ሲመጥልኝ ያስታወስኩት እግሩን የሚያመው ልጅን ለመፈለግ መዞር ጀመርኩ:: የተኙትንም እየቀሰቀስኩ አየሁ:: እንዲያውም ለምን አየሁት የሚል አጣሁ:: በመጨረሻም ጅብሪልን ቀሰቀስከን ብለው ከሁለት ልጆች ጋር ተጣላሁ:: የሰመጠው ጀልባ ላይ ይሆን? እንጃ አግኝቼው አገዘኝ:: ግን ልጁ የለም::

ከጅብሪል ጋር አጠገብ ለአጠገብ አንጥፈን ጋደም አልን:: እንቅልፍ ሊወስደኝ ግን አልቻለም:: እኛ እንዴት ሆነን እንደተረፍን አስቤ የእነሱ መሀል ባህር ላይ እንዴት ሊሆኑ እንደሚችሉ በአይነ-ህሊናዬ ሳልኳቸው:: ያሳዝናሉ:: ስለእነሱ እያሰላሰልኩ.. ሌላው ሌላው ስቃዬን እያሰብኩ፣ የሚሰማኝን የህመም ስሜት እያስታመምኩ ስገላበጥ ሰዓቱ ነጎደ:: «አላህ ወ አክበር» ሲል ለመተኛት አይኔን ጨፈንኩ:: በመጨፈን ምን ሊመጣ? በጨፈንኩ ቁጥር በስቃይ፣ በጣር ተይዘው ባህር ውስጥ ሲወራጩ እያየሁ አድነን..ድረስልን የሚሉ እየመሰለኝ እንቅልፍ በአይኔ ሳይዞር ቆየሁ:: በመሀል ላይ ሲነጋ ሸለብ ሊያደርገኝ ቢሞክርም በቅዠት..ከሰመጡት መሀል




እግሩን የሚያመውን ልጅ ብቅ ጥልቅ ሲል አይቼው..ድብልቅልቅ ያለ ጩኸት ጮኼ ሌሎችንም በጥብጫቸው ነቃሁ:: አንዱ በጠበጥከን ብሎ ሊደበድበኝ ይጎተተኝ ጀመር:: ትዕግስት ከየት እንዳገኘሁ አላውቅም በዝምታ አለፍኩት:: ዝም ባልልም ምንም የማደርግበት ጉልበትም ሆነ ጤና የለኝም:: ግን በስደት ሀገር ጥለን በሰው ሀገር የምንሆነውን፣ የሚገጥመንን ሳናውቅ ከፍቅር ይልቅ ለጸብ መነሳሳት ፍጥነታችንን ታዘብኩኝ:: ‹‹ምን ሆነህ ነው ወዳጄ ምን ገጠመህ?..›› ቢለኝ ምናለ ስል አሰብኩ:: በዛን ሰዓት ብዙ አሰብኩ:: እንቅልፍ እንቢ ስላለኝ ነው መሰለኝ ብዙ..ብዙ.. አሰብኩኝ::

በመጨረሻ ንጋት ላይ እንቅልፍ ወሰደኝ:: ጠዋት ላይ የነቃሁት ቁርስ ተበልቶ አልቆ 5 ሰዓት አካባቢ ነው:: «ይሄ ካምፕ ሶማሊያውያንን ብቻ ማስተናገጃ ነውና እናንተ ኢትዮጵያዊያንን ስለማናስተናግድ እዚህ መቆየት አትችሉም:: ባጀት የለንም..» ተባለ:: ጊቢውን ለቀን መውጣት እንዳለብንም ተነገረ:: አማራጭ ስለሌለ ለመውጣትና በእግር ለመሄድ ስላሰቡ ልጆቹ ቀስቅሰውኝ ነው የተነሳሁት:: ሰዓቱን ሲነግሩኝ ደነገጥኩ:: ማታ ያናገረኝ ሰውዬን ፍለጋ ወደ ቢሮው ሄድኩ:: አልቀናኝም:: አደን መሄዱንና የሚመጣው ቅዳሜ መሆኑን ሰማሁ:: እንደሚሄድ እያወቀ ለምን ቀጠረኝ? ቀኑን ሳስበው ማክሰኞ ነው:: ቅዳሜ ድረስ እዛ መጠበቅ አልችልም:: እሱን ከምጠብቀው ከማክሰኞ እስከ ቅዳሜ ድረስ ሰነዓ እደርሳለሁ ብዬ አሰብኩ:: መንገዱን ከሚያውቁ ሰዎች ጋር ልሄድ ፈልጌ ጉዞ ጀመርኩ::

የመናዊያን በጣም ደጎች ናቸው:: እያበሉ፣ እያጠጡ በመኪና ጭነው ይወስዳሉ:: ጉዞ ስንጀምር ከካምፑ ወጣ ብለን ያገኘናት ማይፋ የምትባል ከተማ ነገር ላይ የታምራት ደስታን «እኛን ነው ማየት ስትመጭ እሱ ብሎት..» የሚለውን ዘፈን ከርቀት ሰማሁ:: እዚህ ቦታ የሚከፍተው ኖሮ ሳይሆን ባህሩ ላይ ተለክፌ ጆሮዬ ያልሰማውን እያቀበለኝ መሰለኝ:: ብርድ ብርድ እያለ ሰውነቴን ያደቀቀኝም ልክፍት ይሆን ብዬ ፈራሁና ደጋግሜ አማተብኩ:: «በስመ አብ በስመ ወልድ..!» ድምጹ ግን ከእኔ አልራቀም:: የባሰ እየቀረበኝ መጣ:: «ፈጣሪ አምላኬ ሆይ በሰው ሀገርማ በልክፍት እንዳላብድ:: ባህር ላይ ሱቅ ደርሼ ሲጋራ ገዝቼ እመጣለሁ ብሎ ተወርውሮ ወደ ባህር የገባው ልጅ ትዝ አለኝ:: ‹‹ልክፍት ነው እዚህ ባህር ላይ ያለ መጥፎ መንፈስ ገና ስንወርድ ታያለህ ጆሮህ ላይ ያንቃጭላል:: የሆነ የመረበሽ ነገር አለው..›› ያሉኝ ይበልጥ አስፈራራኝ::

ኧረ!..ምንድነው የምሰማው? እውን ድምጻዊ ታምራት ደስታ ነው? ፈጣሪዬ ሆይ አንድ በለኝ..» ስል ፈጣሪዬን ተማጸንኩ:: ድምጹ ግን ይበልጥ ቀረበኝ:: ለሌሎቹ ይሰማቸው ይሆን? ልጠይቃቸው ፈለኩ ግን ቢስቁብኝስ..?

አራት ሆነን መኪና እንዲያቆሙልን አላፊውን ሁሉ ስንለምን ነበር:: ራቅ ብሎ በሩ ተከፍቶ የቆመ መኪና አለ:: የሚቆምልን መኪና አጣንና ጉዞ በእግር ስንጀምር ሙዚቃው ይበልጥ ቀረበኝ:: አሁን አወኩ:: እውን ነው ሙዚቃው በሩን ከፍቶ ከቆመው መኪና ውስጥ የሚወጣ መሆኑን ተረዳሁ:: በጣም ገረመኝ:: ለምን አይገርመኝ? ከሀገሬ ውጭ ያውም እንዲህ ያለ ገጠር ቦታ ቀርቶ ከተማ ውስጥም ቢሆን እሰማዋለሁ ብዬ መች አሰብኩና? ለስራ የመጡ ሀበሾች ቢኖሩ እንኳን ቤት ውስጥ እንጂ እንዲህ ያለ ቦታ ከፍተው እሰማለሁ ብዬ እንዴት ላስብ?



ከባህር /ከጀልባ/ ከተወረደ በኋላ ያለውን የእግር መንገድ በዚህ አይነት ሁኔታ ይከዳል:: የመናዊያን በጣም ጥሩዎች ናቸው:: መኪና ይዘው ሲያልፉ የሚችሉበት ቦታ ድረስ ይወስዳሉ::ነዋሪውየሚበላ ለጠየቀው ስደተኛ ሁሉ ያላቸውን ይሰጣሉ:: ከሌላቸው ቋጣ እየ.ገገሩ በለስ አልበለስ ሳይሉ ይሰጣሉ:: ስደተኛውን ፖሊስ እንዳይዘው መንገድ ይመራሉ:: (ፎተው ከኢንተርኔት የተወሰደ)

ሾፌሩ ትውልደ ሀበሻ ነው:: መኪናው ጋር ስንደርስ «ያገር ልጆች..» ሲለን በአማርኛ ሁላችንም ተደሰትን:: «ታዲያ ወዴት ናችሁ? አሁን እኮ እየሄዳችሁ ያላችሁት ወደ ሙከላ ነው:: ከባህር ወደ ወረዳችሁበት:: ስለዚህ ወደ ኋላችሁ ተመለሱ» ብሎ እዛው ከተማ ትንሽ ቀን የሚቆይ ስለሆነ ሊረዳን እንደማይችል ነግሮን አንድ..አንድ ሺህ የየመን ሪያል ሰጠን:: «አይዟችሁ» ብሎን ተለያየን:: ትንሽ መንገድ የሚወስደን መኪና አገኘን:: ከመኪናው ወርደን ዋናውን መንገድ ርቀን በእግር የቻልነውን ያህል አስነካነው:: ደግሞ ወደ ዋናው መንገድ ተመልሰን ሌላ መኪና ለምነን ጉዞ





ቀጠልን:: ይሄኛው ሾፌር ደግሞ እንደራበን ሲነግሩት ሱቅ ሲያገኝ ለሁላችንም አንዳንድ አቡወለድ ብስኩትና ፔፕሲ..ውሀ ገዛልን:: የሚሄድበት ድረስ ወሰደን::

ወርደን ሌላ መኪና ለምነን «አጠቅ» የሚባለው ከተማ መታጠፊያ ድረስ ይዞን ሄደና መኪናውን አቁሞ «ቅርብ ቦታ ፍተሻ አለ» ሲል ቋንቋ የሚችል አንዱ የሆነ ነገር ተናገረ:: ችግር የለም ሲለው መስለኝ ይዞን ሄደ:: ፍተሻው ጋር ፖሊሶቹ አስወረዱን::

ተያዝን።

«ወይኔ ፍተሻ አለ ሲለኝ እንደድሮው መስሎኝ አይዙንም ብዬው..» በቁጭት ተናገረ:: እንቀው..እንቀው አለኝ:: ሁሉም ነገር ከሸፈ አልሆነም:: አይሆኑ ችግር ላይ ወደቅን:: በጣም ደነገጥኩ:: ምን ማለት እችላለሁ? ቋንቋ አልችልÎ የሚችሉት ልጆች ለመኗቸው:: ከእኛ ቀድመው የተያዙ ሰባት ልጆችም ያስገቡን ክፍል ውስጥ አገኘን::

«ከተማ ወደ አለው እስር ቤት ከመወሰዳችን በፊት እያንዳንዳችሁ ሁለት ሁለት ሺህ የየመን ሪያል ስጡን እንለቃችኋለን» አሉ:: የኢትዮጵያ መቶ ብር ማለት ነው:: ለስቱ ልጆች የለንም አንሰጥም ብለው ድርቅ አሉ:: ፖሊሶቹ ደግሞ ከለቀቅን ሁላችሁንም ነው ካልሆነ ሁላችሁንም ወደ ፖሊስ ጣቢያ እንወስዳችኋለን አሉ:: በሸፍን መኪና ጭነው ወሰዱን:: መንገድ ላይ አጋጣሚ ካገኙን ለማምለጥ ሁላችንም ጠበቅን::

ብዙም ከተማዋን ማየት ባልቻልኩበት ሁኔታ ተጓዝን:: ፖሊስ ጣቢያ ስንገባ ልክ እንደቦላሶ «ውይ ግሩም» ብላ ሰናይት ተቀበለችኝ:: በየቦታው «ውይ! ግሩም..» እያለች አቀባበል ልታደርግልኝ የተመደበች ሁሉ መሰለኝ:: በረንዳው ላይ ከእኛ ቀድመው የተያዙ 17 ልጆች ተቀምጠዋል:: ሶስት ፖሊሶች ወረቀት ይዘው አንድ ክፍል ውስጥ ገቡ:: ቃል መቀበያ ክፍል መሆኑ ነው:: ጀመሩ..ቃል የሰጠ ሰው በዛው ወደ እስር ክፍሉ ይገባል:: ቃል ለመስጠት ሲገባ ብጥርጥር ተደርጎ ይፈተሻል:: የእዚህ አይነት ፍተሻ አይቼ አላውቅም:: በፊልም ላይ እንኳን ያየሁ አይመስለኝም:: በዚህ ፍተሻ እንኳን ገንዘብ ቅማልም የሚያመልጥ አይመስልም:: ገንዘቤን እንደሚወስዱብኝ አመንኩ:: ሳጤን ሌቶቹን አጥብቀው አይፈትሹም:: ወንድ ፖሊስ ሴት መንካት በእነሱ ሀራም /ነውር/ ነው:: ልብ ያልኩትን ይህን ክፍተት ነው:: ገንዘቤን ለማስመለጫ ዘዴ ቀየስኩበት::

ከማይፋ ካምፕ ውጡ ተብለን እንደወጣን ፖሊሶቹ ስለሰሙ በየቦታው ተሰማርተው ብዙ ለቅመዋል:: እኛን ጨምሮ 38 ነን የተያዝነው:: ወደ ሰናይት ቀረብኩና «የያዝኩትን ገንዘብ ደብቂልኝ» ብዬ የኢትዮጵያ 3700 ብር



ሰጠኂት፡፡ የልብስ እጥፋቶች፣ ኮሌታ ስር፣ ወገብ ላይ..እፍ አስከፍተው ሁሉ ጣታቸውን ሰደው..የመቀመጫ ተረተር/ስንጥቅ/ሳይቀር ይፈትሻሉ፡፡ እስነዋሪ ነገር ሲሰሩ ማየቴ አናደደኝ፡፡ ከዚህ የበለጠ ነገር ሊደርስብኝ እንደሚችል እንዳስብ አረጉኝ፡፡ ሽፍን ጫማ ያደረገውን አስወልቀው የጫማውን ሶል ጭምር ገንጥለው ይፈትሻሉ፡፡ ኢ-ሰብአዊነት ነው ስል አሰብኩኝ፡፡ ከማሰብ ውጭ ምንስ ማድረግ እችላለሁ? የስደተኛውን ባህሪ ጠንቅቀው ማወቃቸውን ያወኩት /የየመን ሁለት ሺህ/ ስጡን እንለቃችኋለን ሲሉ የለንም ብለው ለእኛ ም ጦስ ከሆኑብን መካከል አንዱ መቶ ዶላሩን እጥፍጥፍ አርጎት ጉንጩ ውስጥ ወሽቆት ነበር፡፡ ፖሊሱ ጣቱን አፉ ውስጥ ከቶ ጎርጉሮ አወጣበት፡፡

ሁሉም እንደተፈተሸ ተፈትሼ ቃሌን ልሰጥ ገባሁ፡፡ ሙሉ ስም ተጠየኩ፣ ተናገርኩ፡፡

«ከዚህ በፊት በዚህ መንገድ መጥተህ ታውቃለህ?» የሚል ጥያቄ ነው ሁለተኛው፡፡

«በፍጹም»

«አሁን ለምን መጣህ?»

«ሀገሬ ነፃ ፕሬስ አለ፡፡ ጋዜጣዎች ላይ እሰራለሁ፡፡ በዛ ምክንያት ችግር ተፈጥሮ ሸሽቼ ነው፡፡» የቻልኩትን ሁሉ ነገርኩ፡፡ አስተርጓሚው በትክክል ይናገር አይናገር ግን የማውቀው ነገር የለም፡፡ የጠየቁኝን ሁሉ መለስኩ፡፡ ወደ እስር ክፍል ስሄድ በጣሳ ሻይና ኩደም የሚባል ወታደሮችና እስረኞች የሚበሉት አመዳም ዳቦ ተሰጠኝ፡፡ የጣቢያው አዛዥ እስኪመጣ ቆይ ተብዬ አንድ ጥግ ቁጭ አልኩ፡፡ ትንሽ ቆይቶ መጣ፡፡ ውጭ እንዳለሁ መታወቂያዬን አየው፡፡ እንግሊዘኛ ተናጋሪ በመሆኑ የምችለውን ያህል አስረዳሁት፡፡ ዞር ከማለቱ ፖሊሶቹ መረጃዬን እያይዘ ፍ/ቤት እንደሚያቀርበኝ ነገረኝ፡፡ ዞር ከማለቱ ፖሊሶቹ እየገፈታተሩ ወደ እስር ክፍሉ ወሰዱኝ፡፡ ሌሎች የተያዙ ልጆችም መጡ፡፡ የተሰጠኝን አንድ ደረቅ ዳቦና ጣሳ ሻይ ይገፍ ለወንዶች ወደ ተዘጋጀው ክፍል ገባሁ፡፡ ከክፍሏ ጥበት የተነሳ እንኳን ለመተኛት ተቀምጦ ለማደርም አትበቃም፡፡ ያውም ሁለቱ ሴቶች ሌላ ክፍል ናቸው፡፡ 36 ወንዶች ነን፡፡ ቁጭ..ቁጭ..እንዳልን ማውራት ጀመርን፡፡ ሴቶቹ ቃላቸውን ሲሰጡ ሰናይት እንዴት ብቻሽን መጣሽ ስትባል ነው መሰለኝ አብሮኝ ባሌ አለ ብላ ተጠራሁ፡፡

ወጥቼ ስንተያይ ፈጠን ብላ «ባል አለኝ ወይም ወንድም ካላልኩ ይተናኮሉኛል፣ ሲጫወቱብኝ ያድራሉ ብዬ ባሌ አለ አልኳቸው ችግር አለው? ለእሷ ደግሞ ወንድሟ ነኝ በል» ነገረችኝ፡፡ ጉዳት ከሚደርስባት ሚስቴ ነች ብል አልጎዳም፡፡ ገብቼ ስጠየቅ ሁለቱንም ያድናል ያልኩትን ተናገርኩ፡፡ ሰርግ ሳይደገስ፣ ሚስት ሳልመርጥ ኧረ!..እንዲያውም





ማግባቴንም ሳላውቅ ባለትዳር ሆኜ ቀረብኩ፡፡ በትዳር ላይ ትዳር ሀገሬ ቢሆን ያስቀጣኝ ነበር፡፡ ለማዳን ስል ሌላም ነገር ባደርግ ምንም አይመስለኝ፡፡

ተመልሼ ወደ እስር ክፍሌ ስገባ ተቀምጬባት የነበረችውም ቦታ ሌላ ሰው ስለ ያዛት ባለው ክፍት ቦታ ሽንት ቤቱ በር ጋ ተቀመጥኩ፡፡ አንዱ የሲጋራ ግብዣ አቀረበልኝ፡፡ ከሲጋራው ይልቅ የሲጋራውን ወረቀት እንዲሰጠኝ ጠየኩት፡፡ የገረመው መሰለኝ በእርግጥም ለምን ሳይገርመው ይቀራል? ሲጋራ ሲጋብዙኝ ወረቀቱን መጠየቁ ጤንነት ላይመስለው ይችላል፡፡ በሰዓቱ እንቅልፌ ሊመጣና ልተኛ የምችልበት ሁኔታ አይደለም ያለው፡፡ የምጽፈው ነገር ቢኖረኝም ሻንጣዬን ተቀብለው ባዶዬን ስለሆን ያስገቡኝ ከደብተሬ ጋር ተራርቄያለሁ፡፡ የሲጋራ ወረቀቱን ሰጠኝ፡፡ ግርግዳ ላይ የተጻፉትን ፅሁፎች መገልበጥ ጀመርኩ፡፡ እዚህ እስር ቤት ውስጥ ለበርካታ ጊዜያት በርካታ ኢትዮጵያዊያን መታሰራቸውን ግርግዳው ላይ የተጻፈው በርካታ መልዕክት ይናገራል፡፡ በእስክርቢቶ፣ በእርሳስ፣ በፓርከር የተጻፈ መልዕክት አለ፡፡ ለየት ያለ መልዕክት አይኔን ሳበው፡፡ በደም የተጻፈ፡፡

«ኢትዮጵያዊያን አገር እያለን እንደሌለን በስደት ስንሰቃይ እንኑር? ወይኔ!..» ይላል፡፡ ከስሩ «..ይህ እስር ቤት በሀይለኛው ግፍ የሚፈጸምበት ቦታ ነው፡፡ በርሃብ ስንቀጣ ምግብ ስጡን ብዬ በመጠየቁ ተደብድቤ ሲነስረኝ በደሜ ነው የጻፍኩት፡፡ 1992..» የሚልም አለበት፡፡ ጻፍኩት፡፡ ስሙ ቢደበዘዝም አብዶ ይላል፡፡

«19 ሆነን የኦሮሞ ልጆች ስቃያችንን እያየን ዛሬ ስድስተኛ ቀናችን ነው፡፡ ወደ ተሻለ እስር ቤት ወስደውን የሚበላ የምናገኘው መቼ ይሆን?..1994ዓ.ም» የሚል በእርሳስ የተጻፈ ጽሁፍ አገኘሁ፡፡ ስለኦሮሞ ሌላም የተፃፈ አለ፡፡ በላቲኒኛ ስለሆነ አልገለበጥኩትም፡፡ ግን ብዙ መሆኑን አስታውሳለሁ፡፡ «የኦሮሞ ልጆች በስደት አለቅን፡፡ የጅማ፣ አርሲ፣ ሐረርና ባሌ ልጆች ነን የታሰርነው፡፡ እንድሪስ ከማል የሚባል የሁሩታ ልጅ ዛሬ ሽንት ቤት ውስጥ ራሱን ሲያጠፋ ለምን አልነገራችሁንም ብለው ደበደቡን፡፡ ወገናችን ነው መሞቱ ያሳዘነን አንሶ ዱላ ጨመሩልን፡፡ ..1999ዓ.ም» ይላል፡፡ ይህቺኛዋ መልዕክት ግን ከሁሉም ትኩረቴን ስባ መጀመሪያ የፃፍኳት ነች፡፡ «የኦሮሞ ልጆች..» የምትለዋ ኦሮሞ ብቻ ነው የተሰደደው? ሌላውስ? የሚል ጥያቄ ፈጠረብኝ፡፡ በእርግጥ የእነሱን ያህል ሌላው ብዛት የለውም፡፡ ታንቆ የሞተው ግን አሳዘነኝ፡፡ እያይዤም ምን ያህል መከራ እንደሚጠብቀን አሰላሁት፡፡

«ሸዋሮቢትን ሸሽተን ብንመጣ የባሰ ሸዋሮቢት ገጠመን! ግንቦት 17/1993 ዓ.ም ታረቀኝ በጋሻው» የሚል በእርሳስ የተጻፈ አየሁ፡፡ ይበልጥ

ትኩረቴን ሳበው:: ለእኔም የገጠመኝ ይሄው ስለሆነ ስለዚሁ ሁኔታ ማሰላሰል ጀመርኩ:: ከፋኝ:: ልጄ..ሚስቴ፣ ጧሪ የሌላት አሮጊት እናቴ ታወሱኝ:: የኪስ ቦርሳዬን አውጥቼ ደርፏሚ ልጄን አቅፌ የተነሳሁትን ፎቶ አየሁት:: አሁን ላይ ሆኜ ሳስበው ሁሉ አያውጣው እንጂ በዛን ሰዓት ስንቱ ይሆን ውስጡ አሮ «እህህን..» በሆዱ የሚያቀነቅነው? የሄደ ሰው ብዙ ያያል፣ ያውቃል:: መሄድ ደጉ ስደት ምን እንደሆነ ከሰማሁት በላይ አየሁት:: ስደት ቢጮሁ ሰሚ የሌለበት፣ ቢከፋ አይዞህ የሚል፣ ቢርብ የሚያጎርስ የማይገኝበት..የሰው ልጅ እንደቅጠል የሚረገፍበት..መከራ የዕለት ተዕለት ገጠመኝ እንደሆነ አየሁ:: ከስደት የተመሰሰው ይህን ሁሉ ደብቆ ቁንጅል እያወራ ስንቱን ለስህተት ዳረገ? ወንጀል ነው እንቀጽ ተጠቅሶ ምዕራፍ አክሎ ይህን ያህል ያስቀጣል ባይባልም ከህሊና ፍርድ የማይሸሽበት ወንጀል ነው ከስደት ተመላሹ እየሰራ ያለው:: ክህሊና ችሎት ሀፅትን ጥሎ የሚያልፍ ስውር ወንጀል ነው::

ለረጅም ሰዓት አሰብኩት:: ብዙዎቹ ባሉበት ደገፍ..ደገፍ እንዳሉ እንቅልፍ ወስዷቸው ሳይ ቀናሁ:: እያንዳንዳቸው የመጡበትን የተለያየ ምክንያት አሰብኩ:: ስንታቸው እግሬ ይውጣ እንጂ ሰርቼ ገንዘብ አግኝቼ.. ብለው ተስፋቸውን ስደት ላይ አርገው ይሆን? ስንቶቹስ አጓጊ የሆነ ህይወት አገኛለሁ ብለው አስበው ነው ከሀገር የወጡት? ስንቶቹስ ውጭ ሀገርን እንደገነት ቆጥረው ይሆን ግብርናቸውን ትተው የመጡት? የእነሱን አሰብኩ እንጂ እኔም ከእስር ሸሽቼ ወጥቼ እስር ገጥሞኝ ያውም በአስከፊ ሁኔታ ታስሬ የለ? በእርግጥ ከዚህ የከፋ እስር ሀገሬ ውስጥ ገጥሞኝ ያውቃል::

ከሀገር ሽሽቴ የተሳካ አልሆነም:: የባሰ የሌላውንም ስቃይ እያየ በሀዘን ድባብ ተጀቡኖ ውስጥ ማድማት እጣ ፋታዬ ሆነ:: ፎቶውን ቦርሳዬ መልሼ ወረቀት ፍለጋ ጀመርኩ:: ኮቲ እድርጌ የያዝኩትን ማስረጃ አገኘሁ:: ጀርባው ላይ የተሰማኝን ስሜት ላሰፍር ተጣደፍኩ:: ሁሉም ተኝትዋል:: «ቢከፋኝ ምን ላመጣ?» የሚል ርዕስ ሰጥቼ ያሰብኩትን ሀሳብ ለመከተብ ብዕሬን ከወረቀት አፋጠጥኩ::

<u>ቢከፋኝ ምን ላመጣ?</u>

ሁኔታው ሲከፋ በነገር ሆድ ሲጎሽ
ፍላጎት ሲታፈን ስሜት ሲኮላሽ
ሀሊና ሲደማ ውስጡ ሲቆሸሽ
ነጻነት ሲጠፋ ተስፋ ሲሟሽሽ
ቤትን አፍርሶ ስደት ሲገባ
አቤት!..ሲያስከፋ አቤት!..ሲያባባ
ነገርን ጥሎ ጨርቅ አንጠልጥሎ
ከወዳጅ ዘመድ ርቆ ኮብልሎ
የራስ ያልሞቀ የራስ ያልደላ
በሰው ሀገር ላይ ምን ሊሞላ





ከመከፋት ጋር ደግሞ መታሰር
ከሀገር ሸሽተው ሲገጥም ሰው ሀገር
ጉዞ ጉዞ ወልዶ ማስቂያው ቢጠፋ
በሀገር ያልተመቸ ሰው ሀገር ቢከፋ
ወዴት ይሰደዷል ወዴትስ ሲጠፋ
መከፋትን ይዞ ቢጨልምም ተስፋ
ተመስገን ማለት ነው ነገም እንዳይከፋ
ደግሞስ ቢከፋኝ ምን ላመጣ
ለስደት ወጥቼ አላበዛም ጣጣ
እቀበለዋለሁ እሱው እንዳመጣ
አዎ!.....እሱ እንዳመጣው...

የመን-አጠቅ የተባለ ቦታ እስር ቤት መታሰቢያነቱ በስደት አለም ታስረው ላሉ ኢትዮጵያዊያን ይሁንልኝ አልኩና ከስሩ ጻፍኩበት::

መጨረሻ ላይ የእንዱን እግር ተንተርሼ ተኛሁ:: እንቅልፍ ግን እኔ ዘንድ ዝር አላለም:: ጎና ጋደም ስል ልጆቹ ባህር ውስጥ ጣር ይዟቸው እንዴት እንደሚንፈራገጡ እየታየኝ ህልምም ቅዠትም ሆነኙብኝና ተሰቃየሁ:: ጠዋት በሩ ሲከፈት ነቃሁ:: ያው ተነስቼ ተቀመጥኩ ለማለት ነው:: እንደነገሩ የተሰራ ቀጭን ቶል በመካከለኛ ብረት ድስትና አንድ አንድ ኩደም የሚሉትን ዳቦ መሳይ ከላዩ ዱቄቱ ቡን የሚል ነገር ተሰጠን:: መብላት አይበለው በላሁ:: በረሀብ እንዳልሞት መብላት ግድ ይለኝ ነበር::

ከጠዋቱ 4 ሰዓት አካባቢ ተጠራሁ:: «ለምን ይሆን ከሁሉ ተለይቼ የተጠራሁት? ዳግም ሊፈትሹኝ ይሆን?..» ልቤ በፍርሃት..እየደለቀ ነው:: ብሬን ለመደበቅ ፈለኩ:: ፖሊሱ ስላጣደፈኝ ተቻኩዬ ወጣሁ:: ወደ በረንዳ ሲወስዱኝ ሊለቁኝ መሰለኝና ተደሰትኩ:: አይ!!..ሀሳቤ.. አይ!!.. ምኞት..ከንቱ ነው:: ሀሳቤ ሁሉ ከንቱ መሆኑን ያወኩት ሰናይትን በረንዳ ላይ ተቀምጣ ሳያት ነው:: ያጀበኝ ፖሊስ «ኑስ ሰዓ ተማም?» (ግማሽ ሰዓት) ብሎኝ ከእኔ ራቀ:: ባልና ሚስት ስለተባልን ማገናኘታቸው ነው:: ለካ ባለሚስት ነበርኩ::

ለሴቶቹ ከእኛ የተሻለ ወታደሮቹ የሚበሉትን በብዛት ሰጥተዋቸው ስለነበር ይዛልኝ የመጣችውን ሩዝ ጥርግ አርጌ በላሁና የባጥ የቆጡን አወራን:: ሰዓቱ ደረሰና ሰናይትን ጠርቶ አስገባት:: ጓደኛዋ አልማዝ መጣች:: እህቴ ስለተባለች ማገናኘታቸው ነው:: ልታወራኝ አማርኛ አጠራት::

‹‹እዋይ!..ጸቂ....›› አለች አማርኛው ጥፍት ሲላት ተደናግጣ::

«ተዛረቢ ይሰምዕዩ ምዝራብ እዩ ዝጽግመኒ..›› አልኳት:: (ተናገሪ እሰማለሁ መናገር ነው የሚያቅተኝ)::

‹ከም ቀልዲ ሀወይ ገይረካ። ናይ በሀቂ ኮይኑ እስካ ትግራዋይ እካ?›› (እንደቀልድ ተናግሬ እውነት ሆነ አንተ ትግሬ ነህ እንዴ?) አለችኝ።

‹‹አይደለሁም ቋንቋውን ስለምሰማ ብቻ ነው›› አልኳት። እንዲህ እያልን የተፈቀደ ልንን ግማሽ ሰዓት ንጹህ አየር ሳብንበት። ለአንድ ሰዓት ያህልም ቢሆን ንጹህ አየር በመተንፈሴ ያሀቺን አጋጣሚ ወደድኳት። ተመቸኝ። በየቀኑ ከሁለቱ ጋር በማደርገው የአንድ ሰዓት ቆይታ ንጹህ አየር እየሳብኩ ምግብ ለሌሎችም ጭምር ይገፍ እየገባሁ ሳምንቱን እንደምንም ገፋነው። በዚህ ሁኔታ ባናሳልፈው ኖሮ ረሃቡ ይጨርሰን ነበር። አብሶ እኔ ዳቦውን ካልሆነ ቶል ተብሎ የሚቀርበውን ከውሀ በቅጥነቱ የሚበልጥ ዘይትና ሽንኩርት ያለው ፈሳሽ ነገር ፈፅሞ አልበላውም።

በሳምንቱ «አጠቅ» በሚባለው ከተማ ፍርድ ቤት ቀረብን። የፍርድ ቤቱ ሂደት አስቂኝም አሳዛኝም ገጠመኝ ነበረው። ሰባት ልጆች ዑግንጅ መጥፎ..መጥፎ ቦታ ወጥቶባቸዋል። መቆም መቀመጥ አቅቷቸው ተቸግረው የሚሆኑት ጠፍቷቸው ማየት አንዱ የሚያሳዝን ነገር ነው። መቀመጥ ያቃታቸውም ቆመው ሂደቱ ቀጠለ። አማርኛ የሚችል የፍርድ ቤቱ ሰራተኛ ኦሮሞ ለብቻ ሀበሻ ለብቻ ብሎ ለያየን ይሄ ነገር አልገባ አለኝ። እነሱ ለብቻ እኛ ለብቻ ቀረብን። ዳኛው ግን ፋይሉን ገልጦ ሳያየው «ሁላችሁም ወደ ሃገራችሁ። ሀገራችን ደሃ ነች እናንተን ማኖር አትችልም» አለ። ቅር አላለኝም እስካሁን ባየሁት ከሀገሬ የሚሻል ነገር አላየሁም። ሀገራችን አልቻልም አላለችንም። ግን የወጣንበት የተለያየን ችግር መሆኑን ማጤንም መስማትም አልተፈለገም። መዝገቡ ሳይገለጥ ተዘግቶ ወደ እስር ቤታችን ተመለስን።





# - 9 -

# ቆይታ በሰነዓ እስር ቤት

ንገረኝ እውነቱን ልገላገል
የወደደውን ይፈትናል ይሉሀል
የወደድከውን ከሆነ የምትፈትነው
ያልፈተንከውን ለምን ጠላኸው?

በማግስቱም ወደ ዋና ከተማው ሰነዓ ተወሰድን።

በዚህ ጉዞ ላይ የነበረው ረሃብና ውሃ ጥም ራሱን የቻለ ጥሩ ቅጣት ነበር። ምሽት ሁለት ሰዓት ከአርባ አምስት ሲሆን ሰነዓ ያለው ኢሚግሬሽን ወይም በእነሱ አጠራር ጀዋዛት ተብሎ የሚጠራው እስር ቤት ደረስን። በጉዞዬ ሁሉ የማሰላስለው ወደ ሀገሬ ስመለስ የሚገጥመኝን ነው። ረሀብ ውስጤን ቢጎዳውም ምን ይሆን መጨረሻዬ የሚል ሀሳብ፣ እልህ..ንዴት፣ ጭንቀት ተባብረውብኛል። ለእነዚህ መፍትሄ ከማግኘት ውጭ ምንም አልታየኝም።

ሰነዓ እስር ቤት እንደገባን የታጎርንበት ግቢ ነገር ጣራ የለውም። እስረኛ እንዳይዘል ከአናቱ ግን በፌሮ ብረት ተዘግቷል። ፀሀይ መሞቂያ ቦታ ነው.. (ሽማሲ ደሱታል በእነሱ አጠራር) ከወደጥግ በኩል አንድ ሽራ ግንቡን አስታኮ በገመድ ታስሯል። ከውስጡ አንድ ጸጉሩን ያሳደገ ግዙፍ ሰው ወጣ። ሸምሰዲን መሀመድ ይባላል። ፊቱ ከግዙፍነቱ ጋር ያስፈራል። መጀመሪያ ላይ ሳየው የሆነ የሆረር ፊልም ላይ የማውቀው ሁሉ መስሎኝ ነበር።

«ምንድን ነው? ከየት ነው የመጣችሁት? ስንት ናችሁ?» በመሳሰሉት ጥያቄዎች አጣደፉን:: ከሁሉም የሚሰማው ብሶት ግን «የሚበላ የለህም? ርቦናል..» የሚል ነው::

ሰሃን ሙሉ ምግብ አምጥቶ እየቀነሰ፣ እየቀነሰ ሰጠን:: ኢሚግሬሽን ወይም ጀዋዛት እስር ቤት ውስጥ 2 የእስር ክፍል አለ:: አሁን እኛ የገባንበት ጸሀይ መሞቅያ (ሸማሲ) የሚባል ቦታ እንጂ እስር ክፍል አይደለም:: ከሁለቱ እስር ክፍል ውስጥ «...ያላችሁን ምግብ ላኩ» ብሎ እየተቀበለ አበላን:: በሆዴ መርቄዋለሁ:: አሁንም ከሰማኝ እመርቀዋለሁ:: ተርቤ አብልቶኛል:: እሱ እጅ ላይ ሞባይል ስልክ ሳይ ለአስረኛ መፈቀዱ ገረመኝ::

«ስልክ መደወል ይቻላል?»

«መደወል ፈልገህ ነው!»

«አዎ!..ባክህ አስደውለኝ?» ኢትዮጵያ ከመመለሴ በፊት የነጻ ጋዜጠኞች ማህበሩ ሊያደርግልኝ የሚችለው ነገር ካለ ለማሳወቅ ፈለኩ:: በሰዓቱ ቢጨንቀኝ እንጂ ምንም ሊያደርግልኝ የሚችለው ነገር እንደሌለ አውቃለሁ:: በሰው ሀገር አይታሰር አይል..

«እዚህ ዘመድ ጓደኛ አለህ?»

«ኢትዮጵያ ነው የፈለኩት:: ሞባይል ካርድ ልሙላ እና..» ፈጣን ምላሽ ሰጠኝ:: አንድ ሺ የየመን ሪያል ተቀበለኝ:: ፖሊሱን ገዝቶ እንዲመጣ ላከው:: ለትንሽ ነገር የሚደለል አይነት ሰው በመሆኑ ከካርድ መልስ የሚያገኘው እልበቃ ብሎ የባሰ ቀንቶ ነበር የላከው:: የኢትዮጵያ ነፃ ጋዜጠኞች ማህበር ፕሬዘዳንት ክፍሌ ሙላት ጋ ደወልኩ:: የመን እንዳለሁና እንደተያዝኩ ነገርኩት:: ጋሽ ክፍሌ ትንሽ ተቆጣኝ:: ቀድሜ ስላልነገርኩት ነው አቆጣጡ ቀጥዬ የነገርኩትን ሌላውን ነገር ሙሉ ለሙሉ ይሰማኝ አይሰማኝ ግን አላረጋገጥኩም:: የኔትወርክ ችግር ቁርጥ..ቁርጥ ሲል ስለነበር ድምጹ ጥራት አልነበረውም:: በዛ ላይ ካርዱም አለቀ:: እንዲያው ቢጨንቀኝ እንጂ ቢሰማኝስ ምን ሊያደርግልኝ ይችላል? መግለጫ ማውጣት በቃ!! የጋዜጠኞች ማህበር እንጂ የባለስልጣናት ማህበር ባለመሆኑ ከእስክርቢቶ ውጭ ምን አለን? የማደርገው ሁሉ ጠፋኝ:: ነገር አለሙ ዞረብኝ:: ሽምሰዲን ነገር ለማወቅ ጉጉት ስላደረበት አይኑ ፈጦ ቅላቱን ጨምሮ በጥያቄ ያጣድፈኝ ጀመር:: «አሀ!..ጋዜጠኛ ነህ?»

«አዎ!..»

«ታዲያ እንዴት ፎቶ ተነስተህ ትመለሳለህ?»

«ታዲያ ምን ማድረግ እችላለሁ? አጠቅ የሚባለው ቦታ ፍርድ ቤት አቅርበውን ሁላችንም ወደ ሀገራችን እንድንመለስ ወስነውብናል::» ፀጉሩን አከክ..አከክ አደረገና ስጋ የሞላው ፊቱን ፈገግታ አከለበት:: ፊቱ ከሰው





የተለየ አካል የተጨመረበት የተጣበበ፣ የተጨናነቀ ነገር ያለው ይመስላል:: ፈገግታ ሲያክልበት ብሩህነት ሳይሆን በተቃራኒ ጨፍጋጋነት ወርሶታል:: ፈገግታው ውበት የለውም:: ውበት ያሳጣው የዛገ ብረት የመሰለው ጥርሱ መሰለኝ:: የሚቅመው ጫት ጥርሱ ላይ ተሰጉዷል:: አረንጓዴ ጫቱ፣ ቢጫነትን አልፎ ቡኒነትንና ጥቁርነትን ያስተናገደ ጥርሱ አንድ ላይ ሲታይ ከለር ማስመረጫ ወረቀት /ሚኖ/ ያስመስለዋል:: ጉንጩ በወጠረው ጫት የማር ስልቻ መስሏል:: አፉ አቅጣጫውን ስቶ ጣመም ብሏል:: ሁሉ ነገር ለእኔ አዲስ ትዕይንት ነው::

«የፍ/ቤቱን ውሳኔ ወደጎን ተወውና ችግር አለብኝ ፎቶ አልነሳም ብለህ መቅረት ትችላለህ:: ቢደበድቡህ እንኳን እንቢ ማለት አለብህ::» እንዴት ማድረግ እና እንቢ ማለት እንዳለብኝ ሳስብ የሰማሁት በሳልመሰለው «ፎቶማ እንዳትነሳ ከተነሳህ እጅ እግርህን አስረው ሀገር ቤት ይከቱሀል አልነሳም እንቢ ማለት ትችላለህ?» አለኝ ደገመና::

«ተመስገን ይህችን ጭላንጭል ያሳየኸኝ አምላክ..» አልኩ ባራሴ:: ሌላ የሚያጽናናኝ ወዳጅ የለኝ ዘመድ:: «ጠንካራ ሁን UNHCR እንዲቀበሉህ ማስረጃህን ይዘሀል?» ሀያት ነች:: የሽምሰዲን ሚስት:: በምን አይነት ካልኩሌሽንና ፎርሙላ ከወንድ ጋር እንደ ታሰረች አልገባኝም ነበር:: ፊቷ ወንዳ ወንድ እንኳን አይደለም:: በኋላ ሲገባኝ እሷ እስረኛ ሳትሆን ባሏ ጋር መሆን ፈልጋ ተፈቅዶላት ነው:: ስትፈልግ ወደ ውጭ ወጥታ ሰርታ ትገባለች:: «አዎ!..በቂ ያልኩትን ማስረጃ ይዣለሁ»

«አይዞህ እኔ የምችለውን ያህል እረዳሀለሁ:: ለአማ አብደላ (አጎቴ አብደላ ይሄ የአረቦቹ አባባል ነው::) እነግረውና ፎቶ እንዳትነሳ አረጋለሁ:: ብቻ ማስረጃህን አዘጋጀው::» ውስጤን ደስታው ሊፈነቅለኝ ደረሰ:: ትንሽዬ ፍራሽና ብርድ ልብስ ሰጠኝ:: ተስፋን ስለዘራብኝ ከአምላክ ሊያጽናናኝ የተላከ መሰለኝ:: ሁላችንም ሜዳው ላይ እንጥፈን ተኛን:: ጭልጥ ያለ እንቅልፍ እንዲወስደኝ ተመኘሁ:: ግን አልሆነም:: ገና አይኔን ጨፈን ሳደርግ ጆልባው ሲሰምጥ ባህሩ ላይ ራሳቸውን ለማዳን ሲፍጨረጨሩ ያየኋቸው፣ በጣር የሚጮሁት ጩኸት እረፍት ነሳኝ:: «አንተስ ማምለጫህን አገኘህና እፎይ ብለህ መተኛት ፈለክ እኛስ?..» የሚሉ መሰለኝ:: ልጆ ርቦት ሲያለቅስ የምሰማ ይመስለኛል:: እናቴ ስታለቅስ እየታየኝ እንዲሁ ለባትት በአይኔ እንቅልፍ ሳይዞር አደረ::

በማግስቱ እንደተባለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ሰራተኞች መጡና ፎቶ መነሳቱ ተጀመረ:: ሽምሰዲን እንዳለው ለእስር ቤቱ ሀላፊ ነገረው:: ሻለቃ ነው መሰለኝ ማዕረጋቸው ያኛ አይገባኝም:: ማስረጃዬን ሲያሳየው «ኢሽ


እዳ? ኢንግሊዚ?» አለው ከያዝኩት ጋዜጣ ውስጥ አንዱን አሳይቶት ጋዜጠኛ መሆኔን ሲነግረው ሲል። ይሄ ምንድነው ነው እንግሊዘኛ ነው? ማለቱ እንደሆነ ሲነግረኝ ገረመኝ። ድንኳኑ ውስጥ ገብቼ ተቀመጥኩ። ፎቶ ማለቱ እንደሆነ ሲነግረኝ ገረመኝ። ድንኳኑ ውስጥ ገብቼ ተቀመጥኩ። ፎቶ እንነሳም ያሉ ሶስት የአርሲ ልጆች በመጥረጊያ እንጨት ሲደበድቡ ማየቴ ውስጤን አመመኝ። ፎቶ የተነሱት ሁሉ ክፍል ውስጥ ሲገቡ እኔ አልነሳም በማለቴ ቅጣት እዛው ጸሀይ መሞቂያው ግቢ ነገር ውስጥ እንድሆን ተወሰኑብኝ።

ይህ ለእኔ ቅጣት ሆኖ አላገኘሁትም። ትንሹ ክፍል ውስጥ 81 ሰዎች አሉ። ትልቁ ውስጥ 246 ኢትዮጵያዊያን አሉ። እዛ ውስጥ ከመተፋፈግ ውጭው ይሻለኛል። የሚገርመው ነገር ትንሹ ክፍል ውስጥ ካሉት 81 ሰዎች ውስጥ 1 ጆርዳናዊ 2 ሰክረው የተያዙ ሳውዲያዊ ሶስት ኤርትራዊ አሉ። ቀሪዎቹ ኢትዮጵያዊያን ናቸው። እኔ ያለሁበት ቦታ 3 ነን። ሴቶች ክፍል 9 አሉ። በአጠቃላይ 332 ኢትዮጵያዊያን በሚገራሽን እስር ቤት ውስጥ አለን። በጣም የሚያሳዝንና የሚያሳፍር ነው።

እስር ቤት ውስጥ ረጅም ጊዜ የቆየው ሽምሰዲን ነው። 2 አመት አልፎታል። ለምን ወደ ሀገሩ እንዳልተመለሰ ስጠይቀው የኦነግ ታጋይ ጭርሱኑ አዋጊ እንደሆነ ነገረኝ። አላመንኩትም። ላምን የምችልበት ምንም ሁኔታ አላየሁበትም። በአወራንባቸው ሰዓት ስለ ኦነግ ምንም የሚያውቀው ነገር የለም። ማንኛውም ሰው የሚታገልለትን ድርጅት አላማ ካላወቀ እሱ የድርጅቱ ታጋይ ሳይሆን እቃ ነው የሚል እምነት አለኝ። ሽምሰዲንም እየታገለ ከሆነ ከዚህ የተለየ አይደለም። ባየው ትንሽ ሲንቀሳቀስ ያለክልካል ዱር፣ ጫካ ሮጦ አዋግቷል ማለትም ይከብዳል። የድሬደዋ ልጅ እንደሆነ ሲናገር ሰምቻለሁ። አባቱ ነጋዴ የነበሩ ሲሆን በደርግ እንደተገደሉ አውግቶኛል። እውነት ከሆነ ማለት ነው። ሰዎች ራሳቸውን ጀግና አድርገው ሲቆልሉ መስማት ምንም አይመስለኝም። ከጀርባቸው ያለውን ባዶነት ሳይበት የፈጠራ ታሪካቸውን እንዳልታተመ ልብወለድ ነው የምሰማው። ያውም በሰነፍ ጸሀፊ የተጻፈ ተልካሻ ልብ-ወለድ። ባልሆነ ታሪክ ራሱን ክቦ በፈጠረው ውሸት ተጀቡኖ ጊዜውን በእስር ቤት እያሳለፈ መሆኑን ለማወቅ አንድ ቀን አልፈጀብኝም። ለምን ይህን ህይወት እንደመረጠው ግራ ገባኝ። ለእኔ ግን መንገድ ጠርጎልኛል። ከጭንቅ ገላግሎኛል። ራሱ የፈጠረውን እውነት አድርጎ ራሱን በማሳመኑ የገባ የወጣውን ሲሰልሉኝ ነው ማለት ይወዳል። እዚህ ጋር ግን እሱ ብቻ አይደለም ሌሎችም አሉ። ያገኙትን ለኤምባሲ ሰላይ ነው ማለት የሚወዱ ሞልተዋል። ግን ምንም የሚሰልል የሌላቸው ናቸው።







ይህ ፎቶ ከየመን ታይምስ ጋዜጣ ላይ የተወሰደ ነው። የመን የእርስ በርስ ግጭት በተነሳበት ወቅት ስደተኞች UNHCR ቢሮ ላይ መፍትሄ ይሰጠን ብለን ተቀመጥን። ዝም ብለው ሳይሆን በውርደት ተረናቀውን ብለው መወጊያ መሸሻ አጥተው ነው። ሰልፍት መሬት ያለምንም መፍትሄ የተቀመጡት ስደተኞች ታስረው ላይ የተነሳ ነው። እኔም ለነፃ እንደገባሁ የታሰርኩበት ጫሬው ፍርግርግ የጸሀይ መሞቂያ ቤት ይህ ነው።

ሌላም እዚህ እስር ቤት ውስጥ ረጅም ጊዜ የቆየ ልጅ አለ። እሱ ደግሞ የአልሸባብ ታጋይ እንደነበር ያወራል። አመት ከሁለት ወሩ ነው። ከሽምሰዲን የተለየ አይደለም። የማይሆን አለም መፍጠር..የማይሆን ታሪክ መተረክ. ሌሎችም አሉ። ይህ ግራ መጋባቴ እውነት እንደሆነ ያወኩት ታዋቂው የኦሮሚኛ ድምጻዊ ኖሁ ጎበና ለአንድ ወር ከአስራ አምስት ቀን አብሮኝ በታሰረበት ጊዜ ነው። ኖሁ ያለኝን እሱው በስልክ ያገናኘኝ ሁለት የኦነግ ባለስልጣኖች ደግመውልኛል።

«አባልና ደጋፊ ከሆነ ሁሉም የኦሮሞ ህዝብ ከጎናችን ነው። እኛን በመደገፋቸው ታስረዋል፣ ተገርፈዋል፣ ተገለዋል፣ ሀገር ለቀው ተሰደዋል። ታጋዮቻችን ግን አሁን ያሉት ኤርትራ ውስጥ ነው» አሉኝ። በእስር ቤት ቆይታዬ የታዘብኩት፣ ያየሁት ብዙ ነው። ሀበሻ ፍቅር ያለው ህዝብ ማለት መሆኑን ያሳዩኝ ብዙ ሰዎችን ያየሁበት ያ-የእስር ቤት ሌላው አጋጣሚ ነው። እስረኛ ወገኖቻቸውን ሊጠይቁ መምጣታቸው ነው ያስደሰተኝ። እዚህ በስደት ሀገር እርስ በርሳችን ካልተረዳዳን ማን ሊረዳን ይችላል? ውጭ ያለው የታሰረውን መጠየቁ አስደሰተኝና ላናገራቸው ተጠጋሁ። ማክሰኞ ቀን ለነፃ ወደ እለው እስር ቤት ቷዘዋውረን እርብ ቀን ነው የመጡት። አንደኛዋ አይኗ ምትሀት ያለው ይመስላል። በጣም ያምራል፣ ይስባልም። ሸዋዬ



ቀልቤሳ ትባላለች:: ጓደኛዋ ሀና ነው ስሟ:: ቁመትሽ ሎጋ ነው..የምታስብል ናት:: ደፍጠጥ ባለው አፍንጫዋ ላይ የሆነ አይን የሚስብ ነገር የተለጠፈባት ትመስላለች:: አይኗ እንደ ጓደኛዋ ጎላ ያለ ነው:: ሁለቱም ጠይምነትን የተላበሱ ናቸው:: እንጀራ ፈትፍተው በላስቲክ.. በላስቲክ መድበው ቋጥረዋል:: ሸዋዬ በቀዳዳው በኩል አቀበለችኝ::

«ሰላም..» አልኳት ሸዋዬን::

«ሰላም! አዲስ ነህ?»

«አሮጌ ነኝ አታይውም ሽበት ጀምሮኛ?» ሁለት ነጭ ሆና የበቀለች ጸጉሬን አሳየኋት:: ከተሳካልኝ ለመቀለድ ፈልጌ ነው::

«ኧረ!..ለእስር ቤቱ ማለቴ ነው?»

«እስር ቤት ተወልዶ ያደገ አለእንዴ? የለም?» መደናገጧን ሳይ..ቀልዴን ቆም አደረኩና ወደ እውነታው መጣሁ:: «አዎ!..ለእስር ቤቱም ለሀገሩም አዲስ ነኝ:: በባዕድ ሀገር እህቶች ሳገኝ ልቀልድ ብዬ ነው:: የተሳካልኝ አልመሰለኝም አስደነገጥኩሽ?..»

«ኧረ!..አልደነገጥኩም» አለች::

«በነገራችን ላይ እዚህ ሁሌም ትመጣላችሁ ማለት ነው? አዲስና የቆየውን ትለያለሽ?»

«በሳምንት በሳምንት ባይሆንም ሲሳካልን እንመጣለን እኛም ባንመጣ ሌሎች የቤተክርስቲያን ልጆች ስለሚመጡ..» የምሰማውን ነገር ታግሶ ማስጨረስ አልቻልኩም:: ስለ ቤተክርስቲያን የሰማሁትን ማመን አቃተኝ::

«ምን?!..ቤተክርስቲያን ነው ያልሽው? ለምን ትቀልጃለሽ? ለማጽናናት ብለሽ ከሆነ ምርጥ እህት ነሽ..» በተራዋ አላስጨረሰችኝም:: እኔ ግን በእውነትም የተሰማኝን ነው የተናገርኩት:: በፈጣሪ እንድንጽናና ያለችኝ እንጂ አክራሪ የሙስሊም ሀገር በመሆኑ ከተያዝኩ ጀምሮ የገጠመኝን ስለማውቀው ቤተክርስቲያን የሚታሰብ መስሎ አልታየኝም ነበር:: «ግን በእርግጥ ቤተክርስቲያን አለ?» እውነት አልመሰል አለኝ:: በርግጥስ እንዴት ሊሆን ይችላል ብዬ ላስብ? አጠቀ የሚባለው ቦታ በተያዝንበት ጊዜ የአንዱን ልጅ ክሩን ከአንገቱ ላይ በጥሶ እንዴት እንዳደረገው አስታውሳለሁ:: ታዲያ እዚህ ሀገር ላይ እንዴት ተብሎ ቤተክርስቲያን ልጠብቅ?

«እውነቴን ነው ምን አስዋሸኝ ሰማዕቱ ጊዮርጊስ ነው ያለው..»

«ዋው! ደስ ይላል»

«ለምን መጣህ ግን? እዚህ ሀገር እኮ ለወንድ ልጅ ስራ ያስቸግራል»





«እኔ ስራ አጥቼ አይደለም ከሀገሬ የወጣሁት»

«የፖለቲካ ችግር ነው?»

«ወደ እሳው ይጠጋ ይሆን? መንግስትን ሽሽት ነው» ምስጢሬን ለማንም መንገሩ አልተመቸኝምና ጨዋታ መቀየር ፈለኩ:: «ሁሌ የምትመጡ ከሆነ ላስቸግርሽ?» በእርግጥም ትልቁን ችግር የማዋያት አይነት በመሆኗ ነው ልጠይቃት ያሰብኩት::

«ምን ፈልገህ ነው? ምን ልተባበርህ?» እኛ ስናወራ የያዙትን ምግብና ልብስ ጓደኛዋ ሀና ማከፋፈሉን ተያይዛዋለች:: ሀና የቀረውን እቃ ወስዳ ላልሰጠችበት ክፍል ለመስጠት መጣች:: ሄድ መለስ ስለምትል የምናወራውን ግማሹን ነው የምትሰማው:: «ልብስ እፈልጋለሁ ገንዘብ አለኝ:: ልብስ በለበስኩት ብቻ..» አቤት!! ፍጥነቷ..«ውይ! የሚሆንህ ካለ ከዚህ ልስጥህ?» ሀና ከያዙት ፌስታል ውስጥ አሮጌ ልብስ አወጣች:: ነጭ ሸሚዝ፣ ቲ-ሸርት፣ አሮጌ ጅንስ..እንባ ተናነቀኝ:: ሰግ ተናነቀኝ:: አለመፈለጌን ራሴን ብቻ በማነቃነቅ መመለሴን አስታውሳለሁ:: ድብልቅልቅ ያለ ስሜት ተሰምቶኛል:: በኋላ ላይ በተረዳሁት መሰረት ቤተክርስቲያን በባህር ለሚመጡ ልጆች ያላችሁን፣ ከምትሰሩበት ቦታ የምታገኙትን ሰብስቡ ተብሎ ራቁታቸውን ለሚመጡ ለመስጠት የሚያደርጉት በጎ ምግባር ነው:: በሰዓቱ ግን ለእኔ ከፋኝ:: «አልፈልግም ገንዘብ አለኝ:: አዲስ ልትገዢልኝ ከቻልሽ..» ሁለቱም ሀሳቤን የተረዱ ይመስላል:: *(ምንም ደሀ ቢሆን ባላደግም የሰው ሙራድ ልብስ ለብሼ አላውቅም:: የታላቅ ወንድሜን አሮጌ ልብስ እንኳን በፍጹም አለብሰም ነበር:: በየዋህነት ልትሰጠኝ ብትል ከፋኝ:: የሄደ ሰው ብዙ ያያል:: ብዙ ያውቃል:: ገና ምኑን ነካሁት?..)*

«አይዞህ!!» አሉ በአንድ ላይ:: የኢትዮጵያ ሁለት መቶ ብር አውጥቼ ሰጠኋት:: «ልብሱን እኔ በራሴ ገዝቼ እልክልሀለሁ ገንዘቡም ለሌላ ነገር ያስፈልግሃል እና 200 ብር በየመን ሪያል 4400 ነው[8] ዘርዝሬ ከልብሱ ጋር አብሬ እልክልሃለሁ::» ሸዋዬ የመልክ ማማር ብቻ ሳይሆን ሰብዓዊ ውበቷም ጎልቶ ታየኝ:: «ምን ምን ትፈልጋለህ?» ጠየቀችኝ::

«ቲ-ሸርት፣ ሱሪ፣ ሸሚዝ፣..በቃ! ለወንድ ልጅ የሚያስፈልግ ነገር አለ አይደል?..» ይገባታል ብዬ ነው:: ፓንት..ካልሲ የለኝም ማለቱ አሳፍሮኛም ነው:: በእርግጥም ያሳፍራል፣ ይከብዳል:: ያውም ገና አሁን ላወቁት ሰው:: «ሌላስ ምን ትፈልጋለህ?» አሁን ሄና ነች የጠየቀችኝ የሚነበብ ነገር ካለ እንደምፈልግ ነገርኳት::

---

[8] ይሄ ያኔ ነው አሁን የእኛ ብር ወርዷል

«መጽሐፍ ቅዱስ እልክልሃለሁ።» ውስጡ ካለው ችግር ጋር የተሰማኝ ደስታ ትንቅንቅ የፈጠሩ መሰለኝ። ስሜቴ ዝብርቅርቅ ሆነብኝ። በእርግጠኝነት ፈጣሪ ሲያጽናናኝ ፈልጎ የላካቸው መሰለኝ። ወሬያችንን ጨርሰን ልንለያይ ስንል «አይዞህ በርታ ጠንካራ ሁን ሁሉ ያልፋል። ፈጣሪ የሚወደውን ነው የሚፈትነው» አለችኝ ሸዋዬ።

«አዎ! የሚወደውን ነው የሚፈትነው...» ስትል ሀናም ደገመችው።

ሁሌ ጥያቄ የሚሆንብኝ ነገር ይሄ ነው። ፈተና የበዛበትን ለማጽናናኛ የተፈበረከች አባባል ስለምትመስለኝ አልወዳትም። «ኧረ እባክሽ!.. እውነት ስለሚወደኝ ነው ህይወቴን ሁሉ በፈተና ሞልቶ የሚያበቃ የኘ? ቤተክርስቲያን ትሄጂ የለም? መልዕክት ንገሪልኝ ጥላኝ እኖ ፈተናውን አቁምልኝ ብሎሃል በይልኝ» አልኳት። እነጋገሬ የሰቀጠጣት መሆኑ ያስታውቅባታል።

«ይቅር ይበልህ» አሉኝ። ሁለቱም አንድ ላይ «ሰላም ዋሉ» ብዬ ግንቡ ጥግ ተቀመጥኩኝ። ብሶት ይሁን ምን የማላውቀው ስሜት ተሰምቶኛ ል። በእርግጥ ለምንድን ነው ፈተናዬ የበዛው? ሌላውን የማይፈትነው ጠልቶት ይሆን? ቀጥታ ተነስቼ እቃዬን ወደ አስቀመጥኩበት ቦታ ሄድኩ ያቺ የፈረደባት ሲከፋኝም ስደሰትም የምጽፍባት ደብተር... ይቅርታ ስደሰትም አልኩ? ደስታ ምንድነው? ስደት ከወጣሁ አይቶቀለሁ እንዴ? ማን አይቶት ይሆን? ያውም በሶማሊያ ያውም በባህር የመጣ ስለደስታ ማውራት ይችላል? ብቻ ደብተሬን ሳብኩት። «ጥላኝ!!» የሚል ርዕስ አስፈርኩና የተሰማኝን አስቀመጥኩት።

ጥላኝ

የፁሉ ፈጣሪ መሆንህን ለምናለሁ
እንደ ፈጠርከኝም አውቃለሁ
አድራጊ ፈጣሪ በመሆንህ
ስትዋከብ ስራ በዝቶብህ
ሁሉን ለመታዘብ ስትቸኩል
እኔን መፍጠርህን ረሰተሀል?
ወይስ የመከራ ቋት ልታሸከመኝ
አስበህ ነው የፈጠርከኝ?
ችግር መከራው ተደራርቦ
ሊሸነቁጠኝ እንገብግቦ
ስናውዝ በመከራ ተይዤ
ስንገዳገድ እንተን ይዤ
ምነው እንዳላየ ሆንክ
ወይስ ረስተሃል እኔን እንደፈጠርክ?
ረስተኸኝ ከሆነ እኔም ልርሳህ
እርዳኝ ብዬ ስልጨቅጭቅህ
አይተህ ከሆነ ዝም ያልከኝ
ለምንድን ነው የጠላኸኝ?
ብዙ ጠየኩህ ምላሽ ሳትሰጠኝ
መጨቅጨቁም አይሰለቸኝ
ንገረኝ እውነቱን ልገላገል
የወደደውን ይፈትናል ይሉሀል
የወደድከውን ከሆነ የምትፈትነው
ያልፈተንከውን ለምን ጠላኸው?
ፍጥረትህ እንደሆነ እያወከው
አንዳን ፈትነህ ሌላውን ያልፈተንከው
ለምንድነው የመረጥከው?
ሚዛን ሰተህ ያበላለጥከው?
አንዱ ጠግቦ ሲያገሳ
ሌላው ተርቦ ሲከሳ
አንዱ በደስታ ሲቦርቅ
ገሚሱ በችግር ሲማቅቅ
አልገባኝም ለምንድን ነው ያዳላኸው
አንዳን ጌታ አንዳን ሎሌ ያደረከው?
ለገሚሽ ሰተህ ለገሚሽ የነፈከው
እውነት እውነት ነው ጠልተኸው
ያልፈተንከው የምታንደላቅቀው?
እውነት..እውነት ነው ወደኸኝ
በፈተና የምታጨናንቀኝ?
ወደኸኝ ከሆነ መከራ ያበዛህብኝ
መቋጫ የሌለው ፈተና የሰጠኸኝ
እጣህ ጥላኝና እፎይ ልበል
ከከመርክብኝ መከራ ልገላገል
ይህን ጽፌ አስቀመጥኩ።





ትንሽ ስቆይና ስረጋጋ ግጥም የጻፍኩበትን ደብተር ገለጥ አድርጌ ከስሩ «መከራ በልክ ሲሆን ፈጣሪን ለማስታወስ ሲበዛ ደግሞ ፈጣሪን ለመዳፈር ይጋብዛል» ብዬ ጻፍኩበት። ጥቅስ ለመጻፍ የግድ ፈላስፋ ወይም ስሙ የተጠራ ምሁር መሆን የለብኝም። ለራሴ የተሰማኝን አስፈርኩ። በዛ..የእኔ መከራ በጣም..ምነው መቋጫ አጣለት? ወዲያው ማሰቢያዬ ውስጥ መጥቶ ውትፍ..ስንቅርቅርቅር ያለ ትዕይንት እንደ ፊልም ይግተለተል ጀመር። ከ90 ሰው በላይ እንደጫኑ የሰመጠው ጀልባ፣ በጣር የሚያወጡት ድምጽ፣ ባህሩ ላይ ያደርጉት የነበረው የጭንቀት ትንቅንቅ፣ ቦሳሶ 3 ቀን በርሀብ ጠውልጎ የተረፈ.ንን ቁርስ የበላው ልጅ፣ እያየ ሚስቱ የተደፈረችበት ልጅ፣ በሶስት ወንዶች የተደፈረው ወንድ፣ 2 እግሩ አልታዘዝህ ብሎት ሰው አዝሎ የሚያንቀሳቅሰው፣ ህጻን ልጅ ታቅፋ ዳግም እርጉዝ የሆነችው ሴት...ሁሉም በየተራ ታዩኝ። ውስጤ ደግሞ ዱጋግሞ አነባ። ለካ የባሰም አለ። ወረቀቱ ላይ ባልፅፈውም ቀና ብዬ ተመስገን አልኩ፣ ሞገደኛው ሀሳቤ ደግሞ «ግን

ለምን?..» የሚል ሌላ ሀሳብ አፈለቀ:: እውነት ግን ለምን ስቃያችን በዛ? እስከመቼስ በጦርነት ስንለበለብ፣ በርሀብ ስንረግፍ፣ በስደት ስንንከራተት እንኖራለን?

ልብ እንዲባል የምፈልገው ያኔ «ጥላኝ» ብዬ የጻፍኩትን ግጥም እዚህ ላይ ማስፈር የፈለኩበት ምክንያት አለኝ:: ግጥሙንም ሆነ በሰዓቱ ላይ ማስፈር የፈለኩበት ... ልብ ያሰብኩትን ሳስፍረው ያኔ የተሰማኝን ስሜት ለማሳወቅ መሆኑ ልብ ይባልልኝ:: በዛ ላይ ስረጋጋና ነገሮች ሲረግቡ «ጥላኝ» ከሚለው ግጥም ከበታቹ ልመና ጨመርኩበት::

*የተሰማኝን ሳልደብቅ*
*በደሉንታ ሳልሸማቀቅ*
*ካልከፋሁ ይህን ማለቴ*
*በአማላጅቷ በእመቤቴ*
*እጠይቅሀለሁ ደቅርታ*
*ዳግም በፈተናህ እንዳልንገላታ*

*ይህን ብልም ፈተናው ግን አልቀረልኝም:: ፍቅሬ፣ ትዳሬ..የልጄ እናት በሞት እንደ ተለየችኝ መርዶውን የሰማሁት በእስር ተንገላትቼ ስመጣ ነበር:: በአመቱ ደግሞ አንዷን የእናቴን ልጅ የወንድሜን መርዶ ሰማሁ:: ከዚህ በላይ ሀዘን ከዚህ በላይ ቁስለትስ ደናር ይሆን? የደረሰበት ካልሆነስ የእኔን መሪር ሀዘን ማን ይረዳኝ ይሆን? እንጃ ማንም ቢረዳኝም ባይረዳኝም የህይወት ሂደቴን..ገፈቴን መጣጣሜን ቀጥያለሁ:: አለትንሩል አለካለች..*

ወደ ትረካዬ ልመለስ...የዛኑ ቀን ሌሎች እስረኛ ጠያቂዎች መጡ:: ሁለት ሴቶች:: አንደኛዋ በቅላቷ ላይ ፊቷን ያበላሸው ማድያት ቀድሞ አይንን ይስባል:: ሁለተኛዋም ጠይም መሆኗ ብዙም አያስታውቅም እንጂ ማድያት አለባት:: ባየሁት ነገር ሁሉ ከአለመደሰቴ ጋር የእነሱም ኑሮ አስደሳች አለመሆኑን ገመትኩ::

«አንተ ልጅ ለሃን አምጣና የሚበላ እንስጣችሁ!» ስትል ነበር ከሀሳቤ የባነንኩት:: ሽምስዲን ለእንደዚህ አይነት ነገር ፈጣን ነው:: ቶሎ እቃ አቀበላቸውና ያዘጋጁትን ምግብ ተቀበለ::

«አንተ አዲስ ነህ? በፊት እሱ ብቻ ነበር እዚህ ውስጥ..» ወደ እኔ እያየች ሀዘኔታ ባለው መንፈስ ጠየቀችኝ::

«አዎ!»

«ሌሎችም አዳዲሶች አሉ መቼ ገባችሁ?»

«ማክሰኞ»

«እደ‍ሀ እግዚአብሄር ያውጣችሁ:: ለመሆኑ ስንት ናችሁ?»





«በጣም ብዙ ነን ወደ 38 አካባቢ::»

«ብዙም አይደለማ?» አባባሏ ገረመኝ:: ይህንን ያህል ቁጥር እንዴት ብዙ አይባልም? አባባሏ እስከዛሬ ካየችው አንፃር መሆኑ ታወቀኝ:: ቢሆንም ግርምት መጫሩ እንዳለ ነበር:: የአንድ ሰው ህይወት፣ የአንድ ሰው እንግልትና ስቃይ የማያሳዝነን ሆነናል:: ለዘመናት በስቃይ፣ በችግር፣ በረሀብ ብሎም በጦርነት መኖራችን ሁሉን አጣጥመን ማየታችን ልባችንን አደንድኖታል:: ወገን ሲረግፍ ማየት በሰቆቃ ውስጥ ማለፍ ግዴለሽ አድርጎናል? መቼ ነው የመከራው ዝናብ የሚያባራው? መቋጫ የሌለው ሀሳብ ውስጥ ገባሁ:: አፌ እንዳመጣልኝ...«ሌላ ጊዜ ከዚህ በላይ ይገባል ማለት ነው?»

«200 እና 300 ሰው በአንዴ ጊዜ ይመጣል» በቀለች የምትባለው ነች ያለችኝ:: በይበልጥ ላወራት ፈለኩኝ:: «እመለሳለሁ ልጆቹን ዛሬ ልጠይቅ» መልሴን ሳትጠብቅ ሄደች:: አልቀናኣ!! በስደት አልቀናል..ያሰኛል:: ይሄ በሶማሊያ በኩል የወጣነው ነው:: በጅቡቲ፣ በሱዳን፣ በኬንያ በቀን ስንት ሰው ይወጣል? ስንቱ በየጫካው ቀርቷል? ስንቱ ባህር ሰምጧል? ስንቱ አካለ ጎዶሎ ሆኗል? በሶማሌስ በኩል ምን ያህል ተጭኖ ምን ያህሉ ሞቶ ምን ያህሉ አምልጦ ነው ይህን ያህል ቁጥር የሚታሰረው? ይሰቀጥጣል:: ማሰቡም ራሱ በጣም ይሰቀጥጣል:: ደስታ እየራቀው እኔነቴን በሰቆቃ መወጠር ሆነብኝ:: ፋይዳ የሌለው ህሊና የሚያደማ ሀሳብ መጎንጎን፣ ከንቱ ድካም ሆነብኝ:: ግራ ገባኝ:: በሌላ ጊዜ ከእስር ወጥቼ እስረኞች የመጠየቅ ወርሃዊ እቅድ ይዤ ጥቂት ልጆችን አስተባብሬ ስንመላለስ 800 እና 900 ሰው እዛው እስር ቤት ተፋፍገው አጋጥመውናል::

ከባህር እንደወረድን ስወድቅ ድንጋይ ልቤን የመታኝ ህመሙ አሁንም አለ:: እያመመኝ በመሆኑ..ጠያቂዎች ካመጡት ምግብ ትንሽ በላሁና ማረፍ ፈለኩ:: በተከታታይ ቀናት እንቅልፍ አልወሰደኝም:: ገና አይኔን ጨፈን ሳደርግ ባህር ላይ በጣር ሲወራጩ ያየሁት፣ በጣር ሲጮሁ የሰማሁት አሳዛኝ ድምጽ..እረፍት ነስቶኛል:: በሚገርም ሁኔታ የመብላት ፍላጎቴም ቀንሷል::

በቀለችና ጓደኛዋ ብዙዬ ተመልሰው መጡ:: ለጥየቃ ከቤተክርስቲያን መምጣታቸውን፣ የማርያም ማህበር ዋነኛው አላማ እስረኛ መጠየቅ፣ የታመመ መርዳት፣ በሀዘን ወቅት ማጽናናት..እንደሆነ ነገሩኝ:: «ተባረኩ!» ከማለት ውጭ ምን እላለሁ?

«ቅድም የሆኑ ልጆች ከቤተክርስቲያን ነው የመጣን ሲሉ አላመንኩም ነበር ለካ እውነታቸውን ነው?» ለማረጋገጥ ነው እጠያየቁ:: የቤተክርስቲያኑ ነገር አልዋጥልህ ብሎኝ ነበር:: አሁን ደግሞ እነዚህም ደገሙት::

«እውነታቸውን ነው። እዚህ ሀገር ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ነው ያለው» አለችኝ ብዙዬ። ውስጤን የሆነ ሀሴት ሲወረው ተሰማኝ።

«ልጆች መጥተው ነበር? እነማን ይሆኑ?» በቀለች ጓደኛዋን ጠየቀች። እንጃ! የሚል መልስ ስለተሰጣት

«ሸዋዬ የምትባል እና ጓደኛዋ ሀና..» ነገርኳቸው፡

«አ!!!!..እነሱማ አገልጋይ ናቸው። ሸዋዬ ዘማሪ ናት» አለች በቀለች። «አ!!!!..እነሱማ አገልጋይ ናቸው። ሸዋዬ ዘማሪ ናት» አለች በቀለች። ሌላ ሌላም ፀጋውን ያደላት በስደትም ለእዚህ የታደለች የሚል አክልኩበት። ሌላ ሌላም ፀጋውን ያደላት በስደትም ለእዚህ የታደለች የሚል አክልኩበት። ከቀኑ 9 ሰዓት አካባቢ ብዙ አወራንና ሁሌም እንደሚመጡ ነግረውኝ ሄዱ። ከቀኑ 9 ሰዓት አካባቢ የፖሊስ ጣቢያው ቁልፍ ያገር በሩን ከፍቶ ሰናይትና አልማዝን አስገባቸው። «ሃዲ መረተክ ሃዲ አክተክ» ያቺ ሚስትህ ይቺ እህት ናቸው አይደል? አለኝ። አሁን ነው እንዲህ አስተካክዬ የጻፍኩት እንጂ ያኔ ምን እንዳለኝ አልገባ ብሎኝ በአስተርጓሚ ነው የገባኝ። የውሸት ሚስት እና እህት እንዳሉኝ ረስቻቸዋለሁ። እግዚአብሄር ይስጠው። አጠቅ የሚባለው ቦታ እነሱን እንዳይተናኮሷቸው የዋሸነው ለመገናኛ ጥሩ ዘዴ ሆነልን።

«አይዋ!» አልኩት። ለጉብኝት ብሎ ማገናኘቱ ነው። ገቡና በሩ ተቆለፈ የጋራ ጨዋታችንን ቀጠልን። ሴቶች ክፍል አእምሮዋን የሳተች ልጅ «እንትን እንዳለች ነገሩኝ። ችግሯ ምን እንደሆነ የሚያውቅ የለም ብቻ «እንትን አደረጉኝ.. ኡኡ...ደፈሩኝ!» እያለች ሌሊቱን ሙሉ ስትጮህ ታድራለች። ብቻዋን.. እንደምታወራ ነገሩኝ። ሌላም ኮንትራት ቤት ለ9 ወር ምንም ሳይከፍሏት ቆይታ ፓስፖርቷ ላይ ቀይ አስመትተው ሊመልሷት የታሰረች..ብቻ ብዙ ብዙ አወሩኝ።

ወደ ሰነዓ እስር ቤት ከተዘዋወርን በአስራ ሶስተኛው ቀን ሌሎች ትዕዝ ከሚባለው ቦታ መጡ። ወደ ሳዑዲ አረቢያ ለመሸጋገር በዝግጅት ላይ እያሉ የተያዙ ናቸው። ረሀብ አቅም ነስቷቸዋል። አንደኛው ወድቆ አፈር የነካውና ግንብ ስር ያስቀመጥነውን ዳቦ አንስቶ መብላት ጀመረ። ውስጤ ተላወሰ። ሳልበላው ያስቀመጥኩት ሁለት ዳቦ ለስንቶቹ ይሆናል? ማልቀስ የማይሆንልኝን ያህል ስደት ላይ ሆደ-ባሻ ሆኛለሁ። እንባዬ ቀደመኝ። ለሽምስዲን ነገርኩት። ከእሱና ሚስቱ የተረፈ ምግብና አራት ዳቦ አወጣ። ሁለቱም እስር ክፍል ያሉትን እየተጣራ ያላቸውን አሰባስቦ አበላቸው። ሶስቱ ሴቶች ስለነበሩ ወደ ሴቶች ክፍል ተወሰዱ። አንደኛዋ ተደግፋ ነው የምትንቀሳቀሰው።

«ምን ሆና ነው?» አጠገቤ ያለውን ጠየኩት። ጠይም ሆኖ ፊቱ ላይ የብር ጉልላት የሚባለውን ያህል አይን ተከምሮለታል።





«ከመኪና ላይ ወድቀው ተሰብራ ነው» ድምፁ ከእሱ ሰውነት የሚወጣ አይመስልም። ጥብቅ ካለ መፃጉ ሰውነቱ ወፍራም አስገምጋሚ ድምጽ መውጣቱ ገርሞኛል። «ስንት ናቸው?»

«ሶስት። አንደኛው ወዲያው ሲሞት ሁለቱን የመኒዎቹ ለስድስት ቀን አስታመዋቸው ከእኛ ጋር አገናኙዋቸው።»

«አሀ..! ለብቻቸው ነበሩ?»

«ከእኛ በፊት ከነበሩት ተጓዦች ጋር ሲጓዙ ነበር። እንደሰማነው ከሆነ ተጭነው ያሉበት ክፍት መኪና ከፊቱ ድንገት መኪና ገባበት። ላለመጋጨት ፍሬን ሲይዝ ወደቁ ጥሏቸው ሄደ።»

«ከላይ ያሉት ሰው መውደቁን..» አቋረጠኝ።

«እንጃ!!..እኛ ግን ጥለናት ላለመሄድ ተጋግዘን ደግፈናት ስንሄድ ተያዝን። አንደኛው የት እንደገባ አላወቅንም።»

«በየት በኩል ነው የመጣኸው? በጅቡቲ ወይስ በሶማሊያ?» የጨዋታውን ርዕስ ማስለወጥ ፈልጌ ነው።

«በጅቡቲ ነው የመጣሁት?»

«ጉዞ እንዴት ነበር?»

«ጥሩ- ነው። መቼም ተሀገር ወጥቶ ምን ቢኮን ዋናው ሕይወት መትረፉ ነው።»

«ምን ያህል ሰዓት ተጓዛችሁ?»

«አንተ እዚህ ቆየህ? እኛንም ያቆዩን ይሆን?» ጥያቄዬን በጥያቄ መለሰው። እኔም መለስኩለትና ሌላ ጥያቄ ብጠይቀውም ሊመልስልኝ ፍቃደኛ አልሆነም። «አይ ተወኝ ያለፈን ማስታወስ በሽታ ነው» በሚል ቃል ዘጋኝ። እውነት ነው። ለእኔም መስማቱ በሽታ ነው የሚሆነኝ። ምን ጥሩ ነገር ሰማሁና ልጓጓ? ተውኩት። እነሱም ከጥቂት ደቂቃ በኋላ በሁለቱ የእስር ክፍሎች ታጎሩ።

በማግስቱ የኤምባሲ ሰራተኞች መጥተው ፎቶ ያነሷቸው ጀመር። በዚህን ጊዜ ፎቶ አልነሳም ያሉትን ፖሊሶች የመቷቸው አመታት ያሳዝናል። ኢሚግሬሽን እስር ቤት ውስጥ እያለሁ አብዛኛውን ጊዜ በመታመም ነው ያሳለፍኩት። ምግብ አልስማማህ አለኝ። ሩዝ መረቅ የሚል ስም የተሰጠው ውሃ ውስጥ ለአራት ሰው አንድ ድንች ከነልጣጩ በስሎ የሚገኝበት ነገር ነው የሚሰጡን። ከጤና ችግሬ ጋር ምግቡ ፈጽሞ አልስማማህ አለኝ። ዕለት ከዕለት የጤንነቱ ነገር እያሳሰበኝ ነው። መጠለያ የሌለበት ቦታ ታስሬ የሚወርደው ዝናብ ሌሊት..ሌሊት ቅዝቃዜውን ቀን ቀን ፀሀዩን መቋቋም አቃተኝ። ጠጣ ላይ ተኝቼ ገና አይኔን ከደን ሳደርግ

እንቅልፍ ሊወስደኝ ሲገዳደር ሲሰምጥ ያየሁት ጀልባ ከነሰዎቹ ይታየኛል:: ራሳቸውን ለማዳን ሲፍጨረጨሩ...ምንም ነገር ያልረዳናቸው፣ በዝምታ ያየናቸው..የጣር ጩኸታቸው እየመጣ እንቅልፍ ይነሳኛል:: ለመተኛት ገርበብ ያደረኩት አይኔን አንኳኩቶ ያስከፍተኛል:: አለመተኛቴ፣ ምግብ አለመውሰዴ ተደማምሮ አቅም ነሳኝ:: ከቅዝቃዜው ጋር ፈጽሞ ልቋቋም አልቻልኩም:: የየመን መሬትን በረገጥኩ በ14 ቀኔ ከእንቅልፍ ማጣትና ከችግሮች መደራረብ ጋር እንደ አእምሮ ጭንቀት አደረገኝ:: ብቻዬን እያወራሁ..ዝናብ እያካፋ ለምን እንደሆነ ሳላውቀው በባዶ እግሬ ስዘዋወር ቆይቼ ተዝለፍልፌ ወደኩ:: ብቻዬን አወራ እንደ ነበር ሲሻለኝ ሽምሰዲን እና ሚስቱ ናቸው የነገሩኝ:: በሰዓቱ ምንም የነካኝን ነገር አላወኩም:: በጭንቀት ተወጥሬ ስለነበር የማውቀውም የማስታውሰውም የለም::

ያለ መጠለያ በፀሀይ ይጋይ የነበረው ሰውነቴ አሁን ደግሞ ወቅቱ ዝናብ በመሆኑ ማስተናገድ ግድ ሆኖበታል:: ራሴን ባወኩኝ በሁለተኛው ቀን ሀይለኛ ዝናብ መጣ:: ራሴን ሽምሰዲን ድንኳን ስር ወሽቅ አድርጌ ባድርም የምተኛበት ቦታ ላይ ከፀሀይ መከላከያ የወጠርኩት ብርድ ልብስ ውሀ ጠጥቶ ጎኔን ማሳረፊያ አጣሁ:: መሬቱም ቅዝቃዜ ይዟል:: ቁጭ ማለትም ሆነ መዘዋወር ስላልቻልኩ የግዴን ጋደም አልኩ:: ከታች የሲሚንቶው ቅዝቃዜ ከላይ ብርድልብሱ የመጠጠውን ውሀ በጠብታ መልክ አዘነበብኝ:: ተባበሩብኝ::

የከፋው፣ የታመመ ላይ ማን የማይበረታ አለ? ተባበሩብኝ:: ህመሜ ብሶብኝ አደረ:: የምድን..የምድን አልመስልህ አለኝ:: ለፖሊሶቹ መታመሜ ሲነገራቸው ምሳዬ ላይ አንድ ጭልፋ መረቅ ጨመሩልኝ:: *(በጣም ደግ አይደሉ?)* የሚሰጡኝን ምግብ ከነአካቴው በልቼው እንደማላውቅ አላወቁም:: ማን ቀና ያድርገኝ? ማን ውሀ ያቀብለኝ? ህክምና የመሄዱ ነገር አልሆነም:: ምኔን እንዳመመኝ እንኳን የማውቅበት ደረጃ ላይ አልነበርኩም:: በህመም ከወደኩ በኋላ አጋጣሚ ሆኖ ብቅ ያለ ጠያቂ አልነበረም:: ለሽንት እንኳን የሚያነሳኝ በማጣቴ ውሀና ሻይ በሚሰጡኝ የፉል ቆርቆሮ /ጣሳ/ እየሞላሁ አጠገቤ ተቀምጧል:: ሽታው ራሱን የቻለ በሽታ ነው::

ፖሊሶቹ አዝነው አንዱ ክፍል ከተውኝ እንዲሞቀኝ ከማድረግ ይልቅ ሽራ ላስቲክ አልብሰውኝ ወጡ:: ተላላፊ በሽታ ስለሆነ እስረኛውን ይበክላል ብለው የባሰ ሞራሌን እንክት! አድርገውት ሄዱ:: በባዕድ ሀገር መሰቃየቴ፣ በእስር መማቀቁ ሳያንስ ያለ አስታማሚ፣ አገላባጭ በሌለበት በህመም መጉደቱ ውስጤን በሀዘን ጎዳው:: ከማልቀስ ሌላ ላደርገው የምችለው የለምና አይዞህ ባይ በሌለበት አስነካሁት:: ከተፈጠርኩ እንደዛን ጊዜ ያለቀስኩ አልመሰለኝም:: እንባዬ ግን አላዳነኝም::





ሽምሰዲን የሚባለው እንዳያገላብጠኝ ከተቀመጠ መነሳት የሚያቅተው ውፍረትና ስንፍና የተዳበሉት ጀብጃባ ነው:: ከፍተኛ የሆነ ራስ ምታትና ውጋት ስለነበረኝ ፈፅሞ መንቀሳቀስ አልቻልኩም:: የሽምሰዲን ሚስት ሀያት፣ ደረቅ ያለ ፍራሽ አምጥታ መውረጃ ስለሌለው የታቆረውን ውሀ ጠርጋ አነጠፈችልኝ:: እንደ ምንም ተንፏቅቄ ያስተካከለችልኝ ቦታ ተኛሁ:: ደገፍ አድርጋ እንዳታነሳኝ እንኳን የመን ያለ ህግና ባህል የዋዛ አይደለም:: እህቴ ወይም ሚስቴ ካልሆነች መንካት ነውር ነው:: ባሏ ሽምሰዲን እንደሆነ እያወቁ እኔን አቅፋ ደግፋ ብትታይ ከፍተኛ ወንጀል ነው ያሳስራል::

እስር ላይ ሌላ ምን አይነት እስር ያስፈርዳል እንዳትሉ:: ሀያት የፍቅር እና የተስፋ እስረኛ እንጂ የህግ እስረኛ አይደለችም:: እንደልቧ ወጥታ ሰርታ ተመልሳ ትገባለች:: ከባሌ አልለይም ብላ እስር ቤት አብራው ገባች:: አበበች የነበረው ስሟን በሀያት፣ ኦርቶዶክስ የነበረ እምነቷን በእስልምና የቀየረችው ለፍቅር ስለፍቅር ብላ ብቻ ግን አይደለም:: በሽምሰዲን ምላስም ተታላ ነው:: የስደተኛነት ማረጋገጫ ለማግኘት ለUNHCR ያቀረበው ጥያቄ ውድቅ ተደርጎበት ሳለ አሜሪካ ሊወስዱኝ ፕሮሰስ እስኪ ጨርሱልኝ ለደህንነቴ ጥበቃ ሲሉ ነው እስር ቤት ተቀመጥ ያሉኝ ብሎ ዋሽቷታል:: ተግጦ እንዳለቀ የበቆሎ እሸት ቆረቆንዳ ሆኖ የታቀፈው እድሉን የውሸት አሪቲ ሰክቶበት፣ የተስፋ አሜሪካን ተጓዥ የፍቅር ምርኮኛ አድርጓት ነው ያለው:: ታዲያ እንዴት እስር ቤት ወንድና ሴት አንድ ላይ ይታሰራል የሚል እሳቤ ሊከሰት ይችላል:: ይህ ሌላ መንገድ ነው:: የመን ብዙ የተገለባበጡ ነገሮች ሲደረግ ይታያል:: ብዙ አስገራሚ ነገሮች ነበሩ:: አሉም:: እንደምንም ከወገቤ ቀና ለማለት ሞክሬ ሳለ ሶስት ትላልቅ ሰዎች መጡ:: ምግብ ሊሰጡን በምልክት ጠሩኝ:: እንዴት ልነሳ? የሽምሰዲንን ሚስት ጠርቻት

«እባክሽ መታመሜን ንገሪያቸውና ለብርድ የሚሆን መድኃኒት ያምጡልኝ» አልኳት:: ነገረቻቸው:: የሚያገላብጠኝ፣ የሚያስታምመኝ እንደሌለኝ ጭምር አስተዛዝና ነገረቻቸውና መጡ:: ፖሊሶቹን ጠርተው ሲያናግሯቸው በሩን ከፍተው እንዲገቡ ፈቀዱላቸው:: በቁመት አጠር የምትለዋ ሴትዮ ገና ስትጠጋኝ እንባዋ ዱብ..ዱብ ማለት ጀመረ:: እኔንም ብሶቴን ቀሰቀሰችብኝ::

«ዋይ!....ሞይቱ እንዲዩ?...» በሀሳብና ጭንቀት ከቀነስኩት ሰውነት ጋር በሽታው ተጨምሮ ጣረሞት ሳያስመስለኝ አይቀርም:: «ዋይ! ሞቶ የለም እንዴ?» ነው ያለችው::

ከሞትኩ ቆየሁ አልኩ በውስጤ:: በጣሳ ለሶስት ቀናት የሞላሁትን ሽንቴን አይታ አዘነች:: ወስዳም ደፋችልኝ::

«መነሳት አቅቶህ ነው?» አንደኛዋ ሴትዮ ትግርኛ ትንሽ ትንሽ ማወቄን ባለማወቃቸው «አጽማ. እንዴዩ ተሪፉ:: እንታይ ክትስዕ ድዓ..እኔ አብዚ. ነገረ ውስጢ አይአትውን..›› አሉ:: «አጥንቱ ቀርቶ ምኑ ይነሳል ብለሽ ነው ይሄስ አይተርፍም:: እኔ እዚህ ነገር ውስጥ አልገባም..» ማለታቸው ነበር ግዙፏ ሴትዮ:: እንባዎቼ የእኔ መሆናቸውን እስክጠራጠር በጆርባዬ እንደተኛ ሁ ተሸኳለው ጆሮዬ ውስጥ ገቡ:: ውስጤ አነባ ማለት ከምችለው በላይ አነባ:: ምን ውስጤ ብቻ አይኔም በደንብ ወጣለት:: ያውም ጆሮዬን እስኪ.ያጥበው::

«ምን ሆንክ ባሰብህ እንዴ?»

«አይ!..» ራሴን በመነቅነቅ ነገርኳት::

«ታዲያ?...»

በእጇ ወደ ተናገሩት ትልቅ ሴትዮ አሳየኋት:: አደይ ይባላሉ:: «ትሰምዕ ዲካ?» አዎንታዬን ራሴን በመነቅነቅ ነው የገለፅኩት:: ደነገጠች:: ይህችኛዋ ሴትዮ ቢድንም ባይድንም እኛ እንሞክር ባይ ናት:: እሳቸው ደግሞ ተስፋ የለውም የሚለው አቋማቸውን እንደያዙ ናቸው:: እሳቸው ትግርኛውን መስማቴ ምንም አልመሰላቸውም:: ያስፈራኝ ተስማምተው ሊያሳክሙኝ አለመቻላቸው ነው:: ለምን አልፈራ አሁን ያለኝ አማራጭ እነሱ ናቸው:: ግዙፏ ሴትዮ የመስማማት አዝማሚያ የላቸውም:: መጥፎ ተናግረው ተስፋ ያስቆረጡኝም እሳቸው ናቸው:: ለእሳቸው እግዚአብሄር ማስተዋሉን ይስጣቸው:: ሌላውን ቋንቋ አያውቅም ብለው መጥፎ ነገርም ሆነ ምስጢር የሚያወሩ ሰዎች ሁሌም ይገርሙኛል:: ቋንቋው ሌላውም ሊያውቀው ስለሚችል የሚያወሩትን መጠን ቢያደርጉት ይህን ያህል ልቤን ባላደሙት ነበር:: የብሄሩ ተወላጅ ያልሆንኩት እኔ እንኳን ይሄው ሰማኋቸው:: በመጨረሻም አንደኛዋ ሩህሩህ አንጀት የተሰጣት አጭሯ በራሷ ወጪ ልታሳክመኝ ፈቀደች:: ፖሊሶቹን በምን ሁኔታ አናግራ እንዳግባባቻቸው ወይም የፈቀዱበት ምክንያት ባይገባኝም ተባብረዋት ህክምና ይዛኝ ሄደች:: በሽታዬን ለእሷ ነግሬያት እሷ በአረቢኛ ለዶክተሩ በቅብብሎሽ ትርጉም ታከምኩ:: መርፌ ተወጋሁ::

በማግስቱ መጥታ መርፌውን እንደምታስወጋኝ ነግራኝ መልሰው አስገብተውኝ ሄደች:: ብርድ ልብስ ደራርቤ ሞቀኝ እና እንቅልፍ ወሰደኝ:: ከእንቅልፌ የነቃሁት ከ18 ሰዓት በኋላ ነበር:: ያውም ሲርበኝ:: በማግስቱ መኝታዬን መልቀቅ ባልችልም የምግብ ፍላጎቴ ተከፍቶ መብላት ፈለኩኝ:: ሴትዮዋም መጥታ መርፌውን ድጋሚ አስወጋችኝ:: በሰላም እንቅልፍ ውስጥ አደርኩ:: ያለማቋረጥ አራቱንም ቀን እየተመላለሰች ለፖሊሶቹ 1000 ሪያል እየሰጠች ወስዳ መርፌውን ታስወጋኝ ነበር:: ሴትዮዋ እያልኩ





የምጠቀመው ስሟን እንድጠቀም ፍቃደኛ ስላልሆነች ነው:: ለስም ማስጠሪያ የተደረገ አይደለም ባይ ናት:: አሁንም ከእኔ ጋር ባላት ግንኙነት እንደ እናቴ የማያት ጥሩ ሰው ናት:: በመሀል ላይ ትንሽ ሻል እንዳለኝ ሸዋዬ ቀልቤሳ የምትባለው ልጅ መጣች:: ግሳኝ ብዬ ዕሬው የነበረውን ግጥም በወረቀት ላይ ገልብጬ ሰው በፈተና ሲወጠር እና ፈተና ሲበዛበት ፈጣሪውንም ቢሆን እንደሚዳፈር አስታውሸበት ብዬ ሰጠኋት:: ምሽቱን ግን ስለዚህ ጉዳይ ደግሜ ደጋግሜ አሰብኩት:: አሰብኩና ሌላ አደራ ብዬ ጻፍኩ…

«አደራ»
አብረኸኝ እንደሆንክ አምናለሁ
ጥለህ እንደማትጥለኝ አውቃለሁ
ጠዋት ማታ አንተኑ እለምናለሁ
አባቴ ጌታዬ እርዳኝ ብዬሀለሁ
ቃል አለህ ከጠዋት
አትሰርዛት አትለውጣት
ትዕግስቱን ስጠኝና ልጠብቅ
ስንቀዠቀዥ እንዳልወድቅ
ከአጠገቤ ምርኩዝ ሁነኝ
እቅፈህ እንድትደግፈኝ
ከበላዬ ሁነኝ ጥላ
ሌላም የለኝ ካንተ ሌላ
መንገድ ጠርገህ ከፊት ምራኝ
ስደናበር ግራ እንዳይገባኝ
ከኋላዬም ተከተለኝ
መከታ ሆነህ እንድትጠብቀኝ
ውስጤ ገብተህ ትዕግስት ሁነኝ
ፈተና እንቅፋቱን ጥረግልኝ
ግራ ቀኙን አንተው ጠብቅ
አልችለውም ብጠነቀቅ
ፈተናውን ቁም በለው
ሁሉም ይሆናል ከፈቀድከው
ይሁን ብለህ ከወሰንከው
ትዕግስቱን ስጠኝና ልጠብቅ
ስንቀዠቀዥ እንዳልወድቅ
ጌታዬ አደራ የልጄን ነገር
በርሃብ፣ በጤና እንዳይቸገር
አድጎ እንዳየው እንደገና
ሳልጠግበው ተለይቼዋለሁ እና
ጠረኑን በቅጡ ሳላሸተው
ድክ ድክ ሲል ሳላየው
የአባት ወጉን ሳላሳየው

ርቂዋለሁ እና ሳልወድ ጥየው
አደራ ጌታዬ በጎውን አሰማኝ
እንዳይታረዝ እንዳይርበው
እንግልት ችግር እንዳይገጥመው
አደራ የምሰጠው ላንተ ነው…››

በዛን ሰዓት ምትትት ያለ ሀሳብ ስለነበር ውስጤ ያለው እንዳለ ነው ያሰፈርኩት:: ግራ ግብት ብሎኝ እያለ የፃፍኳት ነች:: እነዚህን ሀሳቦች (ግጥሞች) ማቅረብ የፈለኩት ሰው ሲጨንቀው እንዴት ግራ እንደሚጋባ ለማሳየትም ጭምር ነው:: ከሁሉ ነገር የከፋብኝ ምግቡን በበላሁ ቁጥር ጨጓራዬን መታመሜ ነው:: የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ጊዮርጊስ ቤተክርስትያን አባላት ሀሙስና አርብ እስረኛ ጥየቃ ሲመጡ የጨጓራ መድሃኒት እያመጡ ልኝ እጠቀማለሁ:: ሸዋዬም ሆነች በቀለች የምለብሰውን አሟሉልኝ:: በተለይ ሸዋዬ የጨጓራ መድሀኒት በማቀበል በኩል በየጊዜው ገንዘቧንም ሆነ ጉል በቷን መሰዋት አድርጋልኛለች:: የሚያስፈልገኝን ሁሉ በማቅረብ ኢሚግሬ ሽን (ጀዋዛት በሚባለው) እስር ቤት በቆየሁበት ሰባት ወር ከ14 ቀን ከእጠ ገቤ አልተለየችም:: ከእስር ቤት ውጭ ያሉት በኑሮ ደስተኛ ባይመስሉም ወገናቸውን ለመርዳት የሚያደርጉት ጥረትና ትግል ይበልጥ ደስ አለኝ::

በየጊዜው UNHCR እስር ቤት መጥቶ እንዲያየኝ ደብዳቤ እጽፋለሁ:: ፖሊሶቹን እንዲወስዱኝ እጠይቃለሁ:: መጀመሪያውኑ እንግሊዘኛ አላርጂክ ነው የሚሆንባቸው:: እኔ ደግሞ አረብኛ አልችልም:: በምን እንግባባ? የሆነ ሆኖ 1 ወር ከ15 ቀን ውትወታና ልመና በኋላ 2000 ሪያል ለአጃቢ ፖሊስ ከፍዬ UNHCR ቢሮ ወሰዱኝ:: ፋጡማ የምትባል ግብጻዊት ፕሮቴክሽን ኦፊሰር ነበረች መረጃዬን አይታ አስያ የምትባል ትውልደ ሀበሻ ጸሀፊጋ መራችኝ:: ፎርም ተሰጠኝና ሞልቼ መረጃዎቼን ኮፒ እያረገች እንድታያይዝ ሰጠኋት:: እስር ቤት ውስጥ ይጠፋብሀል እዚሁ ይቀመጥልህ አለችኝ:: አላመንኳትም:: መረጃዬ ከእኔ አልፎ መውጣት እንደሌለበት አምናለሁና ነው:: ጥሩ እንዳላሰበች ግን በኋላ ተረዳሁኝ:: ቀጠሮ ሳትሰጠኝ ነበር ወደ እስር ቤት የመለሰችኝ:: እስር ቤት ስለሆንክ እንመጣለን ቀጠሮ አያስፈልግህም ነበር ያለችኝ:: በዛ ምክንያት ግን ስንት ስቃይ በላሁ::

በዚህ መሀል አንድ ሀሙስ ቀን ጆሲ የሚባለው ኳስ ተጫዋች (ትክክለኛ ስሙ አህመድ ከሊል) ሊጠይቀኝ መጣ:: ድሬደዋ ካፈራቻቸው የሀገራችን ተጫዋቾች አንዱ ነው:: ለኢትዮጵያ ሙገር ሲጫወት የየመኑ አል-ሄላሊ ክለብ ከአሸናፊ ግርማ ጋር ገዝቶ ካመጣቸው አንዱ ነው:: ከወር በፊት አዲስ አበባ ስደውል ብርሃን የምትባል እህቴን ስልክ ቁጥር እናቴ ሰጠችኝ:: ለእሷ ስደውልላት የመኖሪያ ወረቀቷን ስላላሳደሰች ጆሲን ላከችው:: በእሷ አማካኝነት መታሰሬን ካወቀ በኋላ አልፎ አልፎ እየመጣ ይጠይቀኛል:: ቀጭን የማያስብለው ሰውነቱ ከርዝመቱ ጋር የጥሩ ስፖርተኛ





ተክለ ሰውነት እንዳለው ያየው ይመሰክራል:: ያመጣልኝን አቀበለኝ:: አሁን ስሙን የዘነጋሁት አንድ ሌላም ኳስ ተጫዋች ልጅ አብሮት ነበር:: ያን ሀሙስ ቀን ጆሲ ብቻ ሳይሆን ሌሎች 7 ሰዎች ሊጠይቁኝ ስለመጡ ተደስቼ ዋልኩ:: አርብም እንዲሁ..እስር ቤት በገባሁ በሁለተኛ ወሬ አንድ ልጅ እስረኛ ለመጠየቅ መጣ:: ገና እንዳየኝ «አንተ ምን አመጣህ? የአራት ኪሎ ልጅ ነህ አይደል?» አጠያየቁ እንደሚያውቀኝ እርግጠኛ ሆኖ ነው::

«አዎ! ታውቀኛለህ?»

«የግርማ ወንድም አይደለህ? እህትህ ጽዮን..» አመጣው አልኩኝ! የሚያውቀኝ ሰው ማግኘቴ ደስ አለኝ:: በአዎንታ ራሴን ነቀነቅኩለት::

«ጋዜጠኛ ነህ አይደል?»

እኔ የማላውቀው እሱ የሚያውቀኝ መሆኑ ገረመኝ ቀጠለ.. ‹‹እዚህ ሀገር እኮ ኢትዮጵያ ውስጥ ታዋቂ የሆነ የስነ ጽሁፍ ሰው አለ መወለድ (ትውልደ ሀበሻ) ነው»

«አውቀዋለሁ ያውቀኛል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ::»

«ስልክ ቁጥሩ ካለህ እባክህ ልደውልለት?» ስጠሁትና ሊወጣ ሲል «ሊያገኝኝ ከፈለገ እዚህ ውስጥ ሞባይል ያለው እስረኛ ስላለ የእሱን ስልክ ቁጥር ስጠው» ቁጥሩን ሰጠሁት:: ልጁ ደውሎ ሲመለስ እኔ ጋ ሳይደርስ ያ-ውስጤ ያስበው፣ ውስጤ የሚያውቀው ሰው ደወለልኝ::

«ሀሎ! ወዳጄ ግሩም» አይ በደንብ አስታውሶኛል:: በደንብ ተጽናናሁ::

«ሀሎ! እቶ..»

«አይዞህ..አይዞህ የሚከፈለውን ሁሉ ከፍዬ በነገው እለት አወጣሀለሁ::»

«እሺ!»

«እኔ የማስተምራቸው ልጆች ስላሉ መምጣት አልችልም:: አበበ የሚባል ልጅ እልክልሀለሁ አይዞህ 40 ሺህም ሆነ 50 ሺህ ከፍዬ አወጣሀለሁ..» አቤት ደስታዬ ወዲያው የወጣሁ ያህል ተሰማኝ መሽቶ እስኪነጋ ተጠበብኩ፣ ተጨነኩ:: ችግሬ ሁሉ የተፈታ መሰለኝ:: በነጋታው በጠዋት ተነስቼ ተዘገጃጀሁ:: ግቢ ውስጥ ከወዲያ ወዲህ ስል ቆየሁ:: ጸሀይዋ ብቅ ስትል በጀሪካን ካለው ውሀ አንዱን አንስቼ በብርድ ልብስ የተጋረደችው ግንብ ጥግ ያለች መጸዳጃችን ገብቼ ታጠብኩ:: ከ2 ቀን በፊት እኛ ጋር የገባ ህንዳዊ አለ:: 22 ዓመት የመን ኖሯል:: አረብኛ በደንብ አይችልም ነቅቶ እያየኝ ነው::

«ምን ሆነሀል? ችግር አለ?» ሲለኝ እንግሊዘኛ ሳይሆን የሀገሩን ቋንቋ ያወራኝ ነው የመሰለኝ:: ሁለት ሶስቴ እእእ.. ብዬ ነው የገባኝ:: ህንድ ኩርላ የሚባል ጎሳ ነው አነጋገራቸው ያስቸግራል::

«ዛሬ እፈታለሁ የሚያስፈታኝን ሰው እየጠበኩ ነው»

«አዎ! ለመፈታት ቸኩለሃል?»

«በጣም!» ሠዓቱ ይሮጣል:: ለእኔ ግን የቆመ መሰሎኛል:: ይሄ የስቃይ ማዕከልን ለቅቄ የምወጣበትን ሰዓት በናፍቆት እጠብቃለሁ:: ቁርስ በልተን ጨርሰን ከጠዋቱ 4 ሰዓት ላይ አንድ ሰው መጣ:: በሩ ላይ ስለነበርኩ «ግሩም ተ/ሀይማኖት የሚባል እስረኛ አለ? ቀይ አጭር ወንዳ ወንድ ሰውነቱ ፈርጠም ያለ?» ጠየቀኝ:: የደምሴ ጽጌ «ፍለጋ» መፅሐፍ ታወሰኝ:: ገና ሳየው ውስጤ የነበረኝ ጉጉት ፍስስ አለ:: ስድስተኛው የስሜት ህዋስ ጠቆም ያረገኝ መሰለኝ:: ሽምሰዲን ተንደርድሮ መጣ:: «እኔ ነኝ» መልሱን ከመስጠቴ በፊት እግሬን በእግሩ ረገጠኝ:: ሽምሰዲን ጠያቂ በመጣ ቁጥር ተጋፍቶ ካላናገርኩ የማለት ልምድ አለው:: ዛሬም ያው አባዜው መስሎኝ በግልምጫ ጫማ ጥፊ ቀረደድኩት::

«..አቶ እገሌ..ልኮን ነው ልናስፈታህ መተናል»

«አቶ አበበ?» አለ አፌ:: ውስጤ ግን ብዙ ናቸው ወይስ እንደ አጼ ሀ/ስላሴ ራሱን አክብሮ በብዙ ቁጥር እየጠራ ነው አልኩ::

«አዎ! መታወቂያህን ስጠኝና..» የሽምሰዲን ጉሽማና ረገጣ እንደቀጠለ ነው:: አበበ ተብዬውን ገና ሳየው የተሰማኝ ስሜት ውስጤን አድምቶታል:: «አልፈልግም በል..በል..» ይለኛል ውስጤ:: ለመውጣት ያለኝ ጉጉት ደግሞ «ጥርጣሬህን አስወግድ ተስፋህን አታጨልም» ይለኛል:: ለምን እንደሆን ባላወኩት ስሜት የኪስ ቦርሳዬን አወጣሁና የቆየ መታወቂያዬን ሰጠሁት:: በራሴ የህትመት ድርጅት ስር «ገመና» የሚል ጋዜጣ አሳትም በነበረ ጊዜ የምጠቀምበት መታወቂያ ነው:: ተቀብሎኝ ሄደ::

«ምን መሆንህ ነው ስረግጥህ አይገባህም? ለምን ሰጠኸው?» ያሳደገው ጸጉሩን ሰብስቦ ወደኋላ ያሰረው ሽምሰዲን በድፍርስ ዐይኑ አፈጠጠብኝ:: አይኑ ለምን እንደሆነ አላውቅም ሁሌም ድፍርስ ነው:: እስር ቤት ባይሆንና ባላየው ኖሮ ሲጠጣ ነው ያደረው ብዬ እከራከር ነበር:: «ለምንድን ነው የረገጥከኝ ችግር አለው?»

«ይሄ እኮ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ሰራተኛ አበበ የሚባለው ነው» ራሴን በዱላ የመመታት ያህል ሰነጠቀኝ:: አውጥተው ወደ ሀገሬ ሲመልሱኝ ታየኝ:: ተስፋዬ ሁሉ ጨለመ:: ብርሀን ያበራልኛል ያልኩት እደግ ተመንደግ ብሎ ይከተከተኛል ብዬ ተስፋዬን የጣልኩበት፣ ክፉዬን አይወድም የስኑ ጀሀዓ ሰው ነው ያልኩት ሰው መቃብሬን ቆፋሪ ሆኖ ታየኝ:: የበግ ለምድ





የለበሱ..የሚለው አባባል ታወሰኝ:: አሁን ውጣ ብባልም አልወጣም ብዬ የመጣውን ድብደባም ሆነ የከፋ ነገር ለመቀበል ተዘጋጀሁ:: አበበ የተባለው ሰው ከትንሽ ቆይታ በኋላ ተመልሶ መጣ

«UN ሄደሀል እንዴ?»

«አዎ! ምነው?»

«ሁለት ቀኑ ነው አላለኝም?»

«ሁለት ወሬ ነው ያልኩት ተሳስቶ ነው:: ከኤምባሲ ነው የመጣችሁት አይደል?» ማጣራት ፈለኩ::

«አዎ! አታስብ UNHCR ሄጄ በመታወቂያህ ፋይሉን አስወጣና አንተን እናወጣሀለን»

«አልፈልግም በጣም ባለጌ ሰው ነው አሁን መታወቂያዬን አምጣ!»

«ኖ! ያለኝን ካላረኩማ ይቆጣኛል:: ፋይሉን አስወጥቼ..»

ለሽምሰዲን «ለፖሊሱ ንገርና መታወቂያዬን ያስጠኝ» አልኩ

«ያ-አስከሪ ደሩሪ ይረጃ ቢጣቀቲ» አልኩ:: በተሰባበረ አረብኛ:: ፖሊስ መታወቂያዬን ይመልስ ማለቴ ነበር:: ሽምሰዲን ፖሊሱ እንዲህ በለው ያለኝን አብራርቶ ነገረልኝ:: ስጠው አለና አስመለሰልኝ::

«ባለጌ ነው ንገረው እንዴት እንዲህ ያስባል?» አልኩት እዛው ሆኖ ደወለለት:: ያስወጣኛል ያልኩት ወዳጅ ተብየው ወዳጄ በፊት በደወለልኝ ቁጥር ደወለ:: «ግሩምዬ በጣም ይቅርታ እኔ ሌላ አበበ ነበር የላኩት እሱ ስላልተመቸው ነው ይሄኛውን የላከው..» አላስጨረስኩትም

«እረ..!...በእውነት? ከተማው በሙሉ በአበበ ተጥለቅልቋል በለኛ?» አልኩት በለበጣ::

«እመነኝ ግሩሜ አንተን የሚጎዳ አንድም ነገር አልተደረገም::»

«ከዚህ በላይ..? አሳልፎ ከመስጠት በላይ ምን ይደረጋል? በትክክል ልትረዳኝ ከፈለክ አንተ ራስህ ና ያለበለዚያ ማንንም እንዳትልክ» ስልኩ ተዘጋ:: ምላሽም ሊሰጠኝ አልፈለገም:: በሳምንቱ ለጥየቃ የሚመጡትን ልጆች እከሌን ታውቃላችሁ ወይእያልኩ ጠየኩ:: ለአንዷ ያዘጋጀሁትን ደብዳቤ እንድትሰጠው ጠየኳት:: ተቀበለችኝ:: እሱ የሰራውን ዘርዝሬ በመጻፌ አንድ ነገር ብሆን ተጠያቂ መሆኑን ጠቅሼ ብዙ ቦታ ፋክስ አድርጌ ማሳወቄን ገልጬ ነው የጻፍኩለት:: አልሆነልኝም እንጂ እንደአቅሜ

ማስፈራራቴ ነበር:: በእርግጥም ይሄን ድርጊቱን ከኢትጋማ ጀምሮ ለሁሉም ማሳወቅ ለሚገባኝ አሳውቄያለሁ::

እስር ቤት ከገባሁ 3 ወር ከ10 ቀን ሆነኝ:: ምንም የተለወጠ ነገር የለም:: ለመጣው ለሄደው ሁሉ ደብዳቤ እየጻፈኩ ለUNHCR መላክ ተያያዝኩኝ:: ፖሊሶቹ ድጋሚ እንዲወስዱኝ ብጠይቅም የቀጠሮ ወረቀት ከሌለህ አይቻልም የሚል ሆነ መልሳቸው:: በመሀል አንድ አርብ ቀን የማላውቃቸው እስረኛ ጠያቂ ሀበሾች መጡ::

«ግሩም የሚባለው ጋዜጠኛ ልጅ..»

«እኔ ነኝ ምን ፈለጋችሁ?»

«አይ አንድ ጋዜጠኛ ልጅ ታስሯል ብለውን ነው:: በኢትዮጵያዊነትህ በኢትዮጵያዊነታችን ልንጠይቅህ ፈልገን ነው::» ደስ አለኝ ወገኔ ብሎ የሚመጣ መኖሩ ያስደስታል::

«አመሰግናለሁ» ሴቷ አብረዋት ያሉትን ሁለት ወንዶች አንተ እዛ ክፍል አንተ እዛኛው ክፍል ጋር ላሉት እስረኞች ያለውን ምግብ አከፋፍሉ የሚል ወታደራዊ ትእዛዝ መሰል መመሪያ ሰጠች:: ሲሄዱላት ሸምሰዲንን ለብቻው ማናገር ስለፈለኩ ይቅርታ ብላ ዞር እንዲል አረገችው:: እኔ እንጊት እባላለሁ በማለት ጀመረች:: «ስለአንተ ጉዳይ ምንም ነገር እንዳትነግረኝ በኋላ እኔ የተናገርኩ እንዳይመስልህ:: ታሪክህን ስሰማ ልረዳህ ስለፈለኩ ነው የመጣሁት» በማለት..ጀምራ ብዙ አወራን:: «እዚህ መኖርህን አውቆ የሚከራከርልህ ማህበር ወይም ድርጅት ካለ ወረቀት ጻፍና ፋክስ አድርግ:: እኔም ብሆን እተባበርሀለሁ::»

ፈዝገፔ በዝምታ ከማዳመጥ በቀር ምላሽ አልሰጠኋትም:: እሷንም በምን አምኜ ልላካትና ፋክስታታድርግልኝ? በምን ልመናት? አዛኝ መስላ መረጃዬን ለመውሰድ መሰለኝ:: ከዛ ሰው በላይ ማን ላይ ተስፋ ማድረግ እችላለሁ?

«ለሰጠሽኝ መረጃ አመሰግናለሁ::»

«ስልክ ያለው ሰው ካለ ቁጥር ስጠኝ እና አስፈላጊ ወይም ጠቃሚ ነገር ሲኖር እደውላለሁ::» የሸምሰዲንን ቁጥር ጻፈች:: ተለያየን:: ልጅቷ ባናገረችኝ በ20ኛው ቀን ካለሁበት እስር ቤት ተጠራሁ:: እቃህን ያዝ ተብዬ ስለነበር ልለቀቅ መሰለኝ:: ጅልኛ ማሰቤ የገባኝ መኪና ላይ ስጫን ነው:: ሙሉ በሙሉ ሽፍን በሆነ መኪና ውስጥ እኔና ትንሽ ቦርሳዬ በፌስታል ከያዝኩት ልብሴ ጋር ተጭነናል:: ወዴት እንደሚወስዱኝ አላውቅም:: ቅስመ ኢላዪ (ኢልዩ ፖሊስ ጣቢያ) የሚባል ቦታ ነው-የወሰዱኝ:: ከኢሚግሬሽን እስር ቤት የተለየ ብዙ ነገር አለው:: የሞት ቀጠና





ይመስላል:: (በነገሩ ውስጤ ስላሰበው እንጂ የሞት ቀጠና ምን አይነት እንደሆነ አላውቀውም:: ደሞስ ከዛ አስፈሪ የሀገሬን ልጆች ከጨረሰ ባህር ይከፋል?) እስር ቤት ስገባ የኪስ ቦርሳዬን፣ ቀበቶዬን ሁሉንም ነገር ተነጠኩ:: አንዱ ፖሊስ ገና ቀበቶዬን እንዳየው ‹‹ሀዳ ጀልድ ሳ ትቤዔ!›› አለኝ:: ሚግሬሽን እስር ቤትም ይሉኝ ስለነበር ትርጉሙ ገብቶኛል:: ይሄ ቆዳ ነው አይደል ትሸጠዋለህ ነበር ያለኝ:: አንድ ቁጥር ውስጥ እንድገባ ተደረገ:: ተደራራቢ 10 ጥንድ አልጋዎች አሉ:: ያለው ሰው 52 አካባቢ ይሆናል:: ግራ ተጋባሁ:: ቦርሳዬን መሬት ላይ አስቀምጬ እላዩ ላይ ልቀመጥ ስል «የሀገር ልጅ» የሚል ኮልተፍ ያለ አማርኛ ሰማሁ:: ወደእሱ ሄድኩኝ:: 14 ዓመት እስኪሞላው ናዝሬት ያደገ አህመድ የተባለ ትውልደ ሀበሻ ነው::

እሱ አልጋ ላይ ተቀምጬ ተኩል ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከላይኛው አልጋ የወረዱ ግንባሬ ላይ 4 ቅማሎች አነሳሁ:: ይሄ ግንባሬ ላይ ያገኘሁት ነው:: ውስጤ የተሰገሰጉት 400 ይሁኑ 4000 አላውቅም:: መሬት አልጋ ስር በሙሉ ሳይቀር ይተኛል:: ምግብ ማታ ማታ ኩደም የሚሉትን ዳቦ ይሰጣል:: እሷን ቀማምሼ ተባይ አላስተኛ ብሎኝ ስንቆራጠጥ አድራለሁ:: ተባዩ ሲጫወትብኝ ቆይቶ በሳምንቱ ፍርድ ቤት ቀረብኩ:: ከፍርድ ቤት መልስ ወደ ሌላ እስር ቤት ተወሰድኩ:: ይሄኛው ሁለት በሁለት የሆነች ክፍል ነች:: ግራውንድ በመሆኑ መስኮት የለውም:: መብራት -24 ሰዓት ይበራል:: አንድ ጆርዳናዊ አንድ ፍልስጤማዊ ሁለት ሳዑዲ አረብያዊ..እኔ አምስተኛ ነኝ:: ጽድት ያለ ቦታ ቢሆንም መቃብር ውስጥ የመቆየት ያህል ይጨንቃል::

«ላልምክ ዓረቢ?» ሲያናግሩኝ የማልሰማ መሆኑን ሲያውቁ የሳውዲው ተወላጅ አረቢኛ ላስተምርህ ማለቱ ነው:: «ኦኬ!» ነበር መልሴ:: አሊፍ፣ ባእ፣ ታእ..እያለ አረብኛ ፊደሎችን ጽፎ አነበባቸው:: በእንግሊዘኛ ዓፈልኝ:: የፍርድ ቤት ቀጠሮ እስኪደርስ ድረስ እሱን ማጥናት ጀመርኩ:: በሶስተኛው ቀን ፍርድ ቤት ተወሰድኩ:: እኔ አረብኛ አልሞክርምና አስተርጓሚ እንዲዘጋጅ ለሳምንት ተቀጠርኩ:: እዛው ጨለማ ክፍል ተመለስኩ::

እነዚህ 4 አረቦች ሁኔታቸው አልተመቸኝም:: መጠጥ ክልክል ነው ስለዚህ «በልተም» የሚባል የስካር ኪኒን ይውጡና በላዩ ላይ ሻይ ደጋግመው ይጠጣሉ:: ይሰክራሉ:: በዚህ ጊዜ በስካር የሚያሰራቸውን አያውቁም:: የሀገሬ ሰካራም መለኪያ ጨብጦ ጠርሙስ አንገጭግጮ..ስንቴ ሽንት ቤት ተመላልሶ ገንዘቡን በገፍ ቆጭ አርጎ የሚያገኘውን ስካር እነሱ ሳይወጡ ሳይወርዱ በኪኒኑ እጥፍ ያገኙታል:: ጆርዳናዊው ዶክተር ኪኒኑን ውጦ ስክረና ሰውነቱን በሙሉ በምላጭ ቀዳደ ባለው:: ራሱን ሆዱን ሲደበድብ ከቆየ በኋላ በሩን መደብደብ ዕቃ መሰባበር ጀመረ:: ከዛም ወንድ

ለወንድ..ሲገናኝ መታገል..ብዙ አስቀያሚ ነገር ፈጽሞ እንቅልፍ ሲወስደው እንኳን እኔ አይወስደኝም። ያውም ጀርባዬን ወደ ግርግዳ አዙሬ ጥግ ነው የምተኛው። ሲቃለዱኝ ሲፈልጉ መቃለድ አልፈልግም።

በዚህ አይነት ሰቀቀን ሳምንቱን ቆይቼ ፍርድ ቤት ለመሄድ ተጠራሁና ወጣሁ። ልክ የተፈጥሮ ብርሃን ባየሁ በሳምንቴ ነው የወጣሁት። ጨለማ ውስጥ ስለቆየሁ አይኔ ፍጹም ማየት አልቻለም። አጭበረበረኝ። ብርሀኑ ዐይኔን ሊያስገልጠኝ አልቻለም። አንደኛው እጄ በካቴና ከአንደኛው ሣውዲያዊ ጋር ታስሯል። በሌላኛው እጄ ጸሀይዋን መከላከል ሞከርኩና እንደ ምንም መኪና ላይ ወጣሁ። ፍርድ ቤት አንድ ጎንደር ተወልዳ ያደገች ትውልደ ሀበሻ በእድሜ ጠና ያለች አስተርጓሚ ቀረበች። ያረገቻትን እርጅና የምትጋፋ የወጣት ቀጭን ፋሽን መነጽር አስሬ ከፍ እያረገች ታያለች። ዳኛው የሚላትን ለእኔ እኔ የምላትን ለዳኛው ታስተረጉማለች። በመሀል የምትፈጥራቸው ቃላት እኔን የሚወጋ ጦሮች ያዘሉ ነበሩ። አንድ ከሌላ እስር ቤት የመጣ አሊ ፌቶ የተባለ እስረኛ «ላ..» ብሎ ተነሳ። ሁላችንም ተደናገጥን። አይደለም ማለቱ ነበር።

«አይሆንም ብለሃል ለምንድን ነው?» አለው ዳኛው። ልጁ ተጠርቶ እኔ ጋር ከቆመ በኋላ እሱ ያለውን ተቃራኒ ነው የምትናገረው አንድ ሁለቴ ተሳስታ መስሎኝ ነበር።

«አውቄ አይደለም አማርኛ በደንብ ስለማላውቅ ነው» አለችኝ። ጥሩ የጎንደር ቃና ባለው አነጋገር ምንም ሣትኮላተፍ ከነዘዬው ሳትሰባብር እያወራች አልችልም ማለቷ ገረመኝ። ካልቻለች አማርኛ ሰፍት ዌር ተገጥሞላት ነው አሁን ያወራችኝ? የሚል ሀሳብ አፈለቀ ሞገደኛው ማሰብያዬ። ጥያቄና መልሱ በእስረኛው አስተርጓሚዬ እንደገና ተጀመረ። ለተጠየኩት በሙሉ ቃል በቃል መልስ ሰጠሁ። ያለህን ማስረጃ ለሳምንት አቅርብ ተብዬ ቀጠሮ ተሰጠኝ። አስተርጓሚዬ አሊ ፌቶም ከእኔ ጋር በተመሳሳይ የቀጠሮ ቀን እንዲቀርብ ተወስነና የሌሎች ተራ እስኪደርስ ተቀመጥኩኝ።

የፍ/ቤት ስነ-ስርዓት እኛ ሀገር ካለው ፈጽሞ የተለየ ነው። ዳኛው ቀሚስ /ቶብ/ ለብሶ በላዩ ላይ ኮት ደርቧል። ኢማማውን ትከሻው ላይ ጣል አድርጓል። ይሄ የባህል አለባበሳቸው ነው። የአፋር ጎሳ የሚታጠቁትን አይነት ጀሌ በእነሱ ቁመቱ አጥሮ ጃንቢያ ይባላል። በግምት 15 ሣንቲ ሜትር ስፋት ባለው በጥልፍ ከተንቆጠቆጠ ቀበቶ ጋር ታጥቋል። በጎን በኩል ሽጉጥ ይዟል። እስረኛ የሚያጅቡ ፖሊሶችም ከነክላሻቸው ገብተው ከሰው መሀል ይቆማሉ።

በችሎት መሀል ዳኛውን ወረቀት እያመጡ ጸሀፊዎች..ፖሊሶች ባለ ጉዳዮች ያስፈርሙታል። ሀገሬ ከማውቀው ተለየብኝ። ለነገሩ ሸማ በየፈርጁ ይለበሳል። እነሱም እንደራሳቸው እንጂ እንደኛ መኖር የለባቸውም። ወደ





ጭለማ ክፍሌ ተመልሼ ተጨማሪ 1 ሳምንት ቆየሁ። ማስረጃዬን ይዤ በቀጠሮው ቀን ለመሄድ መኪና የለም ተብሎ ቀረን። ለፍ/ቤቱ ተደውሎ ለሳምንት እንዲተላለፍ ተጠየቀ። ተጨማሪ ቀናት ጨለማ ክፍል ውስጥ ቀጠልኩ። ሲመሽ ሲነጋ በማላውቅበት የተፈጥሮ ብርሃን የማይታይበት ቦታ መቆየትን የመሰለ ምን አስጠሊታ ነገር አለ?

ሣምንቱ በምጥ ደረሰና መረጃዎቼን ይዤ ሄድኩ። የተለያዩ መታወቂያዎች፣ ጋዜጦች ይዣለሁ። አቅርብ ተብዬ ለዳኛው ሰጠሁ። ዳኛው አንዱን መታወቂያ አንስቶ እያየ «ይሄ ፎቶህ ነው?» ተባልኩ።

«አዎ!» ነበር መልሴ።

«ፎርጅድ ትሰራለህ?»

«እንዴ ምን አገናኘው?»

«ይሄ ሁሉ መታወቂያ?..»

«የተለያየ ቦታ የሰራሁበት እና የጋዜጠኛ ማህበሩ..» እንግሊዘኛ ማንበብ የሚችል ተጠርቶ አነበበ። ከዚህ በኋላ የጠነከረው መጣ።

«ወንጀለኛ ነህ የሚለውንእሺ ጋዜጠኛ ነህ ብለን ተቀበልንህ ግን አሁን በሌላ ወንጀል ስለምንከስህ ወንጀለኛ ነህ» አለ ዳኛው።

«በምን ሁኔታ?»

«ድንበር ጥሰህ በመግባትህ ወንጀለኛ ነህ»

«አይደለሁም።

«እንዴት?»

«በ1949 ስምምነት የመን ፈርማለች። UNHCR በእዚህ ሀገር ስደተኛ ያስተናግዳል UN ደግሞ ድንበር ጥሶ የሚገባ ስደተኛ ነው የሚያስተናግደው..» አላስጨረሰኝም። «UNHCR ሆነ አሜሪካን በእኛ ሀገር ምን አገባቸው? አዛዦች አይደሉም።» አስተርጓሚዬ የመን ውስጥ ብዙ ስለቆየ ያውቃቸዋል። «ግሩሜ እያመረሩብህ ነው። እነሱ የUN ስምና የአሜሪካ ስም ሲጠራ አይወዱም» አለኝ።

«የምልህን ምንም ሳትፈራ ሳትለውጥ ጠይቅልኝ።»

«እሺ..ግን እንዳትፈራ አይዞህ..»

«ባክህ ሞቼና ፈርቼ አላውቅም፡፡ ንገርልኝ ብቻ..» ላሸንፍ የምችለው በትክክኛው የእምነት ሎጂክ ብቻ መሆኑን ተረዳሁ፡፡ እነሱ ፈሪሃ እግዚአብሄር አላቸው፡፡

«ይሄ መሬት የማነው?»

«የየመን»

«ከየመን በላይ የማነው?»

«የአላህ» እኔ መጠየቄን ዳኛው መመለሱን ተያይዘናል፡፡

«አንተ የማነህ?»

«የአላህ!»

«እኔ የማነኝ?»

«የአላህ»

«በአላህ መሬት ላይ አንተ የአላህ እኔ የአላህ እሱ ከፈቀደ ብንኖር ምን አለበት?» እውነተኛ ስሜቱን ነበር እግዚአብሄር ከፈቀደ የሚለው..

«ሳሕ-ከላምክ» (ትክክል ተናገርክ) አለና በዋስ ወጥቼ UN እንድሄድ ከተቀበሉኝ ዋስትናው እንዲወርድ ካልተቀበሉኝ ወደ ሀገሬ እንድመለስ ተፈረደልኝ፡፡ ከኢሚግሬሽን (በእነሱ አጠራር ጀዋዛት) እስር ቤት ከተቀየርኩ በወር ከ3 ቀኔ መልሰው እዛው ተወሰድኩ፡፡ በጣም ደስ አለኝ፡፡ መጀመሪያማ የገባሁበት ኡላዬ የሚባለው ጣቢያ ተባይ ማድለቢያ ነው፡፡ እሱ በትክክል እስር ቤት ብቻ ሳይሆን ትልቅ የቅጣት ማዕከል ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ብርሃን የሚናፍቅበት ጨለማ ቦታ ነፍስና ስጋ የሚሟገቱበት ነው፡፡ አሁን ከእነዚህ ሁሉ የስቃይ ማዕከላት ጨርሼ ልወጣ ነው፡፡ በፊት ወደ ነበርኩበት እስር ቤት ተመለስኩ፡፡ ስመለስ ግን ከሽምስዲን ጋር እንድንገኛኝ አልተደረገም፡፡

ሁለተኛውና ጠበብ ያለችው ክፍል ውስጥ እንድንገባ ተደረገ፡፡ ሀበሻ ማየት ናፍቆኝ ነበር፡፡ የጨንራዬ ነገር ፋታ ነስቶኝ ምግብ አላስበላ ብሎኝ ስለከረመ አጥንቴ ገጦ ስጋ ቅብ መስያለሁ፡፡ የመክሳቴ ሁኔታ እንኳን ለሚያየኝ ለእኔም አስጠልቶኛል፡፡ ያለ ማጋነን ከ63 ኪሎ በግምት 50ና 51 ገብቻለሁ፡፡ በዛ ላይ ውሃ ስለሌለ በወር ውስጥ ተራ ደርሶኝ ገላዬን 3 ቀን ብቻ ነው የታጠብኩት፡፡ እሱም አጥቁሮኛል፡፡ ሳሙና ሰጡኝና ታጥቤ ለወር የናፈቀኝን የተፈጥሮ ብርሃን ማየት እግሬ እስኪዝል በሩ ጋር ቆምኩኝ፡፡ ሁለት ሀበሾች መኖሪያ ፍቃድ ለማሳደስ ሲገቡ አየኋቸው፡፡

«ሄይ!..ስሚ እቱ!» ደጋግሜ ተጣራሁና መጡ፡፡

«አቤት! እኛን ነው?»





«ኧረ ጥሩ አይደለም እስረኛ እዚህ መኖራችንን እያወቃችሁ ሠላም አትሉንም?»

«ውይ ይቅርታ ቸኩለን ነው፡፡»

«ምንስ ቢቸኩል የከፋን መሆናችንን ታውቃላችሁ አይዟችሁ፣ እግዚአብሄር ከእስር ያውጣችሁ የሚሉ እህቶች ያስፈልጉናል፡፡» ሁለቱም በዝምታ ተሸበቡ፡፡ «መፈጠርን የሚያስጠላ እስር ቤት ከርሜ ነው የወጣሁት፡፡ የሀገሬ ሰው እዚህ ለጥየቃ የሚመጡ እህቶች ድምጽ ናፍቆኝ ነው የከረምኩት፡፡ ለዚህ ነው የጠራኋችሁ፡፡»

ያቺ የምጠላት የከንፈር መጠጣን ቸሩኝ፡፡ ከረጅም ዝምታ በኋላ..«አሁን ምን እናድርግልህ?»

«ዳር ዳር ያልኩት ፈርቼ ነበር፡፡ ከቻልሽ የጨንራ መድሃኒት ግገርልኝ፡፡ ሰሞኑን መብላት አቅቶኝ ተጎድቼ አይታያችሁም?» አንደኛዋ ብዙዬ ትባላለች ኦሮሞ ነች፡፡ እንባዋ ዱብ ዱብ አለ፡፡ ንግስቲ ደግሞ ኤርትራዊት ስትሆን ቀይ መጠጥ ያለች ረጅም ናት፡፡ ማልቀስ ሳይሆን መርዳት የፈለገች መሆኗ ያስታውቃል፡፡ መጣሁ ብላ ወጣች፡፡ ብዙዬ እንባዋን እየጠረገች ተከተለቻት፡፡ ንግስቲ ገነት ከምትባል እህቷ ጋር (ሃዳ የሚባል ቦታ የሴቶች የውበት ሳሎን አላቸው) ትንሽ ቆይተው ሲመጡ በሁለት ላስቲክ የሞሉት በካርቶን በካርቶን የታሸገ ጭማቂ፣ ብስኩት፣ ወተት ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም የሚደርስ ይመስላል፡፡ ባለ 1 ሊትር ወተት 4፣ ጭማቂ 7፣ ብስኩት 16፣ የቆርቆሮ ለስላሳ መጠጥ 8 ገዝተውልኝ መጡ፡፡ ሊብራክስ፣ ዜንታክ እና አንቲ አሲድ መድኃኒቶች አመጡልኝ፡፡ «አይዞህ አሁን ታገግማለህ ሃሙስ ወይም ዓርብ እንመጣለን» ብለው ተሰናብተውኝ ሄዱ፡፡ ሁሉም እጅ እጄን ሲያዩኝ ፈራሁና አከፋፈልኩ እንጂ ወሩን ሙሉ በበሽታ እንደ መማቀቄ እና በምግብ እንደ መጎዳቴ ሳስቼለት ነበር፡፡

ቅዳሜ 10 ሰዓት አካባቢ በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ በዘፈኖቹ የሚታወቀው ኖሁ ጎበና ተይዞ እስር ቤት መጣ፡፡ ደግነቱ ወደ ኢትዮጵያ የሚሳፈሩት ጠዋት ላይ ተሳፍረው የቀረነው 13 ስለ ነበርን መኝታ በሚገኝበት ሰዓት መጣ፡፡ የአነግ ቀንደኛ አባልም ቀስቃሽም እንደሆነና ካናዳ እንደሚኖር ነበር የሰማሁት፡፡ የመን እንዴት መጥቶ እስር ቤት እንደ ተገናኘን በጣም ገርሞኛል፡፡

ሁሉንም በጥሞና ካየ በኋላ እኔ ያነጠፍኩት ፍራሽ ላይ ቁጭ አለ፡፡ በውስጤ «ለማውራት ተመቸኝ» አልኩ፡፡

«እስር ቤት ሳልገባ ጋዜጠኛ ልጅ እንደታሰረ ሰምቼ ነበር የት ክፍል ነው?» ራሱ አመጣው ጨዋታውን፡፡

«እዚህ ክፍል ውስጥ ነው።»

«ከነዚህ ሶስቱ አንዱ ትልቁ ሰውዬ?» ሽምግል ያለውን መረጠ።

«እ..እ..ልክ አይደለህም እነሱ ኤርትራውያን ናቸው»

«ይሄ መላጣው መሆን አለበት»

«እንዴት እሱን ገመትክ? ሌላው..» አልኩና ተውኩት «ልክ አይደለህም?»

«አንተ ነህ?» አለ ፈራ ተባ እያለ

«አዎ!»

«አትመስልም?» በጣም ተናደድኩ። ሀገሬ እያለሁም አንዳንድ ሠዎች የነበራቸው የተዛባ አመለካከት ያናድደኛል። ወጣት ጋዜጠኛ አይሆንም የተባለ ይመስላል። ቦርጭ ያንዘረጠጠ፣ ጺሙን ያሳደገ፣ ካፖርት የደረበ፣ ሣምሶናይት ያንጠለጠለ፣ ሽበት የደቀለ.. አይነት ነው የሚጠብቁት። በአንድ ወቅት የተቃዋሚ ፓርቲ ሊቀመንበር ቃለ-ምልልስ እንድናደርግ በስልክ ጠየኳቸው። ተስማሙ። ባልነውና በተቀጣጠርንበት ቦታ ስንገናኝ እኔ መሆኔን ለመቀበል አዳግቷቸው ነበር። መታወቂያዬን ካዩ በኋላ ነው ያመኑት። ብዙ ጊዜም ለሌሎች ወጣት የሞያ አጋሮቼም ይገጥማቸዋል። በዚህ ምክንያት በአንድ ወቅት የገለማ አስተሳሰባችንን እንቀይረው በሚል ጠንከር ያለ ሂስ አስፍሬም ነበር። የኖሁ ኀበናም ከዚህ የዘለለ ሃሳብ አልነበረም። «እንዴት አትመስልም አልከኝ?» አልኩት ምክንያቱን ለማወቅ።

«ጋዜጠኛ ብትሆን እዚህ እንዴት ትመጣለህ? በዛ ላይ በእድሜም ትንሽ ነህ?» አዘንኩበት ይሁን አዘንኩለት አላስታውስም። መልስ ለለጠው ግን ፍቃደኛ አልሆንኩም። አላስተዋለም እንጂ እሱስ ታዋቂ ዘፋኝ ሆኖ የመን እንደኔው እስር ቤት ገብቶ አይደል የተገናኘነው? ለጥቂት ደቂቃ በዝምታ ቆየን። ሲጋራውን እየማገ ከሐረር ኦሮሞች ጋር በኦሮምኛ ያወራል። ድምጹ የሆነ ለየት ያለ ነገር እንዳለው ያስታውቃል። በተለይ ኦሮምኛ ሲያወራ ይስባል - ጆሮ ገብ ነው።

«ከሀገር ከወጣህ ስንት ጊዜ ሆነህ?» በሚል ጥያቄ አቋረጥኩት።

አየኝ። አስተያየቱ ነገር አለበት።

«ማነው ስምህ?»

«ግሩም» የጠየኩትን ጥሎ ሌላ ጥያቄ መጠየቁ ምን አስቦ ነው? አስባለኝ «ግሩም..ግሩም አሁን በኢትዮጵያ አቆጣጠር ስንት ነው?» ሁለው ሁላ አልገባህ አለኝ። ምን አስቦ ምን ሊለኝ ፈልጎ ነው?

«1998ዓ.ም» ማለላት የጀመረ መሰለኝ። በረጅሙ ተነፈሰ።

«34 ዓመት ሆኖኛል ማለት ነው? ላውዱ አረቢያ፣ ጀርመን፣ ካናዳ





ኖሬያለሁ» ከመወለዴ 1 አመት ቀድሞ መሆኑ ገረመኝ። ህይወቱን ለዘፈን የሰጠ መሆኑን የሚነበብበት መንፈስ ያሳብቃል። ለኦሮሞ ህዝብ ያለውን የለጠ መሆኑን የሚነበብበት መንፈስ ያሳብቃል። ለኦሮሞ ህዝብ ያለውን ፍቅር አውርቶ አይጠግብም። እስር ቤት ውስጥ የአርሲ፣ የጅማ፣ የሐረር.. እያለ የሚጣሉትን የኦሮሞ ልጆች ሠብስቦ ያስተምራል። «እኛ አንድ ሳንሆን የምንታገለው እንዴት ነው? እንዴት እንጣላ? መጀመሪያ አንድ እንሁን..» ይላቸዋል። (በዚህ ሁኔታ ዛሬ የቀጠለ አይመስለኝም። ምክንያቱም ሀገር መግባቱን ሰምቻለሁ።) እየመጡ የሚጠይቁትን ሁሉ ያምናቸዋል። መጠራጠር እንዳለበት ብነግረውም አላልፈው አይሰጡኝም የሚል ፅኑ ዕምነት አለው። «..መድረክ ላይ ዘፍኖ የመቀስቀስ ፖለቲካ እና ከመድረክ ውጭ ያለውን ፖለቲካ ልዩነት አልተረዳህም። የእኛ ሀገር ፖለቲካ ዋሽቶ ማሳመንና ጥሎ ማለፍ ነው..» ብለውም አልተቀበለኝም።

እንዲያውም በተቃራኒው እኔን የተጠራጠረኝ መሰለኝ። ለምን ወደ የመን እንደመጣ ስጠይቀው በተደጋጋሚ አድበስብሶ አለፈኝ። ማስታወሻ ደብተሬ ላይ በጻፍኩት መሰረት ከሆነ ጥቅምት 4 ቀን 1998 ዓ.ም ነው እስር ቤት የገባው። ከ21 ቀን በኋላ ከኢትዮጵያ ኤምባሲ ወታደራዊ አታሼ ኮሎኔል መሀመድ የተጻፈ ደብዳቤ እንዱ ይዞለት መጣ። ኮሎኔሉ የአፋር ተወላጅ ሲሆን በባድመ ጦርነት ተካፍሎ የማዕረግ እድገት ማግኘቱን የሰማሁት እስር ቤት እያለሁ ነው። አዛኝና ጥሩ ሰው እንደሆነ ከእስር ስወጣ ነው የሰማሁት። በእርግጥም በአሰራር በኩል ብዙ የማይስማማበት ነገር በመኖሩ ከድቶ በአሁኑ ሰዓት አውሮፓ ከትሟል። ያመጡለትን ደብዳቤ ተቀብሎ ሲገ ደረደር ወደእኔ መጣ። «እየሀ ጉድ!! አንብበው» አለና ሰጠኝ። አነበብኩት።

«ድገምልኝ» አለኝ። ደገምኩለት። እጅ ጽሁፉ አስቸጋሪ ስለነበር ለለስኩት። እናቱ መሰረተ-ትምህርት ስትማር ወንከርከር አድርጋ የምትፅፈውን ይመስላል። ያ-ወታደራዊ አታሼ ከኤምባሲ ስራው ከድቶ አሁን ያለው እንግሊዝ ሀገር ነው ስለሁኔታው ቢናገር ደስ ይለኝ ነበር። በጽሁፉ ምክንያት እናቴ መሰረተ ትምህርት ስትማር የነበረው ታወሰኝ። በቁይ ስልካካ ፊቷ ላይ ርዝመቷ ታክሎ እጇን ይዛኝ መሰረተ ትምህርት ለመማር የምትሄደውን አስታወሰኝ። እንባዬ ተንቆረዘዘ፣ ናፍቆቴ ተቀሰቀሰ።

«ምነው?» የድምጻዊ ኖሁ ኀበና ጥያቄ ከሀሳብ መለሰኝ።

«ምንም የሆነ ነገር ታውሶኝ ነው።»

«..እና ምን ልመልሰቸው?» አጠያየቁ ገረመኝ። እሺ በላቸው ብለው ምን ሊወስን ነው? ወይስ ሊታዘበኝ ነው የጠየቀኝ? ታገልኩለት ያለው አላማስ?

«አንተስ ምን ልትላቸው አሰብክ?» ጥያቄውን በጥያቄ መልሼ

አቋሙን ማወቅ ፈለኩ።

«ግራ ገብቶኝ እኮ ነው። ለአንተና ለሚስትህ ፓስፖርት እንሰጣችኋለን። እዛ እስካለህ ማረፊያና የምትንቀሳቀስበት መኪና ይዘጋጅልሀል ..ቦታ ይሰጥሀል እኮ ነው የሚሉኝ።» ሀሳቡ እንደተወላወለበት ገባኝ።

«...እና አንጓህ? ፓስፖርቱ እኮ በዜግነትህ የምታገኘው ነው። ሚስትህም ቢሆን ትውልደ ኢትዮጵያ ስለሆነች መብቷ ነው። እዛ እስካለህ ለሚሰጡህ መንቀሳቀሻ መኪና ስትል መግባት ፈለክ? የሚሰጡህ መሬቱን ከሰማይ መና አውርደውት አይደለም። የሚሰጥህም መሬት አንጉቶህ ከሆነ ታገልኩለት ከምትለው ገበሬ እርሻ ተነጥቆ ነው የሚሰጥህ ያ-ያስደስትሃል? ምኑ ነው የወሰወሰህ?» ሰላሳ አመት መታገሉን ነግሮኛል። ያን ትግሉን በብጫቂ መሬት ሊለውጥ መገዳደሩ ውስጤ ንዴት ፈጥሮብኛል። በእልህ ነው የተናገርኩት።

ከዛ ግን አንድ ቀን በድንገት ትላልቅ አንቴና ያለው ሬድዮ የጨበጡ ሰዎች መጡና ኖሁ ተነስ..ተነስ ብለው ይዘውት ወጡ። በዚህን ጊዜ እቃውን እያዘገጃጀ ምስጢር ያላቸውን ወረቀቶች ጠዋት ሚስቱ ስትመጣ እንድሰጥለት ነገረኝ። ከወረቀቱ ላይ በጻፈው አቡዳቢ ላለው ካናዳ ኤምባሲ እንድታሳውቅለት እንድነግራት ነገረኝ። በዚህን ሰዓት የተሰማኝ ፍርሃት ዛሬ ሳስታውሰው ይሰቀጥጠኛል። ኮሎኔል መሀመድ የጻፈውን ደብዳቤም በራሴ ማስታወሻ ላይ ገልብጬ ያስቀረሁት በዚህ ወቅት ነው። የት እንዳደረሱት የማላውቀውን ያህል ከጊዜ በኋላ ኖሁ ጎበናን ሀገር ገባ ሲባል ሰማሁ።

ወደ እስር ቆይታዬ ልመለስ። በየጊዜው ተመላልሰው እየመጡ የሚያዙ ልጆች ገጥመውኛል። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ሙራድ ከድር ከአርሲ አቦምሳ የመጣ ነው።

የረጅም ጊዜ ጉስቁልና የተጫወተበት መሆኑን ፊቱ ያሳብቃል። ግንባሩ መሀል ላይ ሰፋ ያለ ጎድጓዳ ነገር አለ። ጠባሳ ብቻ አይደለም። የግንባሩ አጥንት ተሰብሮም ይመስላል። መጀመሪያ ያየሁት ጊዜ ተፈንክቶ ቢመስለኝም ቁስለት ስለሌለው የቆየ ለመሆኑ ማረጋገጫ ሆነኝ። እስር ቤት ከገባሁ በግምት ከሀያ ሁለት ቀን በኋላ መሰለኝ ያየሁት። ወደ ሀገር ሊመለሱ ካሉበት ክፍል ጸሀይ መሞቂያ ወደ ሆነው የወጡት። እኔ ወደ አለሁበትና ጣራ ወደሌለው ጊቢ ነገር እያመጡ አጎሯቸው። ምን አጎሯቸው እላለሁ አጎሩን እኔስ እዛው አይደለሁ እንዴ?

ሁሉንም ቀርቤ ለማናገር አልቻልኩም። ግን ማውራት የምችለውን ያህል አውርቻቸዋለሁ። እንዲያውም አንደኛውን ልጅ ለኢንጋማ ፕሬዚዳንት





ክፍሌ ሙላት የጻፍኩትን ደብዳቤ ለቤተሰቦቼ ከጻፍኩት ውስጥ ከትቼ የቤታችንን ስልክ ቁጥር ሰጥቼ ላኩት። አቤል ይባላል። የድሬደዋ ልጅ ነው። በባህር ሲመጣ ሁለተኛው ነው። አጠር አድርጎ እንደነገረኝ ከሆነ ሶማሊያ በርበራ ወደብ ላይ ለሰባት ወር ሰርቷል። በሽክም ስራ ያጠራቀማትን ገንዘብ በሌባ ተዘረፈ። ያውም የቀን ለቀን ዘራፊ በጠራራ ጸሀይ መንገድ ላይ አስቁመው ዘረፉት። እሱ ይወዱኛል፣ ተላመድኳቸው፣ አይነኩኝም ባላቸው የሸክም ጓደኞቹ ነው ጥቃት የተፈጸመበት። «እነዚህ ሰዎች ምን አብረዋቸው ቢኖሩ አመላቸው የሚታወቅ አይደለም ብዬ ያላሰብኩትን መንገድ ወደ የመን መጣሁ። ስመጣ ግን ገንዘብ ስላልነበረኝ ቦሳሶም ወደብ ላይ በጋሪ እቃ ማመላለስ ለሰባት ወር ሰራሁ። ሳዑዲ የሚያደርሰኝ ገንዘብ ሳገኝ ተነቃነኩ።

አጠቅ የሚባል ቦታ ዘራፊዎች አስረው ያለንን ዘርፈው ለፖሊስ ሰጡን። ተጠረዝን። ዞሬ ስቃይ መከራዬን በልቼ በየቦታው ሳንቲም ለማግኘት የማይሰራ ስራ ሁሉ ሰርቼ መጣሁ። ማሪብ የሚባል ቦታ ላይ እርሻ ላይ ተቀጥሬ ሰራሁ። እዛ አካባቢ ለገበሬዎች በቀን ስራ የምንቀጠር ኢትዮጵያዊያን ከሁለት መቶ እንበልጣለን። ስራ ማግኘት አስቸገረ። እኔ ደግሞ ቶሎ ቶሎ ሰርቼ ወደ ሳዑዲያ መሄድ እፈልጋለሁ። በቅናሽ ለማሰራት ለሚፈልጉት ሁሉ ቶሎ ቶሎ ጉልበቴን ሸጬ መሄድ ፈለኩ። በዚህን ጊዜ ሌሎች ወገኖቼ፣ የሀገሬ ልጆች በግሩፕ ደበደቡኝ። ለሁለት ወር አልጋ ይዤ ተኛሁ። በጩቤ የወጉኝ ይኸውልህ።»

ገልጦ አሳየኝ። እርስ በእርስ መባላታችን ስደትም አብሮን መውጣቱ አሳዘነኝ። ሆስፒታል ሆኖ ፖሊሶች በቁጥጥር ስር አዋሉት። ይሄው ዳግም ሀገር ሊገባ ነው። ብዙዎቹ ተመሳሳይ የስቃይ ሰለባ ሆነው ያገኘኋቸው ነበሩ። የሚገርመው ግን ደግመው ደጋግመው ሲመጡ ማየቴ ነው። ሙራድን በዛ ሰዓት ባላናግረውም በወር ከ20 ቀኑ ተመልሶ እስር ቤት ገባ። እኔ መቼም የፈለገ ጠላቴ ቢሆን በዛ መንገድ እንዲመጣ አልመክርም። እኔ ያየሁትን ሁሉም ይየው አልልም። እንዴት ህይወቱን ቢጠላት ነው መልሶ የመጣው አልኩና ትንሽ እረፍት ካደረገ በኋላ ጠየኩት። አመላለሱ ግን አስደነገጠኝ።

‹‹ይሄ ነው የገረመህ? ከዚህ በኋላም ደግሜ እመጣለሁ። ብያዝም እንደገና እመጣለሁ›› አለኝ። ደነገጥኩ ለምን ብዬ ልጠይቀው አልቻልኩም። ምንም ጥሩ ነገር እንደማልሰማ ምሬት ካዘለ ንግግሩ ተረድቻለሁ።

እስር ቤት በገባሁ ሶስቱኛው ወር ወደ ሀገር ሲመለሱ ለቤተሰቤ የሚሰጥ መልዕክት የላኩት ልጅ (አቤል) ዳግም ታስሮ መጣ። ገና ሲያየኝ

‹‹ለወንድምህ ነው ደብዳቤውን የሰጠሁልህ...›› አለኝ:: እኔም ብዙ ጥያቄ አላቀረብኩለትም:: ከሁሉም ተደጋጋሚ አንድ አይነት ነገር ነው የምሰማው:: እኔ እዛው እስር ቤት እያለሁ ሙራድ ለሶስተኛ ጊዜ ተይዞ መጥቶ ተገናኘን:: ገና እንዳየኝ ‹‹አንተ በቃ እዚሁ እየጠበከን ነው? አትወጣም እንዴ?›› አለኝ::

‹‹እናንተ ስንት ዙር እንደምትመላለሱ ጠብቀህ ቁጠር ተብያለሁ›› አልኩና ቀለድኩ:: አስከትዬም ‹‹አንተ ለምንድን ነው ተመላልሰህ የምትመጣው? በቃ! አልቀናህም ለምን አትተወውም?» ..ሳቅ አለና በግርምት አየኝ:: ‹‹ሰባቴ በዚህ መንገድ መጥቻለሁ 10 ጊዜ እስኪሞላኝ እመጣለሁ:: ቢፈልግ ባህር ላይ ልቅር 1 ቀን እስኪሞላልኝ መመላለሴን አልተውም:: ምን ቀረኝ እና እዛ ልቅር?»

«እንዴት ቤተሰብ የለህም እንዴ ምን ቀረኝ ማለት እንዴት ነው? በሰው ሀገር እየታሰሩ መንከራተት ምን ይጠቅማል?»

‹‹ቤተሰብስ ነበረ:: ግን ምን ያደርጋል ይሆናል ብዬ በሰው ወሬ ተታልዬ ብር ሰርቄያቸው ነው የጠፋሁት:: ሳውዲያ..ሳውዲ አረቢያ ሲሉ ብር እንደልብ የሚገኝበት አድርገው ሲስሉት እውነት መሰለኝ:: ከአቦምሳ ቦሌ የምትባለው ቦታ እየሄድክ ሽንኩርት ለቀማ ከምትሰራ እዛ ከብት ጥበቃ የሚያበላ ስራ ነው ብለውኝ ነበር:: እሱም አልሳካ ብሎ ይሄው ያዞረኛል:: እዛው ብቀር የጎዳና ህይወት ለመግፋት ካልሆነ እንዴት ደፍሬ አይናቸውን አያለሁ? የሚሳካልኝ ቢሆን አንድ ቀን ያጎደልኩባቸውን፣ የሰረኩትን ብር አሟልቼ እገባለሁ:: ይቅርታ እላቸዋለሁ ብዬ ነው የምንከራተተው:: ግን ምን ያደርጋል አልሞላልኝም::›› አሳዘነኝ:: ውስጤን ቁጭት ነገር ሸነቆጠኝ:: ከስደት ተመላሹ እየሰራ ያለው ጥፋት በቀላሉ የሚገመት አይደለም:: በእስር ቤት ቆይታዬ ብዙ በጣም ብዙ አስቃቂ ነገሮችን ለማየት ችያለሁ:: ይሄ ሁሉ ግን የተሳሳተ መረጃ የመያዝ እና ችግር የወለደው ነገር ነው::

የራሴም ጉዳይ ፍርድ ቤት በዋስ ወጥቶ UNHCR ከተቀበለው ተቀበለው ካልተቀበለው ግን ወደ ሀገሩ ይመለስ ስላለኝ የዋስ ነገር ውስጤን ይንጠዋል:: ያገኘሁትን ሰው ሁሉ ዋስ የሚሆን ሰው እንዲፈልጉልኝ እለምናለሁ:: አንድ አርብ ቀን ያ ጆሲ (አሕመድ ካሊል) የሚባለው እግር ኳስ ተጫዋች መጣ:: ከአራት ሴቶች ጋር ሆኖ ነው ሊጠይቁኝ የመጡት:: ከሁሉም በእድሜ ጠና ያለችው የሺ ትባላለች:: ገነት/አሁን ዱባይ ነች/፣ ሰላማዊት ጌታቸው (የኮ/ል ጌታቸው ልጅ ናት) አበባ እሸቱ ናቸው ሴቶቹ:: ‹‹አንድ የታሰረ ጋዜጠኛ ልጅ አለ ልጠይቀው እስር ቤት ልሄድ ነው ስላቸው ኧረ! እኛም እንጠይቀው ያፀድቀናል ብለው ነው የመጡት...›› አለ ጆሲ!! ቡና እንደምወድ ማን እንደ ነገራቸው እንጃ በፔርሙዝ ይዘውልኛል::





ውሀው፣ ምግቡ፣ ወተቱ፣ ጭማቂው...በጣም ደስ አለኝ:: ከሁሉም ነገር ይልቅ ኢትዮጵያዊነት ፍቅሩ ሳበኝ:: ባያውቁኝም እንደ ቤተሰብ ነው ያጫወቱኝ::

ስንጫወት ቆይተን በመሀል አህመድ ከሊል (ጆሲ) ሳይመጣ ረጅም ጊዜ የጠፋበትን ምክንያት ሲናገር ‹‹እኔ እና አሸናፊ ግርማ..ሀገር ቤት ሄደን ነበር:: አሼ አልተመለሰም እኔ ሁለት ወር አረፍት አድርጌ መጣሁ:: አንተስ እንዴት ሆንክ ምንም ለውጥ የለም?›› አለኝ:: የነበረውን ሁኔታ ሁሉ አለማምሬ እያሳቅኩ አወራኋቸው:: እያያዝኩናም በዋስ እንድወጣ እንደ ተፈቀደልኝ ነገርኳቸው:: ሁሉም ፊታቸው ፈካ:: ለእኔ ዋስ መፈቀዱ እንደዛ ሊያስደስታቸው ሳይ ተገረምኩ:: አህመድ ከሊል ከሙገር እና አሸናፊ ግርማ ከቡና ነበር ለየመኑ አል-ሂላል ክለብ ሊጫወቱ የመጡት:: ለመውረድ አስግቶት የነበረው ክለብ ከመውረድ ስጋቱ አገግሞ የአመቱ ጨዋታ ተጠናቆ ለእረፍት ወደ አዲስ አበባ ሄደው ነበር:: የመን ለአሸናፊ ብዙ ያልተመቸው ነገር ነበረና አልተመለሰም::

ጆሲ ‹‹ዋስስ አገኘህ?›› ሲል መልሶ ፊታቸው ዳመነ:: ደስታቸው ከሰመ:: ሁሉም ይህን አላሰቡትም ነበር:: ‹‹..ከየት አገኛለሁ? እንደ አንበሳ በብረት ታጥሬ የት እፈልጋለሁ?››...ሳቃቸው ሀዘናቸውን አባሮ ማዘናቸውን ለመደበቅ ጊዜያዊ ጋሻ ጃግሬ ሆነ:: አበባ የተባለችው በሰማችው ነገር የወየበ ፊቷን ለማፈገግ እየሞከረች ‹‹እና ምን ይሻልሀል?›› ስትል ጠየቀችኝ:: ለጥያቄዋ የምሰጣት ምላሽ ጠፍቶኝ በሀሳብ ስንገዳገድ ጆሲ መሀል ላይ ታኮ ይመስል ሰንቅር አለልኝ:: ‹‹ዋስ የሚገኝበት መንገድ የለም?›› ነበር ጥያቄው::

‹‹የተወሰኑ ሰዎች አሉ:: እዚህ እየመጡ ለኦሮሞ ብሔር ተወላጆች ዋስ ሆነው የሚያወጧቸውን እናግሬ ነበር:: እነሱ 10.000 ሪያል ከፈለን ብለውኛል..›› አቤት!! ፍጥነት አላስጨረሰችኝም:: አበባ ከአፌ ነጥቃ ‹‹10.000 ብትሰጣቸው ያስፈቱሀል?..›› አዎንታዬን ገልጬ በማግስቱ ልታመጣልኝ ቃል ገብታልኝ ተለያየን::

ሌሊት እንዴት እንቅልፌ ይምጣ? ስለሰነዓ የሰማሁትን ቦታ ሁሉ በሀሳብ ስዳስስ አደርኩና የምገባበት ጠፋኝ:: ለካ ማረፊያም የለኝ:: በዛ ሰዓት ብቻ ነው የታወሰኝ:: ጉጉቴ ሁሉ ገደል ገባ:: ለመውጣት የምታገለው ጎዳና ለመውደቅ ነው ለካ ማን ሊያስጠጋኝ ነው? ጉጉቴ፣ የመውጣት ፍላጎቴ ሁሉ ከሰመ እና እንቅልፌን ማጣጣም ጀመርኩ::

በማግስቱ ቃሏን ጠብቃ መጣች:: ሰጠችኝም:: 10.000 ሪያል ማለት በዛን ሰዓት 500 አካባቢ የኢትዮጵያ ብር ነው:: ወዲያው የምወጣ

ሁሉ መስሏታል። ደጋግማ ‹‹መቼ ትወጣለህ?..መቼ ትወጣለህ?›› ትለኛለች።

«መቼ ልወጣ እንደምችል አላውቀውም። ሳስበው ባልወጣም ያው ነው። ብወጣም ጎዳና ለምወድቀው ምን አገኛለሁ» ስላት ሰቀጠጣት። ‹‹በስመአብ!!..›› ስትል አማተበችና አቋረጠችኝ። ‹‹ምነው ለምን እንደዚህ ታስባለህ? ቤት የመድኃኒዓለም ነው እኛ እህቶችህ እያለን እንዴት ጎዳና?...ስልኬን ያዝና ስትወጣ ደውልልኝ።›› ስልክ ቁጥሯን ተቀብዬ ሁኔታ ዎችን ለመከታተል ተስፋ ሰነቅሁ። በዚህን ሰዓት እንኳን እኔ ኖሁ ጎበና እንዴት እንደተደሰተ ሳይ ገረመኝ። በቃ! የእኔ ከእስር መውጣት ያስደሰታቸው ወገናዊነት አይደል? ኢትዮጵያዊነት ማለት ውብት ነው አልኩ። አንዳችን ለአንዳችን ይህን ያህል መተሳሰባችን፤ የአንዱ ነጻ መውጣት ሌላውን ማስደሰቱ ውስጤ ጥሩ ስሜት ፈጠረ። ይሄ ስደት ነው። እኔም ፈጣሪዬ ብሎ ወጥቼ እንደ እነሱ ብስተካክል የሌሎችን ችግር በመቅ ረፍ ወይም ሲቀረፍ በማየት እንድደሰት ፈጣሪዬን ለመንኩት። ሰማኝም።

አንድ አነስ የሚባል ለሁሉም ኢትዮጵያዊያኖች ዋስ ሲሆን ስላየሁት የመጣ የወጣውን ሁሉ እሱን ፈልጉልኝ እላለሁ። ምሳ ሰዓት አካባቢ ድምጻዊ ኖሁ ጎበናን ለመጠየቅ መጣ። ወደኋላ መለስ ብዬ ኖሁ ከመወሰዱ በፊት ያለውን ታሪክ ነው ያነሳሁት። እኔ ሳልሆን ኖሁ ለመነው። እሱ ኦሮሞ ስላልሆነ 15 ሺህ ካልሆነ ዋስ አልሆንም አለ። ድምጻዊ ኖህ በሁኔታው አዘነ። ስሜቴን ላለመጉዳት ሲል ቀሪውን 5000 ሺህ ሪያል ሊሞላልኝ ቃል ገባልኝ። አነስ የሚባለው ግን በእንቢታው ጸና። ኖሁ የሚችለውን ያህል ለመነው። በተለይ የአባቴን ስም ካየ በኋላ ድጋሚ እንዳትጠይቀኝ ሁላ ብሏል። ይህን በማለቱ ብዙም አላዘንኩበትም። ውጭ ያለውን ሁኔታ ስለማላውቅ የሚከለክለው ነገር ቢኖር ነው ብዬ አሰብኩ። ከእስር ከወጣሁ በኋላም ቢሆን አልፈለገም አልፈለገም የራሱ አመለካከት ነው። የግድ አመለካከትህን ለውጥ አይባልም። ባለ መቀየሜ በተገናኘንበት አጋጣሚ ሁላ ጥሩ ሰላምታ ነበረን።

በሰዓቱ ግን ተስፋዬ እሳት እንደነካው ላስቲክ ስብስብ፣ ኩምትር ባለበት ጊዜ አንድ ምሽት ‹‹ኖሁ ጎበና እልበስ እልበስ የለ ቡሱራ..›› (ልበስ ልበስ ቶሎ በል) ብለው አወጡት። ከዛን እለት ወዲህ በሩ በተከፈተ ቁጥር ስሜ የሚጠራ እየመሰለኝ እጠብቃለሁ። እሳቀቃለሁ። አሁን በረሳሁት ያኔ ግን የተባረከ ባልኩት ሁኔታ አንድ ሶማሊያዊ ቃሲም ደማሪ የሚባል ሰው መጣ። ዋስ ሁነኝ አልኩት

‹‹እኔ ለሱማሌዎች እንጂ ለሀበሻ አይፈቅዱልኝም ቢፈቅዱልኝ ሞሮ..›› በሚል ማሰሪያ ቃል ዘጋኝ። ተስፋዬ ከጉጉቱ ጋር ተዛዝለው ጸሀይ





እንደ መታው የወር ጎመን ጥውልግ ሲሉ ታወቀኝ። አንድ የታሰረ ሶማሊያዊ ጠራ እና እሱን ማውራት ቀጠለ። የምተኛባት ፍራሽ ላይ ጥቅልል ብዬ ስቀመጥ ራሴን እየታዘብኩት ብስጭቱ ከውስጥ እንደ እሳት ሲቀጣጠል እየታወቀኝ ነበር። ለራሴ ራሴ አዘንኩለት። ሁሉ ነገር መክሸፉ ለምን ይሆን? ለበጎ ነው ብዬ ማሰብም መወሰንም አልቻልኩም። ሶማሌው ወሬውን ሲጨርስ መልሶ ጠራኝ።

‹‹ለምን እዚህ ያለውን የUNHCR ተወካይ አታናግረውም ትንሽ ሳንቲም ብትሰጠው ሴትዮዋን ያስመጣልሀል።..››

«እሺ...ግን እንዴት አገኘዋለሁ። አንተ አናግርልኝ» አልኩት። በእኔ አለመቻል ተሰባብሮ ድምጥማጡ የጠፋ አረቢኛዬ ሊገባው አልቻለም። ቅርብ የነበረ አንዱን ጠራሁና በአስተርጓሚ አስነገርኩት። ተስማምቶ ሄደ።

ከጥቂት ቆይታ በኋላ ሁለት ሆነው መጡ። ከሶስቱ ኤርትራዊያን እስረኞች መካከል ተክላይ የሚባለው የአሰብ ልጅ አረብኛ በትክክል ስለሚናገር ጠራሁትና አስተርጉምልኝ አልኩት። ‹‹ደብር ነፍስክ እኔ እሷን በሶስት ቀን ውስጥ አመጣታለሁ..›› አለኝ። ማምጣት ለሱ ቀላልነቱን ለማሳየት ያደረገውን እንቅስቃሴ ያየ ሰው ወዲያው ከኪሱ አውጥቶ የሚሰጠኝ ያስመስለው ነበር። አሁን ሶስት ሺህ የየመን ሪያል /በዛን ጊዜ የኢትዮጵያ 150 ብር ማለት ነበር/ስጠኝ አለ። ለጊዜው ሁለቱን ሺህ ወሰደ። ፕሮቴክሽን ኦፊሰሯን ሲያመጣ ቀሪውን አንድ ሺህ ልሰጠው ተወሰነ። እሁድ ቀን ተነጋግረን ማክሰኞ ጠዋት እስረኛው ሁሉ አሙ አብደላ/አጎቴ አብደላ/ የሚለው የእስር ቤቱ ቁልፍ ያዥ መጣ። ያለሁበትን በአይኑ ፈልጎ ‹‹ያ-ኮሮም እልበስ..እልበስ እማሙታህዳ›› አለ። መልሶ በሩን ሊዘጋው ሲል ተንደርድሬ ወጣሁ። የምን መልበስ? ዘግቶት ሄዶ የሚመለስ ሁሉ አልመሰለኝም። የUNHCR ቢሮ ሰራተኞች መተዋል ተብሎ እንዴት ልረጋጋ? ከእግዚአብሄር በታች ተስፋዬ በእነሱ ላይ የተመሰረተ ነው። እንደዛ ብሆንም ሲያንሰኝ ነው። ያኔ የነበረኝ ስሜትን ዛሬ አፃፃፌ ሊገልጸው የቻለ አልመሰለኝም። በቃ ደስታው ይሁን እፎይታው ያልታወቀ ስሜት ውስጤን ወሮታል።

አንድ ቢሮ ውስጥ አስገብተኝ ተመለሰ። ከውስጥ እስክንድር ከሚባል ትውልደ ኢትዮጵያዊ አስተርጓሚ ጋር ተቀምጣለች። ለሶስት ሰዓት የፊጀ ቃለ ምልልስ አደረግን። እስከዛን ቀን ድረስ በቃለ-ምልልስ ስጠይቅ እንጂ ስጠየቅ አላውቅም። ቢሆንም ግን የማወራው እውነተኛ በመረጃ የተደገፈ ነገር ነው እና ቅንጣት አልተሳሳቅኩም። እስክንድር የሚባለው አስተርጓሚ ያኔ ነው ትውልደ ኢትዮጵያዊ የመሰለኝ። አይደለም። የድሬደዋ

ልጅ ነው። እግዚአብሄር ይስጠው ሀሳብ በማካፈል ረድቶኛል። UN ቢሮ ውስጥ ካሉት ሌላ በጥሩነቱ ሳላመሰግነው የማላልፈው መሀመድ ዑመር ነው። በሚችለው አቅሙ ብዙዎችን ይረዳል።

‹‹በአንድ ሳምንት ውስጥ ከእስር ቤት አወጣሀለሁ...›› አለችና ሄደች። ወደ እስር ክፍሌ ተመለስኩ። እንደሌላ ጊዜው ክፍሉ ጨለማ አልሆነብኝም። ብርሃን የሆነ ተስፋ ስለ ያዝኩኝ ብርሃን ቢመስለኝም መደነቃቀፌ ግን ያው የወትሮው መሆኑን አበሰረኝ። ቃሏን ለመጠበቅ ትንሽ ብትዘገይም በአስረኛው ቀን መታወቂያው /refuggee mandte/ መጣልኝ። ዳግም ሁለት ሺ.ህ የየመን ሪያል ተቀበለኝ እና መፈቻውን አስፈርሞልኝ መጣ። እቃህን ያዝና ውጣ ስባል ሰዓት ከያዙ ልጆች ቶሎ ብዬ ሰዓቱን አየሁ። ልክ 5፡35።

ቀኑ ታህሳስ 23 1998ዓ.ም ተፈታሁ... ተፈታሁ....





# ክፍል ሁለት
# ሀበሻ በየመን

# - 10 -

# ትውውቅ - እኔና ሰነዓ

ፍታኝ...ፍታኝ..
የሚለው መብዛቱ ታወሰኝ
ባይ ባዩ ይቅርና እኔን ከ`ሰር ፍታኝ
ጌታዬ ሆይ ደቼን ብቻ ስማኝ

የእስር ቤቱን ግቢ ለቅቄ እስክወጣ በእጅ የያዝኳትን አነስተኛ ሻንጣ አህመድ ናይፍ የሚባል ሁሌ እቃ ከሱቅ እንዲገዛልን የምንልከው ቅን ፖሊስ ተቀበለኝ። ‹‹እየመጣህ ጠይቀን›› ብሎ ዋናው መንገድ ድረስ ሸኝቶኝ ስልክ ቤት ያለበትንም ጠቆመኝ። ገባሁና ቁጥሩን ነካክቼ ድምጽ እጠብቃለሁ። ከወዲያ ማዶ ግን ‹‹ዝምታ ነው መልሴ.... ዝምታ ነው መልሴ..›› የሚለውን የመሀሙድ አህመድን ዘፈን የሚያስታውስ ዝምታ ተደጋገመ። ‹‹ጢCC..›› ብቻ ጠርቶ ጠርቶ ይዘጋል። ድጋሚ...ድጋሚ 5..6..7.. 8....ይጠራል አይነሳም። ምን ሊሰማኝ እንደሚችል አስቡት። ወዴት ይሆን መጠጊያዬ? ነገር ሁሉ ጭልም አለብኝ። ከኪሴ ያሉትን ወረቀቶች እያወጣሁ ማየት ጀመርኩ። አገኘሁት። ንግስቲ የምትባል ኤርትራዊት ስልክ ቁጥሯን ሰጥታኝ ነበር። ደወልኩላት። በተቃራኒው ስልኩ ላይ የተጣደች ይመስል አንዴ ሲጠራ መነተፈችውና ‹‹ሀሎ!..›› አለችኝ። ከእስር ከተፈታሁ የመጀመሪያውን ቀልድ የቀለድኩት ያኔ ነው ማለት እችላለሁ።

‹‹ሀሎ!.. ይህ የእኔ ድምጽ ነው... የእኔ ድምጽ ዘውትር ግሩም ከእስር ሲፈታ...›› አቤት ደስታዋ ‹‹ኡኡኡ!!..›› ጩኸቷ የጆሮዬን ታምቡር ሊበጥሰው ደረሰ። ደስታዋ ያሳፈጠኩት ደስታ ጫረብኝ። አወራኂት። ስልኳ

አልነሳ ማለቱን ሁሉ ተናገሬ ስጨርስ ‹‹የት ነህ?›› አለችኝ፡፡ «እስር ቤቱ ግቢ በር ጋ ነኝ፡፡»

‹‹ሀዳ ጀንዱል ብለህ ኮንትራት ታክሲ ያዝና ና ከዛ ገነት ኮፌር ብለህ... እንዲያውም ደውልልኝ እወጣልሀለሁ፡፡››

ሀዳ! ጀንዱል.. ቃሉን እንዳልረሳው ደጋግሜ እያልኩ ፈልጌ አፈላልጌ ታክሲ አገኘሁ፡፡ ቦታው ላይ ሲያወርደኝ ሳልደውልላት ያለችውን ቦታ አገኘቼ ስርፕራይዝ ላደርጋት ገነት ኮፌር የሚል ፍለጋ ቀጠልኩ፡፡ እስር ቤት ውስጥ አረቢኛ መጻፍና ማንበብ አንድ ሳዑዲያዊ አስተምሮኝ ስለነበር ማስታወቂያውን አንብቤ ነበር ለሰርፕራይዝ ያሰብኩት፡፡ በአረቢኛ ኮፌር ማለት የሴቶች የውበት ሳሎን ነው፡፡ ባይም አላገኘው ነበር ግን ሳላየው አልፌዋለሁ፡፡ ሰርፕራይዙ አልተሳካልኝም፡፡

ስልክ ቤት ገብቼ ለንግስቲ ደወልኩላት፡፡ ስወጣ አንድ ኢትዮጵያዊት አገኘሁ፡፡ ደስ አለኝ፡፡ ላናግራት ጉጉት ብዬ እሷን ባየሁበት መስመር ተሻገርኩ፡፡

‹‹እህት ሀበሻ ነሽ?››

‹‹አይደለሁም!!..›› እንደማመናጨቅ አደረጋት፡፡ ልለከፋት መሰሏት መሰለኝ

‹‹ኧረ!.. እባክሽ አማርኛ ሶፍትዌር ተገጥሞልሽ ነው የምታወሪው?›› ተናድጄም ነው፡፡ ብታውቅልኝም ባታውቅልኝም ሰው ናፍቆኝ ከእስር የተፈታ እንቦሳ ሆኜ ቦርቅ ቦርቅ ቢለኝም በሰው ሀገር የማይቦረቅ ሆኖብኝ የታፈንኩ ነኝ፡፡ ደስታ ስለጋረደኝ እንጂ ሆዴን ረሀብ ዱለስ እያደረገው ነው፡፡ የራበው ይጠብሳል? የራበው ይለከፋል? እየነዝኩባት፡፡ እስካሁን ካየኋቸው እህቶቼ ከምላቸው ሁሉ አልመሳሰል አለችኝ፡፡ ቆሜ በአግራሞት ማየቱ ገርሟት ይሁን ችግሬን ተረድታ መለስ ብላ ‹‹ልጅ ሀበሻ ነኝ›› ስትለኝ በንዴት ‹‹ተይው ሀሳቤን ሰርዣለሁ›› አልኳት፡፡ ዞር ስል ንግስቲ ከወደ ላይ ስትመጣ አየኋት፡፡ ተደሰትኩኝ፡፡

‹‹ግሩምዬ በጣም ነው ደስ ያለኝ፡፡ መሳሳም አይቻልም እንጂ ጥምጥም ብዬ ደስታዬን በገለጽኩልህ ነበር...›› ገና በደንብ ሳትቀርበኝ የነገረችኝ እንደ ሀገሬ መሰሉኝ እንዳልስማት መሰለኝ፡፡

‹‹ውስጥሽ ያለውን ደስታ ፊትሽ ይናገራል፡፡ አመሰግናለሁ፡፡›› ተጨባበጥን፡፡ እያወራን አንድ ምግብ ቤት ሄድን፡፡ ሴቶች መግባት ለማይፈቀድላቸው ምላ ጋበዘችኝና በልቼ እስክጨርስ እሷ ውጭ ቆማ ጠበቀችኝ፡፡ የተከራዩበት ቤት ደግሞ ወንድ አይገባም፡፡ የት እንደምታሳርፈኝ እያሰበች ተጨንቃለች፡፡ ከምግብ ቤቱ ስወጣ በሀሳብ ናውዛ አላየችኝም፡፡ ‹‹ምን እያሰብሽ ነው?›› ነገረችኝ፡፡ ‹‹አትጨነቂ ቆይ እስኪ ድጋሚ





ልደውል፡፡›› ተያይዘን ስልክ ቤት ገባን፡፡ አስጠጋሀለሁ ላለችኝ አበባ እሸቱ ስደውል ስልኳ ተከፈተ፡፡

‹‹ሄሎ ግሩም ነኝ..›› ንግግሬን ሳልጨርስ

‹‹ውይ!... ጌታዬ ተመስገን›› ስትል አቋረጠችኝ፡፡ ‹‹አሁን የት ነህ? ከአንድ ሰዓት በኋላ ነው ከስራ የምወጣው.. ወይኔ ደስ ሲል...›› ከስራ ስትወጣ እንደምንገናኝ ነግራኝ ተለያየን፡፡ ነጻ አየር እየተነፈስኩ በእስር እና በነጻነት መሀከል ያለውን ልዩነት እያጣጣምኩ ነው፡፡ በእኔ መፈታት ሌሎች ተደስተው ማየትም ሌላ ደስታ ሆነኝ፡፡

ለሀገሩ ሀገ ሁሉ አዲስ በመሆኔ እስክለምደው አስቸግሮኝ ነበር፡፡ የሴቶች የውበት ሳሎን ውስጥ ወንድ ስለማይገባ የያዝኳትን ሻንጣ እነንግስቲ ጋ አኑሬ ዞር ዞር ለማለት አሰብኩ፡፡ ንግስቲ ስራ መፍታቷ ብቻ ሳይሆን ከእኔ ጋር መጨነቋም አሳዝኖኝ ነው ዞር ዞር ማለት የፈለኩት፡፡ አበባ ስትወጣ ፍለጋ እንዳትቸገር እንደገና ደወልኩና ሀዳ ጀንዱል የሚባለው አካባቢ መሆኔን ነገርኳት፡፡ ልክ ከአንድ ሰዓት በኋላ ያለችኝ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ማለቷ ነበር፡፡ ‹‹እስከዛ ለጓደኛዬ ደውልላት እሷ መጥታ ትወስድሀለች›› ብላ ስልክ ቁጥሯንም ሰጠችኝ፡፡ ለሳም ጌታቸው ትባላለች፡፡ በስልክ ላናግራት ትዕቢተኛ ነገር መሰለኝ ነበር፡፡ ‹‹ሹሜላ የሚባለውን ገበያ እየጠየክ ና ከታክሲ መውረጃው ጋ እጠብቅሀለሁ›› አለችኝ፡፡ የተቆጣች ትመስላለች፡፡ መጠጊያ ፍለጋ ተንከራታች ስለሆንኩ የምር ተቆጥታም ቢሆን አማራጭ የለኝም፡፡ የነገረችኝ ቦታ ግን ከተማውን ለማያውቅ ለአዲስ ሰው ቀርቶ! ለኖረበትም ግራ አጋቢ ነው፡፡

ንግስቲ ታክሲ አሳፈረችኝ፡፡ ሹሜላ የሚባለው የገበያ ቦታ ስደርስ መርካቶ አውቶቡስ ተራን ይመስላል፡፡ ግርግር የነገሰበት መኪና ከመኪና የሚተራመስበት ቦታ ነው፡፡ መቼም ፈጣሪ ረድቶኝ ማለት ይቻላል ሰላማዊትን አገኘኋት፡፡ እንዳሰብኳት ቁጡ ሳትሆን በስርዓት የታነጸች ደርባባ ነች፡፡ ለነገሩ የወታደር ልጅ ናት፡፡ አባቷ ሩዋንዳ ከዘመተው ሰራዊት ጋር ሲሄዱ እሷ እና እህቷ ተደብቀው ወደ የመን መጡ፡፡ ከዛ ጌታቸው ወደ ሀገር ሲመለሱ ተቆጥተው እስከመለሷት ድረስ ምርጥ ልጅ...ጥሩ እህቱ ነበረች...እግዚአብሄር ይስጣት፡፡

እነአበባ ሶስት ክፍል ቤት ነው ያሉበት፡፡ አብረዋት ከሚኖሩት መካከል የሺ የምትባለው ቡና አፍልታ ከእስር ቤት ውጭ ከሰው ተቀላቅዬ የመጀመሪያውን ምሽት አሳለፍኩኝ፡፡ አበባ እሸቱ ከስራ ወጥታ ማታ ስትመጣና ስታገኘኝ ደስታዋ ወደር የለውም ነበር፡፡ ለሌሎት የሚጠቀሙበት የእሷን ክፍል ለእኔ መኝታ አደረገችልኝ፡፡ በማግስቱ አበባ የምትሰራበት ካምፓኒ እንግዳ መቀበያ ውስጥ በምግብ ኃላፊነት የሚሰራው የእህቷ ባል

ብርሀኑ ከሚባለው ጋር ወስዳ አስተዋወቀችኝ፡፡ እህትየው ብርቱካን እሹቴም ሆነች ባሏ ምርጥ ሰዎች ናቸው፡፡ እንደ አበባ ሁሌም ሳቅ በሳቅ ባይሆኑም፡፡

ያረፍኩበት ቤት ውስጥ ሁሉም ጠዋት ወጥተው ማታ የሚገቡ ናቸው፡፡ ቁርስ ምሳ እራት ቤት ውስጥ አይሰሩም፡፡ የእረፍት ቀን አርብ ስለሆነ በዚሁ ቀን ለሳምንት የሚሆናቸውን ምግብ ሰርተው ፍሪጅ ውስጥ ያስቀምጡታል፡፡ መሬታቱን ከሰማበት ቀን ጀምሮ አህመድ ከሊል /ጆሲ/ ጠዋት ይመጣል፡፡ ጆሲ ተኝቼ ከሆነ ቀስቅሶኝ ይዞኝ ይወጣና ቁርስ ያበላኛል፡፡ መሄድ ያለብን ቦታ እንሄዳለን፡፡ አብረን እንቆይና ምሳ እንበላለን፡፡ ከሰዓት በኋላ ትሬኒንግ ስለሚሰራ አብረን እንሄዳለን፡፡ እራት አብረን በልተን ወደቤቱ ይሄዳል፡፡ አንዳንዴ ደግሞ አበባ የምትሰራበት ቦታ ሄጄ ከብርሃኑ ጋር አሳልፋለሁ፡፡ ምሳም እዛ እበላለሁ፡፡

ከእስር ቤት ከወጣሁ ከወር ከአስራ ሶስት ቀን በኋላ ጆሲ ሙከላ የተባለ ደቡባዊ የየመን ከተማ ጨዋታ ነበረው እና ሰኞ ዕለት ምሳ በልተን ባብል የመን ከሚባለው ቦታ ላይ ተሰናብቶኝ ሄደ፡፡ ኪሴ ውስጥ ያለው 30 ሪያል ብቻ ነው፡፡ ግራ ገባኝ፡፡ ‹‹እስኪ ልወዝወዘው ልወዝወዘው በእግሬ ሸጋ ለወዳጄ...›› እያልኩ በእግሬ አላስነካው ጸሀዩ የዋዛ አይደለም፡፡ በ20 ሪያል ታክሲ ላይ ቂብ ብዬ አስጠጊዎቼ ወደሚኖሩበት ሹሜላ ወደሚባለው ሰፈር አመራሁ፡፡ ኪሴ 10 ሪያል ብቻ ቀረኝ፡፡ እራት የምበላው የለኝም፡፡ ጠሜን ክልትው ብዬ አደርኩ፡፡ የማላውቃቸውን አስጠጊዎቼን ቀርቶ በአደኩበት ቤት ውስጥ እንኳን ራበኝ ስጡኝ ማለትን አላውቅም፡፡ ገብቼ ስቀመጥ እናቴ ካቀረበችልኝ አቀረበች ካላቀረበችልኝ የላትም ማለት ነው ወጥቼ እሄዳለሁ፡፡

ማክሰኞ ከቤት ሳልወጣ ተኝቼ ዋልኩ፡፡ የማልዋሸው ኪሴ ውስጥ ባለችው 10 ሪያል አንድ ኩብዝ የሚሉትን ስስ ቂጣ ገዝቼ ምሳ ሰዓት ላይ ባዶውን በላሁ፡፡ የአንድ ዳቦ ግማሽ ቢሆን ነው፡፡ ማባያ ነገር ፍሪጅ ውስጥ አለ፡፡ ካለፍቃዳቸው መውሰድ ሌብነት ሆነብኝ፡፡ ደግሞም አመላቸውን ስለማላውቅ ቢጣሉኝስ ከነአካቴው መውደቂያ ላጣም አይደል?... ይቅርብኝ፡፡ ብቻውን ደረቁን በላሁ፡፡ በእሱው አደርኩኝ፡፡ መጥፎው አጋጣሚ ውሀዬም አለቀ፡፡ የመን የቧንባ ውሀ አይጠጣም፡፡ ከነቆሻሻው ከነአሸዋው ስለሚልኩት በጃርዲያ ማለቅ ነው፡፡ ረቡዕ ከየትም የመጣ ምንም ነገር የለም፡፡ እኔም አልወጣሁ፡፡ ብታመምም ልታመም ብዬ የቧንቧውን ውሃ ጠጣሁ፡፡ ሀሙስ የሆኑ የማውቃቸው ልጆች ጋር ለመሄድ አሰብኩ፡፡ ከዛ በፊት ግን ከፈጣሪዬ ጋር ተነጋገርኩ፡፡ ‹‹ርቦኛል ብዬ ስጡም አለምንም፡፡ ምግብ ፍሪጅ ውስጥ የሞላ ቢሆንም አልሰርቅም፡፡ እንዲሁ ቁጭ ብዬም በርሀብ ማቅቄ አልሞትም፡፡ ፈጣሪዬ ራስን መግደል ሀጢያት እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ግን በርሃብ ጠውልጌ ከምሞት ዛሬ እነ ሰብለ ጋ ሄዳለሁ፡፡ ካገኘሁ እበላለሁ፡፡ ካጣሁም ስመለስ ራሴን እንደማጠፋ ቃል እገባልሀለሁ›› ብዬው ካለሁበት





ሹሜላ አካባቢ ጆውላት ዕዝ የሚባል ቦታ ድረስ አንድ ታክሲ የሚያስፈልገው ሩቅ የሚያስኬድ መንገድ በእግሬ አስነካሁት፡፡ ታዲያ አስነካሁት ያለው አፌ እንጂ ጉልበቴ አቅቶት ሶስት አራት ቦታ እንደ በሽተኛ እያረፍኩ ነው የተጓዝኩት፡፡

ሰብለን እና ሳራን እስር ቤት እያለሁ ለጥየቃ መጥተው ነው የማውቃቸው፡፡ ከተፈታሁ በኋላም ሁለት ሶስቴ ከቤተክርስቲያን መልስ እኛ ጋ ምሳ ካልበላህ ብለው ወስደውኛል፡፡ ያኔ ተግደርድሬ በልመና ነበር የሄድኩት፡፡ ዛሬ ደግሞ ለልመና ነው ተንደርድሬ የምሄደው፡፡ ቀደም ሲል እነሱ ጋር መሄዱን ያላሰብኩት ሁሉም አዳሪ ስለሚሰሩ ቤት የሚገኙት ሀሙስ ከአስር ሰዓት በኋላ እና አርብ ብቻ በመሆኑ ነው፡፡ የሚመጡበትን ሰዓት አስልቼ ስለሆነ የሄድኩት ሰብለ ገና ስትገባ ደረስኩ፡፡ ሙሉ ስሟ ሰብለወርቅ ታደሰ ነው፡፡ የሳሪስ አካባቢ ልጅ ነች፡፡

በሩን እንደከፈተች ሰላምታ ሰጥታኝ ወደ ውስጥ ገባች፡፡ የሚበላ ነገር በትሪ ይዛ መጣችና ‹‹ገና መግባቴ ነውና ምሳ እንብላ..›› አለችኝ፡፡ መሬት ላስቲክ አንጥፋ ያስቀመጠችውን ትሪ አየሁት፡፡ ሳልቀርበው በተቀመጥኩበት ወደ ሰማይ አንጋጠጥኩ፡፡ እይታዬን ጣራው ሲመልሰው በአንደበቴ ‹‹ፈጣሪዬ ሆይ ተመስገን..›› አልኩ፡፡ ምሳችንን አጣጥመን በላን፡፡

‹‹ወንድ ልጅ እኮ ለአንዳንድ ነገር ይቸግረዋል፡፡ ለሳሙናም ለምንም ቢያስፈልግሀ›› ብላ ደረት ኪሴ ውስጥ አንድ ሺህ አምስት መቶ የየመን ሪያል ከተተችልኝ፡፡ ‹‹ለነገ እና ለተነገ ወዲያ አብቃቃዋለሁ፡፡ ከዛ ጆሲ ይመጣል›› ብዬ እያሰብኩ ሳለ

‹‹ዛሬ ሀሙስ አይደለ እንዴ? እንደ ሀገሩ ሰው አለመድክም ሀሙስን አትቅምም?›› አለችኝ፡፡ ‹‹ከፈለኩ አሁን መቃም እችላለሁ....›› በፍጥነት ወደ ውስጥ ገብታ ባልጦ የሚሉትን ከላይ የሚለበስ ጥቁር ቀሚስ አጥልቃ መጣች፡፡ ተያይዘን ወጣን፡፡ ለካ ጫት ልትገዛልኝ ፈልጋ ነው፡፡ እኔ ደግሞ ፍላጎቱ አልነበረኝም፡፡ ረሃብ ባደከመው ሰውነት ምኑን እቅማለሁ?

ይሄን ችግሬን በዚህ ተወጥቼ ጆሲም መጣ፡፡ ያው ለአራት ወር ያለመታከት ያበላኝ ያጠጣኝ የነበረው እሱ ነው፡፡ ሰብለወርቅ ግን ከሞት ያተረፈችኝ መልዕክተኛ አድርጌ አየኋት፡፡ ከልብም ወደድኳት፡፡ አሁን አግብታ አዲስ አበባ ሳሪስ ናት፡፡

የሚያውቁኝ ሁሉ ስራ ያፈላልጉልኝ ጀመር፡፡ አንድ ቀን ብርሃኑ የሚባለው ያስጠጋችኝ ልጅ የእህቷ ባል ስራ አለ ብሎ ጠራኝ፡፡ አንድ ትልቅ አይስክሬም ቤት ማናጀር ይፈልጋሉ ብሎ ይዞኝ ሄደ፡፡ ‹‹አንተ ግሩም ነህ.. ምነው ጠቋቆርክ?›› ብሎ አንዱ ተጠመጠመብኝ፡፡ ሳየው አብርሃም በቀለ የሚባል ልጅ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የማውቀው ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ አገኘሁ፡፡

በእሱ አማካኝነት ብርሃን እህቴን አገኘኋት። በዚህ ስሜት ውስጥ እያለሁ ነው አንድ ስልክ ተደውሎ ዳንኤል ገዛኸኝ ነኝ ያለኝ። በደስታ ሲቃ ተሞልቼ ነው ያወራሁት። ጋዜጠኛ ታምራት ሰርቤሳም አብሮት እንዳለ ነገረኝና ተገናኘኝ። አወራን - በስልክ። ምን ያህል ደስ እንዳለኝ ግን ለሰው ብነግረው የሚያምኑኝ አልመሰለኝም። አንድ ጓደኛዬ ስነግረው በባህር በመምጣታቸው እንዴት ትደሰታለህ? አለኝ። አልገባውም። እኔ ያን የስቃይ እና የሞት ቀጠና በሰላም በማለፋቸው ነው ደስታዬ...

ጥቂት ቀን ቆይተው ሰነዓ መጡ። ዳኒ ከሳ ብሎ አየሁት። ምነው አላልኩትም። ሰው ከሳህ ጠቆርክ ምናምን ማለት አልወድም። በዛ ላይ በስቃይ እንደሚመጡ ገምቻለሁ።[9]

ከታምራትም ሆነ ከዳንኤል ጋር በስራም በወዳጅነትም ያሳለፍነው ቀላል ህይወት አይደለም። በተለይ በገመና ጋዜጣ ያየነው መከራ ዳንኤልን መቼም ቢሆን እንዳልረሳው ያደርገኛል። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ናቸው የከሰሱን። ከሙስና ጋር በተያያዘ ነበር ያጋለጥነው ምስጢር። ከቀድሞው ጠ/ሚኒስትር ታምራት ላይኔ ጀምሮ ብዙ ሰውም ያነካካ ነበር። በዚህ ክስ ምክንያት ስፈለግ ነበር። አንድ ቀን 4 ኪሎ ዘውዲቱ ሆቴል እራት እየበላሁ ሳለ ሲቪል ለባሽ ፖሊስ መጥቶ አጠገቤ ተቀመጠ። ይበላ እንደሆን ብዬ ‹‹እንብላ›› አልኩት። «ብላና ታናግረኛለህ» ብሎ ፊቱን አጨፍግጎ ተኮፈሰ። ጨርሼ ስወጣ ተያዝኩኝ። ሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያ ስፈሬ ቢሆንም እናቴ እንድትሰማ አልፈለኩም። ለነገሩ ብፈልግስ መቼ ፋታ ሰጡኝና! ምሽቱን እስር ቤት ውስጥ ለአራት ተደብድቤ በውሻ አስነክሰውኝ እጄን በካቴና ታስሬ ግቢው ውስጥ ቆማ ሽንት የሚሸናባት፣ አይጥ የሚተራመስበት ቮክስዋገን መኪና ውስጥ አሳደሩኝ። አንድ ሰው ላይ ሊደረግ ከሚገባው በላይ ኢ-ሰብአዊ ድርጊት ተፈጽሞብኝ አደርኩ። በማግስቱ ፍርድቤት ስቀርብ ሁሉን ተናገርኩ። ይህ አይነት ድርጊት ተፈጽሞብኝ ሳለ ዳንኤል መታሰሬን ሲሰማ የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ በመሆኑ ከእኔ ይበልጥ እንደሚፈለግ እያወቀ ጣቢያው ድረስ መጣ። ያ ቅንነቱ ነው። ልሸሽ አላለም።

ፖሊስ ጣቢያ ስተት ብሎ ሲመጣ ‹‹ምን ልታደርግ ነው?›› አልኩት። ሜዳ ላይ በድሮ ጊዜ የቆሙ መኪኖች ውስጥ አይጥ እየተርመሰመሰበት ሽንት እየተሸናበት ግማቱ የማያስቀምጥ በአንዱ መኪና ውስጥ ስለ ሆንኩ አየሁት። ያኔ የነበረው የዳንኤል ቅንነት እዚህ ጋ ነው የተመዘነው።

‹‹እኔ ስለሆንኩ ዋና አዘጋጁ እኔ እገባና አንተን ይፍቱህ...››

---

[9] ከዳንኤል ገዛኸኝ ጋር ያወራነውን (ቃለ-ምልልስ ያደረግነውን) በምዕራፍ 12 ገፅ 173 ላይ ታገኙታላችሁ





‹‹ምን ማለትህ ነው?!.. እንደዚህ ብሎ ነገር የለም። ተመለስ፣ ሆስፒታል ሰው እያስታመምኩ መሰለህ የምትለወጥልኝ...›› ተቆጣሁት። ዳንኤል ግን ያሰበው ከትክክለኛ የፕሬስ ህጉ አንጻር ነው። ዋና አዘጋጁ ካለ አሳታሚው አይጠየቅም። እነሱ ደግሞ ይህን ተግባራዊ እንደማያደርጉት ተስፋ አለኝና አትግባ አልኩት። ስቃዩን ብቻዬን መቀበል ይሻለኛል ብዬ ነው። እሱ ደግሞ እኔ ነኝ መታሰር ያለብኝ አንተ በምን እዳህ ባይ ነው።

ገባ። ቃሉን ሰጠ።

አብረን ለአንድ ሳምንት ስቃያችንን ጥጥት አደረግናት። በሳምንታችን በዋስ ተለቀቅን። ለእኔ ብሎ ላያድነኝ አብሮኝ ተደበደበ። ተካፍለን ለብሰናል፤ ተካፍለን በልተናል። ዛሬ ስደት ላይ እኔ በወጣሁበት መንገድ ወጥቶ ሳይ ያየሁትን ስቃይ አይቶ እዚህ መድረሱን ገምቻለሁ። ዋናው ነገር ያን ሁሉ ስቃይ አልፎ መጥቶ በመገናኘታችን በጣም ደስ አለኝ። ሲያወራኝ ግን እኔ ካየሁትም በላይ ያየ መሰለኝ። በዛን ወቅት ከላይ ከላይ አወራን።

ዳንኤል እና ታምራት ከአደን መጥተው በተያየን በአጭር ጊዜ ውስጥ ከእግር ኳስ ተጫዋቹ አህመድ ጋር ተለያይቼ ኢንተርኔት ቤት አምሽቼ ወደ አስጠጊዎቼ ቤት ስሄድ መግቢያው ላይ የፖሊስ ልብስ የለበሰ ሰው መታወቂያ ጠየቀኝ። ሰጠሁት። ተቀብሎኝ ‹‹ቀጥ ብለህ ሂድ›› አለኝ። መታወቂያዬን ሳይመልስልኝ እንዴት ልሂድ? ደግሞም መሳሪያ ይዟል ፈራሁ። በሳምንቱ እዛው ቦታ ጠብቀው ተያዝኩኝ። በማግስቱ ከUNHCR ፕሮቴክሽን ኦፊሰሯ መጥታ አወጣችኝ። ህይወትህን ለመጠበቅ ከፊታቸው ዞር ብትል በሚል ድለላ አል-ቀረስ ካምፕ እንድገባ አግባባችኝ። በማግስቱ መኪና ተዘጋጅቶ አደን የሚባለው የየመን ሁለተኛ ከተማ ተወሰድኩ። እዛ ስደርስ ዳንኤል እና ታምራትን ቀድሜ ፈለኳቸው። በልጆች አገናኝነት ተገናኘን። ከአቀባበላቸውም ከምኑም ግን ልቤን እንክት ያደረገኝ ያድሩበት የነበረውን የፈረሰ ህንጻ ያሳዩኝ ጊዜ ነበር።

አንድ ሳምንት ቆይቼ ተመለስኩኝ። ምክንያቱም ፕሮቴክሽን ኦፊሰሯ ዋሽታ.. በሳምንት ሁለት ቀን ኢንተርኔት ትጠቀማለህ ብለው የሌለ መረጃ ሰጥተው ነበር የላከችኝ። አደን ያለችው ፕሮቴክሽን ኦፊሰር ግልጹን ነገረችኝ። ‹‹ዱቄት እና ዘይት ተሰጥቶህ ነው አብስለህ የምትበላው እንኳን ኢንተርኔት ልትጠቀም›› አለችኝ።

UNHCR ይህን ቦታ የስደተኛው መቀጫ አድርጎ ነው ያለው። ሁኔታውን ካወኩ በኋላ ወደዚህ ቋምፕ አልገባም በማለቴ እስከዛሬ ድረስ ምንም አይነት ሪሴትልመንት እንዳይሰጠኝ በቀይ ምልክት ተደረገብኝ።

እዚህ የሰው ልጅ መሰቃያ ቦታ ስደተኛውም በዘር፣ በጎሳ፣ በእምነት፣ ተቧድኖ የሚባላበት ቦታ ለምን አልገባህም ተብዬ ዱረብልሶሊሽን አታገኝም የተባልኩት ለምን ይሆን? ይህን ካምፕ በግሌ በ2012 ሄጄ ለማየት ሞክሬያለሁ። እዛ ያሉ ስደተኞች እጅግ በጣም አሳዛኝ ህይወት እንደሚኖሩ ለማወቅ ችያለሁ። እኔ በሄድኩበት ጊዜ ካምፕ ውስጥ ያለምንም መፍትሄ 14 አመት የሞላቸው ሁሉ አጋጥመውኛል። ሰው ጥየቃ ነው ብዬ እዛ ያለ ልጅ አስጠርቼ ነው የገባሁት። እዛው ነዋሪ የሆነ ሰው ካልሆነ መግባት ክልክል ነው ተባለ። እስር ቤትም ይመስላል። ዱቄት እና ዘይት ተሰጥቷቸው የቀረውን ነግደውም አሳ አጥምደውም የራሳቸውን ህይወት ይገፋሉ። ከፍ ዝቅ የማይል ምድራዊ ሲኦል የሆነ ህይወት ነው የሚመሩት። ገና ከመግቢያ በሩ ላይ ጩህ..ጩኽ አለኝ። የያዝኩትን ቦርሳ በስሙ-ፍተሻ ነካ ነካ ተደርጎ ገባሁ።

ስጋ እና አሳ ጽዳቱን ባልጠበቀ ሁኔታ ሜዳ ላይ ላስቲክ ተነጥፎ ዝንብ ከቦ እያንቧቸረባቸው ይሸጣሉ። ከላያቸው የሰፈረው ዝንብ ከቅጠል «እእሽሽሽ..» ተብሎ ዞር ሲል ነው አሳ ይሁን ስጋ የሚያስታውቀው። ለነገሩ አሳ ቀደም ብሎ አስጠሊታ ሽታውን ስለሚረጭ ያስታውቃል። ስደተኛው ጥሮ ግሮ ከአካባቢው ርቆ ሄዶ አሳ አስግሮ ሌላም ስራ ሰርቶ ነው የሚኖረው። የሚሰፈርለት ዱቄት እንኳን ለወር ለሳምንትም የሚሆን አይደለም። በዛ ላይ ህክምና የሚሰጥበት ቦታ ሆስፒታል ይሉታል። ፈጽሞ አስጠሊታና ጽዳት የሌለው ነው። ስደተኛውን ለማሰቃየት የተፈጠረ ካምፕ ነው። እዚህ ካምፕ ብገባ ኖሮ የሚኖረውን ጉዳት አስቤ አለመግባቴን አመሰግኛለሁ።

ዳንኤልም የሚያውቀውን መረጃ ሁሉ ሰጠኝ። መልሱኝ ብዬ በሳምንቴ ወደ ሰነዓ ተመለስኩ። ከኋላ ዳንኤል ታመመና ጠቅልሎ ሰነዓ ለመኖር መጣ። ለእሱ ከእኔ የቀረበ የለምና እኔ ጋር ሆነ። ብዙ ብዙ ያየንበትን ኑሮ ኖረናል። ቆይቶም ታምራት ወደ ሰነዓ መጣ።





# - 11 -

## ዘመነ-ግርምቢጥ

ለማን ያዋዩታል
እንዳው መቃጠል
እሳቱ አይታይ
ዝም ብሉ መከሰል

ሰነዓ ከተማን ሳውቃት ይሄ ነው ብዬ መደምደም የማልችለው ብዙ.. ብዙ እውነት እውነት የማይመስሉ ህይወቶች አይቻለሁ። በተለይ ኢትዮጵያዊያን ላይ በተለያዩ ኃይሎች የሚደርሱ አንገፍጋፊ እና ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶች እለት ከእለት እየባሱ መምጣታቸው ሁሌም ያሳስቡኛል። እስኪ ሰነዓ በኖርኩበት ጊዜ ያየሁት፣ የሰማሁትን ህይወት ጠቅለል አድርጌ ላቅርብላችሁ። ከስደትም አስከፊውን የአረብ ሀገር ስደት... ከአረብ ሀገርም ስለየመን እናውራ።

የመን ውስጥ እንደ ሌላው የዐረብ ሀገር ሁሉ ጥሩም አለ መጥፎም አለ። ሞቱም፣ ዱላውም፣ መደፈሩም፣ ማግኘት፣ ማጣቱም ሁሉም አለ። ያውም የተሻለ ሳይሆን ብዙ ብዙ እውነት የማይመስሉ እውነቶች የተሰገጡበት ህይወት ነው በየመን ያለው።

ችግር የማይነቅለው የለም። ችግር የማያሰድደው የለም። ኢየሱስ ክርስቶስም ተሰዷል። ነብዩም ተሰደዋል። ኧረ ቆራጡ እና ተፈጥሮን በቁጥጥር ስር እናውላለን ያሉት ኮሎኔል መንግስቱም ተሰደዋል። እኛ ለስደት አዲስ አይደለንም። አለም ለስደት አዲስ እንዳልሆነ ሁሉ እኛም

እየተሰደድን ነው። ተሰደናልም ገናም እንሰደዳለን። ሀበሻ በየመን እጅጉን አሰልቺ የሆነ ደግሞም ያልሆነ ዝብርቅርቅ ህይወት ከጥሩ ጎኑ መጥፎው ያመዘነበት ኑሮ መሀል ተሰንጎ ነው የሚኖረው። እርስ በእርስ የጎሪጥ መተያየት፣ ጥርጣሬ.. የበዛበት ነው ህይወቱ። መሰደብ ያ-ሀበሺ.. ሽቃላ.. አሪያ.. ያ-ሱማሌ.. ያ-አስወድ.. የዘውትር መጠሪያ ነው። ኤጭ!.. ድሮስ ክብር በሀገር አይደል? ነው እንጂ። ክብር በሌለበት ተንቆ፣ ተዋርዶ መኖር። የመን ያለ የሀበሻ ቁጥር እንዲህ በዋዛ የሚሰላ አይደለም። በህጋዊ መንገድ የሚኖረውና ህጋዊ ያልሆነው ከ70-80 ሺህ ይደርሳል ተብሎ ይገመታል። ይገመታል ነው እንግዲህ። ደሞም ቢበልጥ እንጂ አያንስም። ወደ ሳዑዲ አረቢያ ተጓዡም ቀላል አይደለም። በ2011 ዓ.ም ብቻ ወደ የመን የገቡት 103,000 የምስራቅ አፍሪካ ስደተኞች ውስጥ ወደ 80,000 የሚሆኑት ኢትዮጵያዊያን ናቸው። በ2012 ዓ.ም ደግሞ የመን ባህር ተሻግረው ከገቡ 107,000 የምስራቅ አፍሪካ ስደተኞች ውስጥ 84,000 ኢትዮጵያዊያን ናቸው። እንግዲህ ከዚህ ውስጥ ሰባት በመቶ የሚሆነው የመን ውስጥ ሲቀር ቀሪው ወደ ሳዑዲ አረቢያ ተሻጋሪ ነው።

ተሰዶ ከሚመጣው ኢትዮጵያዊ በተጨማሪ በእናታቸው፣ በአባታቸው፣ አልፎም በአያታቸው ኢትዮጵያ የሆኑ... ግማሽ ጎናቸው የመናዊ ትውልደ ሀበሻ 5.000.000 /አምስት ሚሊዮን/ አካባቢ ናቸው። ይህ የሚያሳየው የየመንና ኢትዮጵያ ትስስር የጥንት መሆኑንና ሲወልዱ ሲዋለዱ መኖራቸውን ነው። በፊት የመኒዎች በችግር ወደሀገራችን ይሰደዱ ነበር። ዛሬ ነገር ተገልብጦ እኛ ሆነናል ወደእነሱ የምንሰደደው። እንደዚያም ሆኖ ግን አሁንም ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የመናዊ ቁጥር በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ ሳይሆን አይቀርም የመን ከአረቢኛው ቀጥሎ አማርኛ በሰፊው ይነገራል ማለት የሚያስደፍረው።

‹‹ገንዘብ ካለ...›› ሁሉም የመናዊያን የሚያውቋት ተረት ናት። ‹‹እ..ወዲሽሎ.. ኢንደሚኖ....አንቺ..›› በሁሉም ዘንድ የተለመደች ቃል ነች።

ጫት ሲነሳ ሐረርን የማያነሳ የመናዊ የለም።

የዛሬዋ የመን ጥንት ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ ‹‹ሀገረ ናግራን›› እንደምትባል ታሪክ ያስረዳል። ‹‹ኤደን›› ደግሞ ‹‹አደን›› ተብሎ መለወጡን አንዳንድ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ዋና ከተማዋ ሰነዓ ጥንታዊነቷን ለማስረገጥ ከንግስት ሳባ የንግስና ዘመን ጋር ቁርኝት እንዳላት ይጠቀሳል። የመናዊያን ንግስት ሳባ የመናዊት ነች ብለው ያምናሉ። ግብጾች የእኛ ናት እንደሚሉት ማለት ነው። ሳባ የመን ውስጥ ማርብ የተባለ ቦታ ቤተ-መንግስት አላት። ምክንያታቸው ይህ ብቻ ነው። አባቷ ማነው? እንዴት ንግስት ሆነች?... ምላሽ የላቸውም። ምሁሮቻቸውም





ሳባ ኢትዮጵያን አስተዳድራለች እንጂ ኢትዮጵያዊት አይደለችም ሲሉ ሽንጣቸውን ገትረው (ሽንጥ ይገተራል እንዴ?) ይከራከራሉ።

‹‹እምቢኝ!... ያባ ቢላዋ ልጅ! ለማን ተገዛንና በውጭ ንግስት ተዳደርን? አለም ያላወቀው ታሪክ አንቀበልም›› ስል ከብዙዎች ጋር ተከራክሬያለሁ። የመንን የእኛ ንጉሶች ማስተዳደራቸውን አውቃለሁ። እኛ በየመናዊያን ስለመተዳደራችን ግን ማን ተናገረና ያለመረጃ ልቀበል? ‹‹እምቢኝ!!!.. የአባት፣ አያቴን ታሪክ መድገም ቢያቅተኝ ጠብቄ እኖራለሁ›› እያለ ውስጤ ፋከራ ይሁን ቀረርቶ ብጤ እየሞካከረ ብዙ ጊዜ ተከራክሬያለሁ። እነሱን ለመርታት ከመሞከር ይልቅ ድንጋይ መፍለጥ ይቀላልና በእንግልጥል ትቼዋለሁ። ንግስት ሳባ በእነሱ ወይም በቅዱስ ቁርአን ላይ ‹‹ብልቂስ›› ስትባል በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ደግሞ ሳባ ትባላለች። ማክዳም መጠሪያዋ ነው አባቷ ንጉስ ተዋስያን እናቷ ኢስሜኒ ይባላሉ። ከክርስቶስ ልደት በፊት በ982 ዓ.ዓ ነው የነገሰችው።

ይህ ግን ለእነሱ አይዋጥም።

ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከ575ዓ.ም ጀምሮ ንጉስ አብርሃ ለ50 ዓመታት ልጆቹ ደግሞ 20 አመታት የመንን አስተዳድረዋል። በዚህ በተባለው ንጉስ አብርሃ ባስተዳደረበት the year of elephant ወቅት አሁን ያለችው ሰነዓ አቢሲኒያ ዋና ከተማ ሆና አገልግላለች። በዛ ዘመን የተገነቡ ቤቶች ዛሬ ባብ አል-የመን/የየመን በር/ በሚባለው አልድ(የቀድሞው ሰነዓ) አካባቢ አሉ። የየመን ዋና የቱሪስት መስህብ ነው። ከ1000 አመት በላይ ያስቆጠሩ ወደ 14000 የሚጠጉ ቤቶች አሉ።

የሆነስ ሆነና ንጉስ አብርሃ ከኢትዮጵያ መጥቶ የመንን እንዴት ሊያስተዳድር ቻለ? ይህ ለብዙዎቻችን መልስ ያላገኘ ጥያቄ ነበር። መልስ ለማግኘትም በየአቅጣጫው መረጃዎችን መቃኘት ግድ ብሎኛል። በእስልምና እምነት ዙሪያ ያሉ መጽሐፍት ማለትም በሀዲስም ጥሩ ተደርጎ ሰፍሯል።

ከተለያየ አቅጣጫ ባሰባሰብኩት መረጃ መሰረት አብረሃ ወደየመን ከመምጣቱ በፊት በኢትዮጵያ ያለው ንጉስ የጦር አበጋዝ ነው (ከፈለጋችሁ ጀኔራልም በሉት)። በወቅቱ ኢትዮጵያ ላይ የነበረው ንጉስ የትኛውም የመን ባገኘኋቸው መጽሀፍት ላይ ስሙ አልተጠቀሰም። አብርሃን ወደ የመን መላኩ አናዷቸው ወላ ስሙ አልገባ ብሏቸው ይሁን ሰፍሮ አላገኘሁትም። ግን በሌላ ‹‹የኢትዮጵያ ታሪክ›› በሚል ሁለት የፖላንድ ታሪክ ጸሀፊዎች የጻፉትን ትርጉም ላይ ‹‹..በአፄ ካሌብ ጊዜ እንደሆነ እና አብርሃ ለካሌብ ሲገብር እንደነበር›› ተጠቅሰዋል።

አብረሃ ወደየመን ከመምጣቱ በፊት ዙኑዋስ የየመን ንጉስ ነበር። በጣአትና ጥንቆላ የሚያምን እንደሆነም በሰፊው ይነገራል። ለህዝቡ እኔ ነኝ

ፈጣሪያችሁ የሚል ትምክህተኛም ነበር። ግብረአበር ባለስልጣኖቹም እንደ እሱው ትምክህተኞች ናቸው። ለንጉሱ የሚጠነቀል ሰው ነበር። በወቅቱ ለንጉሱ የሚጠነቀለው ሰው እድሜው ገፍቶ ሲያረጅ ለንጉስ የሚጠነቀል አንድ ወጣት ለማስልጠን ጥያቄ ያቀርባል። ንጉሱም አንድ ወጣት ይመርጣል። ወጣቱም ጥንቆላ ለመማር ሲመላለስ ከአንድ ክርስቲያን መነኩሴ ጋር ይገናኛሉ። እሱ ስለሚያምንበት ትክክለኛ ፈጣሪው እግዚአብሄር ያስተምረዋል። ለንጉሱ አልሰግድ በማለቱ ዙኑዋስ ልጁን ሊገለው ፈለገ። ደጋግሞ ሊያስገድለው ሞከረ። አልቻለም። ሰይፉን ቢሰነዝርበትም አልሆነለትም። አልገደለውም። ይህ ልጅ ንጉሱን እንዲህ ይለዋል፡- ‹‹ሕዝብ ሰብስበህ ይህ ልጅ በሚያምነው አምላክ ስም ብለህ ካልሆነ ልትገድለኝ አትችልም›› ንጉሡም 20.000 ሰው በተሰበሰበበት ‹‹በእሱ አምላክ›› ብሎ ገደለው። ሰዉ ሁሉ፣ ‹‹ፈጣሪያችን የእሱ ፈጣሪ ነው›› ብሎ አመነ። ንጉሱ ህዝቡን ጨፈጨፈ። በዚህን ጊዜ ያመለጠ አንድ ሰው ለሮማው ንጉስ ሄዶ ተናገረ። በወቅቱ ሀያል ከሚባሉት ንጉሶች የፋርስ፣ የሮማ፣ የሀበሻ ንጉሶች ነበሩ። ሮማ ለየመን ሩቅ በመሆኑ የሮማው ንጉሥ በቅርብ ላለው የሀበሻ ንጉስ ሄደህ ንገር ብሎ መልዕክት ጽፎ ሰደደው። እንደተባለውም አደረገ።

የሀበሻ ንጉስ አፄ ካሌብ አሸንፋችሁ የመን በእኛ እጅ ቁጥጥር ስር እንድትሆን ብሎ 70.000 ጦር አዘመተ። የዛን ጊዜ የንጉስ ወታደር መሪና አለቃ አሪያል ነበር። ምክትሉ ደግሞ አብረሃ።

ተዋግተውም አሸነፉ። ዙነዋስ የየመን ንጉስ ሸሽቶ ጠፋ። የመን በኢትዮጵያ እጅ ገባች። የጦሩ አዛዥ የነበረው አሪያል ንጉስ ሲሆን አብርሃም ምክትሉ ሆነ። ብዙ ኡለማዎች ምን ይላሉ አብርሃም ብልህ ነው በጦርነት ማንም የማያሸንፈው... በአነጋገሩም በሁሉ ነገሩም አንጎሉ ክፍት ነበር ይላሉ።

አሪያል ንጉሥ የሆነ ጊዜ ግን ህዝቡን መበደል፣ መጨፍጨፍና መዝረፍ ጀመረ። አብረሃ ‹‹ተው›› አለው። ሊሰማው አልቻለም። እንዲያውም እሱን አስሮ መግረፍ ስለፈለገ አብረሃም 70,000 ወታደሮቹን ይዞ ጫካ ገባ።

ጦርነቱን ህዝቡ ፈራ። በጦርነቱ ህዝቡ ሊያልቅ ሆነ። የኢትዮጵያም 70.000 ወታደር ሊያልቅ ሆነ። የንጉስ አሪያልም 70.000 ወታደር ሊያልቅ ሆነ። ለጦርነቱ 3 እና 4 ቀን ሲቀረው ብልሁ አብርሃ ለአሪያል መልዕክት ላከ። ‹‹አሪያል የየመን ንጉስ እኔና አንተ ለወንበሩ ነው የምንጣላው። ህዝቡ ያጠፋው ነገር የለም። ለሁለታችን ጸብ ህዝቡን ከምንፈጅ እዚህ በረሃ ውስጥ ህዝቡ እያየ፣ ወታደሩ እያየ በሰይፍ እኔና አንተ ብቻ እንፋለም። አንተ ከገደልከኝ ሁለቱንም ጦር ሰብስበህ ሀገሩን





ትመራለህ፤ እኔም ከገደልኩህ እንደዛው አደርጋለሁ። ለምን የመን ትበጥበጥ ሁለታችን ይዋጣልን›› ብሎ ላከበት። አሪያል በሰይፍ ሀይለኛ ነበርና ሀይሉን ተማምኖ በትዕቢት ‹‹አንተ ደግሞ እኔን...›› በማለት ተስማማ።

ሁለቱም እንደሚፋለሙ ህዝቡን አሳወቁ።

በማግስቱ ጠዋት ሁለቱም ሰይፍ ይዘው ወጡ። ፍልሚያ ጀመሩ። አሪያል በጣም ጠንካራ ሰው ነበር። ሀይሉም በረታ። አብረሃ ወደኋላ ማፈግፈግ ጀመረ። ተከትሎ አንድ ጊዜ መታው። የአብረሃ አፍንጫ ተቆረጠ። አብርሃ አሽረም የሚባለው ለዚያ ነው። አሽረም ማለት አፍንጫው ቆራጣ ማለት ነው። አፍንጫው ተቆርጦ ደም ሲወጣው አሪያል ግትር ብሎ በአሸናፊነት ስሜት ቆመ። አብረሃ በጣም ደኪ (ብልጥ) ነው። ተንከባሎ ተንከባሎ ወደ ቀኝ ወደ ግራ እያለ አሪያልን አንገቱን ቆርጦ ጣለው። አብርሃ አሽረም የየመን ንጉስ ሆነ።

የአሪያል በአብረሃ መገደልን የኢትዮጵያው ንጉስ ወሬ ሰማ። በጣም ተቆጣ። ‹‹እንዴት እኔ ንጉስ ያደረኩትን ሰው ይገድላል! እግዚአብሄርን የየመንን አፈር ሳልረግጥ እና አብረሃን ይገፔ ፀጉሩን ሳላጭ በህይወት አልኖርም..›› አለ። በዛን ጊዜ አንድ ሰው ጀግና የሚባለው ጠላቱን ማርኮ ፀጉሩን የላጨ እንደሆነ ነው።

አብርሃ ይህን ዛቻ ሰማ። በጣም በብልህነቱ የሚታወቀው አብርሃ አንድ ትልቅ ሰሀን አመጣ። አፈር ሞላበት። ከዛም ራሱን ላጩና በዛ አፈር ላይ አድርጎ ሶስት አራት ወታደሮች አስይዞ ‹‹ሂዱ ወደ ንጉሳችን አድርሱ። ንጉስ ሆይ እኔ አሪያልን የገደልኩት በአንተ ስም እየገዛ ህዝቡን ስለጨፈጨፈ ነው። የኢትዮጵያን ክብር ስላጉደፈ ነው። ህዝቡም በሙሉ ስለተቆጣና ስለተበጠበጠ ለአንተ ስም ብዬ ነው የገደልኩልህ። አሁን ህዝቡ በሰላም እየኖረ ነው። አንተ የእኔን ጸጉር ለመላጨት፣ የየመንን አፈር ለመርገጥ ብለህ አይደል የማልከው አፈሩም ይሄው እርገጥ ፀጉሬንም ራሴ ላጭቼዋለሁ አንተ አትድከም መሃላህ በዚህ ያልፋል›› የሚል መልዕክት ጨምሮ በደንብ እንዲያስረዱት ነግሮ ላከለት።

ለንጉሱ ሲነግሩት በጣም ተደነቀና ‹‹አብረሃ በጣም ብልህ ሰው ነው›› ብሎ ዝም አለ። አብረሃ ግን ልቡ አልተረጋጋም። ንጉሱ አዘናግቶ የቂም በቀል እርምጃ ሊወስድ ይችላል ብሎ በማሰብ ንጉሱን የሚያስደስት ነገር ለመስራት ፈለገ። ከዚያም በየመን አንድ ትልቅ ቤተክርስቲያን አሰራ። አሰራና አዋጅ አወጀ። ‹‹ማንኛውም ሰው በእኔ ግዛት ያለ ሁሉ እዚህ ቤተክርስቲያን ሀጅ ማድረግ አለበት። ሀይማኖታችሁን ቀይሩ ማለት

ሳይሆን መካ ከመሄድ በየአመቱ እዚህ ዚያራ ማድረግ አለባችሁ›› ብሎ አዘዘ፡፡

የህይወቱ ህልፈትም ከዚሁ ግትር አቋሙ ጋር የተያያዘ ነው ይባላል፡፡ ይሄ ቤተክርስቲያን (መስጅድ) አሁንም ባብል የመን የሚባለው አካባቢ አለ፡፡ ዘመኑ የዝሆን ዘመን የተባለበት እና ለህይወቱም መጥፋት ምክንያት የሆነው በዚሁ ሰበብ መካ በዝሆን ከመዝመቱ ጋር የተያያዘ ነው ይባላል፡፡ አብረሃ ለ50፣ ኢዛና እና ቴዛና የተባሉ ልጆቹ ደግሞ ለሀያ አመታት የመንን አስተዳድረዋል፡፡

ከእስር ቤት በወጣሁ ማግስት በአቢሲኒያ ዋና ከተማነት የተቆረቆረች ከተማ ነች ተብሎ ሲወራ የሰማሁት ባብ አል-የመንን ለማየት ጓጓሁ፡፡ ካረፍኩበት ቤት ወጣሁና ታክሲ ፍለጋ ገባሁ፡፡ ብጠብቅ..ብጠብቅ ባብ አል-የመን የሚል፣ የሚጣራ አጣሁኝ፡፡ ዝም ብዬ ወደቤት ከምመለስ ‹‹አልባብ አልባብ..›› በሚለው ታክሲ ላይ ገባሁ፡፡ ሄጄ ዞር ዞር ለማለትና በመጣሁበት አይነት ታክሲ ልመለስ አስቤ ነው፡፡ አሮጌ ቤቶች የበዙበት ቦታ ሲሆን ግርግሩ መርካቶን ያስታውሳል፡፡ ስለፈራሁ ብዙም አልዞርኩም፡፡ የሆነ ኢትዮጵያዊ አየሁና በአማርኛ ሳናግረው በዓረብኛ፣ ‹‹ኤሽ!... ዔሽትጉል..›› (ምን ትላለህ?) ተናድጄ ዞሬ መንገዴን ቀጠልኩ፡፡

ከኋላ ከተል ብሎ ‹‹አኔ አማረኛ አይችልም በዙ..›› አለኝ እየተንተባተበ፡፡ በህጻንነቱ ወደየመን የመጣ ትውልድ ኢትዮጵያዊ እንደሆነና አማርኛ ብዙ እንደማይችል ነገረኝ፡፡ ፋአድ ይባላል፡፡ ወደ ማረፊያዬ የሚወስደኝን ታክሲ አስያዘኝ፡፡

ትንሽ ቆይቶ ጆሲን ሳገኘው «ባብ አል-የመን የሚባለውን ቦታ አሳየኝ» አልኩት፡፡ ይዞኝ ሄደ፡፡ ‹‹ይሄንማ ቅድም መጥቼ አየሁት እኮ አልባብ አልባብ ሲሉ ነበር የገባሁት›› አልኩት፡፡ በትርጉም መታለሌን ነገረኝ፡፡ አልባብ የሚሉት ሲያሳጥሩት ነው፡፡ (አልባብ በር ማለት ነው፣ ባብ አል-የመን ደግሞ የየመን በር ማለት ነበር..) አዙሮ በደንብ አሳየኝ፡፡ የቤቶቹ አገነባብ ልዩ ነው፡፡ ሰነዓ ከተማ ውስጥ ያየኋቸው ጥቁር ሰዎች አብርሃ ያኔ ያመጣቸው አገልጋዮች ናቸው አሉኝ፡፡ በጣም የመብት ረገጣ የሚደረግባቸው ናቸው፡፡

ከእስር ቤት ወጥቼ ያለውን ኑሮ ልለምደው ከበደኝ፡፡ ለነገሩ ሰነዓ ከተማ ውስጥ ያለውም ኢትዮጵያዊ ስደተኛ ቢሆን ጣራውን ሰማይ ያደረገ እስር ቤት ውስጥ እንዳለ ነው የተረዳሁት፡፡ በእርግጥ የየመን መንግስት ለስደተኛው ምቹ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ችግሩ ኢኮኖሚያቸውና የሰዉ ለውጭ ዜጋ በተለይ ለሀበሻ ያለው ጥላቻ ነው፡፡ ያም ቢሆን ህዝቡ በሙሉ አይደለም፡፡ ጥሩዎችም ሞልተዋል፡፡ ህይወት ሁሉ አርቲፊሻል ነው፡፡





ያውም ያልተብለጨለጨ የተሙለጨለጨ፡፡ የማያጓጓ አስጠሊታ አርቲፊሻል ወገን ወገኑን ሲሸጥ የሚታይበት ጣራውን ሰማይ ያደረገ እስር ቤት፡፡ ከብዙ ነዋሪዎች ጋር ያደረኩት ቃለ-ምልልስም ቢሆን የሚያደላው ባዶ ኑሮ፣ የችግር ጎተራ ሆኖ መኖርን፣ ተስፋ ቢስነትን የሰነቀ ህይወት ነው የሚያሳየው፡፡

ኢትዮጵያዊያን ወደየመን የሚሰደዱት በሁለት መንገድ ነው፡፡ በአየር እና በባህር፡፡ በሶማሊያ ወይም በጅቡቲ አድርገው በባህር በህገ-ወጥ መንገድ የሚገቡት በዛ ያሉት ወደሳዑዲ አረቢያ ለማለፍ ነው ፍላጎታቸው፡፡ ከነዚህ ውስጥ ደግሞ ባልሆነ ተስፋ እና በደላላዎች ወሬ ተታለው፣ ሰው ሲያደርግ ስላዩ ብቻ ሳዑዲ አረቢያን ብር የሚታፈስበት የተስፋ ምድር አድርገው ስደት የወጡ ይበዛሉ፡፡ ባህር ተሻግረው ወደ ሳዑዲ ተጓዦች ዘጠና ስምንት በመቶ ግብርና ጥለው ስደት የሚወጡ የገጠር ልጆች ናቸው፡፡ አብዛኛው የሸዋ፣ የአርሲ፣ የባሌ፣ የሐረር፣ የትግራይ የወሎ ልጆች ናቸው፡፡ አካሄዳቸው ሳዑዲ አረቢያን ችግር የሚቀረፍባት ገንዘብ የሚታፈስባት አድርገው በማሰብ ነው፡፡ በእርግጥም ሀሰተኛ ደላሎች የነገሯቸው ነው፡፡ በዚህ መንገድ ሄደው ተይዘው ሀገር የሚገቡ ተመልሰው በባህር ለመምጣት ገንዘብ ሲያስፈልጋቸው ሲኦሉን ገነት አድርገው ይደስኩራሉ፡፡ እነሱም በተራቸው ሌላውን አታለው ዋሽተው እሳት ይከታሉ፡፡

በአየር የሚሰደዱትን ስናይ ደግሞ አብዛኞቹ የሚመጡት ለቤት ሰራተኛነት ቢሆንም የሚገቡበት ቪዛ የአንድ ወር የጉብኝት ከመሆኑ አንፃር መኖሪያ ፍቃድ ሳያስሩላቸው ሁለት አመት አሰርተው መልሰው ለደላላ የሚሰጡዋቸው ሞልተዋል፡፡ ለኮንትራት ስራ ከሚመጡት ውስጥ በብዛት ከአዲስ አበባ የሳሪስን ያህል ሪከርድ የያዘ የለም፡፡ ዋናዋ ደላላ የሳሪስ ሰው በመሆኗ መሰለኝ፡፡ ‹‹የሳሪስ ሰዎች እናቶቻቸው ብቻ ነው የቀሩት..›› ብለው ሲቀልዱ ሁሉ ሰምቻለሁ፡፡ ቀልድ ስል አንዲት የሳሪስ ልጅ ጠቅልላ ወደ ኢትዮጵያ ስትገባ የነገረችኝን ቀልድ ላካፍላችሁ፡፡ ገና ኤርፖርት ስደርስ ቤተሰቦቼ ልጅ አልያዝሽም? አሉኝ፡፡ ግራ ገብቶኝ ‹‹የምን ልጅ›› አልኳቸው፡፡ ወዲያው ተደዋወሉ፡፡ ነገሩ የገባኝ ሰፈር ስደርስ ነው በእቅፍ አበባ የተቀበሉኝ መንገዱ ዳርና ዳር ተሰልፈው ነበር፡፡ ከአረብ ሀገር ሻንጣ እንጂ ልጅ ይዛ አልመጣችም ተብሎ እንኳን ደስ ያለሽ.. ባዩ ብዛት…››

ይቺ ቀልድ ልብ መባል ያለባት ነች፡፡ ከቀልድነቷ በስተጀርባ ያደፈጠ፣ እውነታን ያዘለ መልእክት አለ፡፡ ኑሮን ለማሸነፍ.. ብላ ስደት ሄዳ ልጅ ጨምራ ወደ ሀገሯ የምትመለሰውን ሴት ቤቱ ይቁጠረው ተብሎ እንዲሁ በዋዛ የሚታለፍ አይደለም፡፡ ገንዘብ ይልካሉ፣ ችግር ይቀርፋሉ

ተብሎ ተስፋ የተጣለባቸው በርካታ ሴቶች በአስገድዶ መድፈር አለያም ለገንዘብ ሲባል በተደረገ ግንኙነት ሳይፈልጉ ፀንሰው ወደ ሀገር ቤት ልጅ የላኩ ሞልተዋል። እዚህም ታቅፈው የቀሩ እህቶቻችን ቁጥር ያስደነግጣል።

በእርግጥ ከሌሎች ሁኔታዎች አንፃር፣ ከነፃነት አንፃር.. ከሁሉም አረብ ሀገራት የመን የተሻለ ይመስለኛል። ለሴቶቹ ስቃዩ፣ የሰሩበትን መከልከሉ፣ መታሰር፣ መደብደቡ፣ መደፈሩ... ይቀንሳል እንጂ የለም ማለት አይደለም።

የመን ውስጥ ከፖሊስ ጋር አዩኝ አላዩኝ ድብብቆሽ የለም። ፖሊስ ሆኖ የሚያባርርህ ከእጅ ወደ አፍ የማይባል መሀል ላይ ተንጠልጥሎ የቀረ ኑሮህ ነው። ተስፋ የሌለው ከፍ ዝቅ የማይል በድግግሞሽ የተሞላ ህይወት ይኖራል። ይኖራል!! እየኖሩ መኖርን የሚጠራጠሩበት የመን ውስጥ ለመኖር በባህር ያን ሁሉ ስቃይ መብላት ያሳዝናል። 10 እና 20 ዓመት ሰርተው ጠብ ያላለላቸው፣ ሲታመሙ መታከሚያ አዋጡልኝ ተለምኖ የሚታከሙበት ህይወት አለ። ለመመለስ መሳፈሪያ ተለምኖ፣ እቁብ ተሰብስቦ.. ተበድሮ የመን የሚገባው ቁጥር ትንሽ አይደለም። ከእጅ አይሻል.. ኑሮ ለመግፋት ክብርን አጥቶ ተዋርዶ በሰው ሀገር መንከራተት። የዛኑ ያህል እድልና አጋጣሚ የቀናቸው፣ የተሳካላቸው አሉ።

ከህዝቡ ጋር ተቀላቅዬ መኖር ስጀምር የታዘብኩት ነገር የመን ውስጥ በተለይ ለወንዶች ስራ የለም። /የለም እያሉ ስለሚያሳብቡ ነው የለም ያልኩት/ ፈፅሞ የለም ሳይሆን ለወንድ ልጅ ስራ ማግኘት ከባድ ነው። ክፍያው ምንም ነው። ወር ተሰርቶ የሚከፈለው ለ5 ቀን ቀለብ የማይሆን ትንሽ ገንዘብ ነው። ለሴቶች የተሻለ ስለሚከፈል ሙጥኝ እነሱ ላይ የሚሉ ሞልተዋል። በበኩሌ እነዚህን ‹‹የታዘሉ ወንዶች›› ብያቸዋለሁ። ሰርቶ የሰው እጅ ከመጠበቅ የወጣ ሰው ላይ ያልታዘለ፣ ሸክም ያልሆነ ሀሞተ ኮስታራ ወንድም ሞልቷል። ባይተርፈውም ካለው ላይ የሚረዳ፣ ሲቀፍሉት ለጫት የሚሰጥ ሰርቶ ያገኘም አለ። ይበልጥ ጎብዘው ሰርተው የተለወጡ ሀብት ንብረት ያፈሩም አሉ። በህገ-ወጥ ስራም ተሳትፈው ጥሩ መኖር የቻሉም ማየት ተችሏል።

ጥቂት ሀበሾች በሱስ የተጠመዱ ለጫት፣ ለሲጋራ የዕለት ወጪ ሲሯሯጡ ያገኙትን ሲለምኑ የሚውሉ አሉ። ጥቂቶች ደግሞ ሴት ወንዱ ጫት ወጥቀው ጉንጫቸውን አሳብጠው ሲቅሙ (ስንቅም)፣ ሺሻ ለማጨስ ሲጋፉ... ሲጨቃጨቁ ማየት በየተሄደበት የተለመደ ነው። በሺሻ በኩል ሴቶች እህቶቻችን የበለጠውን ድርሻ ይይዛሉ፣ ኩሽናውን አፋቸው ውስጥ አርገው ጭስ ምገው ጭስ ሲተፉ የከሰል ባቡር የሚባለውን ይመስላሉ። ከሱሰኝነታቸው የተነሳ የሺሻ ማጨሻውን እቃ ይዘው በተጠሩበት ቦታ ሁሉ የሚዞሩ አሉ። ልክ መድረክ ሲያገኙ የሺሻ እቃቸውን አውጥተው





ገጣጥመው፣ እሳት ፈላልገው እንደማይክራፎን አፋቸው ላይ ለጉመው በጭስ ጉም ተገልለው ይውላሉ። በኑሮ መቃጠላቸውን ልብ ሳይሉ (ለመርሳት) ሌላ መቃጠያ የሚሹ ይመስላሉ። ማረራቸውን ዘግይተው ያውቁታል። ሀገር መግቢያ፣ መታከሚያ ሲያጡ ይባንናሉ። እድሜ ማምለጡን፣ ሳይነጋ መጨለሙን ሲረዱ ያኔ በጸጸት እሳት ይቃጠላሉ።

ለመከራ የተፈጠሩ የሚመስሉት እህቶቻችን የሚሸከሙት የአረቡን ክፋት ብቻ አይደለም። የሚሰቃዩት በአረብና በባዕድ ወንድ ብቻ አይደለም። በእኛውም ወገኔ ባሉትም ነው። የነዓለም ደቻሳን በደል አይተን በቁጭት የምንብሰለሰል እኛም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሴቶቻችን ሸክም ነን። የተቸገረ ቤተሰብ ከጀርባዋ የተሸከመች ሴት ለቤተሰቧ ትጨነቃለች። ስደት አልሰምር ያላት ሴት ስለራሷ ትጨነቃለች። በዚህ ላይ ደግሞ የስደቱ የውሸት ሕይወቱ፣ የውሸት ፍቅሩ.. የወንዱ ቅጥፈት የለፋችበትን ለመብላት፣ ጊዜ ማሳለፊያ ለማድረግ፣ ተገፍታ ተገርዳ ያመጣችውን ለመንጠቅ የምላስ ጠለፋውም ይደፋታል። ወገኗም ይገፋታል። መንግስትም ይከፋባታል። በኤምባሲ፣ በኮሚኒቲ፣ በየልማት ማህበሩ... በሰበብ አስባቡ ክፈሉ፣ አዋጡ ነው። ፍቅር የመሰላት በአርቲፊሻል ምላስ የተሳለ ህይወትም ብን ብሎ ጉም ይሆንባታል። ይህን የመን ሰነዓ ውስጥ የታዘብኩት እውነታ ነው። በኋላ ግን ስረዳ በአብዛኛው አረብ ሀገር ያለ ህይወት ተመሳሳይ ነው።

ጥቂቶች በጣም ጥቂቶች ወንዱ እንደቅልብ ስንጋ ተኝቶ ሲገላበጥ ሴቷ ሁለት ሶስት ቦታ ሰርታ መቀለብ ብቻ ሳይሆን የጫት ሲጋራውንም ስትለግሰው ይታያል። አልፎ ተርፎ ገላዋን ሽጣ ይሆነኛል ብላ ራሷን አርክሳ ለሁለተኛ ዙር ከእሱ ጋር ልትረክስ አብልታ፣ አጠጥታ፣ አስቅማ አስጭሳ ትኖራለች። በምላስ ተታላ በወገኗ ተሸውዳ ትኖራለች። ይሄን ግን እየተታለሉ ብቻ አይደለም የሚፈጽሙት። ቢሆንም ግን ጊዜ ለመግፊያ ተብሎ ደልሎ እድሜዋንም የለፋችበትንም አባክና በኋላ ዞር በይ የምንላት ወገኖቿ ነገር ሲታከልባት ሕይወቷን የከፋ ያደርገዋል። ከክፋት ደግነት እንደሚቀል የምናውቅ እኛ ወንድሞቿ ስንጨመርበት ደግሞ ይታያችሁ ምን ያህል ቅስም እንደሚሰብር።

ከሁሉም ከሁሉም በዓረቡ ዓለም ለሴቶች ከጾታዊ ጥቃት ቀጥሎ አሁን አሁን ጎልቶ እየተስተዋለ ያለው አሳሳቢ ጉዳይ ግድያ ነው። እስቲ ለምሳሌ ‹‹አል-ወሳይቂያ›› የተባለ የመን ውስጥ የሚታተም አንድ ጋዜጣ ማርች 2012 ዓ.ም ላይ በአንዲት ኢትዮጵያዊት ላይ የተደረገ ግድያን ምስጢር አጋልጧል። ‹‹እስከህልፈተ-ህይወት ድረስ የሚሰቃዩ ኢትዮጵያዊያን በሰነዓ›› በሚል ርዕስ ምንጩ የየመን ሁማንራይት

ሚኒስቴር እንደሆነ ጠቅሶ ዘገባውን ለንባብ ያበቃውን ጋዜጣ ትርጉም እነሆ፡-

በሁማንራይት መግለጫ ላይ ይፋ እንደሆነው አንዲት ሌይላ የተባለች ኢትዮጵያዊት በምትሰራባቸው ሰዎች እስከሞት የደረሰ ስቃይ እንደተፈፀመባት ታወቀ። በአሰሪዎቿ ተሰቃይታ ለሞት የተዳረገችው የ25 አመት ወጣት እና የአንድ ልጅ እናት የሆነችው ኢትዮጵያዊት ጉዳይ አሁንም አወዛጋቢ እንደሆነ ነው። ሌላው ቀርቶ ከጁን 21/ 2011 ጀምሮ ሬሳዋ እንዳልተቀበረ፣ ሆስፒታል ፍሪጅ ውስጥ እንደሚገኝ ጭምር ጋዜጣው ዘግቧል። (አሁን በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ መረጃ የለኝም።)

ሶስት ሆነው አሰቃይተው እንደገደሏት እና ኢ-ሰብአዊ ድርጊት እንደተፈፀመባት ሬሳውን የመረመረው ዶክተር ገልፀዋል። እንደ ዶክተሩ ገለፃ ከሆነ ገላዋ ላይ ብዙ ቦታ የዱላ ምልክት መታየቱ እና በተለይ ደግሞ የራስ ቅሏ ተሰብሮ መገኘቱ ከፍተኛ ድብደባ እንደደረሰባት ነው የሚያሳየው። ሰውነቷ ላይ ብዙ ቦታ በእሳት አቃጥለዋታል። ፊቷ፣ ወገቧ፣ እግሯ፣ ሆዷ እና በተለያዩ አካላቷ ላይ የተገኘው ጠባሳ ብረት አግለውና በሲጋራ ጭምር እንዳቃጠሏት ያሳያል። በዚህም በጣም ከፍተኛ ስቃይ እንዳሳለፈች ዶክተሩ ቢገልፅም የሰነዓ ሰሜን ቀጠና ፍርድ ቤት ለሶስቱ ተከሳሾች የሰጠው ውሳኔ እጅግ አሳዛኝ ነው። ምንም ሳይባል በዳኛ ውሳኔ በነፃ ተለቀዋል። ከሶስቱ አንዱ በእድሜ ወጣት የሆነው አባቱ ዳኛ በመሆናቸው ብቻ ‹‹በሽተኛ ነው›› ተብሎ በሀሰት ከእስር ነፃ እንዲወጣ ሲደረግ፣ ሁለቱ ላይ ደግሞ የቀረበው መረጃ በቂ ስላልሆነ በሚል በዳኛው ውሳኔ በነፃ ተለቀዋል።

ይህን ሁኔታ ይፋ ያደረገችው፣ በሰብዓዊ መብት የወንድማማቾች ማህበር ሊቀመንበር የሆነችው አመልባሻ ነች። ክሱን እየተከታተለች ያለችው ፋይዛ ሱሌማን ስትሆን እስከ መጨረሻውም እንደምትከታተልና ወንጀለኞቹ ላይ እንዲፈረድባቸው የምትፈልግ በመሆኑ የተከሳሾች ቤተሰብ እያስፈራሯት እንደሆነ ስለጉዳዩ በፌስ ቡክ አመልባሻ ገልፃለች። የኢትዮጵያዊቷ ሟች ሌይላ እህት ሰብዓዊ መብት ውስጥ የምትሰራው ፋይዛ ሱሌማን ቤት ሰራተኛ ነች። ፋይዛ ወንጀሉን ካወቀች በኋላ ወንጀሉን ፈፃሚዎች የፍርድ ቅጣት እንዲያገኙ ጉዳዩን ፍ/ቤት እየተመላለሰች ትከታተላለች። በ25 አመቷ ኢትዮጵያዊት ነፍስ ግድያ የተከሰሱት ሰዎች ቤተሰብ 5.000 ዶላር ካሳ ሰጥተው ከሳሾች ክሱን እንዲሰርዙ ተማፅነዋል። የሟች እህትና አሰሪዋ በዚህ ስላልተስማሙ በድርድር 12.000 ዶላር ድረስ ከፍ አድርገውላቸዋል። በዚህም ቢሆን ላለመስማማት የቆረጠችውና ፍትህ የናፈቀችው ፋይዛ በቤተሰቦቿ በኩል ማስፈራሪያ እየደረሳት እንደሆን አመልባሻ ገልፃለች›› ሲል ጋዜጣው ዘገባውን አጠናቋል።

እንግዲህ እህቶቻችን በየቤቱ እየተገደሉ ተከራካሪ እየጠፋ ነው። ተከራካሪ ማጣት ብቻ ሳይሆን ሬሳቸውም በየፍሪጅ ውስጥ እየቀረ ነው።





የሌይላም ሞት ቢሆን እህቷ በመኖሯ እና የምትሰራባት ሴት የመን ሰብዓዊ መብት ሚኒስቴር ውስጥ ስለምትሰራ ነው ተከራካሪ ያገኘችው። ከዚህ ጋር በተመሳሰለ መልኩ የተከሰተ ሁኔታ የየመን ታይምስ ጋዜጣ ሪፖርተር የነበረ እና በአሁኑ ሰዓት የቢቢሲ አረቢያ ሪፖርተር የሆነው መሀዲ እንደገጠመው ነግሮኛል። የመን ታይምስ ላይ እየሰራ ሳለ ስለአፄ ኃይለስላሴ ታሪክ ይጽፋል። የኢትዮጵያ ኤምባሲ ደግሞ ወቀሳ ለጋዜጣው አዘጋጅ ይልካሉ። ኤምባሲ ሄዶ ‹‹ስህተት ካለ እርማት ልሰጥ እችላለሁ። አለበለዚያ ለምን እኛ የማንፈልገው ነገር ተጻፈ ማለት አትችሉም። ያን ማለት ቦታችሁ አይደለም። የለመዳችሁበት የሀገራችሁን ፕሬስ አፍኑ። እኛ ጋ ነጻ ነው›› ብሎ ተነጋግሮ ይወጣል። ከዚያም ቀጥታ እህቱ ጋ ይሄዳል። ስለውሎው ሲያወራ ሰራተኛዋ ሰማች። ‹‹ኢትዮጵያ ኤምባሲ የምታውቃቸው ከሆነ እባክህ ችግር አለብን ንገርልን›› አለችው። ታሪኩ..

‹‹...አንድ ከንቲባ ቤት የምትሰራ ኢትዮጵያዊ ሰውዬው ሌላ ቦታ ሲሳፈር ልጆቹ ጓደኞቻቸውን ሰብስበው ደፈሩዋት። አረገዘች። ስታረግዝ እንዳይታወቅባቸው ገደሉዋት ....›› ይህን ታሪክ የምትነግረው የሟች የአጎቷ ልጅ ጓደኛ ፍፁም ናት። ሄደው ኤምባሲም መንገር ፈሩ። ለካ በእርግጥም ያስፈራ ነበር። የአጎትየዋ ልጅ እንድትሄድ አደረግን። ምንም ማድረግ አንችልም ተባለች። ኤምባሲው ራሱ ፈራ። የሚገርመው ነገር ሰውየው በስልጣኑ በጣም የሚፈራ ነው። ወደ ህግ ተሄዶ የልጅቷ ጠበቃ በጎ አድራጎት ሙሀሚየን (በነጻ ጥብቅና የሚያገለግሉ) ነበር። እሱም ፈራ። መረጃ እንኳን ሊሰጡኝ ፈሩ። ክሱ እንዲቆም ለልጅቷ ቤተሰቦች በኤምባሲ(በአምባሳደሩ) በኩል ካሳ ተከፍሎ ፋይሉ ተዘጋ። ይሄን የመሳሰሉ የበርካታዎች ሞት ሰሚ እና ተከራካሪ በማጣቱ ተድበስብሶ ቀርቷል። እውነታውን ግን አንድ ቀን መውጣቱ አይቀርም. . .

# - 12 -

# ጋዜጠኛ ዳንኤል ገዛኸኝ

አለም ፈርቶ አለም ርዶ
ቃሉን ሰምቶ ተርገድግዶ
ስምንተኛው ሺህ የተባለው
ስንት ኖረን ስንት ቀረው?

ለምን ተሰደድኩኝ? ለምን እንሰደዳለን? ብለን ብንጠይቅ አይነቱ፣ ምክንያቱ፣ ሰበቡ.. የሚለጠፍለት ታፔላ ብዙ ነው፡፡ ሊጠቀስ የሚችል የማይችል..ብዙ ብዙ ተዘርዝሮ የማያልቅ ምክንያት አለን፡፡ አንድ ሺህ ታፔላ ልንለጥፍለት እንችላለን፡፡ ብንፈልግ አንድ ሚሊዮን ሰበቦች እንደረድራለን፡፡ እውነትም ውሸትም ሊሆን ይችላል፡፡ ግን እያንዳንዱ የራሱ የሆነ እውነታ የራሱ የሆነ ምልከታ አለው፡፡ ሚዛን ቢደፋም ባይደፋም ምክንያቱን እንደ ምክንያትነት ቆጥሮ ራሱን አሳምኖ ስደት ይወጣል፡፡ ራስን ከማሳመን በላይ ምን አለ?

ምንም፡፡

እያንዳንዳችን የራሳችን ጌቶች ለራሳችን፤ በራሳችን ላይ ወሳኞች ነን፡፡ ይሄ ተፈጥሯዊ እሳቤ ብልጭ የሚል ነቁጥ ንጣቢ ነው፡፡ ራሳችን ለራሳችን ጌቶች እንዳንሆን በራሳችን ጉዳይ ወሳኞች እንዳንሆን የሚያደርጉ ከራስህ በላይ እናውቅልሀለን የሚሉ ገዢዎች ይኖሩናል፡፡ አንተ ለምን የሚል ጥያቄ ካነሳህ ወይም መብታችን ነው ካልህ ባልዋልክበት ወንጅለው በአደባባይ ወንድምህን አስመስክረው ይቀጡሀል፡፡ የዚህ ገፈቱ ተጣብቶን ከትውልድ ትውልድ የዘለቀ ቢሆንም ከ1966 ወዲህ ግን እጅግ ከፍቷል፡፡





አብዮት ልጆቿን ትበላለች ብለው አራስ ድመት ሆነው አንድ ትውልድ ቅርጥፍ አድርገው በሉ፡፡ የስደት ታሪካችን «እልልል!» ተብሎለት ይነገር በአዋጅን እስከትሎ በጉልህ ተጻፈ፡፡ ሳይፈዝ፣ ሳይፋቅ የተጻፈ ይመስል ይባስ እየሞቀ፣ እየደመቀ፣ እየፈካ፣ እየበዛ...መጣ፡፡

አሁን ደግሞ በዚህ የኢንፎርሜሽን የግንኙነት ዘመን የገዛ ሃሳብህን..አትግለጽ፣ የገዛ ጽሁፍህን አትጫር ትባላለህ፣ ትባያለሽ፣ እንባላለን፡፡ እነሱ የጻፉትን፣ የሰፉትን ግን እንድትቃወም እንኳን ላይፈቀደልህ ሁሉ ይችላል፡፡ ደሞም አይፈቀድም፡፡ ተናገር ተብለህ ንግግርህ ተመዝኖ፣ ብዕርህ ተገድቦ፣ ልሳንህ ተመርምሮ በመናገር..በመጻፍ መብትህ ተወንጅለህ ትሣሰራለህ፡፡ እንሣሰራለን፡፡

ስንቶች ሞቱ? ስንቶች ቆሰሉ? ስንቶች ታሰረን፣ ተደበደብን.. ስንቶችስ ሀገር ጥለን ተሰደድን? ማንስ ይሄን ያህል ማለት ይችላል? ተሰደናል..ተሰደናል..ስደት አይነቱ ብዙ ምክንያቱ ተቆጥሮ የማያልቅ... ድህነት፣ ስራ አጥነት፣ የህዝብ አለመረጋጋት፣ የፖለቲካ ችግር፣ የእንትን ችግር፣ የችግሮች..ችግር...፣ ማለቂያ የሌለው ችግር..ፈርጀ ብዙ ችግር... ችግር፡፡ የሁኔታዎች ሁሉ ሁኔታ ያሰደደናል፡፡ በሰበብ..ያለሰበብ ተሰደናል፣ ገና እየተሰደድንም ነው፡፡ ችግራችን ፈርጁ በዝቶ ለመከራ የተፈጠርን እስኪመስለን ገፈቱን ያላጣጣመ ኢትዮጵያዊ የለም፡፡

ጦርነት፣ ስደት፣ ርሀብ...በታሪካችን ውስጥ ጉልህ ስፍራ አላቸው፡፡ የእዚህ መጽሀፍ አሁን እያነሳሁት ያለሁትም እስከፊው ስደታችንን ነው፡፡ በስደት መነሻ አላማም ከስደት አስከፊ ገፅታዎች ቁንፅሏን ማሳየት ነው፡፡ እኔ ወደ ወደ የመን ሲመጣ ካለው ችግር ጥቂቱን እነሆ ለማለት ነው፡፡ እኔ ወደ የመን ተከትለውኝ የተሰደዱ ሁለት የነፃ-ፕሬስ አባሎች፣ ተሰደድኩበት የመን ተከትለውኝ የተሰደዱ ሁለት የነፃ-ፕሬስ አባሎች፣ ዳንኤል ገዛኸኝ እና ታምራት ሰርቤላ፣ ከአደን ሰነዓ ድረስ መጥተው የጠየቁኝ ጊዜ የተሰማኝ ደስታ ወደር የለውም፡፡ ጠቅልለው ኑሮ በሰነዓ ካደረጉ በኋላ ቀጠሮ ይዘን ብዙ ነገሮችን አወራን፡፡ በመቅረጸ ድምጼ አገዛ ከጋዜጠኛ ዳንኤል ገዛኸኝ ጋር ያወራነውን በብዕርኛ ልመንዝረው፣ ልለውጠውና ለእናንተ ላውራችሁ፡፡ አብላሉት፣ አጣጥሙት፡፡

«አንድ መጽሀፍ ለማዘጋጀት እስቤ አንዳንድ ነገሮችን እያሰባሰብኩ ስለሆነ የእናንተንም የጉዞ ሂደት አሳዛኝ ነበር እና በዛ ዙሪያ ብናወራ ምን ይመስልሀል?» አልኩት፡፡

«በመጀመሪያ ደረጃ ይህን መጽሐፍ ለማዘጋጀት ማሰብህ በጣም ትልቅ ሀሳብ ነው፡፡ ማንም ያልሞከረው ድንቅ ሀሳብ እንደሆነ እንድታውቅ እፈልጋለሁ፡፡ የተሻለ ሶስተኛ ሀገር ሲሄዱ እንጂ እንዲህ እንዳንተ ሁለተኛ

ሀገር ላይ ሆነው አላሳተሙም:: በተለይ አንተ በስደተኛው ዙሪያ በመሆኑ ያዘጋጀኸው..›› ብሎ አበረታታኝ:: ምስጋናዬ ድጋሚ ይድረሰው::

ዳንኤል ስለጉዞ ታሪኩ ሲያወራኝ «ህዳር 20 ቀን 1998 ዓ.ም ልዩ የትዝታ ቀን ነው» ብሎ ነው የጀመረው:: ለምን ይሆን? ማንም ሰው ቢሆን በህይወቱ ጉልህ ሥፍራ የሚሰጣት ቀን አለችው:: በመጥፎም ይሁን በጥሩ:: ንግግሩን ሲቀጥል..የስደትን ሀሁ ለመቅመስ ጨለማና ብርሃን በፈረቃ ሊለዋወጡ በሚደራደሩበት ወቅት ላይ እኔን እና ጓደኛዬ ታምራት አዲስ አበባ አውቶቡስ ተራ ተገኝተናል:: ለሰዉ ነግቶ የዕለት ተግባሩን ሊከውን ቢሆንም ለእኛ ጨልሞ የስደትን ገፈት ልንቀምስ ነው:: ምንም መረጃ ሳንይዝ ወደ ጅጅጋ ልናመራ ተዘጋጅተናል:: መረጃ ለማግኘት አንተ ቤተሰቦች ጋ ሁሉ ሄደናል:: ምንም እንደማያውቁ ነገሩኝ::[10] ፈጣሪ ይርዳን ብለን ተነሳን:: በፍጥነት መጓዝ፣ መሸሽ ለፈለገ የእኔ አይነት የአውቶቡሱ ጉዞ በጣም አዝጋሚ ነበር:: በመሀል በመሀል ሀሳቤ መሀል ስንቅር..ውትፍ የሚለው ምንም አይነት መረጃ እጄ ላይ አለመኖሩ ነው::

መንገዱን የተማርኩባት፣ ያደኩባት፣ ሙቀቷን ሞቄ፣ አቧራዋን አቡንኜ፣ ቋንቋዋን አውርቼ..ያደኩባት ጅጅጋ ድረስ ነው የማውቀው:: ጠረኗ ከአፍንጫዬ ትዝታዋ ከህሊናዬ ያልጠፋው ጅጅጋን ጥዬ ወደ አዲስ አበባ የተሰደድኩት መቼ ነው? አዎ እኛ በአብዛኛው ስደት የምናውቀው ከክፍለ ሀገር ወደ ክ/ሀገር ወይም ከተማ ነው:: አሁን መረር፣ ከምጠጥ ያለው ሁኔታ ገጥሞኝ ሀገር ጥዬ እየተሰደድኩ ነው:: አዎ እየሄድን ነው:: ሌሎችም በሌላ አቅጣጫ በዚህ ሰዓት ስንቱ ይኮበልላል? በቀን ስንት መቶዎች ይሰደዳሉ? ሀሳቤ ሁሉን ይነካካል::

መረጃ የሚሰጠኝ ሠው ስፈልግ አንድ ሁለት ልጆች ይዞ የሚሄድ ሰው አጓጓዥ መሆኑን በሁኔታው ተረዳሁ:: ቀስ ብዬ ተጠጋሁት:: ለምሳ ከመኪና በወረድንበት ሰዓት ጋበዝነው:: እንደገመትኩትም ልጆቹን ይዞ ወደ ሶማሊያ ድንበር የሚያጓጉዝ ነበር:: መንገድ ላይ ጥብቅ ፍተሻ መኖሩን ፀጉሪ ልውጥ ካገኙ እንደሚያስሩ ጨማምሮ..የቻለውን ያህል አጋኖ አወራልን:: የማመን እንጂ ያለማመን አማራጭ የለንምና አመነው:: የያዝነውን መረጃ ሳንፈራ ሳንጠራጠር ሰጠነው:: አንድ ቋንቋ ማውራት[11] ራሱ ኢትዮጵዊነት ነው:: መወሰድ ቋንቋ ነው ይባላል:: ሰጠነው::

---

[10] እናቴና እህቴ ጃዋን ጋር ሄደው እንደጠየቋቸው እህቴ በስልክ አጫውታኛለች:: ከዚህ በፊት ያስነበብኳችሁን አይነት መከራ ሳላሳልፍ እንዴት ለእናቴ እነግራታለሁ በሰላም መድረሴን ብቻ ነው የተነፈስኩት:: በነገሩ እንኳን እናቴ እኔስ ምን መረጃ ነበረኝ? እንደ ደረስኩም እስር ቤት ስለተቀበለኝ ስለ ስካሄዴም ሆነ ስለ መንገዱ የነገርኳቸው ነገር የለም:: ድንገት ከዚህ መጽሐፍ አሁን ከተረዱ ነው

[11] አንድ ቋንቋ እያወራን መግባባት ያቃተን ስንቴ ነው? አንድ ቋንቋ እያወራን አደዳብ አንዱ አንዱን ያሳረደው? ያረደው፣ የገደለው? የገረፈው፣ ያቀሰለው..አብሮ መብላት እንኳን መች አፋቀረን? ...ዜግነት እየተወራ አደዳብ..አይ ዳኔ!!!.....





አመንነው:: ዶክመንቶቻችንን እሱ ያዘልን:: እኛ ነፃ ሰው ሆነን እጅና እግራችንን ብቻ ይዘን ሄድን:: ብዙ የሚባልላት በአትክልቶቿ የምትጠራው ሂርና አደርን:: በማግስቱ ስንጓዝ ውለን ጅጅጋ ኬላን እየተቃረብን መጣን:: ..አፋርኛ ያወራል:: ወደ አብሮን ያለው ሰው ወደ ጅቡቲ ይደውላል:: ..ሶማሊኛ ያወራል፣ ትግርኛ፣ ኦሮሚኛ ጅጅጋና ሶማሊያ ይደውላል:: ..አማርኛ ብቻ ወደ 6 አይነት ቋንቋ ያወራል:: የግንኙነት አውታሩ ስፋት ገረመኝ:: ጅጅጋ ኬላ ላይ ወርዶ የሚሰራውን ሰርቶ ተመለሰ:: ተፈትሸን አለፍን:: የግንኙነት አድማሳቸውን የቅብብሎሽ ስራቸውን ስፋት፣ ..ህገ-ወጥ ድርጊታቸውን ያወኩት ኬላውን እንዳለፍን አንድ ከፍት ጆንያ የተሸፈነ መኪና መንገዱን ዘግቶ ውረዱ ያለን ጊዜ ነበር:: ልክ እንገታ ነበር የሚመስለው:: በመኪናው ተጭነን አቅጣጫ ቀይረው ወደ ደላላው ቤት... ወደ ደላላው ቤት ከምል ወደ ግዞት (መታገቻ) ቦታችን ተወሰድን ብል ያስኬዳል:: ስንገባ ከሀምሳ እስከ ስልሳ የሚሆኑ ሴቶችና ወንዶች አሉ:: ትልቅ፣ ትንሽ፣ ልጅ የያዙ..ታጉረዋል:: ተስፋ መቁረጥ..መብሳቀል ..በጉልህ ፊታቸው ላይ ይታያል:: እንደኛው ተይዘው ወደ ሶማሊያ የሚሸኙ ናቸው:: የሆነ ድብደባ..ዘረፋ የደረሰባቸው መሰለኝ:: ውስጤ መጥፎ ስሜት እንዳለ ሹክ ያለኝ መሰለኝ:: በርግጥም ነበር::

ገንዘብ እንድንከፍል ተጠየቅን:: አጠያየቁ ራሱ ሀይል ያለበት አይነት ነው:: የተጠየቅነውን ገንዘብ መክፈል ነበረብንና ከፈልን:: አሁን የተቀበለን ደላላው ስሙ ጅጅጋ ውስጥ የሚታወቅ ነው:: ከ15 እና 16 አመት በፊት የታወቀ ተደባዳቢ ነበር::

አስታወስኩት::

ስሙን ቀይሮ እዛ ቦታ ሲራጅ ተብሎ ነው የሚጠራው:: ዳግም ጅጅጋን ስረግጥ ያየሁት የመጀመሪያው የማውቀው ሰው ሆነ:: አንደኛም ሆነ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የተማርኩት ጅጅጋ ውስጥ ነበር:: አሁን ግን በዚህች ከተማ ወጣ ብሎ እንቅስቃሴዬ ተገድቦ የእነሱ ጥቅም ማስገኛ ሆኜ በደላላው ግቢ ውስጥ ታግቻለሁ:: እንደማውቀው ተነጋገርን:: ተግባባን.. መግባባቱ የለወጠው ነገር ባይኖር እንኳን ዱላው አልደረሰብንም:: እንዲያውም ሀምሳ እና ስልሳ ሆነን በአንድ ቶዮታ ላይ ስንጠቀጠቅ ሳንቲም ጨመር አድርገን ፊት /ጋቢና የሚባለው ቦታ/ ከሹፌሩ ጋር ተጫንን:: የጅጅጋ ከተማን ወደ ቀኝ እየተውን በስተግራ (ደሄ ቦታ የኮንትሮባንዲስቶች መንገድ እንደሆነ ሌሎችም ነግረውኛል:: በቀደ መስቀሉ በኩል ዜር አምስት ቀበሌ ይባላል::) በስተግራውን አድርገው ጉዞ ጀመርን:: መነሻችንን እንጂ መድረሻችንን የማናውቅ ተጓዦች ግራ መጋባት፣ ፍርሀት፣ ምን ይገጥመን እንደሆነ በማሰብ በሁላችንም ዘንድ ጭንቀት ይነበብብን ነበር::

አቧራው..ሙቀቱ ራሱን የቻለ ፈተና ሆኖ ሳለ ሹፌሩ አሁንም..አሁንም የሚያጨሰው ሲጋራ ሽታ ተደማምሮ ራስ ያዞራል:: በዚህ ሁኔታ ለ8 ሰዓት ተጉዘን ከአርትሼክ ፀርቀት ያለ በረሃ የሆነ ቦታ ላይ አረፍን:: እዛ አካባቢ የሱማሊያ ጎሳዎች አሉ። የኢትዮጵያ ሱማሌዎችና የሶማሊያ ሶማሌዎች ተቀላቅለው ነው የሚኖሩት:: አረፍት አድርገን በማግስቱ ጠዋት በሌሊት ረጅም ሸንጣም ኒሳን ዲዘል መኪና መጥቶ ወደ መቶ ሰማኒያ የምንሆን ተሰዳጆች አጭቆን ጉዞ ተጀመረ:: ጉዞው ወደ ቡርኦ ቢሆንም ከተማ ውስጥ አልገባንም:: ስደተኛ ከተማ ከገባ ችግር ነው:: እኛ ተወስደን የምንሰጠው ደላላ ልንጠፋበት ስለምንችል ዋስትና ስለሌለው ቡርኦ ከተማን ትተን በ7 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ጫካ ውስጥ አሳረፉን:: እዛ ስንደርስ ወደ 400 የሚደርሱ ኢትዮጵያዊያን አገኘን:: በጣም የሚያሳዝን ሁኔታ ነው:: ወገንህን በእንደዚህ ያለ ሁኔታ ማየትን የመሰለ ምን የሚያሳዝን ነገር አለ? ምን ያህል ቀን እዚህ እንደቆዩ ማንም ምንም ሊነግረን አልደፈረም:: እኛ ለአምስት ቀን እዚያ ስንቆይ ያየሁት ሁሉ የሚሰራው፣ የሚወራው፣ የሚበላው፣ የሚጠጣው፣ መጸዳጃ ቦታው ሁሉ አሰቃቂ ነው:: እርጉዝ አይቻለሁ:: HIV በሽተኞች ነበሩ፣ አካል ጉዳተኞች...

ከአምስት ቀን በኋላ ሌላ አምስት መቶ ብር ክፈሉ ተባልን:: ግዴታ ነው:: ያ ሁሉ ሰው እያንዳንዱ 500 በግዴታ፣ በድብደባ፣ በንጥቂያ፣ በፍተሻ፣ በሰደፍ...አነጣጥረው ሰው ባይመቱም ወደላይ እየተኮሱ በማስፈራራት ለበለቡ:: መክፈል የማይችለውን እየተደበደበ ለብቻው እንዲታሰር ተደረገ:: መክፈል ሳይችል ቀርቶ ድብደባውን መቋቋም ያቃተው በሌሊት ተሰውሮ ያችን 7 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ያለች የቡርኦ ከተማን ፍለጋ ተጓዘ:: ከዛ መኪና አቅርበው በ2 መኪና ጭነውን ጉዞ-ፍርሃት ልበለው ጉዞ-እስራት ተጀመረ:: አንዱ በአንዱ ላይ ተደራርቦ ማለት ነው:: አሁን የከፈልነው ብር የመን ድረስ እንደሚያደርስን ነው የነገሩን:: የከፈልነው አብዶ አሊ ለሚባለው ከሽፍታ ያልተሻለ ሰው ነው:: ብዙ ጋሻ ጃግሬዎች አሉት:: ያሻውን ይቀጣል፣..ያስራል..

ጉዞው ብንሄድ..ብንሄድ የማያልቅ ነው:: አድካሚ:: ሰውነቴ ሁሉ ዛለ:: የሶማሊ-ላንድን መሬት ለቀን ወደ ፑንት-ላንድ ለመግባት ወደ አምስት ቀን ፈጀብን:: አንድ ትንሽ ከተማ ገባን::

እዚህም አንድ እግሩ ቆራጣ የሆነ፣ በሁለት ዱላ ተረድቶ የሚጓዝ ሰው፣ በማርከ ቱ /ከሪሲዳ ፋሚሊውን ማርከ ቱ ነው የሚሉት/ እና በማርቼዲስ የሚታጀብ ትልቅ ሽፍታ ነው:: እንግሊዘኛ አሮሚኛ እየሰባበረ ያወራል:: የእሱ ደግሞ ለየት ያለ ነው:: ከቡርኦ አጅበው ካመጡን ተረክቦ ከከተማ ወጣ አድርጎ የሆነ ኮረብታማ ቦታ ላይ ከመኪና ሳንወርድ እንድንቆይ አደረገ::





በአስተርጓሚ ‹‹አሁን በእኛ እጅ ናችሁ እንኳን ደህና መጣችሁ:: 500 ብር የከፈላችሁት አብዶ አሊ ገንዘቡን አልላከልኝም:: እስኪልክልኝ ድረስ አንድ ቦታ ላይ የኔ ወታደሮች እየጠበቋችሁ ትቆያላችሁ:: ግን የምትቆዩበትን ቀን ምን ያህል እንደሆነ ስለማይታወቅ ለወታደሮቹ የጥበቃ አበል 20 20 ብር ትከፍላላችሁ..›› አለን:: ይሄ ግዴታ ነው:: እንቢ የማይባልበት በረሃ ውስጥ ነው:: ታጥቀዋል:: የሚችል ከፈለ ለማይችሉት የሚችል እያዋጣ ከፈለላቸው:: ከዛች ከተማ የ3 ሰዓት መንገድ ርቀው የሚገኙ ዲንሾሽ የሚባሉ ጎሳዎች አሉ:: የቦታው ስምም ዲንሾሽ ነው:: ብዙ ነገራቸው ከአረቦች ጋር ይቀራረባል:: እነዚህ ሰዎች መካከል ወስደው አሰፈሩን:: ወንዝ አጠገብ ነው ያሰፈሩን::

አስር ደቂቃ ሳይሞላ ተኩስ ከፈቱብን:: እንዲያውም ለጥቂት ነው ከሩምታው ያመለጥነው:: ‹‹ጢው!!!..›› ብላ በጆሮዬ ስር አፏጭታ አለፈች:: ተኩስ የከፈቱበት፣ ምክንያት ‹‹ይሄ ወንዝ ስንሰግድ ውዱእ የምናደርግበት (የምንታጠብበት) ከብቶቻችንን የምናጠጣበት ነው:: እናንተ ካፊር ናችሁ፣ ክርስቲያን ናችሁ፣ ሀይማኖት የላችሁም:: ይህንን ውሃ ታረክሱብናላችሁ›› አሉን:: ምስኪን ስደተኛ ለማባረር ነው ይህ ሁሉ ተኩስ:: ባዶ እጁን ላለ፣ ለራበው፣ ለጠማው ስደተኛ ጥይት...::

ከወንዙ ትንሽ ፈቀቅ ብለን ተቀመጥን ሶስት ቀን አደርን:: መፍትሄ የለም:: ጠባቂዎቹ እኛን ይጠብቃሉ:: ሌሎች ታጣቂዎች ከእነሱ ነጥቀው ለመውሰድና እኛን ለመዝረፍ ተቃኮሱ:: አንድ ሰው ሁላ ሞቷል:: በጣም ፈራን ብዙ ነን:: ተሰባሰብንና መመካከር ጀመርን:: እንደአጋጣሚ በዛን ሰዓት ከኢህአዴግ ጋር ታግለናል ያሉ ሶስት የትግራይ ተወላጆች ነበሩ:: መሀረ፣ ደምስና የደምስ ወንድም ናቸው::

«እኛ በዚህ በረሃ አራት አምስት ጊዜ ተሰደናል:: በሳዑ እየገባን የመን እየተሻገርን ሳዑዲ አረቢያ ሄደን ስራ እየሰራን ስንያዝ ወደ ኢትዮጵያ እየተመለስን ተመላልሰናል:: ነገር ግን እንዳሁኑ አይነት ስደት ገጥሞን አያውቅም:: ይህ በጣም አስቸጋሪ ነው:: አሁን ያለንበት ቦታ ከቦሳሶ በመቶዎች ኪሎ ሜትር ይርቃል..በጣም ሩቅ ነው:: ስለዚህ የግዴታ የሚገድሉትን ገድለው የሚተርፍ ይትረፍ በህይወታችን ቆርጠን ከዚህ ቦታ መጥፋት አለብን» ተባባልን:: ሁሉም ተስማማ:: በወሰንን ቀን ሌሊት መትረየስ ክላሽ ይዘው መጥተው ሴቶች ከስራችን ወስደው ደፈሩ:: በጣም ነው የተጫወቱባቸው:: ምንም ማድረግ አልተቻለም:: ማንንም ማትረፍ አልተቻለም:: ያ ቀን አለፈ::

በማግስቱ ውለን ወደ ምሽት ላይ ሰዎቹ ተሰፋ ቆረጡ:: የተባለውም ደላላ እኛን ለተረከበን ሰው ገንዘቡን ሊልክለት አልቻለም:: ተነስተን ጉዞ

ጀመርን። ጉዞ ስንጀምር ተከበብን ሊፈትሹንና አንዳንድ ነገር ሊያደርጉ መሳሪያ ወደ ሰማይ ተኩሱ። ብዙ ጥረት አደረጉ። እነዚያ የነገርኩህ ታጋዮች በድንጋይ አስፈራርተው ባለመሳሪያዎቹን አሸንፈው ጉዞ ጀመርን። ቢያንስ የ4 ሰዓት መንገድ እንደተጓዝን ህዝቡ ተበታተነ። ግማሹ መኪና እያገኘ ግማሹ ትናንሽ ከተማ ውስጥ እየቀረ ተበታተንን። በመጨረሻ አራት ልጆች ብቻ ቀረን። ከዚህ ቦታ እስከ ቦሳሶ ያለው መንገድ በእግር 17 ሰዓት ያስጉዛል። ያንን አስራሰባት ሰዓት ቀንና ሌሊት እየተጓዝን ካጋመስን በኋላ ውሀ የለም። ምግብ የለም። በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ ገጠመን። ወደ ቦሳሶ የሚወስደውን ዋናውን መንገድ ከያዝን በኋላ የምናገኛቸው አሽከርካሪዎች ሁሉ በጣም ሀበሻን ማየት የማይፈልጉ ክፉዎች ናቸው። ግመሎች፣ በጎች፣ ጭነው ወደ ቦሳሶ ወደብ የሚጓዙ ናቸው።

እንደ አጋጣሚ ሆኖ አንድ መኪና አገኘን። የሁለቱን ሰዓት መንገድ ከወሰደን በኋላ ከዚህ በኋላ ሀላፊነት አንወስድም የፑንትላንድ ወታደሮች (የአብዱል ዮሱፍ ወታደሮች) ይይዟችኋል ውረዱ አሉን። ወረድን።

በእግር ቦሳሶ ገባን። ከኢትዮጵያዊያን ጋር ተቀላቀልን። እዚያ በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ በመቶዎች የሚጠጉ ስደተኞች ነበሩ። እኛ ስንገባ አንዲት እርጉዝ ሴት ጽንሱ ውስጧ እንዳለ መሞቷንና እሷን ለመቅበር ገንዘብ እየተሰበሰበ እንደሆነ ነገሩን። እዛ ሀገር ላይ የቀብር መሬት ማግኘት ይከብዳል። ብዙ ሚሊየን ሽልንግ ይከፈላል። ያቺ ሴት ክርስቲያን ብትሆንም እስላም ነች ተብሎ ስሟ ተቀይሮ ተቀበረች። ሁለት የወለ- ልጆችም ታመው ደክመው ነበርና እነሱም ሞቱ። እንደዚህ ያለ ዘግናኝ ሁኔታ ላይ ነበር የደረስነው።

የተወሰነ ቀን እንዳደርን የአብዱላሂ ዮሱፍ ቤተሰቦች የሆኑ ትልቅ ህንጻ ያላቸው ተወላጆች ቤታቸውን ለቀይ መስቀል አከራይተው በቀን አንድ ጊዜ ስደተኛውን ምግብ ይመግቡ ነበር። እና ምግብ ለማግኘት ያለው ግፊያ፣ ሽሚያ፣ የሰዉ መታመም፣ ህክምና ማጣት ብሎም መሞት..ጠቅላላ እያንዳንዱ ሁኔታ አሳዛኝ ነበር። የቢ.ቢ.ሲ ቴሌቪዥን ያን መረጃ ደርሶት ስደተኛውን መጥቶ ቀረጸ። ከቀረጸ በኋላ የሚሰሩትን ፕሮግራም ሚዛናዊ ለማድረግ ከኢትዮጵያ ውጭ ጉዳይ አንድ ከፍተኛ ባለስልጣን አነጋገሩ። እሳቸውም ወደ ሶማሊያ የሚሰደድ ኢትዮጵያዊ የለም። ሶማሊያ በአሁን ሰዓት ቀውስ ውስጥ ነች። ስለዚህ ከኢትዮጵያ ወደ ሰላም ያጣችው ሶማሊያ የሚሰደድ የለም። በእርግጥ ቤት ሲጠረግ ቆሻሻ ይወጣል አይነት ንግግር ተናገሩ።

ያ ፕሮግራም በተላለፈ በተወሰነ ቀን ልዩነት የኢትዮጵያ ወታደሮች ወደ ቦሳሶ መግባት ጀመሩ። ብዙዎቻችን ፈራን። የባህር ጉዞው ደግሞ በማዕበል ምክንያት ተቋርጦ ነበር። እኛ እዛ በደረስንበት አጋጣሚ ጉዞ





ተጀምሯል። ገንዘባችንን ቶሎ ከፈልንና የባህር ጉዟችንን ጀመርን። ከቦሳሶ ከተማ እስከ መጫኛው የባህር ጠረፍ በእግር በምንሄድበት ሰዓት ወታደሮች መተው በተኩስ ሊበትኑን ሞከሩ። መልሰን ተገናኘን። የሚመራን የጀልባ ሹፌር መሳሪያ ይዟል። በእሱ መሪነት ሌሊቱን ስንጓዝ ቆይተን እኩለ ሌሊት ላይ የሆነ ቦታ አረፍን። አደርንም። ወደ ሚጭኑበት ከከተማው የሚርቅ የባህር ጠረፍ ጉዞ አደረግን። ያ-ራሱን የቻለ ስቃይ እና ፈተና ነበር።

ጠዋት 12 ሰዓት ላይ ጉዞ ጀመርን። ስንጓዝ ቆይተን ቀን ሰባት ሰዓት ላይ መጫኛው ቦታ ላይ ስለደረስን አረፍን። 5 ጀልባ ነበር የቀረበው። ህዝቡ መጫን ጀመረ። ከሚጫነው መካከል እርጉዝ፣ አካል ጉዳተኛ፣ ህጻን ያዘለ፣ ያቀፈ አለ። ብዙ ህዝብ ነው ያለው። እንደ ምንም በጥረት በስቃይ ለመሳፈር በቃን። ጉዞ ተጀመረ። የጀልባው ጉዞ አስቃቂ ነበር። ምንም እንኳን እኔና ጓደኛዬ የተለየ ግፍ ባይገጥመንም ሌሎች ሲደበደቡ ሲሰቃዩ ማየት ራሱን የቻለ በሽታ ነው። በእርግጥ ጀልባው ላይ ስንወጣ ጉሽማው በጣም ያስቸገረው ለጓደኛዬ ታምራት ነበር። ከቁመቱ ማጠር ጋር የአካል ችግር ስላለበት በጣም ፈርቼለት ነበር። በእርግጥም የተወሰነ ተጎድቷል።

ገና ተነስተን አስር ደቂቃ ሳይሞላን ሰዎች ማቅለሽለሽ ቋቅ ይላቸው ጀመር። በዚህ ሁኔታ በመጥፎ ጠረን ተበክለን ተጓዝን። ምሽት ላይ ከሌሎች ጀልባዎች እኛ ያለንበት ተነጥሎ ቀረ። ባለጀልባዎቹ 5 ቱቸው ከነበራቸው ስጋት አንጻር ጀልባዋ የተወጠረላት መረብ ላይ ቆመው ባትሪ ማብራት ጀመሩ። ለጓደኞቻቸው ምልክት መስጠታቸው ነው።

ሊገናኙ አልቻሉም።

ትንሽ እንደተጓዝን የጀልባው ሞተር ጠፋ። በዚህ ሰዓት የጀልባዋ ሾፌሮች «ቡሉ ሁላችሁም በየእምነታችሁ ጸልዩ። የጀልባው ሞተር ጠፍቷል በአስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ነው ያለነው» አሉ። ህዝቡ ተጨነቀ። የሚያለቅስም ያለቅሳል የሚጸልይም ይጸልያል። ከአንድ ሰዓት ጉርጎራ በኋላ የጀልባው ሞተር ተነሳ። ጉዞ ጀመርን እንደፈሩትም አልሆነም። የእጅ ባትሪ ይዘው ማብራት ሲጀምሩ ጓደኞቻቸው ተሰበሰቡ። ተጠባብቀው በጋራ መጓዝ ጀመሩ። አብዛኛው እንደሚባለው የጀልባው ጉዞ ከ36-38 ሰዓት ነው የሚፈጀው። በምንወርድበት ሰዓት ላይ መውረጃው ቦታ ጠፍቶባቸው ቢያንስ ለአንድ እና ሁለት ሰዓት ከዞሩ ከተጨቃጨቁ በኋላ አቅጣጫውን አገኙት። ነገር ግን ብዙ ጊዜ 25 ኪሎ አሸዋ የተሞላ ማዳበሪያ አለ። እሱን ላይ ክብ ሰዓት አድርገው እንደ ኮምፓስ ነው የሚጠቀሙበት። እሱን በባትሪ ቢያዩትም ሊያገለግላቸው አልቻለም። ሸቡዋ በሚባለው

የሚያወርዱበት ቦታ ውረዱ ተባልን። ስንወርድ ውሀው አንገታችን ድረስ ነው። ርቀት የለውም። በቀላሉ ዳርቻውን ለመሻገር ቻልን።

የሚያሳዝነው ነገር ግን ያ-ሁሉ በጀልባ የመጣ ህዝብ ከ10 ደቂቃ በኋላ እዛ በረሃ ላይ የለም። እኔና ጓደኛዬ ብቻ ቀረን። በጣም ደነገጥን። አእምሮአችን ተነክቷል። የሆነ ጩኸት ረብሻ ይሰማናል። ጭው...ያለ በረሃ የባህር ዳርቻ ሆኖ ሳለ ለእኛ ግን ሰው ያለ መስሎ ይታየናል። ይሄ ነገር አልፎ ሰዎችን ስንጠይቅ አዎ! አዲስ ከሆናችሁ የባህር ጉዞ እንዲህ ነው የሚያደርገው ብለውናል። በዚህ ሁኔታ ላይ ውሀ ጥም ርሃብ አለ። ቀላል ሰዓት አይደለም ያለ ምንም ነገር የተጓዝነው። ትንሽ እንደ ተጓዝን ሶስት የወሎ ራያ ልጆች አገኘን። እነሱ የእኛ ሰዎች ናችሁ አሉን። ከዛ አሸዋው ላይ አብረን ተኛን። በማግስቱ ቀን ሰባት ሰዓት በምንነቃበት ጊዜ እነዛ ልጆች የሉም። እኔና ጓደኛዬ ለብቻችን ነን። ትልልቅ ተራራዎች አሉ። ቦታው ጭው ያለ በረሃ ነው። በዛ አካባቢ የመኪና መንገድ ለማግኘት፣ ሰው ለማግኘት ጉዟችንን ቀጠልን። በጠጠር ላይ ነው የምንራመደው። ተራራ እያቋረጥን ዳገቱ ፈታኝ ነው። አሸዋው እስከ ወገብ ሊውጥ ይችላል። በጥንቃቄ እየተጓዝን የመኪና መንገድ አገኘን።

ከዛ ጉዞው ወደ አደን ሆነ። ግማሽ በመኪና ግማሽ በእግር እያደረግን ስንጓዝ በሁለተኛው ቀን ላይ አዛን የምትባል ከተማ ደረስን። ብዙ ኢትዮጵያዊያን አገኘን። አንድ ትልቅ መስጊድ ገብተን አደርን። ጠዋት ተነስተን ወደ አደን ጉዞ ስንጀምር አንዲት ኢትዮጵያዊ አገኘን። «እንዳትንቀሳቀሱ ከዚህ ወደኋላ ጥላችኋት የመጣችሁት የስደተኞች ማረፊያ ጣቢያ አለች። ማይፋ ትባላለች። እዛ ሄዳችሁ ለ10 ቀን የሚያገለግል ወረቀት ይሰጧችኋል። እሱን ይዛችሁ ካልሆነ ብዙ ልጆች በእጠቅ እና በተለያየ ቦታ ተይዘው እስር ቤት ታጉረዋል» አለችን እና እንደገና ዞረን ወደ ማይፋ የሚባለው ካምፕ ተመለስን። በጣም ዋሩ ሰው ናቸው ተቀበሉን የተወሰነ ቀን መጠበቅ ነበረብን።

ኢንተርቪው ተደርገን ወረቀቱ ተሰጠን።

መንገድ ጀመርን። ከስንት ችግር በኋላ በስንት ስቃይ አደን ገባን። ያውም እኔና ጓደኛዬ ታምራት ሰርቤሳ ተለያይተን ነው። እኔ ታመምኩ እና ያለንን ሳንቲም አሰባስቦ አንድ አብሮን የነበረ ልጅ እኔ በአውቶቡስ እንድሄድ አደረገ። ከዛ....»

ተናግሮ እስኪጨርስ መጠየቅ የፈለኩትን ዝም ብዬ አሳለፍኩት። ምክንያቱም ቃለ-ምልልሱን እናደርግ የነበረው በጓደኝነት መንፈስ ነበር። ወደኋላ ብመልሰው አይናደድም አሁን ካለበት የትዝታ መንፈስ ከምገታው





ብዬ ነው። ከዚህ በኋላ ያለውን ወደኋላ ወስጄው በጥያቄና መልስ እንመልከተው፡-[12]

ጥያቄ፡- ዳኒ በትረካህ መሀል የምጠይቅህ ነገር ነበረኝ። በተመስጦ ስለነበርክ እንዳላቋርጥህ ብዬ ነው። ወደኋላ ልመልስህ እና ሶማሊያ ቡርኦ የምትባለው ቦታ ሲያግቷችሁ የነበረው ሁኔታን በደንብ እንድትነግረኝ እፈልጋለሁ። አያያዛቸው፣ የምግቡ ሁኔታ በተለይ ለኢትዮጵያዊያን ተስማሚ አልመሰለኝም። እኔ ሀርጌሳ እያለሁ የገጠመኝ ምግብ አይነት ከሆነ...

ዳንኤል፡- ምግብ ፈጽሞ የለም ማለት ትችላለህ። ሶማሊያዊያኑ የሚያዘጋጁት ከእኛ የምግብ ፍላጎት ጋር አይሄድም። አንዳንድ ልጆች በድፍረት ይበሉታል። እኔና ታምራት ግን ልንበላ አልቻልንም። በጣም አስጠሊታ ሁኔታ ነበር። አንድ አቡወለድ እስከ 50 ብር ገዝተን የበላንበት ሁኔታ አለ። ፈጽሞ ምግብ የሚባል ነገር የለም ብልህ ይሻላል።

ጥያቄ፡- ሌሎች ልጆች ሳናግር አፋኞቹ ሩዝ በበርሜል እየቀቀሉ...የሚል ነገር ሰምቼ ነበር።

ዳንኤል፡- አዎ! አለ። ለምሳሌ እኛን ወንዙ ጋ የያዙን ሰዎች (ተኩስ የተከፈተባቸው እና ወንዙን ታረከሱታላችሁ የተባሉበት ቦታ..) ከሶስት ቀን በላይ ሲያቆዩን ለአንድ ቀን ሩዝ አብልተውናል። እሱም ጥቅም ማግኛቸው ስለሆንን ከእኛም ገንዘብ ስለሚፈልጉ ነው።

ጥያቄ፡- በዘረፋ ሳንቲም ተወስዶባችሁ በሳዑ ገብታችሁም ቢሆን መመገቢያ መሳፈሪያ ያጣችሁበት ሁኔታ ነበር?

ዳንኤል፡- ዋናው እና ትልቁ የኢኮኖሚ ችግር ነው። ገንዘብም ያዝ አትያዝ መብላት መጠጣትህ ስለማይቀር የምታወጣው ነገር በጣም ትርፍ ነው። ያለህን ገንዘብ ለምታገኘው አገልግሎት የምትከፍለው ገንዘብ ብዙ ነው። ያለህን ገንዘብ እስክትጨርስ ትጠቀማለህ። በዛ ላይ ዘረፋም አለ። በዘረፋው ወቅት የምታየው አስጠሊታ ነገር ተይዘህ በሚፈትሹህ ሴቶቹን ለይምሰል ሴት ፈታሽ ያመጣሉ። ግን እጃቸውን ሰው አካል ውስጥ እየከተቱ የሚያደርጉት ጸያፍ ነገር አለ። ወንዶችንም ቢሆን አፋቸውን አስከፍተው ጣታቸውን በመክተት የሚፈትሹት ነገር ያስጠላል።

---

[12] ከዳንኤል ጋር ያወራነው ብዙ ቢሆንም ራሱ በራሱ አጻጻፍ በትንታኔ ስለጻፈው ሳለማርዘም አስብኩና አሳጠርኩት።

<u>ጥያቄ</u>፡- በሳሶ ለስንት ቀን ቆየህ? እዛ ስትቆይ ጋዜጠኛ አይንህ ይታዘባል እና ተደብድበው፣ ተዘርፈው፣ ተደፍረው..አላጋጠመሁም?

<u>ዳንኤል</u>፡- በሳሶ 9 ቀን ነው የቆየሁት፡፡ አመት ሁለት አመት የሞላቸው ሰዎች አሉ፡፡ ቅድም አንተ እንደገለጽከው ገንዘብ በመዘረፍ፣ በማጣት..ያሰቡበት ሳይደርሱ እዛው ለመቆየት የተገደዱ አሉ፡፡ ስራ የለም፡፡ በቂ ነው ብለው ያላቸውን፣ ይዘው የወጡትን ገንዘብ ተዘርፈዋል፡፡ በማዕበልና በተለያየ ችግር ባሰቡት ሰዓት ሳይሳፈሩ ቀርተዋል፡፡ ሶማሊያዊያኑ ከእነሱ ያነሰ ሲያገኙ ቀጥረው ያሰራሉ፡፡ እነሱ ጋር ሰርተው ባህሩን ለመሻገር የሚሞክሩ አሉ፡፡ ተቀጥረው ሲሰሩ በቤቱ አባላት የተደፈሩ አጋጥመውኛል፡፡..ምን ልበልህ ቦሳሶ ያለው ሁኔታ በጣም አስከፊ ነው፡፡ የሰው ልጅ ፈጽሞ ሊኖርበት የሚችልበት ቦታ አይደለም፡፡





# - 13 -

# ስደት ያጠወለገው ልጅነት

ራስን ሆኖ ራስን ማጣት
ወደ ፊት እየሄዱ ወደ ኋላ መምጣት
ቁልቁል መውረድ እንደ ካሮት
አድሮ ቃሪያ ነዕቶ መብከት
ራስ ጠፍቶ በከኖ መቅረት

በተለያየ ጊዜ ለተለያየ ጉዳይ ወደ UNHCR ቢሮ ጎራ ስል መፍትሄ ይሰጠን ብለው በሩ ላይ የሚተኙ ሰዎች አጋጥመውኛል፡፡ በአንድ ወቅት ይሰጠን ብለው በሩ ላይ ... መፍትሄ ይሰጠኝ ብሎ ተቀምጦ ያገኘሁት ካልድ (መንግስቱ) ለገሰ ሶስት ክስት ያሉ ልጆችን ይዞ ነበር፡፡ UNHCR በር ላይ የተቀመጠበትን ምክንያት ጠየኩት፡፡ በወቅቱ ያለበትን ችግር እንዲሁም ከሀገር ከተሰደደበት ጊዜ አንስቶ ያለውን ታሪክ ድረስ ነካ ነካ አድርገን አወራን እና በሌላ ጊዜ ለመገናኘት ቃል ተግባብተን ተለያየን፡፡ የሰማሁት ነገር ውስጤን ቆጥቁጦታል፣ ይበልጥ ለመስማት ፈልጌያለሁ፡፡ በተከታታይ ቀኖች እየደወልኩ ብንገናኝም ሁኔታዎች አልመቻች እያሉ በቴፕ ቀድቼ መረጃ ለማድረግ ያሰብኩት አልተሳካም ነበር፡፡ ይህ የሆነው የመጀመሪያ ልጁ እየታመመች ስለነበር ነው፡፡

(መንግስቱ ለገሰ) ቶሎ ብርግግ የሚል ድንጉጥ ሆኗል፡፡ ለነገሩ ለምን አይሆን ስንት መከራ ያየባት ልጅ ነች የታመመችው፡፡ በዚህ ሰዓት ብዙ አግባብ ባይኖረንም ከጎኑ መሆንን እና ማጽናናት፣ አይዞህ ማለት ነበረብኝ፡፡ የማይዝ የሚጨብጠውን ያጣ አይነት ነበር፡፡ በመንገድ እየሄደ መንገድ ላይ መሆኑን የሚዘነጋ አይነት፡፡ልጅቷ ሻል ያላት ጊዜ ጭል ጭል

ያሉት አይኖቹ የብር-ጓል መስለው ግርማ ሞገሳቸው ይጎላል፡፡ ልጁ በታመመችበት ወቅት ያን የስቃይ ኑሮ አስታውሰህ ንገረኝ ማለት አግባብ አለመሆኑን አውቃለሁ፡፡ እንኳን እሱ ገፈቱን የቀመሰው ይቅርና ዛሬ ይህን ታሪክ ስጽፍ የጨረስኩትን እንባ ከእግዚአብሄር ቀጥሎ አጠገቤ ያሉ ሰዎች ሁሉ አይተውታል፡፡ እንደዛ የሆነባት ራሱን ያጣባት ልጁ ምዕራፍ ጭል..ጭል..

ልክ እንደ ቴያትር ትዕይንት መጋረጃው ሲዘጋ፣ አዳራሹ መብራቱ ሲጠፋ.. በጨለማ የሚዋጠውን ያህል ልባችን..ጨለመበት፡፡ ከል ለበሰ፡፡ የቴያትሩ ሂደት አልቆ ‹‹ተፈጸመ›› የሚለውን አውቀን እስክንነሳበት ትዕይንቱ መቀጠሉ ግድ ነው፡፡ ዳግም መጋረጃው ተከፈተ እና ስንተኛው ክፍል ስንተኛው ትዕይንት ላይ እንዳለን የማናስተውለው የስደት ድራማ ቀጠለ፡፡ ቀናት ተሰልፈው ማለፋቸውን ቀጥለዋል፡፡ ከተሰለፉበት በአንዱ ቀን ለቃለ-ምልልስ ቴፔን ደቅኜ አወራን፡፡ በእርግጥ ሰነዓ ላይ ካጋጠሙኝ በስደት ከፍተኛ መከራን ከቀመሱ በርካታ አሳዛኝ ታሪክ ካላቸው ሰዎች ውስጥ አንዱ ሆነ፡፡ ድንገት ከዚህ በፊት ካነበቡት ትራጀዲ ታሪኮች ቁንጮ ሊሆን ይችላል፡፡ በእርግጥ ምልከታችን ይለያያል፡፡ እኔ ገፈት የቀመሰበትን ህይወት አይቼው ስላለፍኩ፣ በቅርቡም ስለማውቀው ሊሆን ይችላል በጥልቀት የተሰማኝ፡፡

ሰው ስደት ሲወጣ ጓዝ ጉዝጓዙን ይዞ አይደለም፡፡ አንድ ሻንጣ አንጠልጥሎ ነው፡፡ ሌጣ ሆኖ መሰደድ እንዴት ቀላል ነው፡፡ ሌጣ ሆኜ ቢሆን ዛሬ እንደ በቆሎ እሸት ተሸልቅቄ አሮጌ ምዕራፍ ዘግቼ አዲስ ምዕራፍ ባልከፈትኩ ነበር፡፡ እኔ ቀላሉን ሳይሆን ከባዱን ነው የሞከርኩት፡፡ አዳዬም መከራዬም የበዛው ለዛ ሳይሆን አይቀርም፡፡ እኔ ስደት ሲባል የማውቀው ከክፍለ ሀገር ክፍለ ሀገር ያለውን ነው፡፡ እሱን ከሆነ ደጋግሜ ቀምሼዋለሁ፡፡ ከናዝሬት ተነስቼ አርባ ምንጭ ሄጄ ኖሬያለሁ፡፡ ጅጅጋም አግብቼ ወልጄ ሁሉ ኖሬያለሁ፡፡ ከዚህ ውጭ ስደት ተብሎ ከሀገር የሚወጣበትን አላውቀውም፡፡

ሚሊኒየም ሚሊኒየም እየተባለ ሀገር ምድሩ በሚያዳምቅበት፣ በሚያረግድበት ወቅት ነው ስደትን «ሀ» ብዬ የጀመርኩት፡፡ ባለቤቴ አንድ ዘመዷ እና የዘጠኝ ወር ልጇን ይዤ ነው ጉዟችንን ወደ ሶማሊያ ያደረግነው፡፡ ጅጅጋ ድረስ ምንም እክል ሳይገጥመን ነበር በሰላም የተጓዝነው፡፡ ከጅጅጋ ወጣ ስንል ግን ኢትዮጵያ ምድር ላይ ያለን አይመስልም፡፡ አርትሼክ የኢትዮጵያና ሶማሊያ ድንበር ነው፡፡ ግን ብዙ ችግር ያለበት ከተማ፡፡ ደላላዎቹ ከጅጅጋ ጀምሮ እንዴት እንደሚወስዱ፣ እንዴት በጫካ ጫካ አድርገው በስንት ስቃይ ሶማሊያ እንደሚያስገቡ... በዚህ ሁሉ መሀል ያሉት መዓት ማጭበርበሮች ላይ ከፋኝ፡፡





መቼም ሲከፋና ነገር ሲደራረብ አንዴ ነው አይደል? አርትሼክ በገባን በሁለተኛው ቀን ታይፎይድ ነገር አመመኝ፡፡ በቃ! አሁንም አሁንም ሽንት ቤት ነው፡፡ በጣም ታመምኩኝ፡፡ ለ12 ቀን መከራዬን አየሁ፡፡ ህክምና የለም፡፡ እዛው አካባቢ ባለ የባህል ሀኪም መድኃኒት አድርገውልኝ ትንሽ ተሻለኝ፡፡ አሁን መጓጓዣ ማፈላለግ ጀመርኩ፡፡ በኋላ አንድ ነጋጅ የጫነ ቡቴ «እወስዳችኋለሁ፡፡ አንተ ቤተሰቡ..ልጅ አለህ እነዚህ እያንገላቱ ነው የሚወስዱህ» አለኝ በሀዘኔታ፡፡ በማግስቱ መንገድ ጀመርን፡፡ መስከረም 12/2000 የሶማሊያን መሬት ረገጥኩ፡፡

ቡርኦ የሚባለው ከተማ ለመድረስ ሁለት ከተማዎችን አልፈናል፡፡ ፍተሻዎች፣ ዘረፋዎች፣ ድብደባዎችና ብዙ ብዙ ዓይነት ለቅቃዎችን እያየሁ ነው፡፡ ግን ተዉ እንዳልል እኔም ህፃን ስለያዝኩ አፌን ለጉሜ አለፍኩ፡፡ ለነገሩ ሾፌሩ ሶማሊያዊ ሆኖ የተባረከ ባይሆን ኖሮ መከራችንን እየበላን ነበር የምንሄደው፡፡ በአራተኛ ቀናችን ቡርኦ የሚባለው ቦታ ገባን፡፡ ይህን ያህል ጊዜ የሚወስድ ሆኖ ሳይሆን መኪናው ተበላሽቶ ጫካ ውስጥ ስላደርን ነው፡፡ እንደገና ጎማ ተነፈሰ..ጭቃ ያዘውና ብቻ ተወው እባክህ ስቃያችንን አየን፡፡ ቡርኦ እንደገባን የማይሆን መንገድ ሆነብን ለዛ ነው 4 ቀን የተንጓተተው፡፡ መንገዱ ተዘግቷል፡፡ በላሶ ወደሚባለው የባህር ዳርቻ ለመጓዝ ጠየቅን፡፡ መሀል ላይ ላሳኖት የምትባል ቦታ የጎሳ ጦርነት አለ፡፡ ስለዚህ እዚህ እረፍት ማድረግ አለባችሁ፡፡ እስኪረጋጉና ጦርነቱ እስኪበርድ ጠብቁ ልጅ ይዛችሁ አይሆንም መንገድ አታስቡ ተባልን፡፡ ቡርኦ ላይ ሼክ ሀሰን ይባላል የጎሳ መሪ ነው፡፡ እሱ ጋር ቤት ተከራይተን ተቀመጥን፡፡ ኢትዮጵያን ቀደም ብሎ የሚያውቃት ሱማሌ ነው፡፡

በወር መቶ የኢትዮጵያ ብር ክፈሉኝ አለን ሰጠሁት፡፡ እዛው ተቀምጠን የሚመጣውን ስደተኛ ብዛት ስናይ በጣም የሚገርም ነው፡፡ ስለዚህ ለእኛ ምግብ መስራታችን ስለማይቀር በዛውም ጨመር አድርገን ሰርተን በርካሽ ዋጋ ለመሸጥ ወሰንን፡፡ ስደተኛውን ስናየው ተርቦ የሚወድቅ አለ፡፡ ገንዘባቸውን ጫካ ውሀ ጠምቶት የሚያጠጣው አጥቶ የሚወድቅ አለ፡፡ አለ፡፡ ላይ እየተደበደቡ፣ እየተዘረፉ እንኳን አረብ ሀገር ሊገቡ ባህር ሊሻገሩ ግማሽ መንገድ ሳይደርሱ ተሰናክለው ይቀራሉ፡፡ መንገድ ላይ በርሀብ፣ በጠኔ ደክሞ መራመድ አቅቶት ሲጎተት የሚመጣ አለ፡፡ ብቻ ሁሉም ነገር ለቅጣጭ ነው፡፡ ተደፍረው የሚመጡ አሉ፡፡ እዛ በተቀመጥንበት ሰዓት አይናችን የሰው ልጅ ስቃይን እስኪበቃው ድረስ አየ፡፡ አካል ጉዳተኛ ሆኖ የሚጓዝ አለ፡፡ ነፍሰጡር ሆና የምትጓዝ አለች፡፡ ብቻ ተወኝ ያየነው ሁሉ ደስ አይልም፡፡ ከሁሉ ሁሉ ግን ተደፍረው የሚያለቅሱትን፣ መራመድ አቅቷቸው የሚሰቃዩትን ማየቱ ይከብዳል፡፡

ምግብ እየሸጥን ለሁለት ወር ቆየን፡፡ ከዛ በኋላ ትራንስፖርት አለ..መንገድ ተከፈተ ብለውን..ገንዘባችን ሰባስበን በአይሱዙ ተጫንን፡፡ ምን ያደርጋል በግምት 5 ኪሎ ሜትር ያህል እንደሄድን..ውረዱ ተብለን ከአይሱዚው ቁመት ያልተናነሰ ጭድ ተጫነ፡፡ ከዛ ከጭዱ በላይ ሀያ ሁለት ሰው ሆነን ተጫንን መጀመሪያ ላይ «እንዴት ብዬ ነው ይህችን ህፃን ልጅ ይዤ እዛ እላይ የምወጣው?» ብያቸው ነበር፡፡ እነሱ ምን ችግር አለባቸው? «አንተ ጭድ መሀል ትቀመጥና..እግርህን ከጭድ ጋር አስርልሀለሁ፡፡ ህጻን ስለያዝክ ወደዚህ ወደዛ እንዳያደርግህ ያግዝሀል..» አለኝ፡፡ በእሱ ቤት መላ መስጠቱ ነው እንግዲህ፡፡ ይህን ባይልስ ምን አማራጭ አለን? ከጭዱ ላይ ሆነን ጉዞ ቀጠልን፡፡ ለምን ማለት አትችል ሲናገርህ መልስ መስጠት አትችልም፡፡ አስወርዶ ጥሎህ ይሄዳል፡፡ እዛ በረሃ ላይ ቢጥልህ ምን ይውጥሀል? ስለዚህ ዝም ማለት ነው የሚያዋጣህ፡፡ ትንሽ ከተናገርክ ወይም ከተነጫነጭክ ክላሽ ያወርዳሉ፡፡

ያ-ጉዞ 11 ቀን ነው የወሰደው፡፡ ሁለት ቀን ቦሳሶ የሚገባበት መንገድ ሆኖ ሳለ ነው ይህን ያህል የወሰደብን፡፡ ሹፌሩ መንገዱን አያውቀውም፡፡ መንገዱ ላይ ያለ የጎማ ቅርጽ እየተከተለ በጨለማ ሲሄድ መንገድ ስቶ የሄደው ወደ ሞቃዲሾ ነው፡፡ ከዚህ ሌላ የሆነ ቦታ ላይ ጎማ ፈንድቶ የቆምነው ሁለት ቀን ነው፡፡ ተቀያሪ የነበረው ጎማ አንድ ነው፡፡ እሱን ቀየሩ፡፡ ሌላ ሁለተኛ ጎማ ፈነዳ፡፡ ይኼኔ ቅያሪ ከየት ይምጣ? የተጓዘው በተሳሳተ አቅጣጫ ነው መንገድ የለም፡፡ ያደርነው እዚያ ነው፤ ጭድ ላይ እየተኛን ከስራችን እውሬ እየተርመሰመሰ፡፡ አንዳንድ መኪና ላይ ለመውጣት የሚታገለው አውሬ ዱላ ይዘን ስንከላከል ነው ያደርነው፡፡ ተራ ይዘን ግማሻችን እየተኛን ግማሻችን እየጠበቅን እናድራለን፡፡ ከዝንጀሮና ጦጣ በስተቀር ደፍሮ ወጥቶ ያስቸገረን የለም፡፡ ሁለት ቀን እዛ አድረን በመጨረሻ መሄጃ ስናጣ ጎማውን ፈተው የተነፈሰ ከመነዳሪው ውስጡ እንዳለ አድርገው የለበስነውን ጅንስ ሱሪ እና መሰል ጠንካራ ጨርቅ አውልቁ ብለውን ከየሻንጣው አስወጥተውን.. ጠቀጠቁት፡፡ አልበቃ ብሎ ለህጻኗ የያዝነው ብርድ ልብስ ነበር፡፡ የእሱን ሽርጥ ሰጠንና በዚህ ጠቅልሏት ብሎ ብርድ ልብሱን ወስዶ ጎማ ውስጥ ከተተው፡፡ ያልገባ ሱሪና ቲ-ሸርት የለም፡፡ ልክ እንደ ከመነዳሪ እስኪሆን በሌባ ጎማ ጠቀጠቁት፡፡ የሚገርመው እንደዛ ጠቅጥቀውት ከግማሽ ቀን በላይ የተወሰነ ኪ.ሜትር አልሄድንበትም፡፡ ሌላኛው ጎማ ደግሞ ፈነዳ፡፡ ያ-የተጠቀጠቀውም ቀነሰ፡፡ ሁለት ቀን ምግብ በሌለበት ሁኔታ እዛው ጭድ ውስጥ አደርን፡፡ የያዝነውም ምግብ አለቀብን፡፡ እግረ መንገዳቸውን በዛ የሚያልፉ የግመል እረኞች ድኩላ ይሁን ሳላ በጥይት ገድለው ሰጡን፡፡ ግመል ተከትለው የሚሄዱ እረኞችም የግመል ወተት ሰጡን፡፡ የፍየል ወተትም ሰጥተውናል፡፡ እንዲህ እንዲህ ብለን ነፍሳችን አቆየን፡፡ በተለይ ሚስቴ ልጅ ስለምታጠባ ርሃቡ መቋቋም አቅቷት ነበር፡፡ የእናቷን ጡት ብቻ ነው የምትጠባው፡፡ የእናቷ ጡት ደግሞ በርሀብ





ምክንያት ደርቋል፡፡ ስለዚህ የፍየል እና ግመል ወተቱን ማጠጣት ግድ ሆነብን፡፡ ከጠጣች በኋላ ግን ህጻኗ በጣም ታመመችብን፡፡ ጠዋት ላይ ህፃኗን ጋቢና አስቀምጠን ለፈነዳው ጎማ የሚጠቀጠቅ ጉቶ ሰርዶታ እንድናመጣ አዘዙን፡፡ ሳሩን ስትፈነቅሉ አፈሩን እያራገፋችሁት ከምሩ ተባልን፡፡ ሳር ቀጥቋጦ..ተጠቅጥቆ ደቅ..ደቅ.. እያለ ወደዛና ወደዚህ እያጋደለን እየተንገላታን ነፍሳችን ከድንጋጤ ብዛት ደንድና ሞትን ረሳች፡፡ ይህንን የመሳሰለ ስቃይ አሳልፈን ነው በአስራ አንደኛው ቀን እዛች አነስተኛ ከተማ ነገር የገባነው፡፡

ከህጻን እስከ አዋቂ ክላሽ እና ከባድ..ከባድ መሳሪያ ኤም ፎርቲን የታጠቁ ሰዎች ያሉበት ቦታ ነው፡፡ ኢትዮጵያዊያን ወንዶችን ለብቻ ለይተው ሊገሉን ነበር ፍላጎታቸው፡፡ የአካባቢው ሴት ነዋሪዎች አዩን፡፡ ሉሉሉሉሉ... ብለው አተረፉን፡፡ እኔ እንዳውም አንገቴ ላይ መስቀል ነበር፡፡ በዛ መስቀል ችግር እንደሚመጣ አብረውኝ የነበሩት ሰዎች ነገሩኝ፡፡ እኔ የፈለገ ይሁን እንጂ አልፈታም ብዬ ታገልኩ፡፡ በኋላ ግን ከመሞት መሰንበት ነው ያልኩት፤ እንዲያውም እዚህ ውስጥ ክርስቲያን ካለ ከእኛ ጋር አይበላም ክርስቲያን ይህችን መሬት ረግጦ አያውቅም..መሞት መገደል አለበት ያላሉት የለም፡፡ ሊገድሉኝ ነበር፡፡ ባለቤቴ ሙስሊም ስለነበረች ሶማሊኛም ከእኔ በተሻለ ስለምውቅ ያለውን ነገር ሁሉ ነግራቸው ሙስሊም ነው ተብዬ ተረፍኩ፡፡ የዛን ቀን ነው ሼኩም ሳያሰልመኝ የሰለምኩት፡፡ በስም ብቻ ሰለምኩ፡፡ ከመንግስቱ ካልድ ሆንኩ፡፡

እዛ ቀበሌ መንደር ውስጥ አንዳንዶቹ አረቦች ናቸው፡፡ ጥሩዎችም ነበሩ፡፡ አጋጣሚ በምን ይውረዱ በምን አላውቅም ግን እኛ በመጣንበት መንገድ እንደማይሆን እምናለሁ፡፡ ዱቄት፣ ሰንደል፣ ቴምር፣ ዘይት፣ ስኳር፣ አሽግ ጭማቂዎች ሰጡንና ከእንግዲህ በኋላ ይህን ጋራ ብትሻገሩ ሞቃዲሾ ትገባላችሁ፡፡ ያ-ማለት ታልቃላችሁ ስለዚህ ተመለሱ ብለው በሌላ መኪና እንድንመለስ አስገደዱን፡፡ በዛን ወቅት እግዚአብሄር ነው የተፋኝ፡፡ አንድ ሰውነቴንም ሲያዩት ባለስልጣን ነው የምመስለው፡፡ አንተ ወታደር፣ አንተ..እያሉ ጠጣ በሙዝ እንደምትጫወተው እንደ ህጻን ልጅ ለ3 ቀን ተጫወቱብኝ፡፡ ህጻኑም፣ ክላሽ፣ ሽጉጥ፣ የታጠቀውም በመጣ ቁጥር በጥፊ እያሉ አላገጡብኝ፡፡ ሚስቴን እና እብራን ያለችው ዘመዷን ካልደፈርናቸው ብለው ብዙ ነገር ደረሰብኝ፡፡ እኔም አታደርጉም አልኩ ስደት ሴት ቢያደርገኝም ወንድ ነኝ፡፡ መቼም ድብደባውን ተወው፡፡ የቻልኩትን ያህል አግባባኋቸው፡፡ የቻልኩትን ያህል ተደበደብኩ፡፡

ረዱኝ፡፡ ባለቤቴን ሁሉ እንደመድፈር ብለው እዛ ያሉ ሶማሌ ሴቶችን ብቅ ሲሉ ጠብቁ ነግሬ ነው ያስጣሏት፡፡ ልጆን እላዬ ላይ ወርውረው እሷን ይዘው ሲጠብቁ ነበር፡፡ እብራን የመጣችውን በሌላ መንገድ

ሚስቴን በሌላ መንገድ ወሰዷቸው:: እኔ ልጄን ይገኙ ወዴትኛዋ ልሂድ? በማግስቱ ሌላ መኪና መጣ:: ቀያሪ /ሰኮርት ገሜ/ ስለነበረው ሰጁቶት ሰራርተው ልንሄድ ሆነ:: ሚስቴንም ከወሰዱበት እንድትመጣ ተደረገ:: ያን ሁሉ ቀን የፈጀው መንገድ በአንድ ቀን ተኩል ነው ወደነበርንበት ወደ ቡሩኦ የተመለስነው::

ቡሩኦ ስንደርስ ያው ሼህ ሀሰን ጋ ሄድን:: በቃ! ቁጭ በሉ አሁን ደግሞ ጦርነት ተነስቷል:: ምናልባት ረዘም ላለ ጊዜ ይቆያል:: በእርግጥም በታንክ ሁሉ ነው የሚታኮሱት ለአንድ መኖሪያ ቤት ወይም ለአንድ ሰው ታንክ ሲተኮስ ያየሁት ሶማሊያ ውስጥ ነው:: ክላሽ አይጠቀሙም በአንዴ ድምጥማጡን ለማጥፋት ነው መሰለኝ:: ከተማዋን እንዳልነበረች ነው ያደረጓት:: ጎሳ ለጎሳ ቢታንክ ተባብለው ሊያልቁ ነው እያሉ ሁሉም ሰግተዋል:: እዛቹ ቤት ተማልሰን ምግብ መስራት ጀመርሁ:: በዚህን ጊዜ ወደ 13 የሚሆኑ የትግራይ ልጆች ተደብድበው ግማሻቸው በጩቤ ተወግተው ልብሳቸውን ተዘርፈው ራቁታቸውን አባሪዎቻቸው እዛ ነው ሸርጥ ምናምን ያለበሷቸው:: ሰውዬው ለነፍስ ብሎ በፊት እኛ ተከራይተነው የነበረው ቤት ነው ያሳረፉዋቸው::

ስንመለስ ቤቱን ሳከራያቸው ነው ልቀቁና ከቤቱ ጀርባ ግራር አለ እዛ ስር ሁኑ አላቸው:: በእርግጥ እነሱን አስወጥተን መግባታችን ልክ አይደለም:: ተያይዘን ከምንቸገር እኛ ገብተን ምግብ ብናቀርብላቸው ይሻላል ብለን ገባን:: እንደገና ለአንድ ወር በሩኦ ኖርን:: ከወር በኋላ ያ-ሼክ ተደራድሮልን በከተማ ውስጥ ሚኒባስ እያንዳንዳችን 300 ብር ከፍለን ቦሳሶ ድረስ ልንገባ ተነጋገርን:: ድንገት ነው ተነሱ ያሉን መቼም ስደት ሁለ-ነገሩ ድንገተኛ ነው:: ፕሮግራም የሚያሲዝ አይደለም:: ነፍስያህን አንድ ቦታ እስከታሳርፍ መጓዝ..መጓዝ የውስጥህ ጥያቄ ነው:: ያም ፀጋህ አይደለም:: አንድ ቀን የራበው፣ ያበደም ሆነ የመረቀነ ሶማሌ ተነስቶ እስኪገድልህ ነው የምትጓዘው::

በሁለት ቀን ነው ቦሳሶ የደረስነው:: በመሀል ከልካዬ የምትባል ቦታ አለች:: መኪናው እዛ ቆመና ልጅ አቅፌ ስሄድ መሳሪያ የታጠቁ ሰዎች ጫማህ ያምራል ጫማህን አውልቅ ብለው አስወለቁኝ:: በካልሲ ብቻ የሚያቃጥል አሸዋ ላይ ተንዝኩ:: እንደምንም ቦሳሶ ገባን:: አቤት!!!!!.. አቤት!! የሀበሻ መዓት ትንሽዋ መርካቶ ትመስላለች:: ባህሩ አቅራቢያ ሀበሻ ሰፈር ይሉታል:: ሻይ ቤቱ፣ ምግብ ቤቱ፣ መቃሚያ ቤቱ፣ መጠጥ ቤቱ... ሁሉ የሀበሻ ነው:: ጠጋ ብለህ በባህር ለመሳፈር ፈልጌ ነበር ብለህ ከጠየክ የስም መዓት ይንጋጋልሀል:: በሰለሞን፣ በመሀመድ ደሬ፣ በኤሊያስ፣ በጁሀር...ማለቂያ የሌለው የስም ጋጋታ ያዘንቡልሀል:: ያንጋጉት የስም ዝናብ ጋብ ሲል አፌ ላይ እንደመጣ መሀመድ ደሬ አልኩ:: እሱ ጋ





አረፍን:: እሱም መልኩን ያሳመረ እባብ ነው:: ሰዎችን ያሰቃያል ኤልያስ የሚሉት ከእሱ ፈልቅቆ አውጥቶ ለሌላ ሰው ሊያሳልፈን ይፈልጋል::

ከሰዓት በኋላ ከተማዋን ዞር ዞር ለማለት ፈልጌ ወጣሁ:: የምታየው ነገር ሁሉ በጣም ያስጠላል:: ኢትዮጵያ ሆቴል የሚለውን ሳይ ፈገግ ብቻ ሳይሆን ከት አድርጎ አስቆኛል:: ቦሳሶ ሆነህ የማታየው ሰው አይነት የለም:: ከየክፍለሀገሩ የሚመጡት ብዛት ያስደነግጣል:: መቼም በጉዞ ላይ አወኩት አላወኩት አትልም ቦሳሶ ባደረኳት ቀይታ አብሬያቸው የማወራው የምጫወተው ልጆች ነበሩ::

አንድ ቀን የሆነ ልጅ ሰባት ሰዓት አካባቢ ነው ድክምክም ብሎ ጥላ ስር ቁጭ ብሏል:: እኛ ሶስት ሆነን ስንሄድ ድክም ከማለቱ የተነሳ በእጅ ምልክት ቀስ ብሎ የሚበላ እንደሚፈልግ አሁንም በምልክት ነገረን:: ከዛ ሮጠን ስስ ቂጣ የሚመስል እንጀራ ነገር አለ እሱን በድንችና አሳ ወጥ ገዝተን ፊትፊት አድርገን ሰጠነው:: ያችን ከበላ በኋላ ከሱሪው ወገብ ውስጥ ልብሱን ቀዶ ከቶት የነበረውን ገንዘብ አውጥቶ ከምሞት ሀኪም ቤት ውሰዱኝና ሌላ ምግብም ስጡኝ ብሎ መቶ ብሩን ሰጠን:: መንገድ ላይ ተጎድቶ፣ ተርቦ፣ ታሞ በስቃይ ገና ወደ ቦሳሶ የገባ ነው:: ሌላም ብዙ ብር ይዟል:: ሌላውን ተዉ መጓዣዬ ነው በዚህች አሳክሙኝ ስላለ ይዘነው ሄድን:: ሀኪሙ ጉልኮስ ሰካለትና ይተኛ አለን:: በርግጥም ልጁ በጣም ታሟል:: ስቶ ሱሪው ሁሉ ተበላሽቷል:: እዛው ቦሳሶ የሚኖር አንድ ሀበሻ ነበር:: የቆየ ነው እኔ አስታምመዋለሁ አለ:: ጥሩ ነው ወገንህ ነው ከእሱ አንተ ትሻላለህ ሀገሩንም ቋንቋውንም ታውቃለህ ብለን ለሱ አደራ ሰጥተን ሄድን::

በነጋታው ስንመለስ ልጁ መኝታው ላይ የለም:: አስታማሚውም የለም:: የት ሄዱ ብለን ስንጠይቅ ዶክተሩ በንዴት የሆነ ዘበኛ ጠርቶ አባራቸው ብሎ አስወጣን:: እንዲያውም ተከታተሉን:: ፈርተን ቀበታተንን:: በኋላ እዛ ሆስፒታል ውስጥ የሚሰራ ኢትዮጵያዊ የሮቤ ልጅ ነበር:: ማታ ላይ አገኘሁት:: ‹‹..ልጁን ኩላሊቱን ወስደው ገደሉት:: ልብሱ ውስጥ ብዙ ገንዘብ ነበረው ገንዘቡ ይሰጥህ እና አፍህን ዘግተህ ሂድ አሉት:: ያ-አስታማሚ እንቢ አለ:: ሁለቱም አንድ ላይ ነው ሌሊት የተቀበሩት:: የሁለቱንም ኩላሊት ነው የወሰዱት:: እናንተም እንዲህ እንዳታወሩ በቶሎ ሀገሩን ልቀቁ ፈልገው ያጠፏችኋል›› አለን:: አነጋገሩ ፍርሃት ለቀቀብኝ:: ወጣ ወጣ ማለት ተውኩ::

ቦሳሶ በቆየሁበት ጊዜ ሌላ የገጠመኝ አስቃቂ ነገር አንዲት ሴት ለስድስት የፈለጉትን ከተጠቀሙባት በኋላ ገለዋት አይቻለሁ:: የወሎ ሴት ነች ምግብ ትሸጣለች:: ሌሊት ገብተው ለስድስት ከደፈሯት በኋላ በጩቤ አርደዋት ዘረፏት ተብሎ ሬሳዋ እንደወደቀ ነጭ ጨርቅ አልብሰውት

በሰባተኛው ቀን ልንሄድ ስንል እሱ ያስጫናቸው ከመቶ ሀያ እስከ መቶ አርባ የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን እና 78 ሶማሊያዊያን ባህር ላይ አለቁ። አንድ ህጻን ብቻ ተረፈች። ህጻኗን ይዘዋት መጥተው በአይኔ አየሁኝ። ህጻኗን በደላላው መሀመድ ደሬ እጅ እንድትቀመጥ እኔም ባለሁበት ቃል አስገባነው። በፊት ግን ወይ አሳድጋት ካልሆነም ህፃኗን ስጠኝ ይግርት ልሻገር ከተረፈች ተረፈች ከእኛ ጋር ትሁን ላሳድጋት አልኩት። የሶስት አመት ህጻን ልጅ እሷ ብቻ ነች ከ220 ሰው አካባቢ የተረፈችው። ያው ናኩዳ የሚባሉት የጀልባዋ ዘዋሪዎች ምን ጊዜም ምንም አይሆኑም። ይህን ስናይ በመሀመድ ደሬ አንሳፈርም አልን። ያው ቢጨንቅ ነው እንጂ እዛ ጋ ያለ ደላላ የማንንም ሀሳብ ያስቀይራል። አንድ ጅብሪል የሚባል ጎበዝ እና ጥሩ ሰው ነው ተባለ።

እሱም ቅስቃሳ የሚያደርጉ ጭፍሮቹን ልኮብናል። ‹‹በግል ችግር ቦሳሶ የመጣችሁ ታፍሳችሁ እዚህ ጫካ ነው የምትገደሉት የኢትዮጵያ ወታደሮች እዚህ ቅርብ ነው ያሉት›› ብሎ ሊያስፈራራን ሞከረ። የእኛን ወታደሮች በየመንገዱ ስንት አይተናል። የነካን ግን የለም። ደስ እንዲለው ብለን የፈራን መስለን ቦሳሶ በገባን በአስረኛ ቀናችን ተሳፈርን። በመጀመሪያ ጀልባዋን ደብቀው የሚያቆሙበት ጋራ ስር ለመውሰድ ዘጠኝ ሰዓት ነው የፈጀው። ሶስት ሰዓቱን በመኪና ስድስት ሰዓቱን በእግር ነው የተጓዝነው። እንደ ከብት እየደበደቡ ህዝቡን ‹‹ር..ር..ር..›› እያሉ እያሯሯጡ ወሰዱን። በመንገድ የሞተም አለ።

እኔ ህጻኗን አዝዬ እግዚአብሄር ሲረዳኝ ጉልበቱን ሰጥቶኝ እንጂ የሞት ሞት ነው የተረፍኩት። ጋራው ስር ስንደርስ በየጥጋጥጉ ያለ ህዝብ ብዛት ወታደራዊ ማሰልጠኛ የገባሁ ነበር የመሰለኝ። እነዚህ ሁሉ ኢትዮጵያዊ ናቸው ወይ ስል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አዎ! የቀረው ሶማሊያዎች ናቸው አሉኝ። ሶማሌዎቹ ለብቻቸው ሰላሉ ላይ በጣም ትንሽ ናቸው። ትንሽ እንዳረፍን ክፍያ ተጀመረ። የእከሌ ጀልባ ጥሩ ነው፣ የእከሌ..ይሻላል እያሉ ሰዉ ግራ ተጋባ። እኛ እግዚአብሄር ጥሩውን ይምረጥልን እንጂ የትኛው በሰላም ይግባ አይግባ አናውቀውም። መጥፎው አይግጠመን ብለን ፀለይንና ተመዘገብን። ጋራው ስር ደግሞ ለሶስት ቀን አስቀመጡን። ሩዝ በበርሜል እየተቀቀለ ምን እንደሚገባበት አናውቅም እንበላለን።

በእርግጥ በባህር ውሀ ነው የሚቀቀለው። የባህር ውሃ ጨው ጨው እያለህ ጥም አይቆርጥም ትጠጣለህ። በባህር ውሃ ለህጻኗ ወተት ይበጠበጣል። እዛ ሆነህ እነሱ የሚቀቅሉትን ሩዝ ነው መብላት ያለብህ። አንዴ በትልቅ ጭልፋ የሚጨለፈው ከተማ ቢሆን ርካሽ ነው። ከእነሱ ግን



ገንዘብ እስኪያልቅ ትገዛለህ ካለቀ በርሃብ ብትሞት ጉዳያቸው አይደለም።

ታህሳስ አንድ ቀን ሁላችንንም ጫኑን። ቅዱስ ሚካኤል፣ ቅዱስ ገብርኤል ተከተሉን ብለን ተጫንን፣ ጉዞም ተጀመረ።

ከርቀት ሳየው ጀልባ መስሎኝ ነበር። እንጨት በእንጨት ነው ለካ? እየተንገዳገደች እየተገለባበጠች ማዕበል ሲመጣም እየገፋት ውሀው ሲገባም እየተቀዳ ተጓዝን። ከ24 ሰዓት ጉዞ በኋላ ጥቁር ውሃ የሚሉት የህንድ ውቅያኖስ እና ቀይ ውሃ የሚሉት የቀይ ባህር የሚገናኙበት ቦታ ጋር ሲደርሱ ልክ የሩጫ የጀምር ተኩስ/ፊሽካ የተተኮሰ ይመስል ድብደባ ጀመሩ። ህዝቡን እንዳትነሱ፣ እንዳትቆሙ እያሉ በዱላ ጨፈጨፉ። የምትቀመጠው እግርህን አጣጥፈህ በመሆኑ የደከመው አለ። ርሃብ አለ። መታመም ማስታወክ አለ። 20 ሰው የሚይዝ 10ሩ ሞቶ 10ሩ የሚተርፍበት ጉድጓድ አለ። እዛ ውስጥ የነበረ ልጅ ደክሞት እግሩ ተንቀጥቅጦ ልቁም ብሎ ሲነሳ ጭንቅላቱን በመዶሻ ፍርክስ አደረገው። የጅማ ልጅ ነው ከተማ እያለን አውቀው ነበር። ወጣት ገና 17 አመት አካባቢ ያለ ነው። የሰው ልጅ በሚስማር መንቀያ መዶሻ ሲመታ አስበው። ልጁን ፍርክስ ሲያደርገው ሁሉም ተደናግጦ ሲጮሁ ህዝቡን በዱላ መደብደብ ጀመሩ። ልጁ ኡኡኡ... ሲል ዝምበል እያሉ ይመቱታል። ዝም እንዳይል አሞታል ቁጭ በል ሲሉት እንዴት ቁጭ ይበል? ደሙ ይፈሳል። ይሄ ልጅ ይገለብጠናል አሉና እጅና እግሩን ይዘው ወደ ባህር ወረወሩት። አይ እንግዲህ እንዲህ እያሉ ነው የሚቀንሱት እግዚአብሄር ከነልጄ ከነሚስቴ ይጠብቀኝ..የሚለው የሹክሹክታ ልመናዬ ሆነ። ድምጼን ቢሰሙ ይወረውሩኛል እኔስ ግዴለም ልጄን ስል ፈራሁ። ከዛ በኋላ ያለው ጉዞ ተወው የሰቀቀን ነው።

አንዷን ሶማሊያዊ ጡቷን ጨመቅ ጨመቅ አደረጋት። ልታስለቅቀው ብትል በዱላ ቀጋት። እህ! ..እነዚህ ለዘራቸው ያልሆኑ አውሬዎች..አልኩና ይበልጥ ፈራኋቸው። ናኩዳዎቹ ሴቶችን እየደፈሩ ነው የተጓዝነው። እንቢ ያሉትን በመሳሪያ ያስፈራራሉ። ክላሽ፣ ጩቤ ይዘዋል። እዛው ፊት ለፊታችን በጨርቅ ከለል ያደረጉት ከሞተሩ በላይ ያለ መኝታቸው ላይ እያወጡ የፈለጉትን ያደርጋሉ። ሴቶቹ እንቢ የሚሉበት ድፍረት ሊኖራቸው ቀርቶ እኔ ወንዱ እንኳን ፈራኋቸው።

የመን ልንገባ መሬት ይሄው ብለው ጋራ አስጠጉን። ከ41 ሰዓት አስቸጋሪ ጉዞ በኋላ መሬት ለመርገጥ በግምት ወደ 40 ሜትር ያህል ሲቀረን አቆሙ። በዚህን ጊዜ የየመን ወታደሮች አዩንና እንዳንወርድ ሶማሊያውያኑ ይዘውን እንዲመለሱ መሰለኝ ሀሳባቸው ወደ ላይ ተኩስ

ከፈቱ። ሶማሌዎቹም መሳሪያ አነሱ። እንዲያውም ሴቶቹን እያነሱ መወርወር ጀመሩ። ተኩሱ በሁለቱም ወገን ቀጠለ። ሶማሊያዊያኑ ባለጀልባዎች ወረዱና የሆነ ገመድ ነገር ሳብ አድርገው ጀልባዋን ገለበጧት። እግሩን ታሞ በክራንች የሚሄድ ልጅ ሁሉ አለ። አንድ ጀልባ ላይ 128 ነበርን 48 ሰው አልቋል። ሰዉ ተፍጨርጭሮ ራሱን እንዳያድን ተኩስ ተከፍቷል። ግማሹም በጥይት እየተመታ ነው የሞተው። በጥይት ተመተው ከሞቱት መካከል ባለቤቱ /የልጁ እናት/ አንዷ ነበረች።››

ካልድ ወይም በቀድሞ ስሙ መንግስቱ ለገሰ የሚያወራልኝን ገታ ሲያደርግ ቀና ብዬ አየሁት። በእልህ ከንፈሩን ነክሷል። እንባው ግድቡን ጥሶ መድረሻው ሸሚዙ ላይ ሆኖ መሽኳለል ጀምሯል። ቆይቶ ቆይቶ ‹‹ይቅርታ ስሜታዊ ሆኜ ነው›› አለኝ። ቢሆንም ግን ውስጡን እንክት ያደረገ ሀዘን አዝሎ በረመጡ እየተርመጠመጠ መሆኑን ለመረዳት አላዳገተኝም። እኔ ልጁን ይዤ እንደምንም መሬት ለመርገጥ ቻልኩ። ልጁን ማትረፌን ካወኩ በኋላ ሚስቱን እና አብራን ያለችውን ልጅ ፈለኩኝ። ሚስቴ ወድቃ የባህሩ ውሀ እየገፋ እየመለሰ ይጫወትባታል። ግማሽ ሰውነቷ በአሸዋው ተሸፍኗል። የማደርገው ጠፋኝ። የያዝኩት መረጃዎችን፣ ገንዘቤን..የባለቤቴን ህይወት አጥቼ ከባህር ማዶ ስትረግጠው እስከ ጉልበት የሚያሰምጥ አሸዋ ላይ ሁሉን አጥቼ እንደአዲስ ተፈጠርኩ። ባለማወቅ ከወታደሮቹ ጋር ብዙ ግብ ግብ ፈጥሬያለሁ። ለምን መሰለህ መሞቷን ሳውቅ በድንጋጤ ራሴን ስቻለሁ። ስነቃ ነው እናንተ ባትተኩሱ ሚስቴ አትሞትም እያልኩ እኔ በአማርኛ እነሱ በአረቢኛ ግብግብ የፈጠርነው። እንግዲህ አስብ ሁለት ቋንቋ የማይተዋወቁ ሰዎች ፀብ..አሁን ሳስበው በጣም ነው የሚገርመኝ። አረቢኛ የሚያውቁ ደጋግመው የተመላለሱ ስደተኞች ናቸው የገላገሉን። ግብግብ ፀብ በአስተርጓሚ፣ ግልግል በአስተርጓሚ ሆነ ነገሩ።

ሌሊት 7 ሰዓት ከሩብ ነው የወረድነው እስኪነጋ የባለቤቴን ሬሳ ታቅፌ አደርኩ። ልጅቷን አብራን የነበረችው ልጅ (ባዩሽ) ያዘችልኝ። ህጻኗ ደግሞ ታለቅስብኛለች። በመሀል እይዛታለሁ። መጥፎኛ ጠረኔን ለምዳለች። ሲነጋ MSF (Medical sanfrontan) የሚባል ግብረ-ሰናይ ድርጅት ብስኩት ውሀ ይዘው ደረሱልን። ሬሳው አጠገብ ቁጭ እንዳልኩ ነው። መቅበሩንም አገዙኝ። ወታደሮቹ መጨረሻ ላይ አዘኑና ሚስቴን እንድቀብር ተባበሩኝ። እንዲያውም መረጃ ማግኘት ከፈለክ ታህሳስ 4/2000 የሚለውን ወደ እንግሊዘኛ ቀን አቆጣጠር ለውጥና ጠይቅ፣ በቤራሲ በኩል ከገቡት መካከል ሚስቴ እንደሞተች ሁሉ ተጽፏል። ቀብርኩ እና ማይፋ የሚባል ካምፕ ውስጥ ሊወስዱን ሲሉ ለፖሊስ ሊያስረክቡን ነው እናምልጥ ብለው መንገድ የሚያውቁ ደጋግመው የመጡ ልጆች ሲያመልጡ እኔም ህጻን ይዤ ላለመቃሰር ስል አመለጥኩ።››





ካሊድ (መንግስቱ) በሚለው ስሙን እንደለወጠ ሁሉ ልጁ ህጻን ሀዊም ሀዋ ተባለች። ሀዊ ድንገት ማንም ሰው በዚህ እድሜው ከሚያየው ስቃይ በላይ ስቃይን አጣጥማለች። እናቷ በሞት የተለየቻት ህጻን መሳቅ መጫወት ሳትጀምር፣ ርሀብ ጥሟን መናገር ሳትችል፣ ህመሜ እዚህ ጋር ነው ማለት ሳትችል የ11 ወር ልጅ ሆና ነው።

ቀጣዩን መንገድ እንዴት እንደመጣ ሲነግረኝ መፈጠሬን እስከጠላ አለቀስኩ። ‹‹..ፈጣሪ ሆይ ምነው መከራችን በዛ ለካ ከእኔም የባሰ አለ?›› ስል አሰብኩ። አሰብኩ እንጂ ትንፍሽ አላልኩም። የካልድን ጣር ማብዛት ነው የሚሆነው ብተነፍስ። ቀጣዩን የጉዞ ሁኔታ ሲነግረኝ..

‹‹ህፃኗ ርሃብ ሲሸነቁጣት፣ ጡት ስትፈልግ ታለቅሳለች። እብሶ መጀመሪያ ላይ እልም ያለ በረሃ ነው ስታለቅስ ምኔን ልስጣት? አብራኝ ያለችውን ልጅ ጡት ብንሰጣትም እሺ አላለችም። ያለመደችው ጠረን ሆኖባት ነው መሰለኝ። ጡቴን እያጠባኋት፣ ውሀ ጥም ሲያስለቅሳት ምራቄን እየሰጠኋት፣ ተጓዝን። የወንድ ጡቴ ለጊዜው ለቅሶ ማስታገሻ እንጂ ምን ጠብ የሚል ይኖረዋል? ብቻ ጡቴንም፣ ምላሴንም እያጠባኋት ብንጓዝም እኔም አፌ ደረቀ። ውሀ ጥም አቃጥሎኛል። እናት ሆና አብራኝ ያለችው ባዩሽም መከራዋን እየበላች ነው። ከረጅም ጉዞ በኋላ ባዩሽ /አሁን ህያት ነው ስሟ/ አዝላት ስንጓዝ እንቅልፍ ወሰዳት። ጥላ ነገር ፈልገን ልናስተኛት ስንል ምን እናንጥፍላት? እኔ የለበስኩት ሸሚዝ ብቻ ነው ያለን። ቅጠል ምናምን የማይታሰብ ነው አካባቢው ምድረ በዳ ነው። አቧራው ደግሞ ለጉድ ነው ምን እናድርጋት? ባዶ አሸዋው ላይ አስተኝተናት ንፋሱ የሚያነሳውን አሸዋ አይኗ እንዳይገባ ሸሚዜን አልብሰናት በአካባቢው ቤት ካለ ስትነሳ ርቧት ስታለቅስብን የምሰጣት ለመለመን ፍለጋ ጀመርኩ።

ግፋ ቢል ተኩል ሰዓት ያህል ሄጄ አገኘሁ። ከወገቤ በላይ ራቁቴን አይተውኝ የሚለበስ አርጌ ጨርቅ ሰጡኝ። ከዛ በኋላ ያለውን በምን እንግባባ? በምልክት የሚበላ እንደምፈልግ አሳየኋቸው። ሰጡኝ። ይዤ ልሄድ ስል የሆነ ነገር ተናገሩ። ምን እንዳሉኝ ባይገባኝም በመሰለኝ ተረጎምኩት። ቀለበት ያለበት ጣቴን እያሳየሁ የህጻን ልጅ ማቀፍ ምልክት አሳየኋቸው እና በርቀት ልጁ ያለችበትን አቅጣጫ ጠቆምኳቸው።

ገብቷቸው ይሁን እነሱም በመሰላቸው ተርጉመውት ምግብ ጨመሩልኝ። ደስ ብሎኝ ስመለስ አቅጣጫ ሳትኩ። ወደ አንድ ሰዓት አካባቢ ፍለጋዬን ቀጠልኩ። ካርታ ስራ ድርጅት መጥቶ ፕላኑን ቢሰጠኝም የማውቀው አልመስልህ አለኝ። ተስፋ ቆረጥኩ እና ሜዳው ላይ ቁጭ አልኩ። ከእንቅልፏ ተነስታ ቧ ታለቅስ በሀሳብ ታየኝ እና ብድግ ብዬ

በፍጥነት ፍለጋዬን ቀጠልኩ። ለካ ቀርቤ ነበር። ስደርስ ግን ተስፋዬ ከውስጤ ተሟጠጠ። ልጄም ሀያትም የሉም። ሰማይ ምድሩ ዞረብኝ። በፊት በሄድኩበት አቅጣጫ ሄዳ ይሆን ብዬ ፍለጋ ልሄድ ስል የህጻን ለቅሶ ሰማሁ። ሰዎች ሲያልፉ ለካ ፊርታ ከረብታ ነገር ስር ተደብቃ ኖሯል። የያዝኩትን ለሀያትም ለልጄም አቅምሼ ጉዞውን ቀጠልን። መንገድ ሲጠፋን፣ ለመጠየቅ ሲያስቸግረን፣ ሲርበን ያለውን ነገር ሁሉ አስበውና ማይፋ የሚባል UNHCR ለሶማሊያ ስደተኞች ያዘጋጀው ካምፕ አገኘን።

እዚህ እስክንደርስ ድረስ በየመንገዱ ያሉት ትናንሽ ከተማዎች ውስጥ ሁሉ እየለመንኩ ውሀ፣ ወተት..እያቀመስኳት ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት ተጓዝን። ህጻኗ ህክምና የሚያስፈልጋት ነበረች። በምግብም በሁሉም ነገር ተጎድታለች። ጉሉክስ ተደርጎላት ለሰባት ቀን አካባቢ እዛ ህክምናዋን እስክትጨርስ ቆየን። ከዛ እዚህ መቆየት አትችሉም አል-ቀረስ ካምፕ ግቡ ተባልን። አማራጭ የለንም ገባን። እነሱ ናቸው በመኪና የወሰዱን በዛ ሰዓት ሚስቴን አጥቻለሁ፣ ልጄን ማጣት አልፈልግም። እሷን ለማትረፍ ስል አድርግ የሚሉኝን ሁሉ መቀበል ግዴታዬ ነው። በእነሱ መኪና ነው የወሰዱን።

እዛ ካምፕ ስደርስ ግን ለከብት ማጎሪያነት እንጂ ፈጽሞ ለሰው ልጅ መኖሪያ የማይመች እና ሰብዓዊነት ያልተዘራበት፣ ያልበቀለበት ቦታ ነው። የሚሰጡት አስቤዛ እንኳን ልጅ ይገኔ ቀርቶ ለአንድ ራሴም አይበቃም። እዚህ የባሰ ልጄን ሳጣ የምችልበት ሁኔታ እንዳለ ታወቀኝ።

ለሶስት ወር ስቀመጥ ትርፋችን በርሃብ መቆራመድ ብቻ ሆነ። ለልጅቷ ብለው አንድ ኪሎ ዱቄት እንኳን አልጨመሩልኝም። በምግብ እጥረት ጭምር ልጄ ትታመም ጀመር። በኋላም ሆስፒታል መተኛት ግድ ሆነባት። ከባህሩ ጀምሮ ተጎድታ ስለነበረ ደም ሁሉ ተሰጣት። ለጊዜው ትንሽ ተሻላት። ለምኜም ቢሆን ወደ ከተማ ወጥቼ ልጄን ባተርፍ ይሻለኛል ብዬ አሰብኩ። በእርግጥም ያለው አማራጭ ይህ ብቻ ነበር። ከሆስፒታል አውጥቻት አብራኝ የነበረችውን የሚስቴን ዘመድ (ሀያትን) በአደራ እዛ ላሉ እንዲያቆዩዋት ሰጥቼ ልጄን አዝዬ የዘጠኝ ሰዓት መንገድ በእግሬ ወደ አደን አመራሁ።

አደንም የበለጠ የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚል ነገር አልገጥምህ አለኝ። የUNHCR ቢሮ ህፃንዋን አንቀበልም። ለሌላው ሰው ከሚሰጠው እርዳታ ውጭም አንሰጥም አሉኝ። እነሱ የእናቷን ሞት ከምንም አልቆጠሩትም። ብቸኝነቴን ከግምት አልከተቱትም። ለዛውም ተመዝገብና ቀጠሮ ወስደህ ኢንተርቪውን ካለፍክ በኋላ ነው የምንረዳህ ሲሉኝ ሰማይ ምድሩ ዞረብኝ። ምን ላርጋት? ‹‹አልመዘገብም ኢንተርቪውም አልገባም። መጀመሪያ የሙት ልጅ አለችኝ እርዳታ አድርጉላት። ህክምና፣ ምግብ፣





ልብስ፣ መጠለያ ያስፈልጋታል። ተመዝግቤ ለሶስት እና አራት ወር በቀጠሮ ስታቆዩኝ ምን ላድርጋት? ህይወቷ ያልፍብኛል ብል ማን ሰምቶኝ። አለቀስኩ አይኔ እያየ ልጄ ከእጄ ልታመልጥ ነው። ያለኝን አማራጭ ሁሉ ተጠቅሜ የልጄን ህይወት ማትረፍ፣ መታደግ ግዴታ ነው። የአደን UNHCR ሀላፊ ባለችበት ህጻንዋን ቁጭ አድርጌ ወጣሁ።

የስደተኛ መብት አስከባሪ የሰብዓዊ መብት ድርጅት ነው ልጄን አውጥተው አይጥሏትም ብዬ አስቀምጫት ብስኩት ልግዛ ብዬ ጠፋሁ። ምን አማራጭ አለኝ? አንቀበልህም፣ አንረዳህም ብትፈልግ ሜዳ ላይ ተኛ አሉኝ። እነሱ ለ3 ወር ያህል እኔን እያስፈለጉ ሀድራ ለሚባል ድርጅት ሰጧት። ስችል ራሴ ተደብቄ ሳልችል በሰው እያስሳክሁ እንዴት እንደሆነች በየቀኑ እየተከታተልኩ ለ3 ወር ያህል ተቀመጠች። በመጨረሻው አንድ ወር ያህል ልጅቷ ደበቁኝ። በጣም ያፈላልጉኝ ነበር። ከመለሱልኝ እጄ ላይ ትሞትብኛለች ስለዚህ አማራጭ ያደረኩት ተደብቄ ማሳለፍ ነው።

አማራጭ ሳጣ የደበቁኝ ልጄን ለማየት ሄድኩ። እንከማግ አሉኝ። ልጄን ጠልቼ ሳይሆን እጄ ላይ ከምትሞትብኝ ብዬ እነሱ ላይ ጥያት እንደጠፋሁ ነገርኳቸው። አንድ እየከፈሏት ህጻናት የምትጠብቅ ሶማሌያዊት ጋር እንድትቀመጥ ወሰኑ። እኔም እየሰራሁ ራሴን ለመቻል ታገልኩ። ሁሉም የማውቀው ስራ አይነት አይደለም። መኪና ለማጠብ ሞከርኩ። አንድ ኢትዮጵያን የሚያውቅ ሳዑዲ አረቢያዊ ሁኔታዬን አይቶ ‹‹አንተ ለዚህ ስራ አዲስ ነህ በምቾት እንደኖርክ ታስታውቃለህ..›› አለኝ ከረም ያሉ ልጆች ናቸው ያስተረጎሙልኝ። እኔም እውነቱን ነገርኩት።

በአቅራቢያው ያለ ሆቴል ወሰደኝ እና ምላ ካስተርጎሚው ልጅ ጋር ጋበዘን። ለሆቴሉ ባለቤት አስማለውና 30 ሺህ የየመን ሪያል (150 ዶላር) ሰጠው። በየቀኑ አንድ አንድ ሺህ ስጠው አለው። እኔ በማግስቱ ባለሆቴሉ ጋ ሰው ይገኔ ሄድኩና ሁለቱም ለእኔ አስበው እንደሆነ ነገርኩት። ግን ሳንቲሙን እንዴ ቢሰጠኝ ልብስ ስፌት ሞያ ስላለኝ የስፌት መኪናን ገዝቼ እንደምሰራ አስነገርኩት። ሰጠኝ። ተቀብዬ አርጌ የልብስ ስፌት መኪና ገዛሁ። በሰው በሰው አስነግሬ ሀበሻ ልብስ ሰፊ ጀምሯል ተባለ ትንሽ ቤት ተከራየሁ። እዛው ሆኜ ገበያውን አለማመድኩ። ትንሽ ከሰራሁ በኋላ አል-ቀረስ ካምፕ በአደራ እንዲያቆዩልኝ ለምኜ ያስቀመጥኳትን ባዩሽ (ሀያት) አስመጣኋት። ልጄንም ቀን ቀን ሶማሌዋ ጋር እየዋለች ማታ ማታ እወስዳት ስለነበር ምንም ቢሆን ያለ ሴት ከባድ ስለሆን እንድታግዘኝ ለመንኳት። ፍቃደኛ ሆነችልኝ ደስ አለኝም። በእርግጥም ብዙ ረዳችኝ። እሷ ባትኖር ምኑን ከምን አደርገው ነበር። ቤት ውስጥ መስራት (ማብሰል) ስለማልችል

ሁሉን ገዝቼ ነበር የምጠቀመው፡፡ ሴቶች ደግሞ ማብቃቃት ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ልንገርህ ሳንቲም የለኝም፡፡ ማብቃቃት ስላልቻልኩ ነው ያጠረኝ፡፡

አንድ ቀን የየመናዊያኑ ልጆች ወተት እየጠጡ ከአባት እናታቸው ጋር ሲሄዱ ስታይ ልጄ አለቀሰች፡፡ ሳንቲም ደግሞ የለኝም፡፡ ምንም ማድረግ ስላልቻልኩኝ ሄጄ ለመንኳቸው፡፡ አዩን ልጄ እያለቀሰች ነው ግዛላት ብለው ሳንቲም ሰጡኝ፡፡ ይህን ሁሉ የሆንኩት ለልጄ ስል ነው፡፡ የለመንኩት ለልጄ ስል ነው፡፡ አሁን አጋዥ አግኝቻለሁ፡፡ ልጄም ደህና ሆነችልኝ፡፡ ሰነዓም መጣን፡፡ አብረን ከመኖር ብዛት ተጠቃለልን ሁለት ተጨማሪ ልጆችም ወለድን፡፡

ልጄ ግን በየጊዜው እየታመመች ተቸገርኩኝ፡፡ ሰነዓ ከተማም ደህና ተቀበለችኝ፡፡ ጥሩ ስራም አገኘሁ፡፡ በመሀል የመኪና አደጋ ገጠመኝ፡፡ እጅ እና እግሬ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደረሰብኝ፡፡ የUNHCR ቢሮ ምንም ሊተባበረኝ አልቻለም፡፡ የመን ግርግር ውስጥ በገባችበት ወቅት ቤቴን ልቀቅ ብለውኝ ባዶዬን ወጣሁ፡፡ በዚህን ጊዜ ነው ቢሮው በር ላይ መጠጊያ ጭምር የለኝም መፍትሄ ስጡኝ ብዬ የተቀመጥኩት፡፡ ካንተም ጋር የተገናኘነው፡፡

ካልድ ልክ ነበር ከUNHCR በር ላይ የተነሳውም በልጁ መታመም ምክንያት ሆስፒታል ገብታ ነው፡፡ ከዛ በኋላ ቢሮው ቤት ተከራይቶለት ነበር፡፡ ልጁ ግን አንድ ቀን፣ አንድ ሳምንት ቢሻላት ደግሞ ትታመማለች፡፡ ከፋ ያለው መጣና በጠና ታመመች፡፡ የውጭ ህክምና ያስፈልጋታል ተባለ በህክምና ባለሞያዎቹ በኩል፡፡ ቢሮው ደግሞ ምክንያቱ ባይታወቅም ይህን ሊያደርግ እንደማይችል አስታወቀው፡፡ በዚህ በኩል ላደርግ የምችለው ነገር አጣሁ፡፡ በፌስቡክ እና በተለያዩ ማህበራዊ ድረ-ገጾች የእርዳታ ጥሪ ለወገን አስተላለፍኩ፡፡ ይህን ጥሪዬን ሀገር ውስጥ ያሉ እና በውጭም የሚታተሙ ጋዜጦች እና መጽሔቶች ተባብረው አስተላለፉልኝ፡፡ በሰዓቱ ያስተላለፍኩት መልዕክት ***‹‹ስደት ያጠወለገው ልጅነት....ወደ መርገፍ!!››*** የሚል ርዕስ ሰጥቼው ነበር፡፡

*ቃላት ቃላትን ረድተው ሀይል ሆነው ስሜትን መግለጽ እንደሚያቅታቸው ያየሁት አሁን ነው፡፡ ዛሬ.. ዛሬ አይኖቼ ደጋግመው የሚያለቅሱበት በስደት የሚያጋጥሙኝ ሰቆቃዎች በርካታ ናቸው፡፡ ስደት ወጥተን በሰው ሀገር በበሽታ ማቀው፣ አልጋ ይዘው፣ የሚበሉት፣ መድሀኒት አጥተው ማየት ምን አይነት ስሜት ይጭራል? ያሳዝናል የሚለው የሚገልጸው ስሜት አይደለም፡፡ በተለይ ህጻናት ላይ የሚደርሱ ሰቆቃዎች ከምንም በላይ ያሳዝኑኛል፡፡ በHIV ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናት የሚደርስባቸው እንግልት፣ በቫይረሱ ተለክፈው የሚሰቃዩ ህጻናት.. ብቻ ሁሉ ነገር ውስጥ ይበጠብጣል፡፡ ጤና አይሰጥም፡፡ አንድ ታሪክ ላውጋዎት? የእንባ ከረጢቶን ቋጠር ያድርጉት እንዳይዘረገፍ፡፡*





*ህጻን ሀዋ መስከረም 12/ 2000ዓ.ም በአቅፍ ነው ስደት የወጣችው፡፡ገና የአንድ አመት ልጅ እያለች በባህር ወደ የመን ከመጡት እናቷ እና አባቷ ጋር አብራ የመጣችው፡፡ ድንገት ማንም ሰው በዚህ እድሜው ከሚያየው ስቃይ በላይ ስቃይን አጣጥማለች፡፡ እናቷ ባህር ላይ በሞት የተለየቻት ይህች ህጻን እንደ ዛሬው 5 ዓመት ሞልቷት መሳቅ መጫወት ሳትጀምር፣ ርሀብ ጥሟን መናገር ሳትችል፣ ህመሜ እዚህ ጋር ነው በማትችልበት ወቅት የ11 ወር ልጅ ሆና ነው፡፡ አባቷ የወንድ ጡቱን እያጠባት፣ ውሀ ጥም ሲያስለቅሳት ምራቁን እየሰጣት፣ ምላሱን እያጠባት ያን በረሃ ይዟት አለፈ፡፡*

*መንግስቱ ለገሰ ዛሬ በሁኔታዎች አስገዳጅነት ስሙን ቀይሮ ካሊድ ለገሰ ተብሎ ነው የመን ስደተኛ የሆነው፡፡ የስም ለውጡ ታሪክ ብዙ ነው፡፡ ወደ የመን ሲመጡ የባህር ጉዞውን... አጠናቀው ልክ የየመንን መሬት ሊረግጡ ሲሉ ነው እናቷ የሞተችው፡፡ በህገ-ወጥ መንገድ በባህር የሚያጓጉዙትን ሶማሊያዊያን ለመያዝ በተደረገ የተኩስ ልውውጥ በጥይት ተመታ ባህሩ ዳር ህይወቷ ያለፈ ሚስቱን አንብቶ ቀበረ፡፡ ሀዘን ያቆራመደው ካሊድ ልጁን ማትረፍ ነበረበትና ከላይ እንደገለጽኩት ጡቱን እያጠባ.. ማይፋ የሚባለው አነስተኛ ከተማ ድረስ ለመድረስ በመሀል በመሀል ያሉት ትናንሽ ከተማዎች ውስጥ እየለመነ ውሀ፣ ወተት.. እያቀመሳት ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት ተጓዘ፡፡*

*ማይፋ የሚባለው ከተማ እንደገቡም ቢሆን በUNHCR የተወሰደው አርምጃ አል-ቀረስ የሚባለው ኢትዮጵያዊያን ወንድሞቻችንና ሶማሊያዊያን የሚሰቃዩበት ካምፕ ግቡ ተባሉ፡፡ ከባህር ሲወርዱ ጀምሮ በበሽታ የተለከፈችው ህጻን ለወራት ህክምናውን አገም ጠቀም በሆነ ሁኔታ ተከታትላ ለጊዜው ቢሻላትም በሰዓቱ ወደ ውስጧ የገባው የባህር ውሃ ለተለያየ በሽታ ዳረጋት፡፡ በህመምም ለ4 ዓመታት ታግላ ተጓዘች፡፡ ዛሬ ግን ችላ መጓዝ አልቻለችም፡፡ በአሁኑ ሰዓት ሆስፒታል በሞትና ህይወት መካከል ተይዛ የምትገኝ የ5 ዓመት ልጅ ነች፡፡*

*አይኗ አያይም፣ ጆሮዋ አይሰማም፡፡ በምግብ እጥረት ከሚመጣ በሽታ በተጨማሪ የአእምሮ ችግር በሚያስከትል በሽታ አልጋ ላይ ውላለች፡፡ እንደ ዶክተሮቹ አባባል በጣም ከፍተኛ ህክምና ያስፈልጋታል፡፡ ህይወቷ መትረፍ እንዳለበት ሁላችንም የምናምን ይመስለኛል፡፡ ግን እንዴት??*

*ከዚህ በፊት እንደማደርገው ሰዉን አስተባብሬ ለማሳከም አልቻልኩም፡፡ የመን ያለ ሀበሻ በዚህ ሰዓት (የመን በእርስ በእርስ ግጭት ውስጥ ተሰንጋ በነበረበት ወቅት) ሁሉም መለመን አፍሮ እንጂ ተቸግሯል፡፡ እኔም ቢሆን ሱቁን ዘግቼ መኖሪያ ቤቱን ለቅቄ ተሰድጄ ስላለሁ ማድረግ የምችለውን ያህል ላደርግ አልቻልኩም፡፡ ማድረግ ለምትችሉ ሁሉ እባካችሁ?... እባካችሁ.. በመጀመሪያ ደረጃ የሚያስፈልጋት የውጭ ሀገር ህክምና ነው፡፡ ይህን ማመቻቸት የምትችሉ በህክምናው መስክ የተሰማራችሁ፣ ግብረ-ሰናይ ድርጅት ያላችሁ፣ ከግብረሰናይ ድርጅቶችም ጋር ግንኙነት ያላችሁ በበርካታ በሽታ የታጠረች ልጅ ለማዳን*

*እንረባረብ። የህክምና ማስረጃው እጄ ላይ ስላለ ለመላክ ዝግጁ ነኝ። ሌሎችም ቢሆን ለምትብላው፣ ለመድኃኒት የሚያስፈልገውን ወጪ ለመሸፈን አነሰ በዛ ሳትሉ የወገንነታችሁን ለመርዳት ከቻላችሁ የአባቷን ስልክ ቁጥር ከታች ስላስቀመጥኩ ተባበሩ አባካችሁ?*

በእርግጥ በጣም ደስ የሚያሰኝ ምላሽ ነው ያገኘሁት። አቶ አሌ (ከካናዳ) እና ወ/ሮ እምሳለገነት በቀለ (ከአሜሪካ) ዶ/ር ሲሳይ (ከአሜሪካ)፣ ዶ/ር አሸናፊ አንተነህ፣ ወ/ሮ ሙሉመቤት ከአትላንታ ህክምናውን በተመለከተ ለመርዳት እንደሚችሉ ቃል ገቡልኝ። ከኖርዌይ፣ ሆላንድ፣ ደ/አፍሪካ፣ አባትየው ስልክ አስተናገዷል። ሳዑዲ አረቢያም እንድትታከም ለማድረግ ሙከራ ላይ ያለ ወዳጅ ነበረኝ። በተለይ ዶ/ር አሸናፊ አንተነህ የህክምና ወረቀቱን ጠይቀውኝ ለመላክ ስዘጋጅ አሳዛኙ ተጨማሪ መርዶ ደረሰኝ። ሙስተሽፋ ሰበኢን (ሰባኛው መንገድ ላይ ስለሆነ ነው ሰባኛው ሆስፒታል የሚባለው) ህክምናዋን የሚከታተሉት ዶ/ሮች ደሟ ተመርምሮ የኤች.አይ.ቪ ቫይረስ ተሸካሚ ነች ተባለ።

እንዴት ሊሆን ቻለ?

ይህ እጅግ አስደንጋጭ ነገር ነው። ምክንያቱም ካልድ፣ ሚስቱ፣ ልጆቹ ነጻ ናቸው። እሷ ብቻዋን በምን አይነት መንገድ በኤች.አይ.ቪ..ተጠቂ ልትሆን ቻለች? ውስጤ በጣም ብዙ ስንግ ሀሳቦችን አፈለቀ። የምርመራው ውጤት ስህተት ይሆን? ከዚህ በፊት ሌሎችም በዚህ በሽታ ተጠቂ ተብለው ውሸት እንደሆነው ይሆን?..እኔ ለማወቅ የጣርኩት ጥረት ውጤት ሊያመጣ አላስቻለኝም። ከግምት ያለፈ አልነበረም። ካልድ ደግሞ ደጋግሞ የሚነግረኝ የተሰጣት ደም ችግር ቢኖርበት ነው፣ ያኔ ነው ስህተቱ የተፈጠረው ባይ ነው። ደግሞ ደጋግሞ እሱም ሆነ ልጆቹ ተመርምረው ነጻ መሆናቸውን ሲናገር ይሰማል። ከዚህ በኋላ የሚሰጣት ህክምና ዝም ብሎ የግብር ይውጣ መሆኑን አይቻለሁ።

በተለይ ወደ መጨረሻው ቀን ላይ ጻሀይ በየነ፣ አለም መንግስቱ እና አስመረት ገ/እግዚአብሄር የተባሉ ልጆችን ይዤ ምሽት ላይ ሆስፒታል ሄድን። ያለችበት አስቃቂ ሁኔታ ፈጽሞ ልቋቋመው የማልችለው ሰቆቃ ውስጤ ተክሎ ወደ ቤቴ ከተመለስኩ በኋላ እንኳን ረፍት ሰጥቶኝ ልተኛ አልቻልኩም። በእርግጥም ልጂ የታመመብኝ ያህል ነው ውስጤ የቆሰለው።

በዛ ሁኔታ ለሶስት ቀን ቆየች። በአራተኛው ቀን ጠዋት ካልድ ስልክ ደወለልኝ። ሰላም አድራ ይሆን ብዬ ስከፍተው ‹‹ልጄን ጉድ ሆንኩ...ልጄን ጉድ ሆንኩ...ልፋትህ መና ቀረ!.. ልፋትህ መና ቀረ...›› የሚል ለቅሶ ሰማሁ። ስልኩን ዘግቼ በቀጥታ ወደ ሆስፒታል ነው የሄድኩት።





ልጅን በሞት በተነጠቁበት ክፉ ቀን አጽናኝ ወዳጅ ዘመድ ከአጠገብ ሲኖር ጥሩ ነው። ካልድ ደንግጦ የደወለው እኔ ጋ ብቻ ነበር። ሚስቱ እና ሌሎች ሁለት ልጆች ብቻ ሆስፒታል አብረውት ነበሩ። ለዛውም አንዱ ጉድጓድ ሊያስቆፍር ተልኮ ሄዶ ነው ተብሎ አላየሁትም።

ስልኬን አውጥቼ ሰዎች እንዲያጅቡት፣ እንዲያጽናኑት በየአቅጣጫው እየደወልኩ መጥራቱን ተያያዝኩት። ሁሉም አለመስማቱ ነው እንጂ ከሰው ተግባቢው ካልድ እንዲህ ብቻውን አላገኘውም ነበር። ሬሳው ታጥቦ በጨርቅ ተጠቅልሎ ተዘጋጅቶ ስለነበር ገብቼ ሁለት እጄ ላይ አድርጌ ወጣሁ። በህመም የተጎዳች ስለነበረች ቀድሞም ክብደቷ ብዙም አልነበረም ግን ሰውነቷ አሁን በጣም አንሷል።

በታክሲ ወደ ቀብር ቦታው ሄድን። አሁን አንዱ ላንዱ እየነገረ ተሰባስቧል። ቀብርን እና ወደ ቤት አመራን። ተፈጸመ.......ምዕራፉ ተዘጋ። ስደት ያጠወለገው ልጅነት.... ወደ መርገፍ!! ነበር ያልኩት። አጠውልጎ..አጠውልጎ መጨረሻው የተፈራው ሆነ። አንዳንዴ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በአሰቃቂ ተጀምሮ አንድም ደስታ ሳያካትት መጠናቀቁ ያሳዝናል። ፈጣሪ ለምን እንደዚህ አይነት ለስቃይ ብቻ የሚፈጥረው ፍጡር ይኖራል? የሀዊ መንግስቱ ይጣፍጡ ይምረሩ የማታውቃቸው እንደ ልጅ ያላጣጣመቻቸው 5 የስደት አመታት አሳልፋ አለፈች። ሩጫው ሳይጀመር ተጠናቀቀ። የልጅነት ታሪክን ስደት ቀርጥፎ በላው። ውስጤ ሳይረሳት ከማህደሩ አኖራት።

አንዱ ሲቀር ሌላው መኖር እንደሚፈልገውም ይሁን እንደማይፈልገው ኑሮ በተባለበት አቅጣጫ ወዶ ሳይሆን ሳይወድም ይኖራል። ካልድም ህይወት መቀጠሏ ግድ ነው እና እየኖራት ነው። ያን ሁሉ ፈተና አልፎ እንደበቀሉ እሸት ተሸልቅቆ ዛሬ እንደ አዲስ በሰው ሀገር አዲስ ጎጆ ይዞ ይኖራል። የእኔ ብሎ ይዞ የወጣውን አራግፎ አዲስ ጉዞ አዲስ የህይወት ምዕራፍ.......